

የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

(ከ2013 ዓ.ም - 2022 ዓ.ም)

ፍኖተ ብልጽግና

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት

ፕላንና ልማት ቢሮ

ማውጫ ገጽ

መቅድም 1

መግቢያ 3

ክፍል አንድ : ያለፉት ዓመታት የልማት አፈጻጸም

ምዕራፍ አንድ : የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ አፈጻጸም 6

1.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ 7

1.1.1 የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት 7

1.1.2 የድህነት ገፅታ ሁኔታ 7

1.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ 8

1.3 የክልሉ ፊስካል ፖሊሲ 9

1.3.1. የክልሉ የገቢ አፈጻጸም 10

1.3.2. የክልሉ የወጪ አፈጻጸም 12

1.4. የክልሉ የቁጠባ ሁኔታ 16

1.5. የክልሉ የሥራ አጥነት ሁኔታ 17

ምዕራፍ ሁለት : የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም 18

2.1. የግብርና ልማት አፈጻጸም 19

2.2. የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች አፈጻጸም 25

2.3. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አፈጻጸም 26

2.4. የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት አፈጻጸም 28

2.5. የማዕድን ልማት አፈጻጸም 30

2.6. የንግድና ገበያ ልማት አፈጻጸም 31

2.7. የኢንቨስትመንት ሥራዎች አፈጻጸም 33
2.8. የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማት አፈጻጸም 34
ምዕራፍ ሦስት : የመሰረተ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም 37
3.1. የትራንስፖርትና መንገድ ልማት አፈጻጸም 38
3.2. የኢነርጂ ልማት አፈጻጸም 40
3.3. የውሃ ልማት አፈጻጸም 41
3.4. የመስኖ ልማት አፈጻጸም 43
3.5. የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት አፈጻጸም 44
ምዕራፍ አራት : የማህበራዊ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም 47
4.1 የሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት አፈጻጸም 48
4.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት አፈጻጸም 48
4.1.2 የትምህርት ልማት አፈጻጸም 49
4.1.3 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ልማት አፈፃፀም 52
4.1.4. የደቡብ አመራር አካዳሚ ስራዎች አፈጻጸም 54
4.1.5. የጤና ልማት ዕቅድ አፈጻጸም 55
4.2 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት አፈጻጸም 56
4.3 የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ልማት አፈጻጸም 59
ምዕራፍ አምስት : የሕዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥራዓት ግንባታ አፈጻጸም 62
5.1. የሕዝብ አገልግሎትና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም 63
5.2. የፍትህ ዘርፍ አፈጻጸም 65
5.2.1. የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስራዎች አፈፃፀም 65
5.2.2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት አፈጻጸም 66
5.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ 67

5.3.1 የክልሉ ምክር ቤት አፈፃፀም 67

5.3.2 የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሥራዎች አፈጻጸም 68

5.3.3. የስነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎች አፈጻጸም 69

5.3.4 የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዩች አፈፃፀም 70

ምዕራፍ ስድስት : የሰላም ግንባታ ዘርፍ አፈጻጸም 72

6.1. የሰላምና ጸጥታ ሥራዎች አፈጻጸም 73

ምዕራፍ ሰባት : የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት አፈጻጸም 76

7.1. የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች አፈፃፀም 77

ክፍል ሁለት : ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶችና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ

ምዕራፍ አንድ : ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶችና መልካም አጋጣሚዎች 81

1.1 ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች 82

1.2. መልካም አጋጣሚዎች 85

ምዕራፍ ሁለት ፡ የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህሪያት 87

2.1 የክልላችን የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ 88

2.2 የአስር ዓመት ዕቅዱ አስፈላጊነት 88

2.3. የአስር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪያት 90

ክፍል ሦስት : የአሥር ዓመት (2013-2022) የልማት ዕቅድ

ምዕራፍ አንድ : የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና ምሰሶዎች 93

1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች 94

1.1.1 ክልላዊ የረጅም ጊዜ የልማት ራዕይ 94

1.1.2 የቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች 94

1.2. የልማት ዕቅዱ ምሶሶዎች (strategic pillars) 94

1.3. የልማት ዕቅዱ የትኩረት መስኮች 95

ምዕራፍ ሁለት : የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ 106

2.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ 107

2.2. የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ 108

2.3 የፊስካል ፖሊሲ (ገቢና ወጪ) 108

ምዕራፍ ሶስት : የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 110

3.1. የግብርና ልማት 111

3.2. የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች 126

3.3. የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት 129

3.4. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት 134

3.5. የማዕድን ልማት 139

3.6. የንግድና ገበያ ልማት 140

3.7. የኢንቨስትመንት ልማት 144

3.8 የባህልና ቱሪዝም ልማት 146

ምዕራፍ አራት : የመሠረተ ልማት ዕቅድ 152

4.1. የትራንስፖርትና መንገድ ልማት 153

4.2. የኢነርጂ ልማት 156

4.3. የውሃ ልማት 157

4.4. የመስኖ ልማት 160

4.5. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት 161

ምዕራፍ አምስት : የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 164

5.1 የሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት 165

5.1.1 የሥነ-ሕዝብ ልማት 165

5.1.2 የትምህርት ልማት 166

5.1.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ልማት 169

5.1.4. የደቡብ አመራር አካዳሚ ሥራዎች 172

5.1.5 የጤና ልማት 174

5.2 የሴቶችና የሕጻናት ልማት 177

5.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት 183

5.4. የወጣቶችና ስፖርት ልማት 188

ምዕራፍ ስድስት : የሕዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕቅድ 195

6.1. የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ 196

6.2. የፍትህና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥራዎች 197

6.2.1 የፍትህ ሥራዎች 197

6.2.2 ጠቅላይ ፍርድ ቤት 201

6.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ 204

6.3.1 የክልል ምክር ቤት 204

6.3.2. ብሔረሰቦች ምክር ቤት 205

6.3.3. ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ሥራዎች 206

6.3.4 የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን 208

ምዕራፍ ሰባት : የሰላምና ፀጥታ ግንባታ ዕቅድ 210

7.1. የሰላምና ፀጥታ 211

ምዕራፍ ስምንት : ደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት 214

8.1. ደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች 215

ክፍል አራት : የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ምዕራፍ አንድ : የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች 219

ምዕራፍ ሁለት: የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች 223

ምዕራፍ ሶስት : የልማት ዕቅዱ ስጋቶችና ስጋቶቹን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች 226

3.1. የልማት ዕቅዱ ስጋቶች፡- 227

3.2. የልማት ዕቅዱ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች 227

ምዕራፍ አራት : የክትትልና ግምገማ ሥርዓት 229

4.1. የክትትል ሥርዓት 230

4.2. የግምገማ ሥርዓት 231

4.3. የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች 232

መቅድም

ዕቅድ የሁሉም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ሥራዎች መነሻ ተግባር ነው። ባለፉት ዓመታት በክልላችን በርካታ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ዘመን ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በተለይም ባለፉት አስር ዓመታት በክልላችን የመጀመሪያውና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል።

በነዚህም የዕቅድ ዘመናት በክልላችን ተግባራዊ በተደረጉ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተጣሉ ግቦችን ከማሳካት አንፃር አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል ። ሆኖም ግን ባለፉት ዓመታት የህዝቡ የልማት ፍላጎትና ያለው ውስን ሃብት የተጣጣመ ባለመሆኑ እና በመልካም አስተዳደር ጉድለት ምክንያት የህዝቡ የልማት ጥያቄዎች ሙሉ ለሙሉ መመለስና የህዝቡን ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ ማድረስ ሳይቻል መቆየቱን መገንዘብ ተችሏል።

ባለፉት 3 ዓመታት በሃገራችንም ሆነ በክልላችን በተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ የህዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በተጠናና በተደራጀ አግባብ ደረጃ በደረጃና በቅደም ተከተል ምላሽ መስጠት እንደሚገባ በለውጡ አመራር ታምኖበት በርካታ እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል። በዚህም መሠረት በቀጣይ የክልላችንን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮችን በመሠረታዊነት ሊቀርፍ የሚችል ክልላዊ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ይህ የዕቅድ ሰነድ በክልል ደረጃ ከመጠቃለሉ በፊት በክልላችን በፕላንና ልማት ቢሮ አስተባባሪነት የዕቅድ ዝግጅት መመሪያ በማዘጋጀት በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች እንዲተገበር እና ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች በተዘጋጀው ረቂቅ የዕቅድ ሰነድ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላትና የማህበረሰብ ተወካዮች ተሳትፎ እንዲኖራቸው ተደርጓል። እንዲሁም በመላው የየተቋሙ ፈፃሚ ሠራተኞችና የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት በአስተያየት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በመሠረተ ልማት፣ በከተማ ልማት እና በሰላምና መልካም አስተዳደር ክላስተሮች በዝርዝር እንዲታይና በአስተያየት እንዲዳብር ተደርጓል።

በመጨረሻም የክልላችን መስተዳድር ምክር ቤት በመሪ የልማት ዕቅዱ ሰነድ ላይ በስፋት ከተወያየበት እና በአስተያየት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ ተፈፃሚ እንዲሆን ተደርጓል። የዚህ እቅድ ሰነድ ብዝሃ ዘርፎችን ትኩረት በመስጠት የተዘጋጀ ሲሆን በተለይም በሁሉም ዘርፍ የምርታማነት ዕድገት፣ ለአምራቹ ዘርፍ ጥራትና ተወዳዳሪነት፣ ለአገልግሎት ዘርፍ ቅልጥፍና ውጤታማነት፣ ለቱሪዝም እና ለማዕድን ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚተገበር ይሆናል።

ለክልላችን የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ስኬታማነት እና የክልላችን ህዝብ የኑሮ ደረጃን በማሻሻል ብልፅግናን ለማረገገጥ የሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ባለሃብቶች፣ የመላው ህዝብ እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ በሁሉም አካላት ተገቢው ድጋፍና ትብብር እንደሚደረግ ይጠበቃል። እንዲሁም የክልላችን መንግሥት ለዕቅዱ ስኬት ሁሉ አቀፍ ድጋፍ እንደሚያደርግ እና ጠንካራ ቁርጠኝነት ያለ መሆኑን ታሳቢ ተደርጓል።

በመሆኑም በክልላችን የቀጣይ አስር ዓመት የመሪ ልማት ዕቅድ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በመሠረተ-ልማትና በመልካም አስተዳደር ዘርፎች የተጣሉ ግቦችን በማሳካት የህዝባችንን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንደሚቀረፉ ይጠበቃል።

መግቢያ

የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ዝግጅት ሰነዶች ከሚያካትቷቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ውስጥ አሁን ያለንበት ደረጃን መለየት /Where we are/፣ የት መድረስ እንዳሰብን ግብ መጣል/our Goal/ እና ግባችንን እንዴት ማሳካት እንደምንችል /How we achieve our Goal/ ማስቀመጡ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

በዚህም መሰረት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት በዕቅድ ለመምራት የሚያስችሉ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይቷል። ከነዚህም ውስጥ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ፣ የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ዕቅድ፣ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ልማትና የድህነት ቅነሳ ዕቅድ እንዲሁም የ1^{ኛ} እና የ2$^{+ኛ}$ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በክልሉ በመካከለኛና ረጅም ዘመን ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ከረቂቅ ዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ የክልሉ ማህበረሰብና የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ የጎላ ነበር። በዚህም የዕቅድ ዝግጅት ሂደቱ ከላይ ወደ ታች እና ከታች ወደ ላይ የዕቅድ ዝግጅት አሠራር ሂደትን ተከትሎ የተካሄደ ሲሆን በነዚህም የዕቅዶቹ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የትኩረት መስክና የፖሊሲ ጉዳዮች ከተለዩ በኋላ ከታች እስከ ላይ ባለው የክልሉ የአስተዳደር እርከኖች የሚገኙ የአርሶ/አርብቶ አደር ተወካዮች፣ የወጣቶችና የሴቶች ማህበራት ተወካዮች፣ የበጎ አድራጎትና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ የሃገር ሽማግሌዎችና የማህበረሰብ ተወካዮች ተሳታፊ የሆኑበት መድረክ በማዘጋጀት የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የተጠቃለለውን ሰነድ ለክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ እንዲቀርብና አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግና በማስፀደቅ በክልሉ ተፈፃሚ ተደርገዋል።

ባለፉት ዓመታት በክልሉ ተዘጋጅተው ተግባራዊ የተደረጉትን የረጅምና የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችሉ ዝርዝር የአፈጻጸም ግምገማ ማትሪክስ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማካሄድ በክልሉ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች የተመዘገቡ ውጤቶችንን እና ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማመላከት የዕቅድ ሰነዶቹ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፊ ሥራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። በዚህም በክልሉ በርካታ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮችን ለመፍታትና የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችሉ ሰፊ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሰፊ የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ተደርገው አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

በመሆኑም ባለፉት ሁለት ዓመታት በሀገራችንም ሆነ በክልላችን በተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ህዝቡ በየደረጃው የሚያነሳቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በተጠናና በተደራጀ መልክ ደረጃ በደረጃ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ በመሆኑ እና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በ2012 በጀት ዓመት የሚገባደድ በመሆኑ የቀጣይ 10 ዓመት ክልላዊ መሪ የልማት ዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል።

ስለሆነም ይህ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅድ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን የሰነዱ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ክፍል በወቅቱ በነበረው አደረጃጀት እና አዲሱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከመደራጀቱ በፊት በጋራ በአንድ ክልል በነበርንበት ወቅት የተፈፀመ በመሆኑ የአፈጻጸም ግምገማው በነበረው አደረጃጀት ተወስዶ ተዘጋጅቷል። ነገር ግን የሰነዱ የዕቅድ ክፍል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በመቋቋሙ ምክንያት በአዲሱ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት አደረጃጀት እንደገና ተከልሶ እንዲዘጋጅ የተደረገ በመሆኑ በአንዳንድ የዘርፍ ግቦች ዒላማ ከመነሻው ዓመት አፈፃፀም ዝቅ ሊል ችሏል።

በአጠቃላይ የዕቅዱ ሰነድ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን በክፍል አንድ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ፣ በክፍል ሁለት በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የልማት ዕቅዱ አድማስ፣ በክፍል ሦስት የቀጣይ አስር ዓመታት መሪ የልማት ዕቅድ፣ እንዲሁም በክፍል አራት የልማት ዕቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ስርዓት በቅደም ተከተል ተቀምጧል።

ክፍል አንድ

ያለፉት ዓመታት የልማት አፈጻጸም

ምዕራፍ አንድ

የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ አፈጻጸም

1.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

1.1.1 የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት

በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚ ዋነኛ ዓላማ የግብርና ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አስተማማኝ የምግብ ምርትና የኢንደስትሪ ግብይት አቅርቦት እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማጠናከር ለልማት የተመቻቸ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ በመፍጠር ፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሐዊ ዕድገት ማስመዝገብ ነው።

የክልላችን አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከ2008-2012 ዓ.ም የክልሉ ጠቅላላ ምርት በወቅቱ በነበረ ዋጋ በ2008 ዓ.ም ዋጋ ከነበረበት 115.99 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት 220.90 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን የምርት መጠን በ2008 ቋሚ ዋጋ ሲሰላ ደግሞ በ2008 ዓ.ም ከነበረበት 115.99 ቢሊዮን ብር በ2012 ዓ.ም ወደ 165.63 ቢሊዮን ብር ማድረስ ተችሏል።

በ2008 ዓ.ም በተመሠረተ ዋጋ የክልላችን አጠቃላይ ኢኮኖሚ በ2009 በጀት አመት አጠቃላይ የ9.9 በመቶ፣ በ2010 በጀት ዓመት የ10.0 በመቶ፣ በ2011 በጀት ዓመት የ9.0 በመቶ እና በ2012 በጀት ዓመት የ8.3 በመቶ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ሲሆን የክልላችን ያለፉት አምስት ዓመታት አማካይ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት 9.3 በመቶ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ላለፉት ዓመታት አማካይ ዕድገት ዝቅ ማለት በተለይም በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በ2012 በጀት ዓመት ሶስተኛው ሩብ ዓመት ጀምሮ በዓለማችንና በሀገራችን በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በመንግሥት በተወሰዱ በሽታውን የመከላከያ እርምጃዎች ሳቢያ የክልላችን ኢኮኖሚ በተለይም የአገልግሎት ዘርፍ እና የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዳ በመሆኑ ለኢኮኖሚው ዕድገት መቀነስ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ፈጥሯል።

1.1.2 የድህነት ገፅታ ሁኔታ

ሀገራዊ የድህነት ገፅታ ጥናት እንደሚያሳየው እ.አ.አ. በ2016 ከክልሉ አጠቃላይ ሕዝብ ውስጥ ከድህነት ወለል በታች የሚገኘው ሕዝብ /poverty head count index/ 20.7 በመቶ ሲሆን በገጠር 21.9 በመቶ እና በከተማ ደግሞ 14.4 በመቶ ነው። በተመሳሳይ መልኩ በክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በተካሄደው የድህነት ገፅታ ጥናት ከክልሉ አጠቃላይ ሕዝብ ውስጥ 21.9 በመቶ ከድህነት ወለል በታች እንደሚገኝ ያሳያል።

የዚህ ጥናት ውጤት ከባለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር እ.አ.አ በ2005 ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ሕዝብ 38.2 በመቶ የነበረ ሲሆን እ.አ.አ በ2011 ወደ 29.6 በመቶ ዝቅ ብሏል። በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ የመጀመሪያ ዓመት ላይ (እ.አ.አ. በ2016) ከድህነት ወለል በታች የሚገኘው ሕዝብ ብዛት ወደ 21 በመቶ አካባቢ ወርዷል።

ሆኖም በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ በክልላችን ከድህነት ወለል በታች የሚገኝውን ህብረተሰብ ቁጥር ወደ 16 በመቶ ለማውረድ የተጣለውን ግብ ለማሳካት የተሰሩ ስራዎችና የተመሩበት አግባብን በመፈተሽ እና ጉድለቶች በማረም በቀጣይ ዕቅድ ዘመን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅጣጫዎችን በመከተል በልዩ ትኩረት መፈፀም ያሻል።

በዚህ ጥናት የተመለከተው ሁለተኛው ጉዳይ የመንግስት መሠረታዊ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች /welfaire/ አቅርቦት ሲሆን ዜጎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን በቅርብ ርቀት እንዲያገኙ በተሠራው ስራ መሠረታዊ ለውጥ የታየ ሲሆን አካባቢዎችን ከማመጣጠን አንፃር ብዙ መስራት ይጠበቃል።

1.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የክልሉን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ በክፍላተ ኢኮኖሚ ስንመለከት ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በአማካይ የግብርና ዘርፍ 9.4 በመቶ ኢንዱስትሪ 8.9 በመቶ እና አገልግሎት 9.4 በመቶ እድገት አስመዝግበዋል።

የክልሉን ጠቅላላ ምርት ከክፍላተ ኢኮኖሚ ድርሻ አንፃር ስንመለከት የግብርናው ዘርፍ በ2008 ዓ.ም ከነበረው 58.5 በመቶ ድርሻ በ2012 ዓ.ም ወደ 58.8 በመቶ ድርሻ በመጠነኛ ሁኔታ ከፍ ያለ ሲሆን የኢንደስትሪው ዘርፍ በ2008 ከነበረበት 18.2 በመቶ ድርሻ በ2012 ዓ.ም ወደ 17.8 በመቶ ዝቅ ብሏል። ይህም ሁኔታ የክልሉ ኢኮኖሚ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው የመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት በአግባቡ እያመራ አለመሆኑና መዋቅራዊ ሽግግሩ ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

ያለፉት አምስት ዓመታት የክልሉ ኢኮኖሚ አማካይ አፈፃፀም አጠቃላይ ኢኮኖሚው አጥጋቢ በሚባል ደረጃ እያደገ ያለ ቢሆንም በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ከተያዘው አማካይ ዓመታዊ ግብ 11.8 በመቶ አንፃር ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ የክልሉን የግብርና ዘርፍ ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብዓት አቅርቦትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማጎልበት፣ እንዲሁም ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት አጠናክሮ በመተግበር እና ሌሎች የክልሉን አጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን በወሳኝ ደረጃ የሚያሳድጉ ስትራቴጂዎችን በመቀየስ ሰፊ ስራዎች ሊተገበሩ ይገባል።

በተለይም የኢንደስትሪው ዘርፍ አማካይ ዓመታዊ የዕድገት የአፈጻጸም ደረጃ 8.9 በመቶ ላይ ያለ መሆኑ በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ለኢንደስትሪው ዘርፍ ከተጣለው አማካይ ግብ 21.1 በመቶ አንጻር በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ በመሆኑ የተጀመሩ የኢንዱስትሪ መንደር ግንባታንና ሌሎች ሜጋ የግንባታ ፕሮጀክቶችን፤ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ይበልጥ ማጠናከርና የግል ባለሃብቱ በዘርፉ በስፋት እንዲሰማራ በርካታ የማበረታቻ ስትራተጂዎች እና ሰፋፊ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን አጠናክሮ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዠ 1፡ የክልሉ ጠቅላላ ምርት ዕድገት በመቶኛ

የኢኮኖሚ ዘርፍ	የ2009 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2010 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2011 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2012 ዓ.ም አፈፃፀም	የ5 ዓመት አማካይ አፈፃፀም	የ2012 ዓ.ም ግብ
የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች	10.9	8.1	9.8	9.0	9.4	7.8
ኢንዱስትሪ	7.6	17.3	5.0	5.6	8.9	24.2
አገልግሎት	9.3	9.4	10.4	8.6	9.4	9.9
አጠቃላይ ኢኮኖሚ	9.9	10.0	9.0	8.3	9.3	12.1

ምንጭ፡ ፕላን ኮሚሽን

ሠንጠረዠ 2፡- ዋና ዋና አኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የክልሉ ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ

የኢኮኖሚ ዘርፍ	የ2008 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2009 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2010 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2011 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2012 ዓ.ም አፈፃፀም	የ2012 ዓ.ም ግብ
የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች	58.5	59.0	58.0	58.4	58.8	41.8
ኢንዱስትሪ	18.2	17.8	19.0	18.3	17.8	24.0
አገልግሎት	23.3	23.2	23.0	23.3	23.4	34.2
አጠቃላይ ኢኮኖሚ	100	100	100	100	100	100

ምንጭ፡ ፕላን ኮሚሽን

1.3 የክልሉ ፊስካል ፖሊሲ

የክልሉ መንግሥት ፊስካል ፖሊሲ በክልሉ በመተግበር ላይ ያለውን የታክስ ፖሊሲ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በመተግበር የታክስ ገቢን ማሳደግ፣ የወጪ አመዳደብ በካፒታል ፕሮጀክቶችና ድህነትን በመዋጋት ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ማድረግ ነው።

የፊስካል ፖሊሲው ቁልፍ ዓላማ የክልሉን መንግሥት በጀት ጉድለት ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው የጠበበ በማድረግ በክልሉ ቀጣይ ኢኮኖሚ ዕድገት የተመቻቸና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠር ነው

1.3.1. የክልሉ የገቢ አፈጻጸም

ክልላዊ ጠቅላላ ገቢ አሰባሰባችን ሲታይ በ2008 በጀት ዓመት ብር 5.9 ቢሊዮን ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት 10.226 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰበሰ ተችሏል። ባለፉት አምስት ዓመታት በክልሉ በአማካይ ብር 7.994 ቢሊዮን ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን በሁለተኛ ዕ.ት.ዕ በአማካይ ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 9.486 ቢሊዮን አንፃር የ85.2 በመቶ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ለዚህ በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ በየደረጃው ከሚገኝ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተፈጠረው ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራር፣ ተግባሩ በሠራዊት ቅኝት በመፈፀሙ፣ የግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ ስለግብር/ታክስ ያለው ግንዛቤ እያደገ መሆኑ እና የተቋሙ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም እያደገ መሆኑን ያመለክታል።

የአምስት ዓመቱ አማካይ የገቢ አፈፃፀም አጥጋቢ ቢሆንም በተለይ በ2010፣ በ2011 እና በ2012 ዓ.ም በቅደም ተከተል ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 10.2 ቢሊዮን፣ ብር 11.0 ቢሊዮን እና ብር 12.0 ቢሊየን አንፃር ሲታይ የተሰበሰበው መጠን ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። ለዚህም ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ በወቅቱ በሀገር ደረጃና በክልላችን በነበረው ከፍተኛ የሆነ የለውጥ እንቅስቃሴ ህዝቡ በሚያነሳቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች አንጻር ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ግዴታውን ለመወጣት የነበረው ፍልሰት የተቀዛቀዘ በመሆኑ ነበር።

በአጠቃላይ ባለፉት አምስት ዓመታት የክልሉ የገቢ አሰባሰብ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም ዕ.ት.ዕ ላይ በክልሉ መንግሥት ከታቀዱ በርካታ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች፣ በሕዝቡ ውስጥ ከተፈጠረው አዳጊ የመልማት ፍላጎት እና ክልሉ ካለው አጠቃላይ ገቢ የማመንጨት አቅም አንፃር ሲታይ ተጨማሪ ጥረትና ቁርጠኝነት ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ይጠበቃል።

ሠንጠረዠ 3፡- ጠቅላላ የክልሉ የገቢ አፈፃፀም የአምስት ዓመት (ከ2008- 2012 ዓ.ም) በሚሊየን ብር

ተ ቁ	የገቢ ዓይነት	2008	2009	2010	2011	2012	የአምስት ዓመት አማካይ ገቢ በብር	የአምስት ዓመት አማካይ የገቢ ዕቅድ	አምስት ዓመቱ አማካይ ገቢ አፈጻጸም ንፅፅር በመቶኛ
1	መደበኛ ገቢ	5,139.8	6,016.40	7,333.80	7,755.08	8.777	6,986.88	8,288.72	84.29
1.1	ቀጥታ ታክስ	3,090.5	3,252.62	4,175.76	4,585.31	5,189.54	3,776.06	5,019.75	75.2
1.2	ቀጥታ ያልሆነ ታክስ	1,110.0	1,290.50	1,510.66	1,557.49	1,762.56	1,367.18	1,923.67	71.1
1.3	ታክስ ያልሆነ ገቢ	939.19	1,473.27	1,647.37	1,612.27	1,824.73	1,418.03	1,423.54	99.6
2	የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ	810.42	888.34	1,126.44	1,045.02	1.448	1,062.93	1,197.27	88.77
ጠቅላላ የክልሉ ገቢ		**5,950.2**	**6,904.7**	**8,460.2**	**8,800.1**	**10,226**	**8,049.4**	**9,485.99**	**84.85**

ስዕል-1፡ ጠቅላላ የገቢ አፈጻጸም (በብር)



ምንጭ ፡ የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን

የክልሉ ጠቅላላ ገቢ ከክልሉ ጠቅላላ ምርት ጋር ያለውን ጥምርታ ስንመለከት በ2008 ዓ.ም ከነበረበት 8.94 በመቶ በ2012 ዓ.ም ወደ 10.41 በመቶ እድገት ያሳየ ቢሆንም የክልሉ ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው ጠቅላላ ሀብት ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ በዘርፉ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ያሉትን ውስንነቶች በመቅረፍ ጥምርታው እንዲሻሻል ሰፊ ስራዎች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

1.3.2. የክልሉ የወጪ አፈጻጸም

የበጀት አፈጻጸም በ2007 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት የፀደቀዉ ጠቅላላ በጀት 20.972 ቢሊየን ብር ከነበረበት በ2012 የፀደቀ ጠቅላላ በጀት 40.056 ቢሊየን ብር ሲሆን የ2007 በጀት ከ2012 ጋር ሲነጻጸር የተከታታይ ዓመታት ዕድገት በአማካይ 14.12 በመቶ መሆኑን ያሳያል። ዝርዝሩን ቀጥሎ በተመለከተው ሥዕል 2 ላይ ማየት ይቻላል።

ስዕል 2 ፡- ተከታታይ ዓመታት የክልሉ በጀት



በአጠቃላይ ከ2008-2012 የተፈቀደው በጀት ዕድገት በአማካይ 14.12 በመቶ እያደገ የመጣ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በተከታታይ ዓመታት በክልሉ የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ ድርሻ በአማካይ 28 በመቶ ነው። በተከታታይ ዓመታት የጸደቀውን በጀት ከፍተኛው ድርሻ የያዛው የፌዴራል ድጎማ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። የዕርዳታ እና ብድር ድርሻ ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ መምጣቱ የሚጠበቅ ቢሆንም በዘያው ልክ የውስጥ ገቢ ዕድገት እየጨመረ ባለመምጣቱ ለወደፊት በክልሉ አጠቃላይ በጀት ላይ አሉታዊ ሚና መጫወቱ አይቀሬ መሆኑን ያሳያል። ስለሆነም በሚፈቀደው በጀት ላይ ከፍተኛውን ድርሻ መያዝ ያለበት ከክልሉ የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ በመሆኑ በትኩረት ሊሰራ ይገባል።

የፌዴራል ድጎማና በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢ ከጠቅላላ በጀት ጋር ያለዉ ድርሻ ሲታይ በ2003 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 76በ24 በመቶ ድርሻ ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 73በ27 በመቶ ድርሻ ሆኗል።

በሌላ በኩል የፌዴራል መንግስት ድጎማ ብር 4,684,549,984 ወደ ብር 28,924,656,493 ዕድገት ያሳየ ሲሆን እርዳታና ብድር ብር 126,240,000 ከነበረበት ወደ ብር 62,070,563 እየቀነሰ መሄዱ መልካም ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

ስዕል 3፡- ተከታታይ ዓመታት ከፌደራል ድጎማ፣ የክልሉ ገቢ እና ጠቅላላ ያልተሰበሰበ ገቢ ድርሻ በመቶኛ



የክልሉን የበጀት ክፍፍል በተመለከተ የክልል ባለበጀት መ/ቤቶች እና የታችኛው አስተዳደር እርከኖች የበጀት ድርሻ 2008 በጀት ዓመት 38/62 ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት 24/76 ሲሆን የተከታታይ ዓመታት አማካይ ድረሻ 31/69 በመቶ ነው።

የመደበኛና ካፒታል በጀት ድርሻን በሚመለከት በቅደም ተከተል በ2008 በጀት ዓመት ብር 15.050 ቢልየን (62 በመቶ) እና 9.041 ቢሊየን (38 በመቶ) ከነበረበት በ2012 ብር 30.610 ቢሊየን (76 በመቶ) እና 9.447 (24 በመቶ) ሲሆን አማካይ ዕድገቱ 69በ31 ነው። በክልል ባለበጀት መ/ቤቶች ከተመደበው በጀት ውስጥ በ2008 በጀት ዓመት ለካፒታል፣ ለመደበኛ በጀት (ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ) በቅደም ተከተል 58በ42 (44በ56) ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት 60በ40 (57በ43) የደረሰ ሲሆን የተከታታይ ዓመታት አማካይ ድርሻ 59በ41 (53በ47) በመቶ ነው።

የታችኛው አስተዳደር እርከኖች ከተመደበው በጀት ውስጥ በ2008 በጀት ዓመት ለካፒታል፣ ለመደበኛ በጀት (ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ) በቅደም ተከተል 33በ67 (73በ27) ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት 14በ86 (76በ24) የደረሰ ሲሆን የተከታታይ ዓመታት አማካይ ድርሻ 23በ77 (76በ24) በመቶ ሆኗል። ይህ መረጃ ሲታይ በክልል ባለበጀት መ/ቤቶች ከተመደበው በጀት ውስጥ ለካፒታልና ለሥራ ማስኬጃ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በጀት የሚመደብ

ሲሆን በታችኛው አስተዳደር እርከን ለካፒታልና ለስራ ማስኬጃ የሚመደበው በጀት ከደመወዝ በጀት ጋር ሲነጻጸር ድርሻቸው ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

በመሆኑም በተለይም የታችኛው አስተዳደር እርከኖች የተከታታይ ዓመታት የበጀት ዕድገት ሲታይ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም በተጨባጭ በክልሉ በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች መዋቅሮች በመስፋታቸው ከዕቅድ ውጪ ሀብትን ያላገናዘበ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ጭማሪዎች የመደበኛውን በጀት ድርሻ ከፍ በማድረጉ ምክንያት ከሚጠበቀው በላይ በካፒታልና ሥራ ማስኬጃ በጀት ድርሻ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ስለሆነም በጥናት ላይ በመመስረት የካፒታልና የሥራ ማስኬጃ በጀት ድርሻ በመቀነስ የመደበኛውን በጀት በዋናነትም የደመወዝ በጀት ድርሻ ከፍ የሚያደርጉ ጉዳዮችን በመለየት ማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ በቀጣይ መሪ ዕቅዱ ዘመን አሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ የሚሰራ ይሆናል።

ስዕል 4 ፡- ተከታታይ ዓመታት የመደበኛና ካፒታል በጀት ድርሻ በመቶኛ



የክልሉ መንግስት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመድበው በጀት በክልሉ ከሚመደበው ጠቅላላ በጀት አንጻር ሲታይ በ2008 በጀት ዓመት የተመደላቸው በጀት የጠቅላላ በጀትን 60.76 በመቶ ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት ከጠቅላላ በጀት ድርሻው 67 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በዚህም የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከማሳደግና መሠረታዊ አገልግሎትን ከማስፋፋት ጋር የተያያዙትን የግብርናና ገጠር ልማት፣ መንገድ፣ ትምህርት፣ ጤና እና ውሃ አቅርቦት በጀት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትኩረት የተሰጣቸውና ድህነትን በከተማ የመቀነስ ዓላማ ያላቸው የአነስተኛና ጥቃቅን እንዱስትሪዎች ልማት በጀት በዚህ መረጃ ላይ ቢካተት ለዕድገት ተኮር ተቋማት የሚመደበው በጀት ድርሻ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በጀት ዕድገት ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል።

ሠንጠረዥ 4፡ የተከታታይ ዓመታት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተፈቀደ በጀትና ወጪ አፈጻጸም (በብር) እና ድርሻ (በመቶኛ)

የበጀት ዓመት	ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተፈቀደ በጀትና ወጪ አፈጻጸም		
	የተፈቀደ በጀት	የወጪ አፈጻጸም	የወጪ አፈጻጸም በመቶኛ
2008	13,637,775,939	11,687,419,796	86
2009	17,834,770,768	15,094,796,440	85
2010	18,539,534,537	16,823,317,667	91
2011	22,463,293,220	18,842,067,854	84
ተከታታይ ዓመታት አማካይ አፈጻጸም			**86.5**

ከፍ ሲል ባለው ሠንጠረዥ በተመለከተው መረጃ መሠረት የዕድገት ተኮር ሴክተሮች ከተፈቀደው በጀት አንፃር በስራ ላይ ያልዋለ በጀት አፈጻጸም አማካይ 13.5 በመቶ በመሆኑ ወደ ፊት በተፈቀደው በጀት መሠረት በወቅቱ ሥራዎችን በማከናወን አፈጻጸሙን ማሻሻል ያስፈልጋል።

ሥዕል 5፡- የተከታታይ ዓመታት ለዕድገት ተኮር ተቋማት የተፈቀደ በጀትና የወጪ አፈጻጸም ድርሻ በመቶኛ



1.4. የክልሉ የቁጠባ ሁኔታ

በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠይቀው የኢንቨስትመንት መጠን ከፍተኛ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዱና ዋናው ፈታኝ ጉዳይ ለኢንቨስትመንቱ መሸፈኛ የሚያስፈልገው የአገር ውስጥ ፋይናንስ ግኝት ነው። በተለይም የክልሉ የቁጠባ መጠን በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ በመሆኑ ልማቱን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በከፊል ለማቅረብ እንዲቻል የክልሉን የውስጥ የቁጠባ ምጣኔውን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዶ ተግባር ውስጥ ተገብቷል። ይህንን የክልሉን የቁጠባ መጠን የማሳደግ ግብ ለማሳካት በዕቅድ ዘመኑ በርካታ የማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል።

ከነዚህም መካከል የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ የማስተማርና የማነሳሳት እንቅስቃሴዎች፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ተቋማት እስከ ወረዳ ማስፋፋትና በቀበሌ ደረጃ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ኤጀንቶችን፣ የግል ማህበራዊ ዋስትና አገልግሎትን መዘርጋት እና እንዲሁም በልዩ ንቅናቄ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቁጠባ ቦንድና ሌሎች በጅምር ላይ ያሉ የቁጠባ መሳሪያዎችን መጥቀስ ይቻላል። በተጨማሪም በቂ ባይሆንም የመንግስት ወጪን በዋነኝነት በክልል ማዕከልና በተወሰኑ አስተዳደር እርከን የካፒታል ክምችት ለሚፈጥር የኢንቨስትመንት ወጪ በመመደብ እና አብዛኛውን በጀት እድገትን ለሚያፋጥኑ ድህነት ቅነሳ መ/ቤቶች በመመደብ እና የወጪ አጠቃቀም ብክነትን በመቀነስ ውስን የሆነውን የፋይናንስ ሀብት ለታለመለት ዓላማ ለማዋል የተደረገው ጥረት የክልሉን ቁጠባ ከፍ እንዲል አግዟል። እነዚህ የክልሉ ቁጠባን ለማሳደግ የተወሰዱ እርምጃዎች ውጤት ማስገኘታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ።

የክልሉ አጠቃላይ ምርት መጠን አጠቃላይ ፍጆታ "የመንግስት ወጪ እና የግል ኢንቨስትመንት እንዲሁም ቁጠባን" የሚያካትት መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት የቁጠባ ምጣኔ ትርጉም ባለው ደረጃ መጎልበት የክልሉን ኢንቨስትመንትን በላቀ ደረጃ ከማሳደግ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ይታወቃል። በመሆኑም በፋይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ በተደረገ ጥናት ከባንኮችና ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በ2009 ዓ.ም መጨረሻ ጥቅል የተከማቸ የገንዘብ ቁጠባ (Total Financial Saving) 29.5 ቢሊዮን ብር መኖሩን የሚያመለክት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 17.3 ቢሊዮን የተረጋጋ ቁጠባ (Saving Deposite & Time Deposite) ነው።

የክልሉ አጠቃላይ የቁጠባ ምጣኔ በተመለከተ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት እየተስፋፋ ያለውን የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎት በመጠቀምና የህዝቡን የቁጠባ ባህል የበለጠ በማነቃቃት 29.6 በመቶ ሀገራዊ ቁጠባ ለማሳካት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ባለፉት የዕ.ት. ዕ ዓመታት በአማካይ 28.13 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ተመዝግቧል። በቁጠባ ዙሪያ የተገኘውን መልካም አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታትም ማስቀጠል እጅግ አስፈላጊ ነው።

1.5. የክልሉ የሥራ አጥነት ሁኔታ

በዕ.ት. ዕ ዕቅድ የተያዘው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበራዊ ልማት በዜጎች የሥራ ስምሪት እና የኑሮ ደህንነት ሁኔታ መገለፅ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህም የታቀደው ፈጣን የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ልማት ትልቅ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም በሌሎች መስኮች የግል ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ሥራዎችን ለሥራ ዕድል ፈጠራ ማዋል እና በመንግስት የሚካሄድ የልማት ፕሮግራሞች የሥራ ዕድሎችን እንዲያስፋፉ ለማድረግ ታቅዷል።

በክልሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ሥር ከሚካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገት ሁኔታ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ (የዋጋ ግሽበትና የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ሁኔታ) እንዲሁም የሥራ አጥነት ሁኔታ መሆናቸው ይታወቃል። በዚህም መሠረት የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከፌደራሉ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ባደረጉት ጥናት በ2006 በጀት ዓመት የክልሉ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ 15.9 በመቶ እንደነበር ያመለክታል።

ከዚህም በተጨማሪ በ2011 ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተካሄደ ጥናት ሪፖርት መሠረት የክልላችን የሥራ አጥነት ሁኔታ 18.0 በመቶ እንደነበር ያመለክታል። ይሁን እንጂ አሁን ያለውን የከተማና ገጠር የስራ አጥነት ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሳይንሳዊ ጥናት መደረግ እንዳለበት ያመለክታል።

ምዕራፍ ሁለት

የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

2.1. የግብርና ልማት አፈጻጸም

የግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አኳያ የሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ሲዘጋጅ የትኩረት አቅጣጫ የነበሩት የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ የመስኖ ልማትን ማስፋት፣ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ፣ የግብዓትና ምርት ግብይት ማቀላጠፍ፣ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ መጨመር ዋነኞቹ የትኩረት መስኮች የነበሩ ሲሆን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ማረጋገጥ፣ በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው እድገት ማምጣት፣ የህዝቡን ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚ በዘርፍ ደረጃ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል የሚሉት ዋና ዋና ግቦች ነበሩ።

የግብርና እድገት ከ2008 እስከ 2012 በጀት ዓመት በክልላች በአማካይ በዓመት 9.4 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ በዕቅድ ከተያዘው 8 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።

የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት አፈጻጸም

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አንጻር የአዝርዕት ሰብሎች ምርት በ2007 ምርት ዘመን ከነበረው 34.94 ሚሊዮን ኩንታል በ2012 ምርት ዘመን 64.88 ሚ/ን ኩ/ል ለማድረስ ታቅዶ 43.09 ሚ/ን ኩ/ል የደረሰ ሲሆን ከዕቅድ አንፃር 66.4 በመቶ እንደደረሰ ያሳያል። ይህም በ2007 ምርት ዘመን ከነበረው ምርት አንጻር በየአመቱ በአማካይ በ5 በመቶ የምርት ዕድገት አሳይቷል።

የአገዳ ሰብል ምርታማነት ከ30.1 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 55.1 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ በ2012 ምርት ዘመን ወደ 35.7 ኩ/ል በሄ/ር፣ የብርዕ ሰብሎች ምርታማነት ከ17.62 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 34.1 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 25 ኩ/ል በሄ/ር፣ ጥራጥሬ ሰብል ምርታማነት ከ13.66 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 24.7 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 17.8 ኩ/ል በሄ/ር እና ቅባት ሰብሎች ምርታማነት ከ4.79 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 7.4 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 6.4 ኩ/ል በሄ/ር እንዲሁም የጭረት ሰብሎች ምርታማነት ከ17 ኩ/ል በሄ/ር የነበረውን ለማስቀጠል ታቅዶ ወደ 19.2 ኩ/ል በሄ/ር ምርታማነት ጭማሪ አሳይቷል።

የኤክስፖርት ምርቶች ልማት በተመለከተ የሰሊጥ ልማት በ2007 ምርት ዘመን 8,581 ሄ/ር በማልማት 0.04 ሚሊ. ኩ/ል ምርት በ2012 ዓ.ም 28,413 ሄ/ር መሬት በማልማት 0.14 ሚሊ. ኩ/ል ማምረት የተቻለ ሲሆን ምርታማነትን ከ4.7 ኩ/ል ወደ 5.1 ኩ/ል ማድረስ ተችሏል። የቦሎቄ ምርት በ2007 ዓ.ም 195,939 ሄ/ር በማልማት 2.56 ሚሊ. ኩ/ል ምርት በ2012 ዓ.ም 226,376 ሄ/ር መሬት በማልማት 3.82 ሚሊ. ኩ/ል ማምረት የተቻለ ሲሆን ምርታማነትን ከ13.2 ኩ/ል ወደ 17 ኩ/ል ማሳደግ ተችሏል።

ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሆኑ ሰብሎች ልማት አፈጻጸም አንጻር የስንዴ ልማት በ2007 ዓ.ም በ120,566 ሄ/ር በማልማት 3,209,461 ሚሊ. ኩ/ል ምርት የተመረተ ሲሆን በ2012 ዓ.ም 184,637 ሄ/ር መሬት በማልማት 7,255,820 ኩ/ል በማምረት ምርታማነት ከ26.62 ኩ/ል ወደ 40 ኩ/ል በሄክታር ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የቢራ ገብስን በ2008 ዓ.ም 10,474 ሄ/ር በማልማት 334,698 ኩ/ል የተመረተ ሲሆን በ2012 ዓ.ም 8,001 ሄ/ር በማልማት 233,988 ኩ/ል ምርት ተገኝቷል። ከምርታማነት አንጻር በ2012 ዓ.ም 29 ኩ/ል በሄክታር ተገኝቷል።

የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርት አፈፃፀም አንጻር የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርት 61.3 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 174.8 ሚ/ን ኩ/ል ለማድረስ ታቅዶ 173.6 ሚ/ን ኩ/ል የተመረተ ሲሆን ይህም በየአመቱ በአማካይ 5.3 በመቶ የምርት ዕድገት አሳይቷል።

ከምርታማነት አኳያ የአትክልት ሰብል ከ110.4 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 217 ኩንታል በሄ/ር፣ የስራስር ሰብሎች ከ244 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 239 ኩንታል በሄ/ር፣ በፍራፍሬ ሰብሎች ከ105.6 ኩ/ል /ሄ/ር ወደ 257.7 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አዳዲስ መድሃኒት የሌላቸው በሽታዎች በመከሰታቸው ምክንያት የእንሰት ሰብል ከ279 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 239 ኩ/ል ዝቅ ብሏል።

ከመስኖ ልማት አኳያ በክልላችን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ አቅም በህዝብ ንቅናቄ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት በሰፊው በመሰራቱ እየበለጸገ በመምጣቱ የመስኖ ውሃ አማራጮች እየሰፋ ይገኛል። በዚህም ወንዞች፣ ምንጮች፣ የእጅ ጉድጓድ፣ መለስተኛና ጥልቅ ጉድጓድ፣ የቤተሰብና የማህበረሰብ ኩሬ አማራጮች በመዳሰስ እያንዳንዱ አርሶ አደር ቢያንስ የአንድ ውሃ ባንክ ባለቤት እንዲሆን ጥረት በመደረጉ በ2007 መነሻ ዓመት ላይ በባህላዊና ዘመናዊ መስኖ የለማው መሬት 449,000 ሄ/ር ከነበረበት በ2012 ዓ.ም በአንደኛ ዙር እና በሁለተኛ ዙር 313,127 ሄ/ር በማነስ የለማ ቢሆንም በመስኖ በ2007 ዓ/ም 69 ሚሊዮን ኩ/ል ከነበረበት በ2012 ዓ/ም 74 ሚሊዮን ኩ/ል ማምረት በመቻሉ 7 በመቶ እድገት (5 ሚሊ. ኩ/ል) ጭማሪ አሳይቷል።

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ስራዎች አፈጻጸም በተመለከተ የቡና ምርትን ለማሳደግ የቡና ማሳን ከ455,473 ሄ/ር ወደ 598,566 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 608,515 ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን የቡና ምርትን ከ313,000 ቶን ወደ 568,971 ቶን ምርት ለማድረስ ታቅዶ 474,652 ቶን ምርት ማምረት የተቻለ ሲሆን ዓመታዊ አማካይ 416,325 ቶን ተመርቷል። የቡና ምርታማነትን ከ8.5 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 10.5 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ የ5 ዓመታት አማካይ አፈጻጸም 8.58 ኩ/ል በሄ/ር ማምረት ተችሏል።

የቡና ምርት ግብይትን በማሻሻል በግሉ ሴክተርና በህብረት ሥራ ማህበራት በ2007 ዓ.ም ለማዕከላዊ ገበያ የቀረበዉን በዓመት 78,269.24 ቶን ቡና መጠን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 128,200 ቶን ለማድረስ ግብ ተጥሎ በተሰራው ሥራ 96,150 ቶን ማድረስ የተቻለ ሲሆን የ5ቱ ዓመት አማካይ አቅርቦትም 95,761.2 ቶን ሊሆን ችሏል።

የቅመማ ቅመም ግብይትን በተመለከተ በ2007 ዓ.ም 118,860 ቶን የነበረውን አቅርቦት በ2012 በጀት ዓመት 203,372 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 193,204.4 ቶን በዓመት ለገበያ ማቅረብ የተቻለ ሲሆን የ5ቱ ዓመት አማካይ አቅርቦትም 148,910.4 ቶን ሆኗል። የሻይ ግብይትን በተመለከተ በ2007 ዓ.ም 4,531.2 ቶን የነበረውን አቅርቦት በ2012 በጀት ዓመት 9,600 ቶን ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 7,497.2 ቶን ለገበያ ማቅረብ የተቻለ ሲሆን የ5ቱ ዓመት አማካይ አቅርቦትም 5,737.62 ቶን ሆኗል።

ከተፋሰስ ልማት ሥራዎች አንጻር ትላልቅ ተፋሰሶች ወደ ትናንሽና የማህበረሰብ ተፋሰሶች በመከፋፈል ያሉባቸውን የጉዳት ደረጃ በመለየት በጥናት ላይ የተመሠረተ የልማት እቅድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲፈፀሙ በማድረግ በ2007 ዓ.ም 3,689 የነበረው የማህበረሰብ ተፋሰሶች ቁጥር ወደ 18,800 ለማድረስ ታቅዶ ወደ 19,889 (+100) ን/ተፋሰስ ለማድረስ ተችሏል። የማህበረሰብ ተፋሰሶች በተለያዩ የፊዚካል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ከመሸፈን አንጻር 1,721,360 ሄ/ር የነበረውን ወደ 3,679,242 ሄ/ር ለማሳደግ ታቅዶ 3,718,753.25 (+100%) ሄ/ር ማድረስ ተችሏል። በተለያዩ የፊዚካልና ስነሕይወታዊ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ሥራዎች ጥገናና እድሳት የተደረገላቸዉ የማህበረሰብ ተፋሰሶች 8,123,824 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 2,573,544 (31.7%) ሄ/ር ማከናወን ተችሏል ።

ስነ-ህይወታዊ ሥራዎች አፈጻጸም አንጻር በዕቅድ ዘመን 4,244 ኩ/ል ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,952.3 ኩ/ል (+100%) ለማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን 6.5 ቢሊዮን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የሚሰጡ ችግኞች ለማዘጋጀት ዕቅድ ተይዞ 4.66 ቢሊዮን (71.6%) ችግኝ ለማፍላት ተችሏል። 1,167.9 ሄ/ር መሬት ላይ 4.9 ቢሊዮን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞችን ለመትከል በዕቅድ ተይዞ 3.55 ቢሊዮን (72.45%) ተከናውኗል።

የግብርና ግብዓት አፈጻጸም በተመለከተ በዕ.ት. ዕ ዘመን ዓመታዊ የሰብል ምርጥ ዘር አቅርቦት ከ150,297 ኩንታል ወደ 377,332 ኩ/ል ለማድረስ ታቅዶ በተለያዩ የዘር አባዣች አማካይነት 172,910 ኩ/ል (45.8%) ምርጥ ዘር ማቅረብ የተቻለ ሲሆን በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በመጨመር እድገት አሳይቷል። እንዲሁም የሥራስር ሰብሎች ምርጥ ዘር አቅርቦት በ2011/12 ምርት ዘመን መጨረሻ 390,114 ኩ/ል ለማድረስ ታቅዶ በተለያዩ የዘር አባዣች አማካይነት 379,374 ኩ/ል (97%) ማቅረብ ተችሏል። በተጨማሪም የጓሮ አትክልት ምርጥ ዘር አቅርቦት ከ119 ኩንታል ወደ 4,023 ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ 1,112 ኩ/ል (28%) ቀርቦ ተሰራጭቷል።

የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት በተመለከተ በክልላችን ዋና ዋና የአፈር ማዳበሪያ ኤን.ፒ. ኤስ እና ዩሪያ ሲሆኑ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1,773,540 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ 1,773,540 ኩ/ል (100%) የአፈር ማዳበሪያ ቀርቦ ተሰራጭቷል። የፀረ-አረም፣ ፀረ-በሽታና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አቅርቦትና ስርጭት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 237,520 ሊ/ር ለማቅረብ ታቅዶ 84,291 ሊ/ር (35%) ቀርቦ ተሰራጭቷል።

የግብርና ምርምር ሥራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ በግብርና ዘርፍ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመቅረፍ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን ለተጠቃሚው ከማቅረብ አንጻር በሰብል ምርምር 50 ታቅዶ 55፣ በተፈጥሮ ሀብት 31 ታቅዶ 29 እና በእንስሳት 30 ታቅዶ 30 ማቅረብ ተችሏል። የቅድመ ኤክስቴንሽን ሠርቶ ማሳያ፣ ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ ማስፋት ሥራዎችን ለማሳደግ በ135 ገመማዎች ላይ በሠርቶ ማሳያዎች ለማከናወን ታቅዶ 110 ሰርቶ ማሳያዎች/ገመማዎች/ ላይ ማስተዋወቅ ተችሏል። የተለያዩ የአዝርዕት፣የሥራሥር እና ዓሳ መነሻ ቴክኖሎጂ አቅርቦትን የማሻሻል ሥራ ተሰርቷል።

ከኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎች አንጻር 6,010 አዳዲስ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ታቅዶ 5,237 (87%) ማደራጀት ተችሏል። እንዲሁም 19 የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ለማደራጀት ታቅዶ 6 (32%) ዩኒየኖችን ማደራጀት ተችሏል። የተለያዩ የገንዘብ ምንጮችን ተጠቅሞ ብር 1,085,976,375 ካፒታል በማፍራት የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትና የዩኒየኖችን ካፒታል ለማሳደግ ታቅዶ ብር 1,965,826,849 (+100%) ካፒታል ማፍራት ተችሏል።

የመሰረታዊ የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማ እና የዩኒየኖች ቁጠባና ብድር በተመለከተ 1,825,633,021 ብር ቁጠባ ለማስቆጠብ ታቅዶ 1,173,548,215 ብር (64%) ቁጠባ ማስቆጠብ የተቻለ ሲሆን 1,608,614,831 ብር ብድር ላይ ለማዋል ታቅዶ 1,453,396,343 ብር (85%) ብድር ላይ ማዋል ተችሏል።

ለኅብረት ሥራ ማሕበራት የምርት ግብይት ፋይናንስ ከማመቻቸት አንጻር በ5 ዓመት ዉስጥ ለ10,322 ሕብረት ሥራ ማሕበራት 13,721,656,818 ብር የብድር አቅርቦት ለማመቻቸት ታቅዶ ለ3,393 (33%) ህብረት ሥራ ማህበራት 8,631,629,537 ብር (63%) የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም የግብዓት ብድር አቅርቦት 18,099,631,060 ብር ለማመቻቸት ታቅዶ 12,818,325,715 ብር (71%) ብድር የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል።

ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም እንደሚያሳየው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ በምርትም ሆነ በምርታማነት መሻሻሎች የታዩበት ቢሆንም ባለፉት አራት ዓመታት ጎልቶ የታየው የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ሁኔታ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሥርዓት ኋላቀርነት፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር፣ ያልዘመነ የምርት ገበያ እና ህገ ወጥ ግብይትና ዝውውር፣ የኢንቨስትመንት እና የማሰፈጸም አቅም ውስንነት ዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም እንዳያሳይ ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች ነበሩ።

የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት አፈጻጸም

ከእንስሳት ምርትና ምርታማነት አኳያ የሥጋ ምርት በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 289,469 ቶን በ2012 በጀት ዓመት 463,566 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 389,395 ቶን (83.9%) ዓመታዊ ምርት በማድረስ 25.7% ዕድገት ያሳየ ሲሆን የተሻሻሉ ታላቢ ላሞችን ምርታማነት በማሳደግ ዓመታዊ የወተት ምርት ከ975,363 ቶን ወደ

1,098,631 ቶን የተመረተ ሲሆን ይህም 2007 ምርት ዘመን ከነበረው ጋር ሲነጻጸር 11 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። እንዲሁም ዓመታዊ የእንቁላል ምርትን 20,615 ቶን ወደ 31,455 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 27,293 ቶን በማድረስ የ24% እድገት አሳይቷል። የስጋ ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ ዳልጋ ከብት የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት (carcas weight) ከ120 ኪሎ ግራም ወደ 130 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዶ 129 ኪሎ ግራም (99%) በማድረስ 7% እድገት አሳይቷል። እንዲሁም ከአንድ በግ የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት (carcas weight) ከ13 ኪሎ ግራም ወደ 14.5 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዶ 14.4 ኪሎ ግራም (99.3%) ደርሷል፤ ይህም የ9.7% እድገት አሳይቷል።

የወተት ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ ሀገር በቀል እንስሳት ዝርያ የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት ከ1.75 ሊትር ወደ 2.3 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ 2 (87%) የደረሰ ሲሆን በ12.5% እድገት አሳይቷል። ከአንድ ዲቃላ የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት ከ10 ሊትር ወደ 14.5 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ 13.5 ሊትር (93%) ማድረስ ተችሏል። ይህም 26% እድገት አሳይቷል። ዓመታዊ የቆዳና ሌጦ ምርትን ከ4,300,000 ወደ 5,930,000 ለማድረስ ታቅዶ 4,700,000 (79%) በማድረስ የ8.6% እድገት ያሳየ ሲሆን ዓመታዊ የማር ምርትን ከ22,280 ቶን ወደ 40,708 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 40,650 ቶን (99.8%) በማድረስ የ45% እድገት አሳይቷል። ዓመታዊ የዓሳ ምርትን ከ10,658 ቶን ወደ 25,002 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 22,966 ቶን (92%) ደርሷል፤ ይህም በ2007 ከተመረተው ጋር ሲነፃፀር የ53.6% እድገት አሳይቷል።

ከእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ሥራ አኳያ የዳልጋ ከብት ዝርያን በመደበኛ ማዳቀል አገልግሎት በ2007 ዓመት 95,763 የማዳቀል አገልግሎት በመስጠት በ2012 ዓ/ም ወደ 179,120 ማድረስ የተቻለ ሲሆን በ2007 ከዚህ አገልግሎት 31,881 ጥጃ ከነበረበት በ2012 ዓ/ም 99,983 ማድረስ ተችሏል። በሆርሞን የማድራት ቴክኖሎጂ በ2007 ዓ.ም ድረስ 199,104 ላሞችና ጊደሮች ተዳቅለው 37,588 ጥጆች ተገኝተዋል። ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ለ309,435 የዳልጋ ከብት ሆርሞን በመስጠት 280,255 የዳልጋ ከብት ማዳቀል የተቻለ ሲሆን በ2007 ከዚህ አገልግሎት 15,528 ጥጃ ከነበረበት በ2012 ዓ/ም 22,245 በማድረስ በጠቅላላ 108,118 ማግኘት ተችሏል። በተሻሻለ ኮርማ የሚካሄደውን ድቀላ ደረጃ በደረጃ ለመቀነስ ቢታቀደም በማዳቀያ ግብዓት እጥረትና የአርሶ አደሩን ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ በተሻሻሉ የኮርማ ዝርያ የሚደረገውን ድቀላ በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 22,075 በ2012 ወደ 60,920 ያደገ ሲሆን 31,519 ጥጆች ማድረስ ተችሏል። በአጠቃላይ የዳልጋ ከብት ዝርያ ለማሻሻል በመደበኛ፣ በሲንክሮናይዜሽንና በኮርማ በተሰጠ አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሲሆን በ2007 ይካሄድ የነበውን 224,984 የማዳቀል ስራ በ2012 መጨረሻ 285,383 ማድረስ በመቻሉ የሚወለዱ ዲቃላ ጥጆች ከ75,502 ወደ 153,747 በማድረስ በነዚህ አመታት የተወለዱ ዲቃላ ጥጆች ብዛት 606,446 ሲሆን በክልሉ ጠቅላላ ዝርያው የተሻሻለ ዝርያ 790,280 ማድረስ ተችሏል።

የ1 ቀን ዕድሜ ጫጩት ፍላጎት ፈጥሮ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ አንፃር በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 457,436 በ2012 ዓ/ም ወደ 6,889,175 ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም ቄብና ኮክኔ ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ለሴቶችና ወጣቶች ፍላጎት ፈጥሮ ተጠቃሚ የተደረገው በ2007 ዓ/ም 7,757,211 ከነበረበት በ2012 ዓ/ም 6,475,401 ማድረስ ተችሏል።

የተሻሻለ እንስሳት መኖ ልማት በ2007 ከተመረተው 63,250 ሄ/ር በ2012 በጀት አመት 128,043.5 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 116,121.5 (90.7%) ሄ/ር መሬት የለማ ሲሆን በ45.5 % እድገት ያሳየ ሲሆን ከዝርያ ማሻሻል ጋር አቀናጅቶ ለማልማት 2007 የነበረውን 20,296.6 ሄ/ር ወደ 36,682 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 34,163.7(93%) ሄ/ር መሬት ማልማት ተችሏል። ይህም በ40.5 % እድገት አሳይቷል።

የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋንን ለማሳደግ ድንበር ዘለልና መደበኛ የእንስሳት በሽታዎችን ከመከላከል አንጻር በ2007 ከነበረው የክትባት አፈጻጸም 20,330,000 ዶዝ በ2012 በጀት አመት ወደ 42,151,051 ዶዝ ለማሳደግ ታቅዶ 34,563,862 (82%) ዶዝ ክትባት ለተለያዩ እንስሳት ተሰጥቷል። አፈፃፀሙም ከ2007 ጋር ሲነፃፀር በ 41.1 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

የእንስሳት ጤና መሠረተ-ልማት ግንባታን በተመለከተ በ5 አመቱ የእንስሳት ጤና ክሊኒክ 51 እና የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ 525 ለመገንባት ታቅዶ በወረዳዎች፣ በዞኖችና በከተማ አስተዳደሮች በጀት በአግባብ አለመመደብ እና በሕብረተሰብ ተሳትፎ የእንስሳት መሠረተ ልማት ከመገንባት አንጻር ክፍተቶች በመኖራቸው ምክንያት 19 (37%) ክሊኒክ እና 193 (35%) ጤና ኬላ ለመገንባት ተችሏል።

በአጠቃላይ ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም እንደሚያሳየው የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ በምርትም ሆነ በምርታማነት መሻሻሎች የታዩበት ቢሆንም ባለፉት አራት ዓመታት ጎልቶ የታየው የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ሁኔታ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሥርዓት ኋላቀርነት፣ በቂ ያልሆነ መሰረተ ልማትና ኢንቨስትመንት እና ተቋማዊ የማሰፈጸም አቅም ውስንነት ዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም እንዳያሳይ ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች ነበሩ።

ባለፉት ዓመታት የግብርናው ዘርፍ ለክልሉ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ ከማድረግ፣ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ እና ለሌሎች ዘርፎች አስተማማኝ ግብዓቶችን ከማቅረብና ለምርቶች ገበያ ከመፍጠር አንጻር ዘርፉ ውስንነት ነበረበት። ዘርፉ የክልሉን ሕዝብ የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ያልቻለ ሲሆን በርካታ ዜጎች በቂ ምግብ እንደማያገኙ ይገመታል። በመሆኑም 1,039,959 የኅብረተሰብ ክፍሎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም የታቀፈው ሲሆን የዘርፉን የሰው ኃይል ምርታማነት ዕድገትና የምርቶችን ምርታማነት ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ምርቶች የማሸጋገር ሂደቱ ደካማ በመሆኑ አሁንም የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል።

በአጠቃላይ አፈጻጸሙ እንደሚያሳየው ዘርፉ በምርትና ምርታማነት መሻሻሎች የታዩበት ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥ፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሥርዓት ኋላቀርነት፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር፣ ያልዘመነ የምርት ገበያ፣ በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማትና ኢንቨስትመንት፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና ባለፉት አራት ዓመታት ጎልቶ የታየው ሃገራዊና ክልላዊ የፖለቲካ ሁኔታ ዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም እንዳያሳይ ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች ነበሩ።

2.2. የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች አፈጻጸም

የክልሉን አርብቶና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች መሰረታዊ የልማት ችግሮችን ለመፍታት በዋና ዋና የዕድገት አመልካቾች ላይ ያነጣጠሩ የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ የቆየ ሲሆን የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭና ሀብት የሆነውን የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር 4 የመኖ ዘር ማባዣ ጣቢያዎችና 8 የመኖ ባንኮች ማቋቋም የተቻለ ሲሆን እስከ አሁን 564,014 ቤል የመኖ ምርት በመኖ ባንኮች የማከማቸት እንዲሁም 11,010 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሽ በመከለልና ተበይ ካልሆኑ ዕጽዋት በማጽዳት እና 1,841 ሄ/ር የተጎዳ መሬት እንዲያገግም የተለያዩ እስትራክቸሮችን በመስራት ማልማት ተችሏል። ለእንስሳቱ የመጠጥ ውሃ ለማቅረብም በርካታ ባህላዊና ዘመናዊ የውሃ ግንባታዎች የተከናወኑ ሲሆን በተለያዩ የውሃ ተቋማት አካባቢ 180 የእንስሳት ውሃ ማጠጫ ገንዳዎች፤ 23 የእንሰሳት የህክምና መስጫ በረት እና 2 የእንሰሳት ማዳቀያ ክራሽ ግንባታ ተከናዉኖ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ከእንስሳት ጤና አንፃር የተገነቡ 72 የጤና ኬላዎች እና ኪሊኒኮች ሲሆኑ ለ2,946,120 ለተለያዩ እንስሳቶች ክትባት መስጠት ተችሏል። በአካባቢዉ የተሻሻሉ እንሰሳት ዝርያዎች ፍየሎች 5,006፤ የዳልጋ ከብቶች (ጊደሮችና ኮርማዎች) 3,242 እና ዶሮዎች 9,938 ለአርብቶ አደሩ ተሰራጭተዋል። በዚህ ምክንያት ለአካባቢዉ እንሰሳት ምርታማነት መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም በተከታታይነት ከማስፋት አንፃር ብዙ መስራትን ይጠይቃል።

ባለፉት ዓመታት 780 የተለያዩ የመጠጥ ውሀ ተቋማት ግንባታን በማጠናቀቅ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። ከዚህ የተነሳ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ከ32% ወደ 46.89% በማሳደግ የማህበረሰቡን ችግር ለማቃለል ጥረት ተደርጓል። ይሁንና የአርብቶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ የተበታተነና አካባቢዉ ደረቃማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አሁንም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህብረተሰብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ባለመሆኑ በቀጣይ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

ከትምህርት ልማት አኳያ 219 የመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ እና 2ኛ ሳይክል ት/ቤቶች፣ 22 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና 3 የመሰናዶ ት/ቤቶች አገልግሎት መስጠት በመቻላቸው 296,126 ወይም ከአጠቃላይ የአርብቶ አደር ህዝብ 41% ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛና መሰናዶ ት/ቤቶች ገብተው እንዲማሩ ተደርጓል። በእነዚህ በተገነቡ የትምህርት ተቋማት አርብቶ አደሩ ግንዛቤዉ እየጨመረ በመሄዱና የትምህርትን ጠቃሚነት በመረዳቱ በመደበኛ ትምህርት ልጆቹን በፈቃደኝነት ማስተማር ጀምሯል። በቦታ ርቀትና በተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ አስተሳሰቦች መማር ለማይችሉ

የአርብቶ አደሩ ልጆች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ በአካባቢያቸው በተገነቡት ዘጠኝ ሆስቴሎች አስፈላጊው የሰው ኃይል ተመድቦላቸው የምግብ፣ የመኝታ፣ የሕክምና፣ ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ የደንብ ልብስ፣ የጽህፈት መሳሪያና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች በመስጠት ባለፉት ዓመታት 18,140 ተማሪዎች ተመዝግበዉ የሆስቴል አገልግሎት በማግኘት ትምህርታቸዉን መከታተል ችለዋል።

2.3. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አፈጻጸም

በሁለተኛው የዕ.ት.ዕ ትኩረት ከተሰጣቸው መስኮች አንዱና ዋነኛው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ሲሆን ይህም ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን ነው። የዕ.ት.ዕ አፈጻጸም ክልላዊ ግምገማው የሚያሳየው ባለፉት ዓመታት የኢንዱስትሪ ዘርፍ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 8.9 በመቶ መሆኑን ያሳያል።

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ልማት ዘርፍ በክልላችን ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር በገጠርና በከተማ ለ3,740,166 ተጠቃሚዎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ3,871,899 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን ይህም በገጠር በቋሚ እና በጊዜያዊ ለ1,572,365 ወጣቶች እና በከተማ ለ2,299,534 ዜጎች (1,243,180 ቋሚና 1,056,354 ጊዜያዊ) የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። በገጠር የዕቅዱ 71 በመቶ ብቻ መፈፀሙና በከተማ 46 በመቶ በጊዜያዊ ስራ ላይ የተፈጠረ መሆኑ እንደጉድለት ተገምግሟል።

የማምረቻ ቦታ፣ ሼድ እና የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ በገጠር 231,116 ሄ/ር ታቅዶ 84,046 ሄ/ር (36.3%) የመስሪያና ማምረቻ መሬት ለወጣቶች የተላለፈ ሲሆን በከተማ 2,126 ሄክታር የለማ መሬት ለማዘጋጀት እና 4,976 ሼድ ለመገንባት ታቅዶ 2,800 ሄክታር መሬት በማዘጋጀት እና 8,699 ሼዶች በመገንባት ለኢንተርፕራይዞች ማስተላለፍ ተችሏል። አፈጻጸሙ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ሲነጻጸር ጥሩ ቢሆንም ተገንብተው ለተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሼዶችና ህንጻዎች የመሰረተ ልማት አለመሟላት፣ የተገነቡበት ቦታ ለገበያ ምቹ አለመሆንና የሚቀርበው የመስሪያ ቦታ የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ያለመሆን ችግር ተስተውሏል። በዕቅድ ዘመኑ 107 የምርት ማሳያና መሸጫ ህንፃዎችን ለመገንባት ታቅዶ 99 (92.5%) ህንፃዎች የተገነቡ ሲሆን ሁሉም ህንጻዎች ለ460 የኢንዱስትሪ ባለቤቶች በማስተላለፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በከተማ ቀደም ሲል የተደራጁትንም ሆነ ወደ ዘርፉ በአዲስ መልክ የሚገቡትን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራ ለማስጀመር ወይም ለማስፋፋት የፋይናንስ አቅርቦት ወሳኝ በመሆኑ የብር 3,370,665,246 ብድር ለማመቻቸት ታቅዶ 3,906,778,132 ብር ብድር ተሰራጭቷል። ከዚህ ጎን ለጎን በዘርፉ ያለዉን የፋይናንስ እጥረት ለማቃለል የቁጠባ ባህል ማዳበር ወሳኝ በመሆኑ 3,688,100,000 ብር ለማስቆጠብ ዕቅድ ተይዞ 2,631,329,352 ብር ማስቆጠብ ተችሏል። የብድር አቅርቦቱ አሁንም ካለው ፍላጎት አንጻር ውስን ነው።

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ በደቡብ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበርና ኢትዮጵያ ልማት ባንክ የ2 ቢሊየን ብር የማምረቻ መሳሪያ ለ932 ኢንዱስትሪዎች እንዲቀርብላቸው ለማመቻቸት ታቅዶ ለ469 ኢንዱስትሪዎች የ697,729,824 ብር ማምረቻ መሳሪያ ተገዝቶ ቀርቦላቸዋል። ለ1,184 ኢንዱስትሪዎች የ1,943,345,842 ብር የስራ ማስኬጃ ብድር እንዲያገኙ ለማመቻቸት ታቅዶ ለ102 ኢንዱስትሪዎች የ17,820,037 ብር የስራ ማስኬጃ ብድር ማቅረብ ተችሏል። በዚህ ረገድ ያለው የፋይናንስ አቅርቦት ከፍተኛ ጉድለት ያለበት ነው። ምንም እንኳን በገጠርም ሆነ በከተማ የብድር አቅርቦቱ ቢኖርም ቁጠባው የተረጋጋ ካለመሆኑም በላይ ሙሉ ለሙሉ ለኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት የማይውል እና የብድር ፍላጎትን መሸፈን የማይችል እንዲሁም የተሰራጩ ብድሮችን ለታለመለት አላማ አውሎ በወቅቱ ብድሩን ከማስመለስ አንጻር የነበሩ ክፍተቶችን ለቀጣይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ችግሮችን መቅረፍ ያስፈልጋል።

የኢንዱስትሪና ዩኒቨርሲቲዎች ትስስር አፈፃፀም አንጻር በክልሉ ከሚገኙ 7 ዩኒቨርሲቲዎችና 22 የቴ/ሙ/ስ/ተቋማት ጋር 300 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በማስተሳሰር በምርምር የተገደፈ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ዘርፉን የማጠናከር ስራ ለመስራት ታቅዶ 546 ኢንዱስትሪዎችን ከትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ከገበያ ትስስር አንጻር በገጠር ለ9,944 ኢንተርፕራይዞችና ህብረት ስራ ማህበራት በእንስሳትና በሰብል ልማት ለተሰማሩ ወጣቶች ላመረቷቸው ምርቶች የ1.067 ቢሊየን ብር፣ በከተማ በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለገቡ የ9.2 ቢሊየን ብር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 12.8 ቢሊየን ብር እና ለ13,420 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የ2.513 ቢሊየን ብር የገበያ ትስስር በመፍጠር የኢንዱስትሪዎች የገበያ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ታቅዶ ለ9,738 ኢንዱስትሪዎች የ1.370 ቢሊየን ብር (54.5%) የገበያ ትስስር ተፈጥሯል። ሆኖም የተፈጠረው የገበያ ትስስር የኢንተርፕራይዞችን የእርስ በርስ ውድድርና የገበያ አድማሳቸውን የሚያሰፋ ሳይሆን በአብዛኛው በመንግስት ገበያ ላይ የተንጠለጠለና የተወሰኑ የስራ ዘርፎች (ኮንስትራክሽን ግንባታ) ላይ ያተኮረ ሲሆን በሁሉም ዘርፍ የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ገበያ ላይ ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ማድረግ በርካታ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ ታይቷል።

በአጠቃላይ የማንፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም በአጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ለዘርፉ ከአቅም በታች የማምረት ችግር በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል በክልሉ አምራች ዘርፉን ሊሸከም የሚችል አደረጃጀት ወጥ ሆኖ አለመደራጀትና ዘግይቶ ከተደራጀም በኃላ በተደጋጋሚ ለውጦች መደረጋቸውና የተሟላ ሰው ይዞ ወደ ተግባር አለመግባት፣ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ዘመናዊ የሥራ አመራርና የጥራት ሥርዓት የተጠናከረ አለመሆኑ፤ ኢንዱስትሪዎች ከዩኒቨርስቲ፣ ከምርምር እና ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር ደካማ

መሆኑ፤ለጥናትና ምርምር በቂ ፋይናንስ አለመመደቡ፤ ጥራት ያለው መሠረተ ልማት አለመስፋፋቱ እና የመሬት አቅርቦት እጥረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

2.4. የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት አፈጻጸም

በእቅድ ዘመኑ የከተማ ፕላን ሽፋንን 100% ለማድረስ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል። የተለያየ ደረጃ ያላቸውን 427 ፕላኖችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 426 (99.7%) ተዘጋጅቷል። 4 መዋቅራዊ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ3 ከተሞች (75%) ተዘጋጅቷል። የህዝብ ብዛታቸው ከ20 ሺህ እስከ 100 ሺህ ለሆኑ 23 ከተሞች ስትራቴጂክ ፕላን፣ የሕዝብ ብዛታቸው ከ20 ሺህ በታች ለሆኑ 275 ከተሞች መሰረታዊ ፕላን እና ለ23 ከተሞች የማስፋፊያ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለሁሉም ከተሞች በዕቅዱ መሰረት 100% ተዘጋጅቷል። እንዲሁም ለ2,700 የገጠር አገልግሎት ማዕከላት ስኬች ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,575(58.3%) ተዘጋጅቷል።

ክልላዊ የከተሜነት ደረጃ ቀደም ሲል ከነበረበት 17.5 ከመቶ ወደ 25 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ የከተሜነት ደረጃውን 25 በመቶ (100%) ማድረስ ተችሏል። የገጠር አገልግሎት ማዕከላትን ከክልላዊ መስፈርት አንፃር በመፈተሽ 249 የከተማነት ዕውቅና ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 216 (86.7%) እውቅና ተሰጥቷል።

የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ በከተሞች 26,840 ሄ/ር የለማ መሬት አዘጋጅቶ ለማህበርና ለግል መኖሪያ ቤት መስሪያ፣ ለንግድና ኢንቨስትመንት፣ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለማምረቻና መሸጫ፣ለመንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ለኢንዱስትሪ ልማት የሚውል መሬት ለማቅረብ ታቅዶ 23,753.25 ሄ/ር (88.5%) ተዘጋጅቷል። መሬት ከማስተላለፍ አንጻር ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት 22,520 ሄ/ር ለማስተላለፍ ታቅዶ 13,304.91 ሄ/ር (59.08**%**) ለማስተላለፍ ተችሏል።

ወደ ሊዝ ያልገቡ ከተሞችንና አዲስ የከተማ እዉቅና የሚሰጣቸዉ ከተሞች ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ በ194 ከተሞች ታቅዶ ሁሉም ከተሞች ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ ተደርጓል። የመሬት ሀብት ቆጠራ ሥራን በ166 ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በ132 ከተሞች (79.5%) ተከናውኗል። በመሆኑም ከመሬት ዝግጅት አኳያ ከእቅድ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይ ቢሆንም ከማስተላለፍ ጋር ተያይዞ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ስለሆነ በዘርፉ የሚታየው የአገልግሎት አሠጣጥ ከቅሬታ ያልተላቀቀ በመሆኑ በቀጣይ በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል።

የቤቶች ልማትና አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ ለመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም፣ በከተሞች ለልማት ተነሺዎች፣ ለመምህራን እና ለነዋሪዎች፣ ለድሀ ድሀ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ለተቋማት አገልግሎት እና ለጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚሰጡ በተለያዩ አማራጮች 211,056 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 46,156 (21.86%) ተከናውኗል። በሁሉም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለ147,000 ዜጎች አዲስ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 111,444

(75.8%) የተከናወነ ሲሆን ብር 50,000,000.00 የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 43,950,458.00 (87.9%) ተከናውኗል። በከተሞችና በገጠር ማእከላት ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እንደየአከባቢው ነባራዊ ሁኔታ 30 አዳዲስ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 30(100%) ተዘጋጅቷል።

ከመሠረተ ልማትና ከከተሞች ማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች አኳያ የ86 ኪ.ሜ የአስፋልት መንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 98.7 ኪ/ሜ (100%)፣ 886 ኪ.ሜ የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 639.79 ኪ. ሜ (73.04%)፣ የ8,897 ኪ.ሜ የአዲስ መንገድ ጠረጋና ከፈታ ለማከናወን ታቅዶ 7,801.04 ኪ/ሜ (87.68%)፣ የ3,983 ኪ.ሜ የአዲስ ጠጠር መንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 3,418 ኪ/ሜ (85.81%)፣ የ60 ኪ.ሜ የነባር አስፋልት መንገድ ጥገናና ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ 25.93 ኪ/ሜ (43.22%)፣ እንዲሁም የ3,428 ኪ.ሜ የነባር ጠጠር መንገድ ጥገናና ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ 3,405.27 ኪ/ሜ (99.34%) ለማከናወን ተችሏል። በአጠቃላይ የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን ከነበረበት 35% ወደ 80% ለማድረስ ታቅዶ 73.87% ማድረስ ተችሏል።

ከቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አንጻር በከተሞች የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋን ከነበረበት 30% ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዶ 64% ላይ ማድረስ ተችሏል። ከሚመነጨው ኦርጋኒክ ቆሻሻ ከነበረበት ወደ 40% ለመቀየርና ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 28% የሚሆነውን መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ተችሏል። በከተማ ጽዳትና ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ላይ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲደራጁ በማድረግ ለ2,500 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 2,736 እና በአረንጓዴ ልማት ለ1,000 ዜጎች ታቅዶ 2,191 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በዚህም 50 ከመቶው ተጠቃሚዎች ሴቶች ናቸው።

ከኮንስትራክሽን ስራዎች አፈጻጸም አንፃር የኮንስትራክሽን ዲዛይን ዝግጅትና ኮንትራት አስተዳደር ስራዎችን በአማካሪ የማይሸፈኑ 4,935 መካከለኛና አነስተኛ ግንባታዎች የተሟላ ዲዛይን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ5,115 ግንባታዎች የተሟላ ዲዛይን የተዘጋጀ ሲሆን ከፍተኛ ደረጃ ላላቸው 256 ግንባታዎች ለአማካሪ ግዥ የሚሆን ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 234 ማዘጋጀት ተችሏል። የ5,241 ፕሮጀክቶች መነሻ ዋጋ ጥናት በማድረግ የተቋራጮች ደረጃ በመወሰን የተቋራጭ ግዥ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ5,349 ሰነድ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የሚዘጋጁ 5,241 ዲዛይኖች እና ግንባታዎች 100% ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋዊያን ተደራሽ እንዲሆኑ ከዲዛይን ዝግጅት እስከ ግንባታ ሂደት የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በሰፊው ተከናውኗል።

ከግንባታ ጥራት ክትትልና ቁጥጥር አንፃር ለ5,241 ፕሮጀክቶች የግንባታ መርሐ-ግብር በማዘጋጀት የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 5,016 (96%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ለ5,016 (96%) ስፍር በመውሰድ ማዘጋጀት ተችሏል። ከፍተኛ ደረጃ ላላቸውና በአማካሪዎች ክትትል ለሚደረግባቸው 256 ግንባታዎች ዙሪያ የአማካሪዎችን የሥራ አፈፃፀም ላይ በየወሩ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ234ቱ ተከናውኗል።

ክትትልና ቁጥጥር ለተደረገባቸውና በዕቅድ ዘመኑ ለሚጠናቀቁ 5,273 ፕሮጀክቶች ጊዜያዊ ርክክብ እና ለ5,252 ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ የ2,750 (52%) ግንባታዎች ጊዜያዊ ርክክብ እና የ1,930 (37%) ግንባታዎች የመጨረሻ ርክክብ ተከናውኗል።

2.5. የማዕድን ልማት አፈጻጸም

የክልሉን የማዕድን ሀብት በዓይነትና በመጠን በጥናት እየለዩ በዘርፉ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ በተደረገው ጥረት የማዕድን ሀብት አለኝታ ጥናት ሽፋኑን ከ41% (የክልሉ የቆዳ ስፋት) ወደ 51.63% ለማድረስ ታቅዶ 45.4% ማድረስ የተቻለ ቢሆንም በዕቅድ የተያዘውን ቦታ ለማጥናት የሚያስችል በጀት ባለመመደቡ፣ በመሳሪያ ታግዞ የተሟላ ጥናት ማድረግ የሚችል በቂ ልምድ ያለው ባለሙያ አለመኖር እና በሀገር ደረጃ ጥናት እንዲያካሄድ ሃላፊነት የተሰጠውም ተቋም ተደራሽ ያለመሆኑ፣ እንዲሁም በጥናት ሥራ የሚሰማራ የግል ዘርፍ በገበያ ላይ ያለመኖር ለአፈጻጸሙ ማነስ እንደ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው።

ይሁን እንጂ እስካሁን በተካሄዱት ውስን ጥናቶች ተስፋ ሰጪ የሆኑ በተለይም በኤክስፖርት ምርትነት የሚታወቁና የውጭ ምንዛሪ ሊያሥገኙ የሚችሉ ከወርቅ በተጨማሪ እንደ ጋርኔት፤ አኳማሪን፤ ኢመራልድና አፓል ዓይነት የጌጣጌጥ ማዕድናት በክልሉ እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል። በተጨማሪም ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ፊልድስፓር፣ ካኦሊን፣ ታልክ፣ ሲልካሳንድና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉትን ማዕድናት በጥናት የመለየት ሥራ እንዲከናወን በማድረግ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ሀገሪቱ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ የማዳን ሥራ መስራት ተጀምሯል።

በክልሉ የሚገኘውን ዕምቅ የማዕድን ሀብት በህጋዊና በፍትሀዊ መንገድ የሚለማበትን አሰራር በመዘርጋትና አልሚዎችን በስፋት በማሳተፍ ዘርፉ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ከፍ ከማድረግ አንጻር በዘርፉ 7,000 ኪሎግራም ወርቅ እንዲመረት ታቅዶ 4,533.57 ኪሎ ግራም (64.76%) ወርቅ ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ማድረግ ተችሏል። ይሁን እንጂ በህገ-ወጥ የወርቅ ምርትና ዝውውር በስፋት መኖሩ፣ ወርቅ በሚመረትባቸው አካባቢዎች ያለው የፀጥታ ችግር፣ የመሰረተ ልማት አለመሟላት፣ የወርቅ ክምችት ያለባቸው ቦታዎች በጥናት ያለመለየት፣ አምራቾች በዘመናዊ የማምረቻ ቴክኖሎጂ ያለመታገዝ እና በየደረጃው በሚገኙ አመራሮች ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆን እንደ ጉድለት ተገምግሟል።

የጌጣጌጥ ማዕድን ምርት 50 ቶን ለላኪዎች ለማቅረብ ታቅዶ 32.74 ቶን (65.5%) ማቅረብ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ አምራቾችን ከላኪዎች ጋር እንዲገናኙ በማድረግ የገበያ ትስስሩን በማጠናከርና በማዕድኑ ላይ እሴት እየጨመሩ ለገበያ ማቅረብ የሚያስችሉ ሥራዎችን በስፋት መስራትን ይጠይቃል።

የአነስተኛና ባህላዊ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት በወቅቱ የነበረዉን 1,220 የባለፈቃዶች ቁጥር ወደ 4,200 ለማሳደግ ታቅዶ 1,414 ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም 100 የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ማዕድን ማምረትና የምርመራ ፈቃድ በመስጠት በቁጥር 50 ከነበረበት ወደ 150 ለማሳደግ ታቅዶ አሁን ላይ ቁጥራቸው 14 ብቻ በሥራ ላይ የሚገኙ ናቸው። ይሁን እንጂ በክልሉ በየደረጃው የተሰጡ የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደርን አስመልክቶ የሚታየውን ችግር ለመፍታትና ከሀብቱ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ በተለይም ደግሞ በወጣቱ ሲነሳ ለነበረው የተጠቃሚነት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት አንፃር አለአግባብ የተያዙ የማዕድን ይዞታዎችን ለሥራ አጥ ወጣቶች ክፍት የማድረጉ ሥራ ባለፉት ዓመታት በተለይም ደግሞ በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን በስፋት መከናወኑ እንደ ስኬት የሚወሰድ ነው።

የወጣቶች ሥራ እድል አንጻር ለ101,621 ስራ አጥ ወጣቶችን በዘርፉ ሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ107,305 (+100%) ወጣቶችን ስራ ዕድል ተጠቀሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለአፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ መሆን ዋነኛው ምክንያት መንግስት ለሥራ-አጥ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ልዩ ትኩረት በመስጠቱና የተቀመጠውንም አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መንቀሳቀስ በመቻላቸው ነው።

በማዕድን ማምረት የተጎዱ አካባቢዎችን 63 ስ.ኪ.ሜ የሚሸፍን ቦታ መልሶ ለማልማት ታቅዶ 62.31 ስ.ኪ. ሜ መልሶ ማልማት የተቻለ ሲሆን በማዕድን ማምረቻ አካባቢ ለሚገኙ የህ/ሰብ ክፍሎች በባለፈቃዶች የሚከናወነው የማህበረሰብ ልማት በተመለከተ ግን ሙሉ በሙሉ አሰራሩን ተከትሎ ተግባራዊ እንዲደረግ ከማድረግ አንጻር ጉድለት ያለበት ነው።

በአጠቃላይ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዘመናት በተደረገው ጥረት አበረታች ወጤቶች የመመዝገባቸውን ያህል የዘርፉን አፈፃጸም ወዳላቀ ደረጃ እንዳይሸጋገር ካጋጠሙ በርካታ ተግዳሮቶች መካከል የዘርፉ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ውስነት፣ የበጀት እጥረት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የሎጂስቲክስ አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፣ የባለድርሻ አካላት የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ያለመኖር፣ የማዕድን ሥራዎች በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የሚስተዋለው የጸጥታ ችግርና ህገ-ወጥ ምርትና ግብይት መኖር በዘርፉ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

2.6. የንግድና ገበያ ልማት አፈጻጸም

ህጋዊ የንግድ አሠራር ሥርዓት በመዘርጋትና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥርዓት ከማዘመን አንጻር በክልሉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማዘመን በተደረገው ጥረት የኦን ላይን አገልገሎት መስጠት የተቻለ ሲሆን በተዘረጋው አሰራር መሰረት ለ330,887 (85.8%) ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት፣ ለ369,989 (85.81%) ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ፈቃድ መስጠት አገልግሎት፣ ለ343,258 (+100%) ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት መፈፀም ተችሏል። በመሆኑም በክልላችን የንግድ ፈቃድና ምዝገባ ህግ መሰረት የተመዘገቡ

ነጋዴዎች ቁጥር በዕቅዱ መነሻ 57,903 ከነበረበት በአማካይ በየአመቱ በ57% እያደገ በ2012 ዓ.ም 330,887 ደርሷል። በተጨማሪም ለ9,760 በግብርና ምርቶች አቅራቢነት እና ለ126 በነዳጅ ማደያ አገልግሎት ሰጪነት ለተሰማሩ በድምሩ ለ9,976 (78.65%) የንግድ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል።

መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶችን አቅርቦትና ስርጭት ከማጠናከር አኳያ በምርቶች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለመቀነስ በተዘረጋው ፕሮግራም መሠረት መንግስት በከፍተኛ ድጎማ የሚያቀርባቸው ምርቶች (ስኳር፣ ስንዴ እና ዘይት) በየአከባቢው እንዲያሰራጩ የተመረጡ የሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎች እንዲሰራጭ የተደረገ ቢሆንም በውጭ ምንዛሬ እጥረት እና በአቅራቢና በአሰራጭ ተቋማት በሚፈጠሩ ችግሮች የተነሳ የአቅቦትና ስርጭት መቆራረጥ፣ በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ነጋዴዎች እና በተቆጣጣሪ አካላት አካባበቢ የሚታይ የሌብነት ተግባር ምክንያት የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም።

ዘመናዊ የንግድና ግብይት መሰረተ-ልማት በማስፋፋት የገበያ ትስስር ከማሳደግ አንጻር በዕቅድ ዘመኑ 1,638(100%) ነባር እና አዳዲስ የሰብልና እንስሳት የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን እና 3 (60%) የሁለተኛ ደረጃ የግብርና ምርት ግብይት ማዕከላት ማቋቋም ተችሏል። በመሆኑም የግብይት ማዕከላት በመቋቋማቸው የሰብልና የእንስሳት ምርቶች ጥራታቸውና ደህንታቸው ተጠብቆ ለሀገር ውስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ አቅርቦት በአይነትና በመጠን ጭማሪ አሳይቷል። በዚህም አምራቹና አርሶ አደሩ በተሻለ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት ጥራት፣ተደራሽነትና ቀጣይነት ላይ ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ። በተመሳሳይ መልኩ የሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አምራች አከባቢዎች ተደራሽ በማድረግና በማቋቋም ብሎም የተቋቋሙትም ማዕከላት በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ከመምራትና ከማስተዳደር ረገድ ከጅምር ስራዎች የዘለሉ ተግባራት አልተፈፀሙም።

በክልላችን ከተመረቱ የግብርና ምርቶች ለገበያ የቀረቡ ምርቶችን በተመለከተ የአገዳና የብርዕ ግብይት በዕቅድ ዘመን መነሻ 1,217,864 ቶን ከነበረበት ወደ 24,469,064 ቶን፣ የጥራጥሬ ምርት ከ120,347 ቶን ወደ 3,328,611 ቶን፣ የቅባት እህል ከ18,277 ቶን ወደ 305,709.6 ቶን፣ አትክልትና ፍራፍሬ ከ1,161,014 ቶን ወደ 10,507,412 ቶን፣ ጥጥ ምርት 6,590 ወደ 203,523.2 ቶን፣ እጣንና ሙጫ ከ817 ወደ 1,133 ቶን፣ እንቁላል ከ50,625,000 ቁጥር ወደ 80,269,855 ቁጥር፣ ዶሮ ከ7,838,508 ወደ 18,331,273 ቁጥር ማቅረብ የተቻለ ሲሆን 16,119.5 ቶን ጫት ምርት ቀርቧል። በተጨማሪም የቁም እንስሳት በቁጥር ከ827,624 ወደ 31,391,135፣ ዓሳ ምርት ከ5,538 ቶን ወደ 57,258 ቶን፣ ማርና ሰም ከ6,515 ቶን ወደ 140,532 ቶን በማሳደግ እንዲቀርብ ተደርጓል።

የግብርና ምርቶችን ለኤክስፖርት ገበያ ከማስቀረብ አንጻር በሁለተኛ ዕ.ት.ዕ ዘመን የሰሊጥ ምርት 120,000 ቶን ታቅዶ 30,790 ቶን፣ የጥራጥሬ ምርት 344,536 ቶን ታቅዶ 250,778 ቶን፣ የቁም እንስሳት ምርት 1,718,905 ቁጥር ታቅዶ

979,733 ቁጥር ፣ የቆዳና ሌጦ ምርት 17,585,375 ቶን ታቅዶ 10,362,271 ቶን፣ ማርና ሰም ምርት 101,571 ቶን ታቅዶ 70,139.14 ቶን እና የሙዝ ምርት 4,783 ቶን ታቅዶ 6,356 ቶን ለማዕከላዊ ገበያ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

2.7. የኢንቨስትመንት ሥራዎች አፈጻጸም

የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ዘርፍ ዓለም አቀፋዊና አገር አቀፋዊ ገጽታዎች ያሉት በመሆኑ ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መንግስት ለኢንቨስትመንት ምቹ አካባቢን በመፍጠር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን በመሳብ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጠበቅበትን የማይተካ ድርሻ እንዲያበረክት ለማስቻል በሁለቱም ዙር ዕ.ት.ዕ ዘመን የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የቅድመና ድህረ ኢንቨስትመንት ምክር አገልግሎት፣ የኢንቨስትመንት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በየደረጃው ለሚገኘው አመራርና ህብረተሰብ በመስጠት ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል፡፡ በሁለቱም የዕቅድ ዘመናት 240,084 ሄ/ር የገጠር ኢንቨስትመንት መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 263,504.89 ሄ/ር (+100%) ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን 190,089.5 ሄ/ር የገጠር መሬት ለመለካት ታቅዶ 194,315.6 ሄ/ር (+100%) መለካት ተችሏል፡፡ ባለሀብቱን፣ ህብረተሰቡን እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ወደ ግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መዳረሻ የሚወስድ 938.05 ኪ.ሜ መንገድ ጥገና ስራ ማስተባበር ታቅዶ 1,464.05 ኪ/ሜ (+100%) ተከናውኗል፡፡

ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ አንጻር:- 31,290 ዙር የፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ሥራ ለመስራት ግብ ተጥሎ 30,862 ዙር (98.6%) ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ዓመታት ልማታዊ ባልሆኑና መሬት ይዘው በውላቸው መሰረት ሳያለሙ በተቀመጡ ባለሀብቶች ላይ ከማስጠንቀቂያ እስከ ውል ስረዛ ድረስ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት በማድረግ በ720 ፕሮጀክቶች ላይ ውል የመሰረዝና በ68 ፕሮጀክቶች ላይ መሬት የመቀነስ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ከመሬት ውል ማቋረጥ 59,524.72 ሄ/ር መሬት ከባለሀብቶች ተቀንሷል፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ፕሮጀክቶች በኩል ድጋፍ ተደርጎላቸው ማልማት ባልቻሉ ባለሀብቶች ላይ ደግሞ በአንድ በኩል በህግ አግባብ ወቅቱን የጠበቀ ህጋዊ ርምጃ መውሰድ ባለመቻሉ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትሃዊ እርምጃ ከመውሰድ አንፃር የመቀዛቀዝና አልፎ አልፎ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመኖራቸው በገጠርም ሆነ በከተማ ልማታዊ ባልሆኑ ባለሀብቶች እጅ የሚገኝ መሬትን ወደ ልማታዊ ባለሀብቶች በማስተላለፍ ረገድ ክፍተቶች ነበሩ፡፡ በዕቅዱ ዘመን ፕሮጀክቶችን ተከታትሎ ከመደገፍና ከማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከማሸጋገር አንፃር የሚጠበቀውን ያህል ስራ ተሰርቷል ማለት አያስደፍርም፡፡ ለዚህ ዋነኛ ምክንያት መሰረተ ልማት ከመዘርጋት፤ ብድር ከማመቻቸት፤ ለኢንቨስትመንቱ በቂ ዋስትናና ጥበቃ ከመስጠት አንፃር ካሉ ክፍተቶች፤ ከሎጅስቲክና በጀት ችግር ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቶችን በዓመት ሁለት ጊዜ በመከታተልና በመደገፍ ማብቃት ባለመቻሉ ሲሆን በሌላ በኩል በባለሀብቱ የሚታይ ክፍተት ደግሞ በቂ የኢንተርፕረነርሺፕ

ዕውቀት፤ የፕሮጀክት ማኔጅመንትና የፋይናንስ አቅም አለመኖርና በሰለጠነ ባለሙያ መታገዝ አለመቻል የችግሮቹ መገለጫዎች ናቸው።

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመስጠት አንጻር :- በዕቅድ ዘመኑ 3,237 የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ግብ ተጥሎ 2,460 (75.99%) ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ከነዚህ ባለሀብቶች ይመዘገባል ተብሎ ከታቀደው ካፒታል 12.62 ቢሊዮን ብር ውስጥ 27.365 ቢሊዮን ብር (+100%) ተመዝግቧል። ከስራ እድል ፈጠራ አኳያ በእቅድ ዘመን በጥቅሉ ለ973,683 ዜጎች ቋሚ እና ጊዚያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ግብ ተጥሎ 1,159,805 (+100%) ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል።

2.8. የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማት አፈጻጸም

የባህልና ታሪክ ልማትና አጠቃቀም ከማሳደግ አኳያ የክልሉን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማንነት መገለጫ የሆነውን ባህልና ታሪክ የጋራ እሴቶቻቸውን በማጉላት ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ የመኖር ባህልን ለማዳበርና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማስፋፋት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማስቻል 65 የሀገር በቀል ዕዉቀቶች አጠቃቀም ለማሳደግ ታቅዶ 55 (84.6%)፣ በቁጥር 610 የባህል ተምሳሌቶች የመለየት የመመዝገብና የመሰነድ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 580 (95%) ማከናወን ተችሏል። እንዲሁም ለቱሪስት መሰህብነት የዋሉ የለሙ ክብረ በዓላት በቁጥር 35 ታቅዶ 34 (97%) ማከናወን ተችሏል።

የባህላዊ ቅርሶች ጥበቃና ልማትን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ 5 ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ የማስመዝገቢያ/መምረጫ ሰነዶች (Nomination Dossier) ለማዘጋጀት ታቅዶ የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር፣ የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ በዓል ፍቼ ጨምበላላ እና የጌዴኦ ባህላዊ መልክዓ ምድር በድምሩ 3 (60%) የተከናወነ ሲሆን የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር በዓለም አቀፍ ቅርስ ሳይት እና የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ በዩኔስኮ የሰው ልጅ ወካይ ቅርስ ሆኖ ተመዝግቧል። እንዲሁም የጌዴኦ ባህላዊ መልክአ ምድርም ዕጩ የዓለም ቅርስ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመጨረሻ የማስመዝገቢያ ሰነዶች ዝግጅት ስራ ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለዩኔስኮ ተልኳል።

በክልሉ የሚገኙ ባህላዊ ቅርሶችን በቁጥር 7,481 ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 7,694 (+100%)፣ 5,124 ለመጠበቅ ታቅዶ 3,292 (64%)፣ 1,200 ለማልማት ታቅዶ 1,001 (83%) ተከናውኗል። በክልሉ የሚገኙ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማጥናትና ለማደራጀት እንዲያስችል የተሰበሰቡ 1,500 ባህላዊ ቅርሶችን ወደ ዳታ ቤዝ የማስገባት ሥራ ተሰርቷል፡

በዕቅድ ዘመናቱ አነስተኛ ተናጋሪ ያላቸውና በመጥፋት አደጋ ላይ ያሉ ቋንቋዎች በቁጥር 12 ባህላዊ መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት ታቅዶ 12 መዝገበ ቃላት በማዘጋጀትና በማሳተም ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። የብሔር ብሄረሰቦችን

በሰነድ 34 ተረቶችን፣ ቃላዊ ታሪኮችን፣ ሰነቃልና ወጎችን በማዘጋጀት ለማሳተም ታቅዶ 62 ማከናወን ተችሏል። የብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ሰዋሰዉ 23 ለማዘጋጀት ታቅዶ 16 (69%) ማከናወን ተችሏል።

የተፈጥሮ መስህቦች ጥበቃና ልማት አጠቃቀምን በተመለከተ በክልሉ የሚገኙ የተፈጥሮ መስህብ ሃብቶችን በመለየት፣ በመመዝገብ፣ በመከለል፣ በመጠበቅ እና በማልማት ከተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ተጽዕኖዎች እንዲጠበቁ እንዲሁም የተጎዱ መስህቦች እንዲያገግሙ በማድረግ ለሥነ ምህዳራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች እንዲውሉና ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ 475 አዳዲስ የተፈጥሮ መሰህቦችን ለመመዝገብ ታቅዶ 393 (83%)፣ 400 ለመጠበቅ ታቅዶ 326 (82%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዘርፉ ሁሉ አቀፍ ለውጥን ለማምጣት የሚያስችል ክልላዊ የ10 ዓመት የቱሪዝም ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል።

በዕቅድ ዘመናቱ 8 የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማካለልና ዳግም ማካለል ለማካሄድ ታቅዶ 6 የተከናወነ ሲሆን 4ቱ የሎካ፣ ጨበራ ጩርጩራ፣ ማዜ እና ጊቤ ሸለቆ ብ/ፓርኮች የክለላ (የድንበር ማሳወቅ) ስራ የተሰራ ሲሆን ሌሎቹ 2ቱ በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የተከናወኑ አነስተኛ የጥበቃ ቦታዎች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በማዜ እና ሎካ አባያ ብ/ፓርኮች በኮንክሪት የቋሚ ድንበር ምልክት (ቢከን) ተከላ ተከናውኗል።

የክልሉን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች ለማስተዋወቅ የፕሮሞሽን ስራዎች በመስራት 1.613 ሚሊዮን የውጭ ሀገር እና 24 ሚሊዮን የሀገር ውስጥ በድምሩ 25,613,000 ቱሪስቶች ክልሉን ይጎበኛሉ ተብሎ ታቅዶ 963,766 የውጭ አገር እና 34,309,610 የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች በድምሩ 35,273,376 (+100%) ቱሪስቶች ክልሉን ጎበኝተዋል። ከቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከጥበቃ ቦታዎች 27,000,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 31,799,900 (+100%) መሰብሰብ ተችሏል።

የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋትና ለማጠናከር 366 አዲስ የአገርህን እወቅ ክበባትን ለማቋቋም ታቅዶ 406 (+100%) የተከናወነ ሲሆን፣ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ ሴክተር መ/ቤቶች 630 ነባር ክበባትን ለማጠናከር ታቅዶ 728 (+100%) ተከናውኗል።

የዘርፉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ዓይነት፣መጠን እና ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ደረጃቸውን የጠበቁ የኮከብ ደረጃ ምደባ ለማግኘት ከተወዳደሩት ሆቴሎችና ሪዞርቶች ውስጥ ከኮከብ ደረጃ ከ1-4 በቁጥር 32 ሆቴሎች ያገኙ ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ በደረጃ ያልታቀፉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተፈጥረዋል። በዕቅድ ዘመኑ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብዛት 27,251 ለማድረስ ታቅዶ 30,303 (+100%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ተቋማት ብዛትም 19,152 ታቅዶ 58,072 ተከናውኗል። በተጨማሪም 188 አባላት ያሏቸው 17 ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው አስጎብኚ ማህበራት ተደራጅተዋል።

በክልሉ በተለያዩ ዞኖች በቁጥር 19 አዲስ የባህል ማዕከላትን ለማቋቋምና ነባሮችን ለማደራጀት ታቅዶ 20 የተከናወነ ሲሆን በቁጥር 27 የተለያየ ደረጃ ያላቸው ቤተ-መዘክሮች (ሙዝየሞች) ለማቋቋምና ለማደራጀት ታቅዶ 25 (92.5%) ተከናውኗል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በባህልና ቱሪዝም 205,792 ዜጎች ጊዜያዊና 98,810 ቋሚ በድምሩ ለ304,602 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

ከስፖርት ልማት አፈጻጸም አኳያ የስፖርቱን ውጤታማነት ለማሳደግ የተለያዩ የስፖርት ኮሚቴዎች፣ ምክር ቤቶችና ፌዴሬሽኖች የማደራጀትና የማጠናከር ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን 150 የተደራጁና የተጠናከሩ ክለቦች ለማደራጀት ታቅዶ 46 (31%) ክለቦችን ለማደራጀት የተቻለ ሲሆን በቁጥር 35,748 የተደራጁና የተጠናከሩ ቡድኖች ለማደራጀት ታቅዶ 31,598 (88.39%) ቡድኖችን ማደራጀት ተችሏል።

የስፖርት ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትን በተመለከተ ሶስት የ1ኛ ደረጃ፣ ሰባ ዘጠኝ የ2ኛ ደረጃ እና ሁለት መቶ ስልሳ ስምንት የ3ኛ ደረጃ የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትን ለመገንባት ታቅዶ በቅደም ተከተል 2 (67%)፣ 52(66%) እና 288(107%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን 3 የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ 1 አገልግሎት ማሰጀመር ተችሏል። በየደረጃው 3,972 በገጠር የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸዉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,312 (83%) እና 407 ካርታና ፕላን ያላቸዉ የከተማ ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 359 (88%) ማዘጋጀት ተችሏል።

ህብረተሰቡን በስፖርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግን በተመለከተ በባህል ስፖርቶች ዉድድርና ፌስቲቫል 3,478,168 ለማሳተፍ ታቅዶ 2,752,135 (79%)፣ በአርብቶ አደር ዉድድር 342,155 ለማሳተፍ ታቅዶ 122,960(36%)፣ በተለያዩ ሻምፒዮናዎች 83,600 ለማሳተፍ ታቅዶ 62,677 (74%) እና በታዳጊ ወጣቶች ፕሮግራም የምዘና ዉድድር 7,600 ለማሳተፍ ታቅዶ 4,750 (63%) ለማሳተፍ ተችሏል።

በክልል ደረጃ ስፖርት ስልጠና ማዕከል 500(ሴት 250) ስፖርተኞችን ለማስገባት ታቅዶ 330 (66%) ስፖርተኞችን ወደ ስልጠና ማዕከል ለማስገባት ተችሏል። በስፖርት ክለብ በወንድና በሴት 1,470 ኤሊቶችን ለማስገባት ታቅዶ 1,125 (76%) ወደ ክለብ ማስገባት የተቻለ ሲሆን ወደ ብሔራዊ ቡድን 96 ኤሊቶችን ለማስገባት ታቅዶ 74 (77%) እና በአካዳሚና በጥሩነሽ ዲባባ ስልጠና ማዕከል 154 ኤሊቶችን ለማስገባት ታቅዶ 113(73%) ማስገባት ተችሏል።

ምዕራፍ ሦስት

የመሰረተ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም

3.1. የትራንስፖርትና መንገድ ልማት አፈጻጸም

የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ በተመለከተ ባለፉት የዕቅድ ዘመን የአሽከርካሪዎችን ክህሎት፣ እውቀትና ስነምግባር ከማሳደግ አንጻር 90 አዲስ ብቃታቸው የተረጋገጠ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማቋቋም ታቅዶ 89 (99%) የተቋቋመ ሲሆን 186,250 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 198,094 (+100%) መስጠት ተችሏል።

የአሽከርካሪዎች የተግባር ሥልጠናና ምዘና ማዕከላት /ትራፊክ ኮምኘሌክስ/ 3 አዲስ ለመገንባት ታቅዶ የሀዋሳ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ግምባታው ተጠናቆ ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች የሚቀሩ ሲሆን የአርባምንጭና የሆሳዕና ከተማ ትራፊክ ኮምፕሌክስ ከዓለማቀፍ ደረጃ አንፃር ቦታው በቂ ባለመሆኑና የተቋራጭ ድርጅቶች በውለታው መሠረት ባለመሥራታቸው ውለታቸው ተቋርጧል።

የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ከማሳደግ አንጻር 289,300 ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 280,325 (97%) ምርመራ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ድንገተኛ የተሽከርካሪ ምርመራ ለ92,150 ለማድረግ ታቅዶ 50,902 (55%) ማድረግ ተችሏል። የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት 44 ለማቋቋም ታቅዶ የግል ባለሀብቶችና ድርጅቶች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራና ምቹ ሁኔታ ቢኖርም በዘርፉ ለመሠማራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት 4(9%) ብቻ የተከናወነ ሲሆን 350 የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ለማቋቋም ታቅዶ በከተሞች ላይ ያለው የመሬት አቅርቦት ችግር ምክንያት 162(46%) ተቋቁሟል።

የህዝብ ትራንስፖርትን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ ትራንስፖርት የሚሰጥባቸው የሥምሪት መስመሮች 2,019 ለማከናወን ታቅዶ 1,878 (93%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን፤ ዞኖችን ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚያገናኙ 136 የስምሪት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 135 (99%) የስምሪት መስመሮችን መክፈት ተችሏል። እንዲሁም በትራንስፖርት የተጓጓዘ ተሳፋሪ ቁጥር 51,593,887 ለማድረስ ታቅዶ 90,234,981 ለማድረስ ተችሏል።

የትራንስፖርት አገልግሎቶች አደረጃጀትና ስምሪትን ከማሳደግ አንጻር 89 አዲስ አነስተኛ መናኸሪያዎችን ለመገንባትና ሥምሪት እንዲሰጥባቸው ለማድረግ ታቅዶ 104(+100%) የተገነባ ሲሆን የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትን በማደረጀት 64 ለማድረስ ታቅዶ 62(97%) ማደራጀት ተችሏል። የከተማ ታክሲ 62 ማህበር ለማደራጀት ታቅዶ 77 (+100%) ማደራጀት ተችሏል። እንዲሁም የ184 መናኸሪያዎች ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ የ89 (48.3%) መናኸሪያዎች ደረጃ ማሻሻል ተችሏል።

የትራንስፖርት ሽፋንን ለማሳደግ አማራጭ የከተማ ትራንስፖርት ከማስፋፋት አንጻር 5 አማራጮች ወደ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማስገባት ታቅዶ 3ቱን በማስፋፋት አፈጻጸሙን 60% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 36 የውሃ ላይ ትራንስፖርት ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 14 (39%) ማከናወን ተችሏል።

ጭነት ትራንስፖርትን በተመለከተ በክልሉ የሚገኙ የጭነት ተሽከርካሪዎች መረጃ በመጫን ችሎታ በደረጃ እና በአገልግሎት ዘመን የማደራጀት ስራ የተሰራ ሲሆን 43 አዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን ለማደራጀት ታቅዶ 40 (93%) ማህበራትን ማደራጅት ተችሏል። ለጭነት ተሽከርካሪዎች መናኸሪያ እንዲገነባ ለማድረግ 16 ታቅዶ በ3 ከተሞች (በወልቂጤ፣ በሶዶ እና በሀዋሳ) ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን በክልሉ መንግስት በየዓመቱ የሚመደበው በጀት በጣም ዝቅተኛ መሆንና ዞኖች በራሳቸው በጀት መገንባት ባለመቻላቸው ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት ተገምግሟል።

የመንገድ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሥራዎች በተመለከተ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከመቀነስ አንጻር በየዓመቱ በ10% የመንገድ ትራፊክ አደጋ በመቀነስ ከመነሻው 1,249 የነበረውን የአጠቃላይ አደጋ መጠን ወደ 738 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም የተሽከርካሪዎች ቁጥር እና በመንገዶች ቁጥርና ርዝመት በጣም የጨመረ መሆኑ፣ ዘርፉ እንደ ሀገር በተሟላ ሁኔታ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆን፤ የህገ-ወጥ ሞተር ሳይክሎች በከፍተኛ ሁኔታ ሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ መግባት፤ የተሰፋሪ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር እና የአሽከርካሪዎች ግንዛቤ ማነስ ምክንያት ወደ 1,183 አደጋ ከፍ በማለትና እንዲሁም በየዓመቱ በ10% የህይወት ጉዳት /ሞት/ በመቀነስ ከመነሻው 371 የነበረውን የሞት አደጋ መጠን ወደ 203 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 594 በመጨመሩ በተያዘው GTP እቅድ መሠረት አለመሳካቱን ያመለክታል። በየዓመቱ 10% የንብረት ጉዳት /በገንዘብ/ ሲተመን በመቀነስ ከመነሻው 18,449,641 የነበረውን የንብረት ጉዳት ወደ 10,905,460 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 13,890,236 ማድረስ ችሏል።

ከመንገድ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች አንጻር በመደበኛ የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም 3,351 ኪ.ሜ የመንገድ ጥናትና ዲዛይን በአማካሪዎችና በራስ ኃይል ለመስራት ታቅዶ 2,671 ኪ.ሜ (79.7%) የተጠናቀቀ ሲሆን በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 14,631 ኪ.ሜ የመንገድ ጥናትና ዲዛይን በተደራጁ የዩራፕ አማካሪዎች ለመሥራት ታቅዶ 13,572.71 ኪ.ሜ. (92.7%) ለማጠናቀቅ ተችሏል።

ከድልድይ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች አንጻር በመደበኛ ፕሮግራም የ129 ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን ለመሥራት ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁ ሲሆን በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 322 የድልድይ ጥናትና ዲዛይን ለመሥራት ታቅዶ የ226 (70%) ድልድዮች በማጠናቀቅ ለግንባታ ዝግጁ ማድረግ ተችሏል።

ከመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች አንጻር በመደበኛ የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም ላይ 5,235 ኪ.ሜ መንገድ በራስ ሀይል ለመገንባት ታቅዶ 4,960 ኪ.ሜ (94.7%) የተገነባ ሲሆን 691 ኪ.ሜ መንገድ መልሶ ግንባታ ታቅዶ 930.9 ኪ. ሜ (+100) መንገድ ተገንብቷል።

በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከተጀመረበት 2004 ዓ.ም ጀምሮ 8,030 ኪ.ሜ በአነስተኛ ተቋራጭና አማካሪ ማህበራት ለመገንባት ታቅዶ 6,144 ኪ.ሜ. (76.5%) ተጠናቋል።

የድልድይ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በመደበኛ የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም 89 ድልድዮች ለመገንባት ታቅዶ 54 ድልድዮች የተጠናቀቁ ሲሆን በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 118 ድልድዮችን ለመገንባት ታቅዶ 36 ድልድዮች ተጠናቋል። በአጠቃላይ 207 ድልድዮችን ለመገንባት ታቅዶ 90 (43.5%) ድልድዮች ተገንብተዉ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል።

የመንገድ ጥገና በተመለከተ የፈዴራል መንገድ ፈንድ አስተዳደር ጽ/ቤት በሚመድበዉ በጀት የ21,465 ኪ.ሜ መደበኛ ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 17,982.48 ኪ.ሜ (83.7%) ተከናውኗል። እንዲሁም 7,521.10 ኪ.ሜ ወቅታዊ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 4,721.08 ኪ.ሜ (62.7%) የተከናወነ ሲሆን በድምሩ 28,986.1 ኪ.ሜ የመንገድ ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 22,703.56 ኪ.ሜ (78.3%) ጥገና ተከናውኗል።

ከስራ ዕድል ፈጠራ አንጻር በመንገድ ጥናትና ዲዛይን፣ በመንገድ ግንባታና ጥገና እንዲሁም በድልድይ ዲዛይን ግንባታና ጥገና ስራ ለሚሰማሩ 420,000 ዜጎች ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ13,460 (ሴት 1,350) በቋሚ እና ለ236,540 (ሴት 69,327) በጊዜያዊነት ሲሆን በጠቅላላው ለ250,000 (ሴት ለ70,677) ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

በአጠቃላይ በዘርፉ አፈፃፀም ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ የትራንስፖርት አቅርቦትና ማኔጅመንት ችግር፣ ምቹ የሆነ የመንገድ መሠረተ ልማት አለመኖርና ያሉትም ቢሆኑ የመሠረተ ልማት ተደራሽነት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ የጭነት ትራንስፖርት የመናኸሪያ አቅርቦት ያለመኖር፣ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጥረት፣ የመንገዶች ጥገና በወቅቱ አለመደረግ፣ የካፒታል ፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ያለማድረግ፣ ዲዛይን ችግር መኖርና የመፈፀም አቅም ውስንነት፣ ጠንካራና ተከታታይ የሆነ የድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙን በመርሃ ግብሩ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የመገምገም ዉስንነት፣ የመንገድ ግንባታንና ጥገና ስራዎች በተቀመጡ ስታንዳርዶች ከመስራት አንፃር በሚፈለገዉ ደረጃ አለመሆኑ፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር ዘርግቶ በተጨባጭ በችግሩ ስፋት ልክ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ፣ የቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር እና ብልሹ አሠራር መኖር ዋነኞቹ ክፍተቶች ናቸው።

3.2. የኢነርጂ ልማት አፈጻጸም

በክልላችን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለመደገፍ በቂ፣ አስተማማኝ እና ተመጣኝ የሆነ የኢነርጂ አቅርቦት መኖር ወሳኝ ነው። ስለሆነም በክልላችን ሃይል ማመንጨት የሚችሉ 25 ወንዞች ላይ የአዋጪነት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በ7 ወንዞች ላይ ጥናት የተካሄደ ሲሆን አፈጻጸሙም 28% ነው። በሌላ በኩል

ደግሞ ከ42 አነስተኛ ወንዞች ሃይል በማመንጨት ሀ/ሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በ11 ወንዞች ላይ ግንባታ በማካሄድ ሃይል ማመንጨት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 26 በመቶ ነው። የፒከ/ማይክሮ ሀይድሮ ፓወር ጥናትና ግንባታ ሥራ በበጀት እጥረት፣ በዘርፉ ያለው የባለሙያ የእውቀትና ክህሎት ክፍተት፣ በዘርፉ ተወዳዳሪ የሆኑ አማካሪና የግንባታ ተቋራጮች በበቂ ሁኔታ ያለመገኘት እና የኤሌክትሪክ ሁሉ አቀፍ ፕሮግራም ጋር በቅንጅት ያለመሥራት ምክንያት በዝቅተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ይገኛል።

የሶላር ቴክኖሎጂ ስርጭትና ተከላ በተመለከተ የሶላር ማሾ ስርጭት 696,524 ታቅዶ 486,305 (69.82%)፣ የቤተሰብ ሶላር ስርጭት 147,262 ለማድረግ ታቅዶ 79,428 (53.93%) እና ሶላር ሲስተም በተቋም ተከላ 1,425 ለማካሄድ ታቅዶ 2,813 (+100%) ማከናወን ተችሏል።

ለ10,975 ቤተሰብ ባዮጋዞችን ለመገንባት ታቅዶ 4,363 (39.75%) በመገንባት 17,452 ቶን የሚገመት ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ወደ አካባቢ እንዳይለቀቅ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን 1,039 ሄክታር ደን ከወድመት ለማዳን ተችሏል።

ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች በተመለከተ 2,065,400 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 1,319,527 (60.84%) በማሰራጨት 1,319,353 ቶን የሚገመት ካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ አካባቢ እንዳይለቀቅ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን 100,552 ሄክታር ደን ከወድመት ለማዳን ተችሏል።

3.3. የውሃ ልማት አፈጻጸም

የመጠጥ ዉሃ ዘርፍ የውሃ ሃብት ጥናትና አስተዳደር፡- ባለፉት አመታት በክልሉ ለመጠጥና መስኖ አገልግሎት የሚውሉ የውሃ መገኛዎችን በቅድመ ጥናት በመለየት ለጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ እንዲሁም ውሃን አሽገው ለገበያ ማቅረብ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች መረጃውን በግብዓትነት መጠቀም እንዲቻል በዕቅድ ዘመኑ መነሻ በ11,000 ካሬ ኪ/ሜ ቦታ ላይ ብቻ ተጠንቶ የነበረውን የውሃ ሀብት አለኝታ ጥናት በ2012 ዓ/ም 226,478 ካሬ ኪ/ሜ ለማድረስ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ዕቅዱን ማሳካት ተችሏል።

ለክልሉ ሕብረተሰብ የሚቀርበው የመጠጥ ውሃ ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑን ከማረጋገጥ አንፃር አዳዲስ የመጠጥ ውሃ መገኛዎች ወደ ግንባታ ሂደት ከመተላለፋቸው እና የተገነቡ የውሃ ተቋማት ለመጠጥ ከመዋላቸው በፊት የውሃ ጥራት ፍተሻ ማረጋገጫ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን ተገንብተው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ላይም ወቅቱን የጠበቀ የናሙና ፍተሻ በማድረግ የጥራት ቁጥጥር ስራ ተሠርቷል።

በዚህ ረገድ በ200 ውሃ አካላት ላይ ተጓዳኝ ምርመራዎችን በማካሄድና የጥራት ደረጃቸውን በማረጋገጥ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ታቅዶ 154፣ በ10,000 አዳዲስ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መገኛዎች ላይ የፊዚኮ ኬሚካል ምርመራ በማካሄድ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 3,640፣ በ2,500 ነባርና አዳዲስ የውሃ ተቋማት ላይ የባክቴሪኦሎጂካል ናሙና ምርመራ ማካሄድና የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 3,006፣ ለከተማ

ነዋሪዎች የሚቀርብ 300 የውሃ ተቋም ላይ የውሃ ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ 224 እና በክልል ውስጥ የሚገኙ 250 ኢንዱስትሪዎች በውሃ አካላት ላይ የሚለቁትን ፍሳሽ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ 864 ኢንዱስተሪዎች ፍሳሽ የጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ ተችሏል። በሌላ በኩል በፍሎራይድ ለተበከሉ የማኅበረሰብ የመጠጥ ውሃ ተቋማት 50 የሙከራ የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ለመገንባት ታቅዶ 17 በመገንባት ህብረተሰቡ የተጣራ ንጹህ መጠጥ ውሃ እንዲያገኝ ተደርጓል።

በማማከር፣ በግንባታ እና በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ለሚሰማሩ 10,915 ባለሙያዎች እና 1,135 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ3,229 ባለሙያዎች እና ለ701 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ መስጠት የተቻለ ሲሆን ለ10,000 ባለሙያዎች እና ለ1,000 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ዕድሳት ለመስጠት ታቅዶ ለ1,411 ባለሙያዎች እና ለ293 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ማደስ ተችሏል።

የገጠርና ከተማ መጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን፡- በገጠር 89,200 የመጠጥ ውሃ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ለማከናወን ታቅዶ 20,525 (23%) የመጠጥ ውሀ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ስራ ማከናወን ተችሏል። እንዲሁም በከተማ በድምሩ 658 የመጠጥ ውሃ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ለማከናወን ታቅዶ 203 (30.85%) ማከናወን ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ የሲቪል ስራ ዲዛይን የሚቀራቸው 16 የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ጥናት ማጠናቀቅ ተችሏል።

የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ፡- በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን ከ40% ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 6,324 ተቋማት ተገንብተው 5,491,821 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2007 ዓ/ም መጨረሻ የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በዕ.ት.ዕ I ስታንዳርድ 47.52% ማድረስ ተችሏል። በሁለተኛ የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን ከ64% ወደ 80% ለማድረስ ታቅዶ 7,370 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 1,017,287 (518,816 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2012 መጨረሻ የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በዕ.ት.ዕ II ስታንዳርድ 40.62% ማድረስ ተችሏል።

የከተማ መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ፡- በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 343 ተቋማትን በመገንባት በዕ.ት. ዕ I ስታንዳርድ 2,249,149 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን 100% ለማድረስ ታቅዶ 40 ተቋማት ተገንብተው 1,065,977 (47.39%) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2007 ዓ/ም መጨረሻ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በዕትዕ I ስታንዳርድ 73.46% ማድረስ ተችሏል።

በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን 315 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት በዕ.ት.ዕ I ስታንዳርድ 385,912 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን 73.46% ወደ 100% እንዲሁም በዕ.ት.ዕ II ስታንዳርድ 669,465 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ ሽፋኑን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ 74% ለማድረስ ታቅዶ ከ2008-2009 ዓ/ም ለሁለት

ተከታታይ የዕቅድ ዘመኑ ዓመታት በተከናወነ ተግባር 68 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 130,000 (66,300 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2009 መጨረሻ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በዕ.ት.ዕ I ስታንዳርድ 75.33% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ2010-2012 ዓ/ም በቀሪዎቹ ሦስት የዕቅድ ዘመኑ ተከታታይ ዓመታት በተከናወነ ተግባር 75 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 189,200 (96,492 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2012 መጨረሻ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በዕ.ት.ዕ II ስታንዳርድ 55.39% ማድረስ ተችሏል።

በአጠቃላይ በዕ.ት. ዕ II ስታንዳርድ የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን ከ2011-2012 ዓ/ም በተከናወነ ተግባር 7,370 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 1,017,287 (518,816 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ የማድረግ እና የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን ከ2010-2012 ዓ/ም የዕቅዱ ተከታታይ ዓመታት በተከናወነ ተግባር 75 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 189,200 (96,492 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የክልሉ አማካይ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንም 42% ማድረስ ተችሏል።

የመጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደርና መሳሪያዎች ጥገና፡- ከመጠጥ ውሃ ጥገናና ተቋማት አስተዳደር አንጻር አገልግሎት የማይሰጡ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት የተቋማት ብልሽት ምጣኔን ለመቀነስ በታቀደው መሰረት በመጀመሪያው ዕ.ት.ዕ ዘመን 2,840 ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት የተቋማት ብልሽት ምጣኔን በዕቅድ ዘመኑ መነሻ 2002 ዓ/ም ከነበረበት 27% ወደ 10% ለማውረድ በታቀደው መሰረት ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል።

በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን 247,423 አገልግሎት የማይሰጡ ውሃ ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 23.16% ወደ 7% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 15,178 መጠጥ ውሃ ተቋማትን ጥገናና መልሶ ግንባታ ስራ በመስራት የተቋማት ብልሽት ምጣኔን ወደ 9% ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

በአጠቃላይ በውኃ ዘርፍ ባለፉት ዓመታት ውጤቶች ቢመዘገቡም አሁንም በዘርፉ በርካታ ክፍተቶች አሉበት። ለዚህም እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ፣ ውስን የገንዘብ አቅምና የአጠቃቀም ማነቆዎች፤ ውስን የሆነ የቴክኒክ አቅም፤ ዝቅተኛ የባለድርሻ አካላት እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፣ ፈጣን የከተሞች መስፋፋት እና ጠንካራ የሳኒቴሽን ፖሊሲና ተቋማዊ ኃላፊነት አለመኖር ይገኙበታል። በመሆኑም በቀጣይ እነዚህን ፈታኝ ፈተናዎች ለማለፍ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል።

3.4. የመስኖ ልማት አፈጻጸም

በአነስተኛ መስኖ ጥናትና ዲዛይን 57,762 ሄ/ር፣ በመካከለኛ መስኖ 48,921 ሄ/ር፣ በከፍተኛ መስኖ 15,750 ሄ/ር፣ በከርሰምድር መስኖ ጥናትና ዲዛይን 16,050 ሄ/ር በድምሩ 138,483 ሄ/ር ማልማት የሚያስችሉ የመስኖ ኘሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በአነስተኛ መስኖ ጥናትና ዲዛይን 16,442 ሄ/ር፣ በመካከለኛ

መስኖ 27,729 ሄ/ር፣ በከርሰምድር መስኖ ጥናትና ዲዛይን 657 ሄ/ር በድምሩ 44,828 (33%) ሄ/ር የጥናትና ዲዛይን ስራ ተከናውኗል።

የ9 ተፋሰስ ውሀ በጀት ጥናት ለማከናወን ታቅዶ ዕቅድ ሲዘጋጅ ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ (የተለጠጠ ዕቅድ) በመሆኑ ምክንያት የ2 (22%) /ወይጦና ብላቴ/ ተፋሰስ የዉሀ በጀት ጥናት ተጠናቋል፣ በክልሉ አራቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች (ባሮ-አኮቦ፣ ኦሞ-ጊቤ፣ ገናሌ-ዳዋ፣ እና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች) የመስኖ ፖቴንሻል ጥናትን በማከናወን በክልሉ በአነስተኛ፣ መካከለኛና ሰፋፊ መስኖ መልማት የሚችል 1,131,652.27 ሄ/ር መሬት መለየት ተችሏል።

በግንባታ ረገድ የአዲስ አነስተኛ መስኖ ግንባታና ነባር መልሶ ግንባታ 35,367 ሄ/ር፣ በመካከለኛ መስኖ 15,206 ሄ/ር፣ ሰፋፊ መስኖ 3,900 ሄ/ር፣ በአፈር ግድብ መስኖ 630 ሄ/ር፣ የከርሰምድር መስኖ ፕሮጀክት ቁፋሮና የመስኖ አዉታር ዝርጋታ 5,085 ሄ/ር በድምሩ 60,188 ሄ/ር ማልማት የሚያስችሉ የመስኖ ግንባታ ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ የአነስተኛ መስኖ ግንባታና ነባር መልሶ ግንባታ 12,267 ሄ/ር፣ በመካከለኛ መስኖ 8,991 ሄ/ር፣ ሰፋፊ መስኖ 5,345 ሄ/ር፣ የከርሰምድር መስኖ ፕሮጀክት ቁፋሮና የመስኖ አዉታር ዝርጋታ 483 ሄ/ር በድምሩ 27,086 ሄ/ር (45%) መሬት በማልማት 82,853 አባዎራዎች ተጠቃሚ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን በዘመናዊ መስኖ የሚለማ መሬት መጠን ወደ 69,425 ሄ/ር ማድረስ ተችሏል።

በክልላችን ካለው የውሃ ሀብትና የመሬት የመልማት አቅም አንጻር ሲታይ እስከ አሁን የተከናወነው የመስኖ ልማት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ይገኛል። ለዚህም እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል ውስን የሆነ ተቋማዊ አቅም፣ በመስኩ የሰለጠነ የሰው ሃይልና የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣ ውስን የቴክኖሎጂ አቅምና የገበያ ትስስር ይገኝባቸዋል።

3.5. የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት አፈጻጸም

የመንግስት የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ አገልግሎትና አስተዳደር በተመለከተ፡- በዕቅድ ዘመኑ የዋይድ ኤሪያ መረጃ መረብ (WAN) በአራት ተቋማት የተዘርጋና የአካባቢያዊ መረጃ መረብ (LAN) ዝርጋታ በየአከባቢው ተደራሽ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ሲሆን በአብዛኛው ተቋማት በስታንዳርድ መሰረት ያልተሰራ በመሆኑ WAN የተደራሽነት ችግር እና LAN ከፍተኛ የሆነ የጥራት ችግር ይታያል። ለኢንፎርሜሽን ስርጭትና ለገጽታ ግንባታ የሚያገለግሉ 75 የድረ ገጽ ልማት ለማከናወን ታቅዶ 71 (94.6%) ተከናውኗል። ይሁን እንጂ የድህረገጽ ልማት ስራዎችን በአንጻራዊነት ጥሩ ቢሆንም የድህረገጽ ልማት ስራ ስትራቴጅክ ያለመሆን፣ ችግር ፈቺ የድህረገጽ ልማት ስልጠና ያለመስጠት እና የለሙ ድህረገጾች ወቅታዊ የማይደረጉ በመሆናቸው ምክንያት የውጤታማነት ችግር የተስተዋለባቸው ናቸው።

አስፈላጊ መሆናቸው የታመነባቸው 10 ሶፍትዌሮች ለመንግስት መ/ቤቶች ለማልማት ታቅዶ 10 ሶፍትዌሮች የለሙ ሲሆን 13 ሶፍትዌሮችን ወደ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ የማላመድ ስራ ለማከናወን ታቅዶ 11 (85%) ሶፍትዌሮችን ማላመድ ተችሏል።

የወረዳኔት መሰረተ ልማት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማትን ቁጥር 45 ለማድረስ ታቅዶ 42 (93%) ተቋማት ላይ ተከናውኗል። ሆኖም የታችኛው መዋቅሮች ዞኖች በተለይ የወረዳና ከተማ አስተዳደር የወረዳኔት ክፍያ ባለቤትነት ስሜት ማጣት እና አለመክፈል የመረጃ ልውውጥና አስተዳደር ስርዓታቸውን እንዳይሻሻል አድርጎታል።

በዕቅድ ዘመኑ 52 ዌብ ሳይቶችንና ሲስተሞች ደህንታቸው ተጠብቆ ሆስት ለማድረግ ታቅዶ 24 (46%) ሆስት የማድረግ ስራ ተሰርቷል። 4 የክልል ተቋማትን የባክአፕ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 3 (75%) ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም 3 የመንግስት ተቋማት በአነስተኛ ወጪና አስተማማኝ የክላውድ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ2 (67%) ተቋማት ማሰካት ተችሏል።

ዘመናዊ ኢ.ኮ.ቴ መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ለ8 ተቋማት የተጠናከረ አውቶሜትድ የሆነ የአሰራር ስርዓት፣ አገልግሎትና የመረጃ አያያዝ አንዲዘረጋላቸው ታቅዶ በ13 (+100%) ተቋማት መተግበር ተችሏል።
በየደረጃው 19 የስልጠና ማዕከላት ለማቋቋም ታቅዶ 14 (74%) ማቋቋም የተቻለ ሲሆን ማዕከሉ ከተቋቋመ በኃላ የሚሰጠውን አገልግሎት እሴቶች በአግባቡ የሚለካ መለኪያ ያለመኖር፣ ስልጠና ማዕከል ደረጃ ስታንዳርድ አለመኖር እና ለማቋቋም በቂ ሀብት ያለመመደብ ችግር ታይቷል። እንዲሁም በየደረጃው 19 የጥገና ማዕከላት ለማቋቋም ታቅዶ በበጀት እጥረት ምክንያት 5 (26%) ለማቋቋም ተችሏል።

የለሙ ሲስተሞችና ሶፍተዌሮችን ለማስተዳደር የሚያስችል የተገነባ የዳታ ማዕከል አቅም 75% ለማድረስ ታቅዶ 67.5% ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የለሙ፣የተዘረጉና የቀረቡ መሠረተ ልማቶችን አስተማማኝነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ለ50,000 የኢ.ኮ. ቴ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ30,000 (61%) ማከናወን ተችሏል። የዕድሳት ማዕከሉን በቁሳቁስ 80% ለማሟላት ታቅዶ 70% ማድረስ ተችሏል። ተቋማት የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር 37 ተቋማት የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ 31 (84%) ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የስኩልኔት መሰረተ ልማቶች ቴክኒክ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የስኩልኔት አገልግሎት በተገቢው እንዲሰጡ ለ588 ትምህርት ቤቶች ቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ542 (92%) ማድረግ ተችሏል።
የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስታንዳርዶች፣ ህጋዊ ሥርዓትንና ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ለ700 የግል የኢኮቴ ኢንተርፕራይዞችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫና ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 375 (54%) ፈቃድ የመስጠት

ስራ ተከናውኗል። እንዲሁም በ80 የግሉ የኢኮቴ ዘርፍ ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት/ምርት የሚገባቸውን ሀገር አቀፍ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ስለማሟላታቸው የክትትል ስራ ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል።

ውጤታማ የግል ኢኮቴ ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከማሳደግ አንጻር 20 የግል ኢ.ኮ.ቴ ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 18 (90%) ማከናወን ተችሏል። ለ240 የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የክህሎትና የግንዛቤ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን ለ700 የግል ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ375 (54%) የመስጠት ስራ እና 80 የግል የኢ.ኮ. ቴ ዘርፍ ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት/ምርት የሚገባቸውን ሀገር አቀፍ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ማሟላታቸው ክትትል በታቀደው መሰረት ተከናውኗል። በተጨማሪም 20 ኢንተርፕራይዞችን በግብዓት ለማጠናከር ታቅዶ 18 (90%) ማከናወን ተችሏል።

በሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ ካጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ በፖሊሲ ደረጃ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ያገኘ አለመሆኑና በዚህም የዲጂታል መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት በሚፈለገው ደረጃ የተከናወኑ አለመሆኑ፣ የመንግሥት እና የግል ተቋማት የዲጂታል አገልግሎት አጠቃቀም ባህል፣ ልምድና አቅም አናሳ መሆን፣ የግሉን ዘርፍ የሚያበረታታ አሠራር አለመኖር እና በዘርፉ ጀማሪ የሆኑ የሥራ ፈጣሪዎች በቂ የሆነ ፋይናንስ አለማግኘታቸው የሚጠቀሱ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው።

ምዕራፍ አራት

የማህበራዊ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

4.1 የሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት አፈጻጸም

4.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት አፈጻጸም

የአገራችን ሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ዓላማ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የዜጎች የኑሮ ሁኔታና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡ ፖሊሲው ተግባራዊ በተደረገባቸው ባለፉት 20 ዓመታት የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል "የተመጠነ፣ ደስተኛና የበለፀገ ቤተሰብ ይኑረን" የሚለውን እሳቤ የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ የቤተሰብ አንዲት በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ /15-49 ዕድሜ/ የምትገኝ ሴት በዕድሜ ዘመኗ ትወልዳቸው የነበሩ ልጆች ቁጥር በ1985 ዓ.ም በጣም ከፍተኛ ከነበረበት 7.7 ልጆች በ2008 ዓ.ም ወደ 4.4 ልጆች ዝቅ ብሏል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ በአነስተኛ ደረጃም ቢሆንም በመቀነስ 3.2 በመቶ በፖሊሲው ዘመን ወደ 2.9 በመቶ የደረሰ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ (ምንጭ፡ DHS 2016)፡፡

መሠረታዊ የጤና አገልግሎት በሁሉም የክልሉ የከተማና የገጠር ቀበሌያት ተደራሽ በመሆኑ በሠለጠኑ ባለሙያዎች በጤና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች መጨመርና በውጤቱም የእናቶችና ህፃናት የሞት መጠን እየቀነሰ ከመምጣቱም በላይ በከፍተኛ ትኩረት በዘመቻ በመካሄድ ላይ ያለው የተፋሰስ ልማት ሥራ ውጤታማ በመሆኑ መስኖን በመጠቀም የግብርና ምርት የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ቁጥርና የግብርና ምርት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ በክልሉ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሁኔታ በመሻሻል ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም የተነሳ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች በፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች ውስጥ ተካቶ በመታቀድ በትኩረት እየተሰራ በመሆኑ የክልሉ የደን ሽፋን በየዓመቱ እየጨመረ መጥቶ በ2012 ዓ.ም 23 በመቶ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

በክልሉ የዲሞግራፊ ሽግግር ከከፍተኛ ውልደትና ሞት ምጣኔ ወደ ዝቅተኛ ውልደትና ሞት ምጣኔ የሚደረግ ጉዞ ነው። በዚሁ መሠረት የወሊድ ምጣኔ (total fertility rate) ወደ 4.4 ዝቅ ብሏል። ለውልደት ምጣኔ መቀነስ ዋናው ጉዳይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋን ከፍ ማለቱ ነው። ሴቶች በትምህርት ያላቸው ተሳትፎ እያደገ መምጣት፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻና የመሳሰሉ የባህል ተጽዕኖዎች ደረጃ በደረጃ እየተወገዱ መሄድ እና ሴቶች በሀብት ባለቤትነትና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የነበራቸው ተሳትፎ መሻሻል የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን አፈጻጸም የተሳካ እንዲሆን ያደረጉ ክንዋኔዎች ናቸው። የሥነ ሕዝብና ልማት ፖሊሲ ረጅም ጊዜ ያላስቆጠረ መሆኑ፤ በየደረጃው ያለው መዋቅር ጠንካራ አደረጃጀት የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑና ሥራውን በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወን ውስንነት መታየቱ እና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን የመከታተያና የመገምገሚያ ማዕቀፉ ደካማ መሆኑ እንደ ዋና ዋና ችግሮች የታዩ ናቸው።

4.1.2 የትምህርት ልማት አፈጻጸም

የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት፡- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 51.8% በ2012 መጨረሻ ወደ 72.3% ለማድረስ ታቅዶ በየዓመቱ አፈፃፀሙ ከፍና ዝቅ እያለ መጥቶ 56.3% ደርሷል። በሌላ በኩል ዞኖች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት ያለ ሲሆን ከፍትሐዊነትም አንጻር የሰፋ ክፍተት አለበት።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት በተመለከተ ሕፃናትን በትክክለኛ እድሜያቸው ወደ ትምህርት ቤት እንዲላኩ በማድረግ የትምህርት እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በየዓመቱ ጥረቶች ቢደረጉም በ2008 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ንጥር ተሳትፎ 49.4% የነበረውን በ2012 ዓ.ም 54% ማድረስ የተቻለ ቢሆንም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከ6,227 ወደ 7,925 ለማሳደግ ታቅዶ በመንግስት፣ በግል ድርጅቶች፣ በሕብረተሰቡና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች በተደረገው ርብርብ 779 (45.88%) ትምህርት ቤቶች በመገንባት ወደ 7,006 ከፍ ማድረግ ተችሏል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2007 ዓ.ም 104.9% የነበረውን ወደ 102% ለማሻሻል ታቅዶ በየደረጃው በተደረገው ርብርብ የተሳትፎ ምጣኔውን 94.4% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የጾታ ምጥጥኑንም ከ0.9 ወደ 0.98 ለማድረስ ታቅዶ 0.91 ማድረስ ተችሏል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ ሕፃናቱ በትክክለኛ እድሜያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ በማድረግ ከ98% ወደ 99% ለማድረስ ታቅዶ በ2012 ዓ.ም 87.7% ላይ ሲሆን ከተጣለው ግብ አንፃር በ10.4% ልዩነት ያለውና ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረገው ዋናው ምክንያት በትምህርት ቤቶች የተሟላ ግብዓት ያለመኖርና ለተማሪዎች ምቹና ሳቢ ያለመሆናቸው፣ በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉ ልጆች ለስራ ባይደርሱም ተቀጥረው ገቢ በማግኘት ወላጆችን ለመርዳት በሚል ፍላጎት ወደ ከተሞች የሚያደርጉት ፍልሰት እና ወላጆች ስለትምህርት ጠቀሜታ ባላቸው ዝቅተኛ ግንዛቤ በተለይ ሴት ልጆችን ከትምህርት ገበታ ማስቀረት ናቸው።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከ641 ወደ 1,585 ለማሳደግ ታቅዶ 199 (21.08%) ትምህርት ቤቶች በመገንባት ወደ 840 ማድረስ ተችሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ አንጻር በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከ9-10ኛ ክፍል 42.5 በመቶ ወደ 74.0 በመቶ እንዲሁም ከ11-12ኛ ክፍል ከ9.5 በመቶ ወደ 22 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ በቅደም ተከተል 47.9 በመቶ እና 20.9 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ አንጻር ከ9-10ኛ ክፍል ያለው ትምህርት ንጥር ተሳትፎ 25.2% (ሴት 23.5%) ወደ 66.5% (ሴት 60%) ለማድረስ ታቅዶ 27.1% (ሴት 25.7%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ11-12ኛ ከ9.1% (ሴት 8.5%) ወደ 18.5% ለማድረስ ታቅዶ 11.5% (ሴት 9.7%) ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ከዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ ዝቅተኛ እንደሆነና በአጠቃላይ በሁሉም ደረጃ ያለው ንጥር ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛና ከዓመት ዓመት የመዋዠቅ ሁኔታ እንደሚታይበት መረዳት ይቻላል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ በቅድመ መደበኛ ትምህርት አንጻር ልዩ ፍላጎት ያላቸው እድሜያቸው ከ4-6 ዓመት የሆናቸው ሕፃናትን በሚኖሩባቸው ቀበሌያት ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠርና መረጃ በመሰብሰብ በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር እንዲሳተፉ በተደረገው ጥረት በ2007 ዓ.ም የነበረውን 1.04 ተሳትፎ በ2012 ዓ.ም ወደ 50% ለማድረስ ታቅዶ 9.2% ብቻ ለማድረስ ተችሏል።

ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ አንጻር፡- በ2007 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1-8) ከ3.5 በመቶ ወደ 64 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 21.8 በመቶ ማሳደግ የተቻለ ሲሆን ከ9-10ኛ ክፍል ከ1.4 በመቶ ወደ 32 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 8.4 በመቶ ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም ከ11-12ኛ ክፍል የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቁጥር ከ269 ወደ 6,404 ለማሳደግ ታቅዶ 3,884 (ሴት 1,561) እንዲሆን ተደርጓል።ይሁን እንጂ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ ከዕቅድ አንጻር አፈፃፀሙ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለበት ያመለክታል

በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ሁሉም እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት እንዲሁም ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርትን በፍትሃዊነት ለማዳረስ በቅድመ መደበኛ በ2007 ዓ.ም ቤንች ማጂ 30.9% እና ደቡብ ኦሞ 23.7% የነበረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተመዘገበው አፈፃፀም 38.2% እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎን ከ85.8% ወደ 85.9% የደረሰ በመሆኑ አፈፃፀሙ መሻሻል ያሳየ ቢሆንም ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ትምህርት ተሳትፎን ከ11.8% ወደ 55% ለማድረስ ታቅዶ በዳሰነች 3.5%፣ በሀመር 3.5%፣ በሱርማ 5.7% እና በኛንጋቶም 8.8% ሲሆን አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ የ2012 ዓ.ም መረጃ ያመለክታል።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት ኘሮግራም አንጻር በ2007 ዓ.ም በክልላችን 4,319,281 ጎልማሶች ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ሲሆን ይህን ችግር ለመቅረፍ በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ 95 በመቶ የሚሆኑትን ለማስተማር ታቅዶ በ2012 ዓ.ም 3,432,563 (81.65%) (ሴት 1,784,178) ጎልማሶች ትምህርት ተከታትለው ያጠናቀቁ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በ953,984 (ሴት 506,896) ጎልማሶች በመማር ላይ ይገኛሉ። በሕዝብ ቁጥር ፕሮጀክሽን መሠረት ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ጎልማሶች በ2012 ዓ.ም ወደ 5,853,997 እንደሚያድግ ስለሚጠበቅ እና ሽፋኑንም 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 81.65% ነው።

የትምህርት ጥራትና ተገቢነትን ከማረጋገጥ አንጻር፡- የትምህርት አመራሩ ትምህርት ቤቶች በብቃት በመምራት የሚፈለገዉ የሰዉ ሀይል በማምረት ረገድ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ የ2ኛ ዲግሪ አንዲኖራቸዉ ግብ ተጥሎ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ከ1-8ኛ ክፍል የሰለጠኑ ር/መምህራን ሽፋን ከ27.6 በመቶ ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 48.2% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ1-8ኛ ክፍል የሰለጠኑ ሱፐርቫይዘሮች ሽፋን ከ61.7 በመቶ ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 86.9% ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም ከ9-12ኛ ክፍል የሰለጠኑ ር/መምህራን ሽፋን ከ11.2 በመቶ ወደ 48.6% ለማድረስ ታቅዶ 33.1% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ9-12ኛ ክፍል የሰለጠኑ ሱፐርቫይዘሮች ሽፋን ከ33.3 በመቶ ወደ 93% ለማድረስ ታቅዶ 77.7% ማድረስ ተችሏል።

በክልላችን መምህራን ትምህርት ኮሌጆች በዲፕሎማ መርሃ ግብር ለ4,413 ዕጩ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ተመርቀው ማስተማር ስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን በዚህም ለደረጃው የሰለጠኑ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ሽፋን ከ26.3% ወደ 40% ለማሳደግ ታቅዶ 29.9% ማድረስ ተችሏል።

የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን በሁሉም ኮሌጆች በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም 105,71 **(**ሴት 32,916) መምህራን ተመርቀው በማስተማር ስራ ላይ ይገኛሉ። ይህም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /ከ1-8ኛ ክፍል/ ለደረጃዉ የሰለጠኑ መምህራን ሽፋን ከ61.8% ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ 96.1% (ሴት 31.9%) ለማድረስ ተችሏል።

ከሁለተኛ ደረጃ (9-10ኛ) መምህራን አንፃር 16,515 (ሴት 3,571) መምህራን በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ሰልጥነው በማስተማር ላይ ሲሆኑ ለደረጃው የሰለጠኑ የ2ኛ ደረጃ መምህራን ሽፋን ከ91.7% ወደ 98% ለማድረስ ታቅዶ 85.7% (ሴት 90.4%) ብቻ ማሳካት ተችሏል።

ከመሰናዶ (11-12ኛ) መምህራን አቅርቦት አንጻር 913 (ሴት 86) መምህራን በሁለተኛ ዲግሪ ስልጠና አጠናቀው በማስተማር ላይ ሲሆኑ ይህም በ2007 ዓ.ም 11.25% የነበረውን ለደረጃው የሰለጠኑ መምህራን ሽፋን ወደ 21% ለማድረስ ታቅዶ 13.6% ብቻ መፈፀም ተችሏል።

የክፍል-ተማሪ ጥምርታ በተመለከተ በትምህርት ቤት መሻሻል ትግበራ መሰረት ከ1-4ኛ ክፍል ከ1፡67 ወደ 1፡50፤ ከ5-8ኛ ክፍል ከ1፡56 ወደ 1፡50፤ ከ1-8ኛ ክፍል ከ1፡63 ወደ 1፡50 ለማድረስ ታቅዶ ከ1-4ኛ 1፡62፤ ከ5-8ኛ 1፡55 እንዲሁም ከ1-8ኛ 1፡59 ማድረስ ተችሏል። በተመሳሳይ ከ9-10ኛ ክፍል ከ1:65 ወደ 1:40 እና ከ11-12ኛ ክፍል ከ1:52 ወደ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ እንደቅደም ተከተላቸዉ 1:66 እና 1:53 ማድረስ ተችሏል።

የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በስታንዳርዱ መሰረት አሳትሞ ለተማሪዎች ለማቅረብ በተደረገው ጥረት የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በሁሉም የክፍል ደረጃ 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ በአማካይ 1፡2 እንዲሆን ተደርጓል።

በትምህርት ቤቶች ስታንዳርድ መሰረት በ2012 ትምህርት ዘመን በአጠቃላይ የመጀመሪያ እና የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች ሁኔታ ሲታይ 32.8 በመቶ ብቻ ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መማሪያ ክፍል ሲኖራቸው ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም 70.6 በመቶ ደረጃውን የጠበቀ መማሪያ ክፍሎች ያላቸው ናቸው።

ትምህርት ቤቶች ደረጃ በተመለከተ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9.84% በደረጃ1 (ስታንዳርድ የማያሟሉ) ፣ 79.77% በደረጃ 2 (በመሻሻል ላይ ያሉ) ፣ 10.28% በደረጃ 3 (ስታንዳርዱን ያሟሉ) እና 0.085% በደረጃ 4 (ስታንዳርዱን በከፍተኛ ደረጃ ያሟሉ) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውጤት ስንመለከት 4.3% በደረጃ 1 ፣ 68.9% በደረጃ 2፣ 26.6% በደረጃ 3 እና 0.2% በደረጃ 4 ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ከታቀደው አንፃር በሁሉም ደረጃዎች ዕቅዱን ማሳካት አልተቻለም።

ይህም የሚያሳየው አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ከስታንዳርዱ በታች መሆናቸውን እና ለመማር ማስተማሩ ስራ እና ለተማሪዎች ውጤት መቀነስ እንዲሁም የትምህርትን ውስጣዊ ብቃት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የሆነ ችግር ያስከተለ መሆኑን ያሳያል።

የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማሻሻል መርሀ ግብርን አጠናክሮ ከመተግበር አንፃር፡- በክልሉ የሬዲዮ ትም/ት የሚያገኙ ትም/ት ቤቶች ሽፋን 65% ማሳደግ ተችሏል። የሳተላይት ትምህርት በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ቀጥታ ሥርጭት ያላቸው ትም/ቤቶች ሽፋን ከ59.3% ወደ 88%፣ የኮምፒዩተር ላብራቶሪ የተቋቋመላቸው ትም/ቤቶች ሽፋን ከ46% ወደ 67% ማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም በኢለርኒንግ/ክላውድ ፕሮጀክት በሰርቨሮች የታገዘ የኮምፒዩተር ላብራቶሪ የተቋቋመላቸው ትምህርት ቤቶች ሽፋን ከ4% ወደ 10% ማሳደግ ተችሏል።

የተማሪ መጠነ ማቋረጥን በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን የ1ኛ ክፍል ከ25.2% ወደ 14.5% ለመቀነስ ታቅዶ በ2011 ዓ.ም ከተመዘገቡት 873,907 ሕጻናት መካከል 14.5% በተለያየ ምክንያት በማቋረጣቸው 14.5% ማድረስ ተችሏል። የመጀመሪያ ደረጃ (1-8 ክፍል) ከ18.4% ወደ 13% እና ከ9-10 ክፍል ከ16.3% ወደ 8.3% ለመቀነስ ተችሏል። እንዲሁም ከ11-12 ክፍል ከ11.7 ወደ 3.4 ለመቀነስ ተችሏል።

የተማሪ መጠነ መድገምን ከ1-4 ክፍል ከ5.3 ወደ 8.8፣ ከ5-8 ክፍል ከ6.2 ወደ 8.6 እና ከ1-8 ክፍል ከ8 ወደ 8.6 ከፍ ያለ እና ከ9-10 ክፍል ከ8.4 ወደ 7.3 መቀነስ የተቻለ ሲሆን በ2ኛዉ ዕ.ት.ዕ ላይ መጠነ መድገምን ሁለት በመቶና በታች ለማስመዝገብ ግብ የተጣለ ቢሆንም የተለጠጠ ዕቅድ በመታቀዱ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ማሳካት አለመቻሉ ይታያል።

4.1.3 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ልማት አፈፃፀም

የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በተመለከተ በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን በሙያ ደረጃዎች የብቃት ምዘና መሣሪያ ዝግጅት ከ613 ወደ 813 ለማሳድግ ታቅዶ 422(52%)፣ ከመሪ መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የኢንዳስትሪ መዛኞች የማፍራት

ሥራ ከ1,422 ወደ 9,271 ለማሳደግ ታቅዶ 10,952 ማሳካት የተቻለ ሲሆን የምዘና ማዕከል የማደራጀትና ዕዉቅና የመስጠት ሥራ ከ252 ወደ 8,748 ለማሳደግ ታቅዶ 6,714 ማድረስ ተችሏል። በሁሉም ሙያዎች በኢንደስትሪዉ ከተሰማሩ ባለሙያዎች ብቃታቸዉ የተረጋገጠላቸዉ ዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ ሙያተኞች መጠን ወደ 50 ለማድረስ ታቅዶ 21 በማድረስ 42 በመቶ ማሳደግ ተችሏል።

የስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃት በምዘና ማረጋገጥ መጠን ከ30,000 ከነበረበት ወደ 131,886 ለማሳደግ እና በ5 ዓመቱ 659,430 ለማድረስ ታቅዶ ዓመታዊ የመመዘን መጠን ወደ 92,817(74%) ያደገ ሲሆን በ5 ዓመቱ አጠቃላይ 301,598 (46%) መመዘን ተችሏል።

የሰልጣኝ ልማት በተመለከተ በ2ኛው ዕ.ት.ዕ በመንግሥት እና በግል ቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጆች/ተቋማት ከደረጃ I - V 411,464 ሰልጣኞችን ለማሰልጠን ታቅዶ 282,834(69%) የሰለጠኑ ሲሆን ከሰልጠኑት መካከል 140,859(ሴት 49.8%) ሰልጣኞች ናቸው።

ገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠና የዜጎችን ሥራ አጥነት በመቅረፍ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ በሚደረገዉ ጥረት 1,300,544 ሰልጣኞች ለማሰልጠን ታቅዶ 518,877 (ሴት 180,829) የተከናወነ ሲሆን ከእቅዱ አንፃር 40% ማከናወን ተችሏል።

የሴቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥ በተመለከተ በሁሉም ሙያ የሴት ሰልጣኞች ቁጥር ከ49 ወደ 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 49.67 በመቶ፣ በአሰልጣኝነት ከ17.8 ወደ 32 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 22.3 በመቶ እና በአመራርነት ከ3 ወደ 12 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 12.3 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የተቋማት ተደራሽነት በተመለከተ ተደራሽነትን ለማሳደግ ተቋማትን የማስፋፋት ሥራ በማከናወን የቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጆች ከ35 ወደ 134 ወረዳዎች ለማሳደግ ታቅዶ 68(51%) ተከናውኗል።

የሥልጠና ጥራትን ማሻሻል በተመለከተ በመንግስት ኮሌጆች የስልጠና መሣሪያዎች ግብዓት በወርክሾፕ ስታንዳርድ ለማሟላት ከ16.3 ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ 21 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የቴክኖሎጅ ሽግግርና ኢንዳስትሪ ኤክስቴንሽን ተግባር በተመለከተ ቴክኖሎጅዎችን በእድገት ቀጠና እና በገበያ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ዓመታዊ የዕሴት ሰንሰለት ትንተና ብዛት ከ300 ወደ 312 ለማድረስ ታቅዶ 440(+100%) ማድረስ ተችሏል። የተሸጋገረ አዋጭ ቴክኖሎጂዎች በቁጥር ከ130 ወደ 1,242 ለማድረስ ታቅዶ 1,267(+100%) ቴክኖሎጅዎችን ለአባዥ ኢንተርፕራይዞች ማሸጋገር ተችሏል። በቴክኖሎጂ የተፈጠረ ሀብትን ለማሳደግ በተሸጋገረ ቴክኖሎጂ የተፈጠረ ሀብት መጠን በሚሊዮን ከ16 ወደ 249 ለማድረስ ታቅዶ 190.4(76.5%) ሚሊዮን ብር ማድረስ ተችሏል። የኢንተርፕራይዞችን ብቃት ለማጎልበት በተሟላ ድጋፍ እስከ ደረጃ 4 ብቁ የሆኑ

ጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ብዛት ከ8,722 ወደ 63,621 ለማሳደግ ታቅዶ 65,034(+100%) ማድረስ ተችሏል።

4.1.4. የደቡብ አመራር አካዳሚ ስራዎች አፈጻጸም

ተቋም ተኮር አገልግሎት ከማስፋት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ ከክልሉ የተውጣጡ የጀማሪ አመራር አካላት፣ የቀበሌ አመራር አካላት፣ የከተማ ዘርፍ አመራር አካላትና ግንባር ቀደም ፈጻሚዎች፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል አመራርና ፈጻሚዎች፣ የተለያዩ ሴክተር ባለሙያዎች (የጤና ኤክስቴንሽን፣ የኮንስትራክሽን፣ የከተማና ገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የፍትህ ፣ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት፣ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ)፣ የወጣቶች እና የሴቶች ሊግና ማህበራት፣ የፓይለት ቀበሌ ፕሮጀክት አመራሮች፣ የክልሉ ፖሊስ ኃይል አባላት በአጠቃላይ 19 የተለያዩ አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት የአመራርና የፈጻሚዎች ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ላይ በመሥራት የተቋማት አፈጻጸም ደረጃ እንዲሻሻል ጥረት ተደርጓል።

ክልል አቀፍ ችግሮችን በመለየትና በማጣከር እንዲሁም ሥልጠናዎችን በማቀድና በአፈጻጸም ወቅትም ያሉ ጥንካሬዎችንና ጉድለቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እየገመገሙ ከመምራት እና ለቀጣይ ሥራዎችም ትምህርት ከመውሰድ አንጻር በስትራቴጂው ዘመን 18 ጊዜ ለመሥራት የታቀደ ሲሆን 20 ጊዜ የባለድርሻ ውይይት በማድረግ ከፍተኛ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል።

የመካከለኛና ጀማሪ አመራር ስልጠናን በተመለከተ 24,242 አመራር ለማሰልጠን ታቅዶ 16,637 /68.6%/ መካከለኛና ጀማሪ አመራር እንዲሰለጥኑ ተደርጓል። የታቀደውን ያክል መፈጸም ያልተቻለው በተለይ በ2011 እና 2012 በጀት ዓመት ያለው ሀገራዊና ክልላዊ ነባራዊ ሁኔታ ባለመፍቀዱ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። በሁለተኛው የዕድገትና ትንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በልዩ ሥልጠናዎች ለ26,184 ግንባር ቀደም ፈጻሚዎችና ከጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ለሚላኩ አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ23,184 /88.5%/ ሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት ተችሏል።

የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ከማጎልበት አንጻር በአምስት ዓመቱ 44 የሥልጠና ሥራዎችን የሚያግዙና ክልላዊ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ የሚያፈልቁ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለመሥራት ታቅዶ 55 የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተከናውኗል። የተሰሩ ጥናቶችም ለክልሉ መንግስት ውሳኔ ግብዓትነት ፋይዳ የነበራቸው ሲሆን የጥናቱ አፈጻጸም ከዕቅዱ ሲነጻጸር ከፍተኛ ነበር። በቀጣይም የጥናትና ምርምር ዘርፉን በግብዓትና በሰው ኃይል አደረጃጀት ማጠናከር ከተቻለ ትልቅ አጋዥ አቅም መሆን እንደሚችል አሳይቷል።

ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋፋት የአካዳሚውን ዕቅድ አፈጻጸም ከማሳደግ አንጻር ከአቻ ተቋማትና ከውጭ ሀገራት 8 የተለያዩ ተሞክሮዎችን ለመቀመር የታቀደ ሲሆን 3 ጊዜ ከቻይና ሀገር የውጭ ተሞክሮ

በአካዳሚው አመራሮችና ከፍተኛ ባለሙያዎች እና 4 ጊዜ የአቻ ተቋማት ተሞክሮ በመቀመር የተግባራት አፈጻጸም እንዲያድግ ተደርጓል። የዕቅድ አፈጻጸሙ 87.5% ነው።

4.1.5. የጤና ልማት ዕቅድ አፈጻጸም

የጤና አገልግሎት ሽፋን፡- የጤና አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለማዳረስ በተከናወኑ ሥራዎች በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የጤና አገልግሎት ሽፋን በጤና ጣቢያ 88.6% የደረሰ ሲሆን በቀጣይ ዓመት በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ጤና ጣቢያዎች ተጠናቀው ስራ ሲጀምሩ የጤና አጠባበቅ ጣቢያ ሽፋኑ ወደ 91% ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል። በጤና ኬላ 94%፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 27%፣ በአጠቃላይ ሆስፒታል 82.7% እና በሪፈራል ሆስፒታል 50% ማድረስ ተችሏል።

የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎት በተመለከተ የእናቶች ሞት መጠን ከ100,000 በህይወት ከተወለዱ ህጻናት አንጻር ከ420 እናቶች በ2012 ወደ 199 ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም ወደ 401 መቀነስ ተችሏል።

በክልሉ የአንድ እናት አማካይ የውልደት መጠን ብዛት ከ5.6 ወደ 4.1 የቀነሰ መሆኑን እና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነት /CPR/ መጠን በአራት ዕጥፍ ያህል (ከ11.9% ወደ 44.6%) ያደገ እንደሆነ ያሳያል። አንድ የገጠር እናት የመውለድ ብዛት በአማካይ 6 ከነበረበት ወደ 5.2 የቀነሰ መሆኑ የሚያበረታታ ቢሆንም በከተማ ከምትኖር እናት (2.3) በበለጠ ጊዜ የምትጸንስ መሆኑን ያሳያል። እንዲሁም ያልተማረች እና ሁለተኛ ደረጃና ከዛ በላይ በተማረች እናት መካከል የአገልግሎት ተጠቃሚነት ልዩነት የሚታይ ሲሆን ይህም በአገልግሎት ፍትሃዊነት (Equity) ዙሪያ መሻሻል እንዳለበት ያሳያል።

የጨቅላ ህጻናት ሞት መጠን ከ36/1,000 ወደ 30/1,000፣ ከ1ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ከ85/1,000 ወደ 43/1,000፣ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሞት ከ142/1000 ወደ 55/1000፣ ከእርግዝናና ወሊድ ጋር በተያያዘ የእናቶች ሞት ከ420/100,000 ወደ 401/100,000 መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም እስከ አንድ ዓመት በህይወት ይኖራሉ ተብሎ ከሚገመተው ህፃናት አንጻር ከ12-59 ወራት የሆኑ ህፃናት ሞት መጠን 26/1,000 መሆኑን ያሳያል።

ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ በክልሉ የቲቢ በሽታ ምርመራና ህክምና አገልግሎት ተደራሽነት ከማሳደግ አንጻር 100% ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የመድኃኒት ክትትል አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ከነበረበት 88% ወደ 90% ከፍ ብሏል። የግል የጤና ተቋማት ከአጠቃላይ ቲቢ ልየታ የ15% ድርሻ ያለው አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ ችለዋል። በክልላችን በየዓመቱ ከ33,705 በላይ ሰዎች በቲቢ በሽታ ሊጠቁ እንደሚችሉ ይገመታል። በ2012 ዓመት የቲቢ በሽታ መጠነ ልየታ የተጣለው ግብ 87% ሲሆን አፈፃፀሙ 65% ነው።

የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ የወባ በሽተኞች በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 638,814 በ2012 ዓ.ም ወደ 202,493 የደረሰ ሲሆን በ68% መቀነሱ አበረታች ውጤት መመዝገቡን ያሳያል። በክልሉ ዝቅተኛ የወባ መተላለፍ ዕድል በሚታይባቸው 112 ወረዳዎች ወባን የማጥፋት ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት በ2011 ዓ.ም በ112 ወረዳዎች ከሚገኙ ቀበሌዎች መካከል ለ24 ተከታታይ ወራት ወባን ሪፖርት ያላደረጉ ሽፋን 34% መሆኑ ታይቷል። በሌላ መልኩ በክልሉ በወባ ምክንያት የሚታመሙ መጠን ሰዎች ዕቅድ 5/1,000 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን አፈጻጸሙ 11/1,000 በመሆኑ ዝቅተኛ ሆኖ ተመዝግቧል።

የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ/ስርጭትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር በክልላችን ጠቅላላ 57,655 ያህል ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩና መጠኑም /HIV Prevalence/ 0.42% መሆኑን ያመላከተ ሲሆን አዲስ የቫይረሱ ስርጭት በሁሉም እድሜ ደረጃ 0.07% ይሆናል። ቫይረሱ በደማቸው ይኖራል ተብሎ የሚገመቱ ከ15 ዓመት እድሜ በላይ የሆኑ አዋቂ ሰዎች ላይ መጠኑ /HIV Prevalence/ በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 0.6% ወደ 0.42 መቀነስ አሳይቷል።

የጤና ሁኔታን በተመለከተ የክልሉ የጤና ሁኔታ ሲታይ የአንድ ሰው በህይወት የመኖር እድሜ 64 ወደ 69 ማድረስ የታቀደ ሲሆን በ2011 ዓ/ም አማካይ የእድሜ ጣሪያ 65.5 ዓመት ሲሆን ለሴቶች 67.3 ዓመት እና ለወንዶች ደግሞ 63.7 ዓመት መሆኑን የ2018 (እ.አ.አ) World Health Rankings ሪፖርት ያሳያል።

በአጠቃላይ በጤናው ዘርፍ የታዩ ድክመቶች በተመለከተ አብዛኛው የሃይጂንና አካባቢ ጤና አገልግሎቶች ሽፋን መሻሻል አለማሳየቱ፣ ጤና ተቋማት በአብዛኛው የግብዓት አቅርቦት፣ የባለሙያ ተነሳሽነት፣ የአቅም እና የጤና መሰረተ-ልማት ክፍተት መኖር፣ የአገልግሎት ቀጣይነት አሰራር/ሂደት ደካማ መሆን /inadequacy in Continuum of care/ ፤ የከፍተኛ ህክምና ተቋማት በቅርብ ርቀት የማይገኙ መሆኑ እና የቅብብሎሽ ስርዓቱ የተጠናከረ አለመሆን፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መኖር፣ የአገልግሎት ጥራት መጓደል፣ ከግል የጤና ተቋማት የተሟላ እና ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ያለመኖር፣የጥናትና ምርምር ስራዎች ዝቅተኛ መሆንና ያለውንም የመጠቀም ልምድ አናሳ መሆን፣ መሰረታዊ የሆኑ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብዓቶች አለመሟላት፣የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ቅድመ ብልሽት መከላከልና የጥገና ስርዓት ያልዳበረ መሆን፣አዳዲስ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን የህክምና መሳሪያዎች አያያዝ፣ አሰራርና የአጠቃቀም ጉድለት መኖር ናቸው።

4.2 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት አፈጻጸም

የሴቶች ዘርፍ፡- የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሴቶችንና ህጻናትን ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማዳን በተሰራው የግንዛቤ ሥራ 1,970,484 (46%) የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ የተቻለ ቢሆንም ካለዉ የሕዝብ ቁጥር አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። የሴቶችን መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር 4,221,042 የህብረተሰብ ክፍሎችን የሴቶችን ህገ መንግስታዊና ሰብአዊ መብትና ጥቅማቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ ተችሏል።

የሴቶችን የኢኮኖሚ አቅም ከማሳደግ አንጻር ለሴቶች በተፈጠረላቸው የተለያዩ የግንዛቤ ሥራዎች 11,836,237 ሴቶች በተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ብር 3,878,409,356 ማስቆጠብ የተቻለ ሲሆን መቆጠብ ከጀመሩት 1,546,972 ሴቶች በተለያየ የገቢ ማስገኛ የሥራ መስኮች በመሰማራት ብር 6,405,280,926 የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።

የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተለያዩ ጊዜያቶች በተሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በክልል ደረጃ የውሳኔ ሰጭነት በክልል ምክር ቤት 48.8 በመቶ፤ በህግ ተርጓሚ 15 በመቶ፣ በአስፈጻሚ አካላት 25 በመቶ ሲሆን በዞን ደረጃ በምክር ቤት 37.57 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ 10 በመቶ፣ በአስፈጻሚ አካላት 21 በመቶ፣ እንዲሁም በወረዳ ምክር ቤት 37.45 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ 22 በመቶ እና በአስፈጻሚ አካላት 19 በመቶ ለማድረስ ተችሏል። ይሁን እንጂ የሴቶች የአመራርነትና ውሳኔ ሰጭነት ሚና በሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ በቀጣይ በትኩረት ሊሰራ ይገባል።

የሴቶችን ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንፃር በክልላችን በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማስወገድ በተሰሩ ሥራዎች ካሉን 231 ገጠር ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ 17ቱን ነፃ ማውጣት የተቻለ ሲሆን ካሉን 4,172 ገጠርና ከተማ ቀበሌያት ውስጥ 510 ያህሉን ነፃ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ከሚፈፀሙባቸው ቀበሌያት ስፋት አንፃር ሲታይ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ነው። ከዚህ በተጨማሪ 14,718 ሴቶች ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲጠበቁ ማድረግ ተችሏል፤ እንዲሁም በሴትነታቸው ከሚደርስባቸው ከተለያዩ የኃይል ጥቃቶች 15,624 ሴቶች እንዲጠበቁ ተደርጓል።

የስርዓተ-ጾታ ማካተት ተቋማዊነት ከማረጋገጥ አንጻር በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ሁሉም ሴክተሮች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን ተቋማዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የታቀደ ቢሆንም ማከናወን የተቻለው 22% ብቻ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ሴክተሮች የስርዓተ ጾታ ጉዳይን በዓመታዊ ዕቅዳቸው የሚያቅዱ ቢሆንም ተግባራዊነቱን እየገመገሙና ማስተካከያ እያደረጉ ከመሄድ አንፃር ትልቅ ጉድለት ያለው ነው።

የህጻናት ዘርፍ፡- በዓለምና በአህጉር አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም በሀገራችን በወጡ ህጎች፣ አዋጆች፣ደንቦች እና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ በተለያየ ርዕሰ ጉዳዮች (በሴቶችና ህጻናት ጥቃት፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ በምቹ ችሎት አስፈላጊነት፣ በህፃናት ትምህርትና ጤና) ዙሪያ ለ46,923,833 (ሴት 23,470,778) ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ ለ29,263,323 (ሴት 15,243,766) ህብረተሰብ ግንዛቤ በመስጠት የእቅድ አፈፃፀም 62.36% ማድረስ ተችሏል።

ህፃናት ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ አንጻር በገጠርና በከተማ ቤተሰብን ለማጠናከር የሚያስችሉ የምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተግባራዊ በማድረግ በተደረገ ጥናት የሴት ልጅ ግርዛት 53.2 በመቶ፣ የህፃናት ጋብቻ 24.7 በመቶ እንዲቀንስ የተደረገ ሲሆን በህፃናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ህገ ወጥ

ዝውውርና በሴቶች ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ የተለያየ ጥረቶች ቢደረጉም ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም።

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት ለማጠናከር የማህበረሰብ አቀፍ፣ የማዋሀድና ማቀላቀል፣ የአደራ ቤተሰብ፣ የጉዲፈቻና የህፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን በነዚህ አማራጭ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች 370,130 (ሴት 179,697) ታቅዶ 542,451 (ሴት 263,675) ህፃናት ተጠቃሚ አንዲሆኑ ተደርጓል። በማህረሰብ አቀፍ ፕሮግራም 461,043 ከጎዳና በህገ ወጥ ዝውውር እና 36,540 ከተቋማት ወደ ቤተሰቦቻቸው የተቀላቀሉ፣ 2,762 በአደራ ቤተሰብ፣ 6,995 በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ፣1,209 በህፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት፣ 736 ጥቃት የደረሰባቸው ህጻናት የተሃድሶ ማዕከል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የህጻናት ተሳትፎን ለማሳደግ ወጥነት ያለው የህፃናት ፓርላማዎች የሚቋቋሙበትና የሚመሩበት የአሰራር ማዕቀፍ (የህፃናት ፓርላማ ጋይድላይን) እንዲዘጋጅ በማድረግ 177 የህፃናት ፓርላማ 24,355 (ሴት 12,190) አባላት በማፍራት እና 235 በወረዳ ደረጃ የህፃናት መብት ክበባት እንዲቋቋሙ የተደረገ ሲሆን የህጻናት አደረጃጀቶች ስልጠና፣ የልምድ ልውውጥና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናከሩ ተደርጓል። ለ121,539 (ሴት 119,195) የሴቶችና ህፃናት መብቶችን ለማስከበር ታቅዶ 110,665 (ሴት 108,036) ሴቶችና ህጻናት የመብት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የወጣቶች ዘርፍ፡- የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በገጠር ግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች 5,300,000 (ሴት 2,597,000) ወጣቶች ለስራ ያላቸው አመለካከት ተቀይሮ ወደ ስራ ገብተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ1,737,493 (ሴት 714,678) ወጣቶች በቋሚነትና በጊዚያዊነት ወደ ስራ በመግባት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

በአፍላ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጋላጭ የሆኑ 4,000(ሴት 2,000) ተጋላጮች በገቢ ማስገኛ ስራ መስኮች ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 3,822 (ሴት 1,739) ተጋላጮችን ወደ ስራ ገብተው ተጠቃሚ ሆነዋል።

በህይወት ክህሎትና በማህበረሰብ ውይይት የወጣቱን ግንዛቤ ከማሳደግ አንጻር 4,181,736 (ሴት 2,030,986) ወጣቶች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,389,920 (ሴት 1,066,371) ወጣቶች ግንዛቤያቸውን በማዳበር የአሉታዊ አቻ ግፊቶችን መቋቋና የአካባቢያቸውንም ችግር በጋራ እየፈቱ ጤናማ ህይወት እንዲመሩ ማድረግ አስችሏል።

በጎ ፈቃድ አገልግሎት በተመለከተ፡- በተቀረፀው የወጣቶች ፕሮግራም መሰረት በእቅድ ዘመኑ በዓመት በአማካይ 4,477,073 (ሴት 1,566,975) ወጣቶችን ከ14 በላይ በሆኑ መስኮች ተሰማርተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 14,449,221 (ሴት 5,591,646) ማለትም በየዓመቱ በአማካይ 2,899,844 (39% ሴት) በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ተሰማርተው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። በአገልግሎታቸው በአጠቃላይ 41,305,969 (42% ሴት) በየአመቱ በአማካይ 8,261,194 (40% ሴት) የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ አድርገዋል። ለ5 ተከታታይ ዓመታት በየመስኩ ተሰማርተው በሰጧቸው አገልግሎቶች በመንግስትና በህብረተሰብ ይወጣ የነበረን ግምቱ በገንዘብ 8,623,623,100 ብር የሆነ ወጪ ማዳን ተችሏል።

የወጣቶችን ጉዳይ ተቋማዊ ከማድረግ አንጻር ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች እና በወጣቶች ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የወጣቶችን ጉዳይ በልማት ዕቅዶቻቸው ፕሮግራምና ፕሮጀክቶቻቸው አካተው እንዲሰሩና ከእቅድ እስከ ግምግማ ባለው ሂደት ወጣቶች እንዲሳተፉ እንዲያደርጉ ለማድረግ የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች ከመጽደቃቻው በፊት የወጣቶችን ጉዳይ ያካተቱ መሆናቸውን እንዲረጋገጡ የማድረግ፣ እንዲሁም ከክልል ጀምሮ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አስፈጻሚ ሴክተሮች ፎካል ፕርሰኖች እንዲመደቡ፣ በክልል ደረጃ ቁልፍ ድርሻ ያላቸው 16 ሴክተሮች የወጣቶችን ጉዳይ አካተው እንዲሰሩ እና በዞን ደረጃ 12 ሴክተሮች፣ በወረዳና ልዩ ወረዳ ደረጃ 10 ሴክተሮች የወጣቶችን ጉዳይ አካተው እንዲሰሩ ተደርጓል።

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት በህብረተሰቡ ዘንድ በሴቶች፣ በህፃናትና በወጣቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፣ ለሴቶችና ለወጣቶች የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በቂና ዘላቂ አለመሆናቸው፣ የሴቶች የመደራደርና የመወሰን አቅም ማነስ፣ የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ውክልና በዋና ዋና የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ማነስ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኃይል ጥቃቶች መበራከት፣ የሴቶችና የወጣቶች ቁጠባ ባህል አለመዳበር፣ የሕግ አፈጻጸም ክፍተት፣ ሴቶችንና ወጣቶችን የመደገፍና ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጪነት የማምጣት ችግር እና የመንግስት ተቋማት የሴቶችን፣ የህፃናትንና የወጣቶችን ጉዳይ የዋና ሥራቸው አካል አድርገው አለመሥራት የታዩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመታት ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ተጠቃሚነታቸው፣ ውክልናቸውና ተሳትፎአቸው እንዲረጋገጥና በክልሉ ልማት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል።

4.3 የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ልማት አፈጻጸም

የማህበራዊ ደህነነት ልማት ጥበቃን በማስፋፋት በችግሮች ተጠቂ የሆኑ ሰዎች የማህበራዊ ካሽ ትራንስፈር ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ቁጥር 7,500 ወደ 10,800 ለማድረግ ታቅዶ 67,188 (+100%) ሰዎችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም ለተለያዩ የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ 194,218 ዜጎች ለማህበራዊ አገልግሎት የሚሆን የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት የማህበራዊ ደህንነታቸዉን ለማረጋገጥ ታቅዶ 105,807 (54%) ዜጎች የተለያዩ ድጋፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ለአካል ጉዳተኞች በተሃድሶ ማዕከል የተቀናጀ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ 27,345 አካል ጉዳተኞችን በማዕከሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 30,741 (+100%) ዜጎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። እንዲሁም በማሕበረሰብ ውስጥ ልዩ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠረላቸዉ ጫሪና ደጋፊ ያጡ አረጋውያን ከ3,400 ወደ 4,560 ማሳደግ ተችሏል።

የአካል ጉዳተኞች የሙያ ሥልጠናና የሥራ ስምሪት አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረጉ ሰዎች ከ1,200 ወደ 1,550 ከፍ ሲል ለአካል ጉዳተኞች በተሃድሶ ማዕከል የተቀናጀ አገልግሎት ለመስጠት 27,345 አካል ጉዳተኞችን በማዕከሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 30,741(+100%) ዜጎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። በመንግስታዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት አንጻር በሀገር ውስጥ 1,062,000 ዜጎችን በሥራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ ለ585,371 (55%) ሥራ ፈላጊዎች ድጋፍ በመስጠት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊነት ዙሪያ ለ9,286,918 (ሴት 4,643,458) የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ ለ16,410,080 (+100%) (ሴት 8,237,275) ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

ከውጭ ሀገር ስራ ስምሪት አንፃር በቤት አያያዝ ሙያ 16,500 ዜጎች ለማሰልጠን ታቅዶ ለ72,800 (ሴት 65,250) ስልጠና ተሰጥቷል። በክብካቤ ሙያ (Care giving) 25,700 ዜጎችን በማሰልጠን በዉጭ አገር እና በሀገር ዉስጥ ወደ ስራ ለማሰማራት ታቅዶ 9,762(ሴት 9,300) ስራ ፈላጊዎች ለዉጭ አገር ስራ ስምሪት ብቁ የሚያደርጋቸዉን ምዘና አልፈዉ 1,999 ዜጎች የቅድመ ጉዞ ስልጠና በመዉሰድ ዉል ጸድቆላቸዉ በዉጭ አገር ስራ ተሰማርተዋል።

የሙያ ደህንነት፡- ጤንነትና የሥራ አካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር አንጻር በ15,865 ድርጅቶች የሥራ ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 12,582 (79%) የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር በማድረግ በልማት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የአፈፃፀም ችግሮችን የመለየትና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

የሥራ ክርክሮችን 100% በስምምነት ለመፍታት ወይም ዕልባት ለመስጠት ታቅዶ ከቀረቡ 4,958 ውስጥ 4,840 (98%) የሥራ ክርክሮች በስምምነት በመፍታት በተከራካሪ ወገኖች መካከል የእሽናፊና ተሸናፊነትን መንፈስ በማስቀረት በአሠሪና ሠራተኛው መካከል መልካም ግንኙነት በመፍጠር በሥራ ክርክር አለአግባብ ሊባክን የነበረውን የምርት ጉልበት፣ ጊዜና ወጪ እንዲቀንስ ተደርጓል።

በ2,310 ድርጅቶች የስራ ቦታ ትብብር እና ሁለትዮሽ ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ 197 (9%) ድርጅቶች በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የስራ ቦታ ትብብር እና የሁለትዮሽ ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት በመዘርጋት ያለ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በራሳቸው አለመግባባትን የመፍታት ልምድ እየዳበረ በመሄዱ የኢንዱስትሪ ሠላም እንዲሰፍን ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት የቀጥታ ድጋፍ ሴፍቲኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎችን በቅንጅት በመለየትና አገልግሎቱን በተቀመጠው ሥርዓት መሠረትና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር አፈጻጸሙ ደካማ መሆኑ፣ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሠሩ ሥራዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመፈፀማቸው፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሕጻናት የሚሰጡ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፣ ወጣቶች የሱስና የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በቂ የሆነ የመከላከል ሥራ አለመሰራቱ፣ ሕጻናት ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ቤተሰብን የመደገፍና የማጠናከር ሥራ በሚፈለገው መጠን አለመሰራቱ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ በጎዳና ላይ የሚተዳደሩ ሴቶችና ሕጻናት ወደ ጤናማ ማኅበራዊ ሕይወታቸው እንዲመለሱና ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ የትብብርና የቅንጅት አሠራሩ ያልተጠናከረ መሆኑ ማህበራዊ ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ መፍታት እንዳልተቻለ የአፈጻጸም ግምገማው ያሳያል።

ምዕራፍ አምስት

የሕዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥራዓት ግንባታ አፈጻጸም

5.1. የሕዝብ አገልግሎትና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም

የሪፎርም ስራዎች በተመለከተ የህብረተሰብ እና የህዝብ ክንፍ ተሳትፎን በየደረጃዉ በሚገኙ ተቋማት ከማሳደግ አንጻር በዕ.ት. ዕ 2ኛዉ ዘመን ግብ ተጥሎ ተግባራዊ እየተደረገ የቆየ ሲሆን የህብረተሰብ ተሳትፎ ማረጋገጫ ስርዓትና የገጠር ቀበሌ ፓኬጅ ሰነዶችን ከልሶ በማዘጋጀት በአሰራሩ ላይ በየደረጃዉ ለሚገኙ ሁሉም የመንግስት ተቋማት አመራሮች፣ ፈጻሚዎች እና የቀበሌ ስራ አስኪያጆች ሰልጠና 100% ለመስጠት ታቅዶ 95% ለሚሆኑ ስልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም በሁሉም የአስተዳደር እርከን ለሚገኙ የመንግስት ተቋማት አመራር፣ ፈጻሚዎች እና ለህዝብ ክንፍ አባላት 100% ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 75% ተከናውኗል።

በስታንዳርድ መሠረት አገልግሎት የሚሠጡ የመንግስት ተቋማትን ከማሳደግ አንጻር በክልል፣ በዞን እና በወረዳ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 100% ለማድረስ ታቅዶ 47 በመቶ መሆኑን በ2010 በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ ተቋማት በስታንዳርድ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር ክፍተት እንደሚታይ ተገምግሟል።

በሚዛናዊ የውጤት ተኮር ስርዓት ተቋማዊ ውጤታማነት ከማሳደግ አንጻር በውጤት ተኮር ዕቅድ በየደረጃው ማቀድና ካስኬድ አድርጎ በማውረድ የተለመደ አሠራሩን ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት 100% ለማድረስ ታቅዶ 92% ደርሷል። ከነዚህም ውስጥ በተደራጀ መረጃ ላይ ተመስርቶ መመዘን የቻሉ ተቋማት 50 በመቶ የሚሆኑት ናቸው።

በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ተቋማዊ ለውጥ ደረጃ ላይ የደረሱ ተቋማት መጠን በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ በሁሉም የአስተዳደር ዕርከን 50 ፐርሰነት ለማድረስ በታቀደው መሰረት በ ቢ.ፒ. አር ድንሰ ሀሳብ ስልጠና የመስጠት፣ሙያዊ ድጋፍና ክትትል የመሰጠት፣ የአገልግሎት አሰጣጥና ዕቅድ አፈጻጸምን ለማሻሻል ነባር አደረጃጀቶችን በመከለስና አዳዲስ የተቀረጹ አደረጃጀቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የምክር አገልግሎት የመስጠት እና የተጠናውን አደረጃጀት የማስተግበር፣ የመከታተልና የመደገፍ ሥራዎች ተከናውኗል።

በተጨማሪም በመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ዝግጅትና ትግበራ ለተቋም ተልእኮ መሳካት አስተዋጽኦ የሌላቸዉ የአደረጃጀትና የስራ መደቦች እንዳይቀረጹ ጥንቃቄ የተሞላበት ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ የሰዉ ሀይል ቁጥር እንዳይጋሽብ እና የክልሉን መንግስት ከአላስፈላጊ የደመወዝና ስራ ማስኬያጃ ወጪ ማዳን አስችሏል።

በለውጥ ሠራዊት ግንባታና ትግበራ የለዉጥ ሠራዊት ማፍራት የቻሉ ተቋማት መጠን ለማሳደግ ታቅዶ በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ሞዴል 25%፣ ግንባር ቀደም 50% እና ሠራዊት 25% ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሰነድ የማሻሻል፣ በየደረጃው ለሚገኙ ተቋማት ስልጠና የመሥጠት፣ ድጋፋዊ ክትትል የማድረግና አፈፃፀም በለውጥ ሠራዊት ግንባታ መመዘኛ ማኑዋል መሰረት መመዘንና ደረጃ መስጠት ስራ ተከናውኗል።

የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ትግበራ ለማጠናከር የሚያስችል የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ማስተግበሪያ ማኑዋል በመከለስ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ተደርጓል። ቢሆንም መርሆቹን ከመተግበር አንፃር በርካታ ክፍተቶች እንዳሉ ከተደረጉ ጥናቶች መረዳት ተችሏል።

የሰው ሃብት ስራዎች አፈጻጸም በተመለከተ የተቋማት አደረጃጀት ለማሻሻል የአደረጃጀት ጥያቄዎችን የሥራ ደረጃ ማሻሻያ፣ ልዩ ልዩ የጥቅማ ጥቅም ማጥናት፣ የሥራ ደረጃ ምዘና በማድረግ መወሰን፣ በአደረጃጀትና በስራ ምዘና ስልጠናዎችን፣ የምክር አገልግሎትና ድጋፋዊ ክትትል እና የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ስራዎች የተከናወነ ቢሆንም የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን (JEG) ስርዓት ማጠናከር፣ የክፍያ፣ የጥቅማ ጥቅምና የማበረታቻ ስርዓትን መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የሠራተኛ ፍልሰት መቀነስና የተረጋጋና ሳቢ መዋቅር በመፍጠር የሰራተኛውን ማህበራዊ ፍላጎቶች መሠረት ያደረጉ ስራዎች አንጻር ውስንነት ታይቷል።

የአሰራር ስርዓት መሰረት በማድረግ በክልሉ በየአስተዳደር እርከኑ የ4,710 የመንግስት ሰራኞች የትምህርትና የሙያ ብቃት ማስረጃ ተጣርቶ 3,207 (68.09%) ህገወጥነት የተረጋገጠ ሲሆን ይሁን እንጂ የአፈፃፀም ብቃት፣ ከቅልጣፌ፣ ውጤታማነት እና ከተጠያቂነት አንፃር በርካታ ጉድለቶች እንዳሉ በተለያዩ ጥናቶች የተረጋገጠ በመሆኑ በቀጣይ መሪ ዕቅድ ዘመን በትኩረት ይሰራሉ።

የሰው ሃብት ልማት ስራዎችን ለመምራት የሚያስችል መመሪያና ማኑዋል የማዘጋጀትና የማጸደቅ፣ የስልጠና አፈፃፀም ክፍተት ዳሰሳ ጥናትና ፍላጎት የመለየት እና የክልሉን የሰው ሃብት ልማት ዕቅድ የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል።

አዳዲስ ወጣት ምሩቃንን ወደ ሲቪል ሰርቪሱ የሚቀላቀሉበትን ሥርዓት መዘርጋትና ማስተግበርን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በክልሉ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት እንዲቀጠሩ ተደርጓል። እንዲሁም የአመራርና የፈጻሚ የአጭርና የረዥም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና ከመስጠትና ከማስተባበር አንጻር በየደረጃው ለሚገኙ አመራርና ፈፃሚዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

ይግባኝ ውሳኔ አሰጣጥ ከማሻሻል አንጻር በይግባኝ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ ላይ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት የመስጠት እና የአገልግሎት ተደራሽነት ለማረጋገጥ በመደበኛና በተዘዋዋሪ ችሎት በመሰየም ተደራሽ ለማድረግ ተሞክሯል። በተጨማሪም የይግባኝ ጉዳዮችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በመደበኛና በተዘዋዋሪ ችሎት ቀልጣፋና ፍትሐዊ ውሳኔ በመስጠት እንዲፈፀም እየተደረገ ቢሆንም ከጥራት አንፃር ሰፊ ክፍተት ተስተውሏል።

የሰው ሀብት አሠራርና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በማዘመን የዕለት ተዕለት ተግባራትን ከማኑዋል አሰራር ይልቅ በሲስተም ዳታቤዝ የታገዘ ዘመናዊ አሠራር የተከተለ እንዲሆን የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት (ICSMIS) በመተግበር e-governance ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም ወደ ትግበራ በገቡ 44 ተቋማት ላይ በአግባቡ

ከመምራት አንጻር ውስንነቶች የተስተዋሉ ሲሆን በቀጣይም በነባር ተቋማት ላይ ትግበራውን የማጠናከር እና አዳዲስ ተቋማትን ወደ ትግበራ ለማስገባት በትኩረት ይሰራል፡፡

የለውጥ መሳሪያዎች አተገባበርን በተመለከተ በአብዛኛው የመንግስት ዘርፎች ላይ ልዩነትን ያላገናዘቡ ተመሳሳይ የለውጥ ሀሳቦች፣ መሳሪያዎችና የመተግበሪያ ስልቶች በስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸው የአገልግሎት ስርዓቱን በሚጠበቀው ልክ ለውጥ እንዳያመጣ አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ የመንግስት ዘርፍ በአገልጋይነት መንፈስ የተሞላ ቀልጣፋ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማቅረብ ባለመቻሉ ክልላዊ የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጥሯል። በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ያለው ሠራተኛ በከፊል የብቃት ክፍተት ያለበትና በቂ ክፍያና ማበረታቻ የሌለው በመሆኑ የመፈጸም አቅሙ ክፍተት ስር የሰደደ እንዲሆን አድርጎታል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶችን ከማሳካት አንጻር የተሟላ የአገልጋይነት ስሜት ለመያዝና የለውጥ ሥራዎችን ለመተግበር በቁርጠኝነት እንዳይንቀሳቀስ አድርገውታል።

5.2. የፍትህ ዘርፍ አፈጻጸም

5.2.1. የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስራዎች አፈፃፀም

በዕቅድ ዘመኑ በሥራ ላይ በሚገኙ 10 ህጎች ላይ ሳይንሳዊ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ በ6 ህጎች ላይ ጥናት ተደርጓል ፤ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ህግ ይረቀቅልኝ ጥያቄ የቀረቡ 28 አዋጆች፣ 100 ደንቦችና 63 መመሪያዎች በድምሩ 191 ረቂቅ ህጎች ላይ አስተያየት ወይም የመጀመሪያ ረቂቅ በማዘጋጀት፣ በማረምና የህግ ቅርጽ በማስያዝ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፤ እንዲሁም 44 ሕጎች ላይ የቋንቋ ትርጉም ሥራ በመሥራት ለሚመለከተው አካል ማድረስ ተችሏል፡፡

የወንጀል መዛግብት የማጥራት ምጣኔን 99% ለማድረስ ታቅዶ 97 በመቶ ፤የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማሰጠት የመንጠባጠብ ምጣኔ በአማካይ ወደ 1.81% ለመቀነስ ታቅዶ 4.2%፣ በዐቃቤ ህግ ይግባኝ የሚጠይቅባቸው መዝገቦች ውጤታማነት በአማካይ 90.6% ለማድረስ ታቅዶ 74.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በተከሳሽ የሚጠየቁ የይግባኝ ጉዳዮች የማፅናት አቅም በአማካይ 94.3% ለማድረስ ታቅዶ 90% ማድረስ ተችሏል፡፡ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶችና ህጻናት) ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች የማጥራት ምጣኔ በዕቅድ ዘመኑ በአማካይ 99% ለማድረስ ታቅዶ 99.2% ማድረስ ተችሏል፡፡

የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር የሙስና ምርመራ መዝገቦች የማጥራት ምጣኔ 98.61% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ በሙስና ከተመዘበረ 234,865,193 ብር የመንግስት ሀብትና ንብረት መካከል 127,634,434 ብር ለመንግስት ተመላሽ ተደርጓል፡፡ የታክስ/ግብር/ ማጭበርበር ወንጀል ተገቢውን ምርመራ በማጣራት፣ ክስ በመመስረትና ውሳኔ በማሰጠት የማጥራት ምጣኔን በዕቅድ ዘመኑ በአማካኝ 95.6% ለማድረስ

ታቅዶ አፈጻጸሙን 92.42% ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የማስቀጣት ምጣኔ 96.4% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 99% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የመቋረጥ ምጣኔን ደግሞ ወደ 0.96% ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

የዐቃቤ ህግ የሰበር መዝገቦች በአማካኝ 90.2% ውጤታማ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 87.8% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በተከሳሽ የሚጠየቁ የሰበር ጉዳዮች 94% ለማፅናት ታቅዶ አፈጻጸሙን 100% ማሳካት ተችሏል።

በዕቅድ ዘመኑ 12,553 የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ቀርበው በ11,642 መዝገቦች ላይ ክስ በመመስረት የማጥራት ምጣኔን 92.7% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የማስወሰን አቅም በአማካይ 96% ለማድረስ ታቅዶ በ10,028 መዝገቦች ላይ ውሳኔ በማሰጠት አፈጻጸሙን 86.1% ማድረስ ተችላል። እንዲሁም በፍ/ቤት ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ውሳኔ ከተሰጠበት ብር 1,416,043,301.96 መካከል የአፈጻጸም ክስ በመመስረትና በድርድር ብር 1,194,759,195.65 (84.4%) በማስመለስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ተደርጓል።

የሁለተኛውን የብሄራዊ የሰብዓዊ መብት ድርጊት መረሃ-ግብር በተቋማችን እና በክልሉ ፈጻሚ ተቋማት ተግባራዊ እንዲሆን የሰብዓዊ መብት ድርጊት መ/ግብር ማስተባበሪያ ፅ/ቤት እንዲቋቋም፣ በተቋማቱ ፎካል ፐርሰኖች እንዲመደብ እና በዕቅዶቻቸው አካተው እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው የተያዙ፣ የታሰሩ፣ በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች አስተዳደርና አያያዝ በህግ መሰረት ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ከክልል ማዕከል እስከ ታችኛዉ መዋቅር በሰምንት ሁለት ጊዜ የማረፊያ ቤት ጉብኝት እየተደረገ መብታቸው እንዲጠበቅ ተደርጓል። እንዲሁም 23ቱንም ማረሚያ ተቋማት በየደረጃው ባሉ ዐቃቢ ህጎች ወቅታዊ ጉብኝት በማድረግ በየፖሊስ ማረፊያ ቤቶች እና በየማረሚያ ተቋማት የተጠርጣሪ እና የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት አጠባበቅና አያያዝ ዙሪያ ወቅታዊ ግብረ መልስ እየተሰጣቸው ችግሮች እንዲታረሙ ጥረት ተደርጓል።

5.2.2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት አፈጻጸም

የዳኞች ብቃት በሚሰጧቸው ውሣኔዎች ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ብቃታቸውን ለማሳደግ ባለፉት አስር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በርካታ ተከታታይ ሥልጠናዎችና መደበኛ ትምህርት ደረጃ በማሻሻል አቅማቸውን የመገንባት ስራ ተሰርቷል።

የክርክር መዛግብት ከመክፈት አንጻር በክልሉ ፍርድ ቤቶች ጠቅላላ ይከፈታል ተብሎ የታቀደው 1,292,140 መዛግብት ሲሆን 2012 በጀት ዓመት አጋማሽ 1,029,266 መዛግብት በመክፈት አፈፃፀሙ 79.6 በመቶ ሲሆን የመወሰን አቅም ከማሻሻል አንጻር የሚቀርቡ የወንጀልና የፍትሐብሔር መዝገቦች የመወሰን አቅም 95% ለማድረስ ታቅዶ በዕቅድ ዘመኑ ከቀረቡት መዛግብት በአማካይ 90% ማድረስ ተችሏል። የማጣራት አቅም ከማሻሻል አንጻር የዳኞችን ውሳኔ የመስጠት አቅም እንዲጐለብት ተከታታይ ሥራዎችን በመስራት የማጣራት አቅምን 100%

ለማድረስ ታቅዶ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ 96% ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የዳኛ መዝገብ ጥምርታ አንጻር አንድ ዳኛ በአማካይ ከ200 እስከ 350 መዛግብት በዓመት ውሳኔ እንዲሰጥ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንፃር በበዕቅድ ዘመኑ በአማካይ አንድ ዳኛ እስከ 222 መዛግብት ላይ ሊወሰን ችለዋል።

በይግባኝ የማይሻር ውሳኔ ከመስጠት አንጻር በ2008 ዓ.ም 88 በመቶ የነበረውን በ2012 ዓ.ም 93 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 84.97 በመቶ በይግባኝ የማይሻር ውሳኔ መስጠት ተችሏል።

የውሳኔዎች ተገማችነትን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ወጥነት እና ተገማችነት ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲሁም ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን አመኔታ ለመጨመር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣው የቀለብ አወሳሰን ረቂቅ መመሪያ በመተግበሩ ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ውሳኔ ለመስጠት በማስቻል በኩል ውጤቶችም ተገኝተዋል። ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (ኢኮኖሚ ነክ፣ የወንጀል፣ የሕጻናትና ሌሎች ጉዳዮች) የራሳቸው ችሎት ኖሯቸው እንዲታዩ የሚደረግበት አሠራር በመዘርጋት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል።

በዕቅድ ዘመኑ የተገኙት ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከቅጣት አወሳሰንም ሆነ ከቀለብ አወሳሰን መመሪያው አንጻር ሥልጠናዎች የተሰጡ ቢሆንም የክህሎት ክፍተት በመስተዋሉ የውሳኔዎች ወጥነትና ተገማችነት የተፈለገው ደረጃ አለመድረሱን በክልሉ ፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተደረገ ጥናት ያመላከተ በመሆኑ በቀጣይ መሪ ዕቅድ ዘመን በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

5.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ

5.3.1 የክልሉ ምክር ቤት አፈፃፀም

አምስተኛው የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ከ2008-2012 የነበረውን የሥራ ዘመን የሚያመለክት ሲሆን። በዚሁ የሥራ ዘመኑ ምክር ቤቱ 9 መደበኛ ጉባዔና 1 አስቸኳይ ጉባዔዎችን በማካሄድ የአስፈፃሚውን ዓመታዊ ፊዚካልና ፋይናንሻል ዕቅድ በመመርመር እንዲፀድቅ አድርጓል።

የተለያዩ አዋጆች ወጥቷል፣ በዓመት አራት ጊዜ የአሥፈጻሚ አካላትን አፈፃፀም ሪፖርቶች በመመርመር በጽሁፍና በአካል ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፣ እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ በአመት አራት ጊዜ በአካል መስክ በመውረድ ክትትልና ቁጥጥር አድርጓል፣ የህዝብ አስተያት መድረክ ተዘጋጅቷል፣ ቅሬታና አቤቱታ ምላሽ ተሰጥቷል፣ ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፣ አቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፣ በሬዲዮ ፕሮግራም መረጃ ለሕዝቡ እንዲደርስ ተደርጓል፣ የምክር ቤቶች ፎረም ተካሂዷል። ምክር ቤቱ ባለፉት አስርት ዓመታት 193 አዋጆችን፣ 18 ደንብና 5 የውሳኔ ሀሳቦችን መርምሮ በማጽደቅ ተፈፃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።

ዕቅድና ሪፖርት መመርመር አስፈፃሚው አካል በዕቅድ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ዕቅዱን እንዲያቀርብ በማድረግ በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ ተመርምሮ ተገቢው ግብዓት ታክሎበት ለምክር ቤቱ ቀርቦ እንዲፀድቅ ተደርጓል። ከሪፖርት አንፃር በየሩብ ዓመቱ ለቋሚ ኮሚቴዎች የሚላከው ሪፖርት ተገምግሞ የጽሁፍ ግብረ መልስ እንዲደርሳቸው ከመደረጉም በተጨማሪ በዓመት ሁለት ጊዜ የሥራ ኃላፊዎችን በአካል በመጥራት በዕቅድና በአፈጻጸም ሪፖርት ላይ ማብራሪያ እና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተከናውኗል።

ምክር ቤቱ በህገ መንግሥቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በክልሉ የውስጥ ጉዳይ የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ባለቤት፣የህዝብ ውክልና ስራን የሚሰራና ለህዝቦች ቅሬታ እና ፍትህ ማጣት እና መጓደል መፍትሄ የሚያበጅ እንደ መሆኑ መጠን በህጉ መሠረት የሚቀርብለትን የህዝብ አቤቱታና ጥቆማ በመቀበል መርምሮ ምላሽ የመስጠት ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል። በዚሁ መሠረት ባለፉት አስር አመታት ምክር ቤቱ 88 የህዝብ አቤቱታዎችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ በመመርመር ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል።

ባለፉት ዓመታት ከህዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መነሻ በማድረግ ችግሩ በስፋት በሚታይባቸው ሴክተሮች በትራንስፖርት ስምሪትና ታሪፍ፣ በንግድ ዘርፍ በፍጆታ ሸቀጦች፣ በገቢ አሰባሰብና ግብር ትመና፣ በፍትህ ዘርፍ በሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅና አከባበር፣ በወንጀል መከላከል፣ በእናቶች ጤና አጠባበቅ፣ በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት፣ በፕሮጀክት አፈፃፀምና አተገባበር፣ በሴቶችና ወጣቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ዙሪያ የህዝብ አስተያየት መድረኮች በተለያዩ የክልሉ ከተሞች በማዘጋጀት ከህዝቡ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል። በዚህም በመንግሥት አሰራር የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት፣ የግልፀኝነትና ተጠያቂነትን አሰራር በማስፈን የህዝቡ ከልማትና መልካም አስተዳደር ተጠቃሚነት ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል።

5.3.2 የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሥራዎች አፈጻጸም

ህገ መንግሥታዊ የመብት ጥያቄዎችን በተመለከተ ከማንነት አንጻር ከቀረቡት 8 የማንነት ጥያቄዎች ተቀባይነት በማግኘቱ ጥናት በማካሄድ በ5ቱ ላይ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን 3ቱ ከአገራዊ ለውጡና ከአደረጃጀት ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ በተፈጠረው ክልላዊ አለመረጋጋት ምክንያት ውሳኔ ሊያገኝ አልቻሉም። ከወሰን ማካለል ጥያቄ ጋር በተያያዘ 4 ጥያቄዎች ቀርበው 2ቱን (50%) ጥናትን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን 2 ጉዳዮች ሳይቋጩ ተንጠልጥሎ ይገኛል።

ፍትሃዊ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ሥርጭት ዙሪያ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ 2 ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 1 (50%) ጥናት ማካሄድ ተችሏል።

ከህገ-መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት አኳያ 22 የህገ-መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በሚል ጥያቄ የቀረበ ሲሆን 11 (50%) ጥያቄዎች ውሳኔ የተሰጠባቸው ሲሆን ቀሪ 11 በመታየት ሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው።

የህገ-መንግሥትና ፌዴራሊዝም ግንዛቤ ማሳደግን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ የህብረተሰቡን የህገ-መንግስትና የፌዴራሊዝም ግንዛቤ ጎልብቶ በህገ-መንግሥቱ የተጎናፀፋቸውን መብቶች እንዲጠቀምበትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ እንዲችል በአውደ ጥናቶች፣ በሲምፖዚየሞች፣ በኮንፍረንሶች፣ በጥያቄና መልስ ውድድሮች፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ የክልሉን ህገ-መንግሥት ሰነድ በማሳተምና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ በሚወጡ አምዶች የሕገ-መንግሥትና የፌዴራሊዝም ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል።

የሕዝቦችን አንድነትና ትስስር ማጠናከርን በተመለከተ የብሔረሰቦችን የጋራ እሴቶችን ለማጥናትና ለማጎልበት ባለፉት ዓመታት 7 የብሔረሰቦችን የጋራ እሴቶችን ለማጥናት ታቅዶ 4 (57.1%) በማጥናት ተግባራዊ ተደርጓል።

ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦች ድጋፍና ክትትል ማድረግ አንጻር 17 የብሔረሰቦች ቋንቋ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 7 (50%) ቋንቋ ጥናት በማድረግ ለዞን፣ ለልዩ ወረዳዎች፣ ለብሔረሰቡ ተወላጆችና ለተለያዩ ከፍተኛ ት/ት ተቋማት እንዲሰራጭ ተደርጓል። እንዲሁም የብሔረሰቦች ባህልና ታሪክ ጥናት ለማካሄድ በታቀደው መሰረት የክልላችን ብሔረሰቦች የማንነት መገለጫ እሴቶቻቸውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተጠንተው ለመጪው ትውልድ ማሻገር እንዲችሉ ምክር ቤቱ በጋራ ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ባለፉት ዓመታት የብሔረሰቦች ባህልና ታሪክ እንዲጠና አድርጓል።

5.3.3. የስነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎች አፈጻጸም

የስነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ትምህርትና ስልጠና ከመስጠት አንፃር ለ9,713 አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ9,875 መስጠት ተችሏል። የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች በGTP-2 እቅድ ለ33,220 ከክልሉ መምህራን ኮሌጆች ለሚመረቁ እጩ መምህራን ለመስጠት ታቅዶ ለ22,342 (67.2%) ተመራቂ ተማሪዎች ተሰጥቷል። በስነ-ምግባር አውታሮች አማካይነት ባለፉት አመታት በየዓመቱ እስከ 9,090,460 የህብረሰተብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአማካይ በየአመቱ 3,773,160 (41.82%) የህብረሰተብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል። የስልጠና ሞጁሎች ዝግጅትን በተመለከተም 21 ሞጁሎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ በተለያዩ ርዕሶች 19 (90.47%) የስልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅቷል።

የስነ-ምግባር አውታሮች አደረጃጀት በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ከ1,500 በላይ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰሮችን የማደራጀት፣ የፀረ-ሙስና ጥምረትን፣ የሴቶችና የወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረኮችን እስከ ቀበሌ ድረስ የማደራጀት፣ የስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ክበባትን በሁሉም የመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ኮሌጆች የማደራጀት ሥራ ተሰርቷል። በእቅድ ዘመኑ ለ6,744 የሥነ-ምግባር አውታሮች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-

መልስ መስጠት ታቅዶ ለ4,856 (72%) መስጠት የታቸለ ሲሆን የስነ-ምግባር አውታሮች 45 የጋራ መድረኮችን ለማድረግ ታቅዶ 33 (73.3%) መድረኮችን ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም በስነ-ምግባር አውታሮች አማካኝነት በሙሰኞች ሊመዘበር የነበረና የተመዘበረ ብር 343,136,722. ብር ወደ መንግስት ካዘና እንዲመለስ ተደርጓል።

ባለፉት አመታት 75 ጥናቶችን በተለያዩ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ በሆኑ ርዕሶች ላይ ለማጥናት ታቅዶ 66 (88%) የሙስና መከላከል ጥናቶችን ማድረግ ተችሏል። የአሠራር ስርዓት ጥናት ትግበራ፣ በተቋማት ለሚከናወኑ የአሠራር ስርዓት ሙያዊ እገዛና ድጋፍ፣ ለቀረቡ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥቆማዎች 100% ምላሽ ተሰጥቷል። ተቋማዊ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ እንዲሁም የስነ-ምግባር ደንብና የህግ ረቂቅ ማሻሻያ ድጋፍ ሥራዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ በተያዘው እቅድ መሠረት ምላሽ መስጠት ተችሏል።

የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ በተመለከተ የኃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብትና የገቢ ምንጭ ምዝገባ ለማካሄድ በታቀደው መሰረት 76,264 የአዲስ ምዝገባ፣ የእድሳትና የአገልግሎት ማቋረጥ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆነ የ18,165 የሀብት አስመዝጋቢዎች ሀብት መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራ ለማከናወን ታቅዶ የአስር ዜጎች ሀብት የማጣራት ስራ ተከናውኗል።

የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ በተመለከተ እስከ 2010 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ አንድ ላይ ሥራው ሲከናወን የቆየ ሲሆን ላለፉት ስምንት ዓመታት በ1,502 የክስ መዝገቦች ላይ ምርመራ በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት ታቅዶ በ1,237 የክስ መዝገቦች ላይ ውሳኔ የመስጠት ስራዎች ተከናውኗል።

በሙስናና ብልሹ አሰራሮች የተመዘበረ የህዝብና የመንግስት ሀብት ለማስመለስ በታቀደው ዕቅድ መሠረትም ከተመዘበረው 164,452,797 ብር ውስጥ 111,177,179 ብር (67.60%) ወደ መንግስት ካዝና የማስመለስ ስራ ተሰርቷል። በተጨማሪም በሙሰኞች የተወረረ 292,400 ካሬ ሜትር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል።

5.3.4 የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዩች አፈፃፀም

የመንግስት ኮሙዩኑኬሽንና የሚዲያ ግንኙነት :- የልዩ ልዩ ህትመቶችን ማዘጋጀትና ማሰራጨትን በተመለከተ ዓመታዊ መጽሀፍ ህትመት 1400 ኮፒ ለማሳተም ታቅዶ 1500 ኮፒ ታትሟል፣ የመጽሄት ህትመትና ስርጭት 70 ዕትም ለማሳተም ታቅዶ ወደ 76 ዕትም ማሳተም ተችሏል፣ ዜና መጽሄት በዕትም 600 ዕትም ታቅዶ 530 ታትሟል፣ ብሮሸርና በራሪ ወረቀት በዕትም 1500 ታቅዶ 1600 ታትሟል እንዲሁም ስቲከር፣ፖስተርና ፖስት ካርድ ህትመትና ስርጭት በዕትም 250 ታቅዶ 300 ዕትም ማድረስ ተችሏል።

መረጃዎችን በብሮድካስት አዘጋጅቶ የማሰራጨትና ተደራሽ የማድረግ አገልግሎት፣ የሬዲዮና የቴሌ ቪዥን ዜና በቁጥር 6,000 ለመስራት ታቅዶ 6,400 ዜናዎች ተሰርቷል። የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም በቁጥር ከ4,000

ለመስራት ታቅዶ 4,015 መስራት ተችሏል፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ዶክመንታሪ በቁጥር 300 ታቅዶ 289 አዘጋጅቶ ማሰራጨት ተችሏል። የቪዲዮ ቀረጻና ፎቶ ማንሳት በዙር 1,300 ለመስራት ታቅዶ 1260 ማከናወን ተችሏል።

የመንግስት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ዕቅዶችንና አፈጻጸሞችን ከማስተዋወቅ አኳያ የፎቶ ኤግዚቢሽ በዙር 900 ለማሳየት ታቅዶ 869 ኤግዚቢሽን ማሳት ተችሏል። የመስክ ልማት ጉብኝቶች በዙር 1,000 ለማካሄድ ታቅዶ 1010 ማከናወን ተችሏል። ዲዛይንና ሌይ አውት በዕትም 1,500 ለመስራት ታቅዶ 1,453 መስራት ተችሏል።

የሚዲያ ሞኒተሪንግና ጥናትና ምርምር በተመለከተ ባለፉት እቅድ ዘመን በአገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች የሚተላለፉ ዘገባዎችን እና አለም አቀፍ ሪፖርቶችን ሞኒተር ለማድረግ 3,740 ታቅዶ 3600 ማከናወን ተችሏል። ሳምንታዊ የሚዲያ ሞኒተሪንግ መረጃዎችትን ትንተና ምክረታሳብ ለማከናወን 4,000 ታቅዶ 3,906 ተፈጽሟል። ወርሃዊ የሚዲያ ሞኒተሪንግ መረጃዎች ትንተና 1,350 ታቅዶ 1,296፣ የሩብ አመት የሚዲያ ሞኒተሪንግ መረጃዎች ትንተና 400 ታቅዶ 306፣ የግማሽ አመት የሚዲያ ሞኒተሪንግ መረጃዎች ትንተና 250 ታቅዶ 216 ተከናውኗል። በተጨማሪም አመታዊ የሚዲያ አዝማሚያ ጥናት 113 ታቅዶ 108 ማከናወን ተችሏ።

ሳምንታዊ የህዝብ አስተያት ለመሰብሰብ፤ ለማደራጀትና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ 5,886 ታቅዶ 5,184፣ ሳምንታዊ የህዝብ አስተያት አሰራር ይዘት ግብረ-መልስ ለዞኖችና ልዩ ወረዳዎች 5,886 ለመስጠት ታቅዶ 5184፣ የፖሊንግ (polling) ስራዎች 2,622 ታቅዶ 2,592፣ ወርሃዊ የህዝብ አስተያየት አዝማሚያ ጥናት 1፣340 ታቅዶ 1,296፤ የሩብ አመት የህዝብ አስተያየት አዝማሚያ ጥናት ማካሄድና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ 500 ታቅዶ 432፤ የግማሽ አመት የህዝብ አስተያየት አዝማሚያ ጥናት ማካሄድና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ 234 ታቅዶ 216፣ አመታዊ የህዝብ አስተያየት አዝማሚያ ጥናት ማካሄድና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ 125 ታቅዶ 108፣ ወቅታዊ ጉዳዮችን፤ የህብረተሰቡን ጥያቄዎችና አስተያየቶች መሰረት ያደረገ ከባቢያዊ ቅኝት 444 ለማካሄድ ታቅዶ 302፤ የህዝብ አመለካከት ጥናት ለማካሄድ 444 ታቅዶ 324 ተካሂዷል።

በመንግስት መረጃ ማእከልና ዲጂታል ሚድያ አስተዳደር፡- በቁጥር 52,326 በተቋሙ የተዘጋጁ መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያዎች ለመልቀቅ ታቅዶ ተፈጽሟል። 48,870 ከሌላ የዜና ምንጮች የተወሰዱ መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያዎች ለመልቀቅ ታቅዶ ተከናውኗል። 967 የተቋሙን አገልግሎቶች እቅድና ሪፖርቶች መለጠፍና አፕዴት ለማድረግ አንዲሁም 967 የሀገር ውስጥና የዉጭ ዘገባዎችን በሶሻል ሚዲያ ለመልቀቅ ታቅዶ ተከናውኗል። በመረጃ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ለማየትና ግብረ-መልስ ለመስጠት 52,326 ታቅዶ ተከናውኗል።

ምዕራፍ ስድስት

የሰላም ግንባታ ዘርፍ አፈጻጸም

6.1. የሰላምና ጸጥታ ሥራዎች አፈጻጸም

በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች የሚከሰቱትን ግጭቶችን አስቀድሞ ለመከላከልና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ሥርዓቱን በማዘመንና በማጠናከር እንዲሁም የሰው ሀይል በተገቢው ሁኔታ በማደራጀት ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ የክስተትና የአመላካች የሁኔታ መረጃዎችን ከየአከባቢው በማሰባሰብና በማደራጀት በየደረጃው የሚገኙ አመራር አካላት መረጃውን እንደ ግብዓት በመጠቀም የፀጥታ ችግሮች ወደ ሁከትና ብጥብጥ ደረጃ ሳይሸጋገሩ የመከላከልና የማስቆም ስራ በተገቢው ሁኔታ ተከነውኗል። በዚህ እንደ ክልል 90 ፐርሰንት የግጭት ስጋቶችን አስቀድሞ ማምከን ተችሏል። የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱ ሪፎርሙን ተከትሎ በአዲስ መልክ ወደ ተግባር እንዲገባ ከተደረገው ካለፉት ዓመታት ወዲ በክልሉ ውስጥ የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮችን አስቀድሞ የመከላከል አቅም እየተፈጠረ በመምጣቱ በክልሉ የሚኖሩ ዜጎች አንፃራዊ የሆነ ሰለማዊ አውድ ውስጥ ሆነው ከአከባቢ አከባቢ በሰላም መንቀሳቀስና መስራት የሚችሉበት ሰላማዊ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ እየተፈጠረ እንዲመጣ ማድረግ ተችሏል።

በሀገር ደረጃ ብሔራዊ መግባባት እንዲኖር እንዲሁም በክልልችንም አብሮነትና መተሳሰብ እየጎለበተ እንዲመጣ ለማድረግ የሰላም ግንባታ ሥራዎች በክልሉ በሁሉም አከባቢዎች እስከ ቀበሌ ድረስ በስፋት ሲከናዎን ቆይቷል። በየአከባቢው የሚኖረው ህብረተሰባችን የሰላምና የመቻቻል ጉዳይ አጀንዳ ሆኖ እንዲወያይ ልዩነቶችና ያለመግባባቶች ሲኖሩ በሰለጠነ መንገድ በሰላማዊ ሁኔታ የመፍታት ባህሉን ዳግም ለማጎልበት እንዲያግዝ በክልሉ የሰላም ምክር ቤት በየደረጃው እንዲደራጅ በማድረግ ከ2,312 በላይ የሰላም ኮሚቴና ከ1,215 በላይ የሰላም ክበባት አደረጃጀቶች ተፍጥረዋል። ይህንን አደረጃጀት በስፋት በመጠቀም ዜጎች በየማህበራዊ መሰረታቸው በአከባቢው ሰላምና የህዝብ ዳህንነት ጉዳይ ባለቤት እንዲሆኑ እና የየአከባቢያቸውን ሰላም እንዲጠብቁ ለማድረግ በአብዛኞቹ የክልሉ አከባቢዎች ህብረተሰቡ ከሚመለከተው የመንግስት አከላት ጋር በመሆን የአከባቢውን ሰላም የማስጠበቅና ሀላፊነትን በጋራ እንዲወስዱ ማድረግ በመቻሉ በክልሉ ሰላምን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።

የሰላም ግንባታ ሥራዎቻችን በህዝቦች መካከል ሲዘራ የነበረውን ጥላቻና የእርስ በእርስ ጥርጣሬን ለመቅረፍ ብሎም ብሄራዊ መግባባትን ለመፍጠር በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ መልካምና ሰላማዊ ግንኙነቶች ጎልብተው መቀጠል እንዲችሉ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት ከሰባት ሚሊየን ለሚበልጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ከሃምሳ ሶስት ሺ ለሚልቁ ባለድርሻ አከላት በሁሉም አካባቢዎች በሰላም ግንባታና ብሄራዊ መግባባት ዙሪያ የማህበረሰብ ተኮር ውይይት ማድረግ ተችሏል።

ሀይማኖትን መሰረት የሚያደርጉ ያለመግባባቶችንና የፀጥታ ችግሮችን ለመፍታት ብሎም የህብረተሰቡ የመቻቻልና የመከባበር እሴት ለማጎልበት በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ከአንድ ሚሊየን ለሚበልጡ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ከሀምሳ ሺ ለሚበልጡ ባለድርሻ አከላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርቷል።

ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሀይማኖት ነክ አስተዳደራዊና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ከመፍታት አንፃር አንድ ቤተ እምነት ከሌላ ቤተ እምነት ወይም በራሱ ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ መዋቅሮች ከሚገኙ አስተዳደራዊ ከሆኑ ጎዳዮች ጋር በአምልኮ ቦታ፣ ከቀብር ቦታዎች፣ ሀይማኖታዊ ሥርዓትና በዓላት ማክበሪያ አደባባዮች፣ ከድምፅ ብክለትጋር የሚያያዙ ጥያቄዎች፣ እንዲሁም በውስጣቸው ከኃይማኖቱ ከአስተዳደርና ከአመራር ሥርዓት ጋር በተገናኘ የሚነሱ የእርስ በርስ ያለመግባባት ወደ ፀጥታ ስጋት የሚሸጋገርበት ሁኔታ ሲኖር ሀይማኖቶች ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ተከትለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከማድረግ አንፃር በርካታ ችግሮችን መፍታት ተችሏል።

በክልላችን በተለያዩ አከባቢዎች ተከስተው የነበሩ ግጭቶች ምክንያት ለበርካታ ዜጎች ህልፈተ-ህይወት፣ የአካል ጉዳት፣ የስነልቦና ቀውስ፣ መፈናቀልና የንብረት መውደም ምክንያት ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። እነዚህን ችግሮችን ከመሰረቱ ለመፍታት የህግ የበላይነትን ከማስከበር ጀምሮ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቀየአቸው እንዲመለሱ ለማድረግ መጠነ ሰፊ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

የአከባቢ ፀጥታ ጥበቃ ሥራዎች በተመለከተ በየቀበሌ የሚገኘውን የሚሊሻውን ሀይል በህብረተሰቡ ተሳትፎ ከመልካም አስተዳደርና ከኪራይ ሰበሳቢነት ችግሮች አንፃር በመገምገምና በማጥረት ቀደም ሲል በነበረው 120,000 የሚሊሻ አባላት ተጨማሪ 15,000 አዳዲስ የሚሊሻ አባላትን በማሰልጠን የሚሊሻውን ሀይል በአዲስ መልኩ ስምሪት በመስጠት ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን የአከባቢ ጥበቃ ሥራ እንዲጠናከር ማድረግ ተችሏል። ላለፉት ዓመታት እንደ ክልል ለሀገር መከላከያ ከ26 ሺ በላይ ተተኪ ወጣቶችን ከክልሉ ሁሉም አከባቢ በመመልመል ወደ ሀገር መከላከያ ተቋም እንዲቀላቀሉ ማድረግ ተችሏል።

የወንጀልና ትራፊክ አደጋ መከላከል በተመለከተ የማህበረሰብ አቀፍ ወንጀል መከላከል ትምህርት ሽፋንን በማሳደግ የህብረተሰብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በየዓመቱ የተሰጠ ሲሆን በቀበሌ ደረጃ የፖሊስ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ከ964 ወደ 4,109 ለማሳደግ ታቅዶ 1,455 አዲስ ማዕከላትን በመክፈት አገልግሎቱን ወደ 2,416 ማዕከላት ለማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የይድረሱልኝ ጥሪ ምላሽ አንጻር ከቀረቡ የይድረሱልኝ ጥሪዎች ውስጥ 100% አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 96% ምላሽ ለመስጠት የተሰጠ ቢሆንም በስታንደርዱ መሰረት በከተማና በገጠር ምላሽ ከመስጠት አንጻር ውስንነቶች ያሉ በመሆኑ በቀጣይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የተደራጁ ወንጀሎችን ከመከላከል አንፃር በክልሉ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን፣ ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን፣ የጦር መሳሪያ ዝውውርንና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን በመከላከልና በመግታት ረገድ ሰፋፊ ሥራዎች በመሰረታቸው የህገ ወጥ እንቅስቃሴ ምጣኔ የመግታትና የማስቆም ስራ የተሰራ ሲሆን በዝውውር ወቅት የተያዙ ንብረቶችን ለመንግስት ገቢ ማድረግ ተችሏል።

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች አንጻር በሁሉም አካባቢ በየደረጃ ከሚገኙ የመንገድ ደህንነት ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት የትራንስፖርት አዋጅና ደንቦች እንዲከበሩ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ደንብ ተላልፈው የተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት እንዲቀጡ ተደርጓል።

በአጠቃላይ በዕቅድ ዘመኑ ወንጀልን በመከላከል የወንጀል መጠንን ከ65,800 ወደ 14,332 ለማውረድ ታቅዶ ወደ 26,693 ዝቅ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ይህም ከዕቅድ አንጻር 63.43% ለመፈጸም ተችሏል።

የወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ አፈጻጸም በተመለከተ የታክቲክ ምርመራን የማጣራት አቅም በ2007 በጀት ዓመት 80% ከነበረበት በ2012 ዓ.ም ወደ 85% ለማሳደግ ታቅዶ የተሠራ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑም አቤቱታዎችንና ክሶችን ተቀብሎ የማጣራት አቅምን 87.86% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከትራፊክ አደጋ ምርመራ አንጻር ምርመራ የማጣራት አቅምን 85% ለማድረስ ታቅዶ 76% ለማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የሙስና ወንጀል ምርመራ የማጣራት አቅምን 85% ለማድረስ ታቅዶ 70% ማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም የታክስ ማጭበርበር እና የኢኮኖሚ ነክ (ጉምሩክ) ወንጀሎች ምርመራ የማጣራት አቅምን 85% ለማድረስ ታቅዶ በቅደም ተከተል 75.86% እና 78.5% ማድረስ ተችሏል።

የፀጥታ ሀይሉን አቅም ከመገንባት አንፃር በክልላችን የወንጀል መከላከል ስራዎቻችንንና ግጭቶችን ለማስቆም ከዚህ ቀደም ሲል የነበረው የልዩ ፖሊስ ሀይል በጥራም በመጠንም ከማሳደግ አንፃር በርካታ ቁጥር ያለቸዉን የልዩ ኃይል አባላትን በማሰልጠንና በስጋት ቀጠናዎች ላይ ስምሪት በመስጠት የህብረተሰቡን ሰላም የማስጠበቅ ስራዎችን በስፋት መስራት ተችሏል።

የወሳኝ ኩነት ስራዎች ተደራሽ ከማድረግ አንጻር፡- የወሳኝ ኩነት ስራዎች ተደራሽ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የምዝገባ ጽ/ቤቶች ለመክፈት 4,120 ታቅዶ 3,873 (94%) ቀበሌያት የምዝገባ ጽ/ቤት በማቋቋም ምዝገባ አገልግሎት እንዲጀምሩ ተደርጓል።

በዕቅድ ዘመኑ 1,323,823 ኩነቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ በአመራርና ፈጻሚ ስራውን በባለቤትነትና በቁርጠኝነት ከመምራትና ከመስራት አንጻር ውስንነት መኖር፣ በቀበሌ ደረጃ የራሱ የሆነ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ባለሙያ አለመኖር፣ የቅንጅታዊ አሰራር አለመጠናከር እና ወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት 605,246 በመመዝገብ ሽፋኑን (46%) ማድረስ ተችሏል።

ምዕራፍ ሰባት

የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት አፈጻጸም

7.1. የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች አፈፃፀም

ከየዘርፉ የሚለቀቁ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነስን በተመለከተ ከደን ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት እንዲቀንስ ለማድረግ የደን ሽፋን የማሳደግ ወይም አዳዲስ የደን መሬት መፍጠር፣ የደን ሀብት ውድመትን የመቀነስ እና የሬድ ፕላስ ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ የማድረግ ሥራዎች ተሰርቷል።

የአካባቢ ደህንነት መብቶች መከበራቸውን ከማረጋገጥ አንጻር የአካባቢ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በክልል ደረጃ በዕ.ት.ዕ ዘመኑ 4 ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 አዋጅ (የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የብክለት ቁጥጥርና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ) እና አንድ ደንብ (በድምፅ ብክለት ቁጥጥር) ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ስራ ተከናውኗል።

የደን ልማትና ጥበቃ ሥራዎች አፈጻጸም በተመለከተ የደን ሰደድ እሳት ከመነሳቱ በፊት ቅድመ መከላከል ለማድረግ የሚያስችል እና ከተከሰተም ባሕላዊና ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመቆጣጠር የሚያስችል ማንዋል ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት አንድ ማኑዋል ማዘጋጀት ተችሏል። በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን በመተግበር ተፈጻሚነታቸውን ከመከታተል አንጻር ለ20 ዙር ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 12 ዙር ተከናውኗል።

ለአርሶ/አርብቶ አደሮች የቤተሰብ ገቢ ከ5-10% ያህል ከደንና ደን ዉጤቶች እንዲያገኙ ለማድረግ ለ525,000 ታቅዶ ለ330,341 አካላት ሙያዊ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በመደበኛ ከደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ጎን ለጎን ለ200,000 ለወጣቶች፣ ሴቶችና ገቢያቸዉ አነስተኛ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በዘርፉ የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸዉ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ122,483 የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

በክልሉ ዉስጥ ያሉ የእንጨት ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም 70,174 ቶን እንዲደረስ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 44,593.3 ቶን በተደረገው ድጋፍ ተመርቷል። ዘላቂ በሆነና አከባቢያዊ ተጽዕእኖ በሌለው መንገድ ለማገዶነት ሊውል የሚችል 480,029 ሜትር ኩብ እንጨት እንዲመረት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 657,503 ሜትር ኩብ ለማምረት ተችሏል። እንዲሁም ለግንባታ ሊውል የሚችል 3.84024 ሚሊዮን ሜ/ኩብ ምርት እንዲመረት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 4.18777 ሚሊዮን ሜ/ኩብ እንዲመረት ድጋፍ ተደርጓል። በተጨማሪም የቀርከሃ እና ሽመል ደኖችን በዘላቂነት መጠበቅ መንከባከብና ምርት ለገበያ እንዲቀርብ ከማድረግ አኳያ 10,000 ሜትር ኪዩብ ምርት ለገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ ታቅዶ 16,267.5 ሜ/ኩብ ማከናወን ተችሏል።

የክልሉን የደን ሀብት በዘላቂነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጠቀሜታቸው ያደገ ስነ ምህዳር ከመፍጠር አኳያ በጊቤ 3 ግድብ ዙሪያ 260,000 ሄ/ር የተራቆተ መሬት ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 321,897.9 ሄ/ር የተጎዳ መሬት ከንክኪ ነጻ በማድረግ ለማልማት ተችሏል።

አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርአትን በመጠቀም 559,046 ሄ/ር የተፈጥሮ ደን በዘላቂነት በመጠበቅ፣ በመንከባከብ እና ጥቅም ላይ እንዲውል ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 453,328.1 ሄ/ር ደን ሕብረተሰብን ባሳተፈ መልኩ ተከልሎ የጥበቃ፣ የመንከባከብና የአጠቃቀም ሥርዓት ማስፈን ተችሏል። 70,000 ሄ/ር የተመናመኑ የተፈጥሮ ደኖች መልሰው እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ 79,528.70 ሄ/ር እንዲያገግም ተደርጓል።

ለሰው ሰራሽ ደን ልማት ሊዉል የሚችል 48,000 ሄ/ር መሬት እንዲለይ፣ እንዲከለልና የዛፍ ዝርያ ፍኖተ ካርታ (Road Map) እንዲዘጋጅ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 42,510 ሄ/ር ድጋፍ ለማድረግ ተችሏል። 72,178.6 ሄ/ር የሰው ሰራሽ ደን ለመከለል ታቅዶ 48,983.6 ሄ/ር ተከልሏል። እንዲሁም 223,771.2 ሄ/ር የተፈጥሮ ደን ለመከለል ታቅዶ 181,393.44 ሄ/ር ተከልሏል።

ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸዉ 165,326 ኪ.ግ የተለያዩ የዛፍ ዘሮች በህብረተሰቡ ተሳትፎ ለማዘጋጀት ታቅዶ 334,367 ኪ.ግ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ 5 ቢሊዮን ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 4.429 ቢሊዮን የደን ችግኝ ለማዘጋጀት ተችሏል። በተጨማሪም የክልሉን የደን ሽፋን በየዓመቱ በ1% በማሳደግ የደን ዘርፍ ዘላቂ ጠቀሜታ ለማረጋገጥ እንዲቻል 4.25 ቢሊዮን የደን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 3.95 ቢሊዮን የደን ችግኞች መትከል ተችሏል። በዚህም 813,012 ሄ/ር መሬት በችግኝ ተከላ ለመሸፈን ታቅዶ 960,396 ሄ/ር በአዲስ የደን ችግኝ ተከላ ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን የችግኞች የፅድቀት ደረጃ በአማካይ ከ78 በመቶ ወደ 85 መቶ ለማሳደግ ታቅዶ ባጋጠመዉ የዝናብ ዕጥረትና በተለያዩ ምክንያቶች የጽድቀት መጠኑ አማካይ 81 በመቶ ሊሆን ችሏል።

የብዝሀ-ሕይወትን በዘላቂነት ለመጠቀም 2 መመሪያ እና 4 ደንብ ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል። በእፅዋት ብዝሀ-ህይወት ዘርፍ በማህበረሰብ ዘር ባንኮች እንዲጠበቁ ለተለዩ የሰብል ዝርያዎች የሚሆን 20 ቦታ ለመምረጥና ለማዘጋጀት ታቅዶ 17 ማህበራት ለነባር ዘር ማባዣ የሚሆን ቦታ ተመርጦ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። በአካባቢው የጠፉ 30 ነባር ዝርያዎችን ከጅን ባንክ በማምጣትና ከአካባቢው በማፈላለግ ለማባዛትና ለማሰራጨት ታቅዶ 125 ተለያይነት ያላቸው ሰብሎች በማህበራቱና በአርሶአደር ማሳ እንዲባዙና እንዲጠበቁ ተደርጓል።

በዘ-ቦታ ጥበቃ 323,000 ካ. ሜትር መኖ ለማልማት ታቅዶ 247.123 ካ/ሜ፣ ተከናውኗል። ዝርያው በመጥፋት የሚገኝ የሸኮ ዳልጋ ከብት ን/ዝርያ አንዲጠበቅ፣ እንዲሻሻል፣ አንዲባዛና በመጨረሻም ራሱን የቻለ የሸኮ ዳልጋ ከብት ንኡስ ዝርያ ጠባቂ ማህበረሰብ (breeding society) እንዲመሰረት የሚሠራ የመማክርት ጉባዔ በማቋቋም የዝርያዉ ቁጥር እንዲጨምር ተደርጓል።

መድኃኒትነት ያላቸው የዕጽዋት ዝርያዎችን በሥፍራ (ዘ-ቦታ) ለመለየት፣ ለመሰብሰብና ለመጠበቅ በዝርያ ቁጥር 44 በዕቅድ ተይዞ 72 ዓይነት መድኃኒትነት ያላቸው የዕፅዋት ዝርያዎች በተለያዩ ዞኖች በመንግስት ችግኝ ጣቢያ፣

በት/ቤት፣ በእምነት ቦታዎች በማህበረሰብ ዘር ባንክና በአርሶ አደር ማሳና በመድሀኒት አዋቂዎች ማሳ እንዲጠበቁ ተደርጓል። ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው በቁጥር 24 ነባር ሰብል ዝርያዎችን፣ 22 የአትክልትና ፍራፍሬ፣ 10 የቅመማ-ቅመም እና 40 የደን ዕጽዋት ለመለየት፣ ቆጠራ ለማካሄድና መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ በቀደም ተከተል 72፣ 45፣ 12 እና 52 ተከናውኗል።

ክፍል ሁለት

ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶችና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ

ምዕራፍ አንድ

ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶችና መልካም አጋጣሚዎች

1.1 ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች

ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የማስመዝገብ ተግዳሮት

ባለፉት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና በዘርፎች መካከል ሊኖር ከሚገባው ትስስር አንጻር ሲታይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ክፍቶች ነበሩበት። ምንም እንኳ ባለፉት ዓመታት የድህነት መጠንን መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ጊዜ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ 21 በመቶ እና ከክልላችን ጠቅላላ ህዝብ 21.9 በመቶ የሚሆነው ዜጋ ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ጥናቶች ያሳያሉ(ምንጭ- ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ 2006 ዓ/ም)። ከዚህም ባለፈ በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት፣ ሥራ አጥነትና ልዩ ልዩ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶች ተከስተዋል። እነዚህም ክፍተቶች የዕድገቱን ቀጣይነት አጠራጣሪ ከማድረጋቸውም በዘለለ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የኑሮ ጫና እያሳደሩ ይገኛሉ።

በመሆኑም በቀጣይ በኢኮኖሚው ውስጥ የተከሰቱ አንኳር ችግሮችን በመፍታት እና የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ በማስፈን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቱሩፋቱን ለህብረተሠቡ እንዲዳረስ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፣ የግለሠቦችን የኑሮ ደረጃ ተጨባጭ በሚባል ሁኔታ የሚያሻሽል፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚቀንስ፣ የዋጋ ግሽበትን፣ ሥራ አጥነትንና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶችን የሚያስተካክልና በኢኮኖሚ ዘርፎች ጠንካራ ትስስር ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ ለውጥን የሚያመጣ መሆን አለበት ።

በቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ሚዛን መዛባት

ባለፉት ዓመታት ኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ተከስቷል። ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንት ፍላጎቱን በአጠቃላይ ቁጠባው ማርካት ባለመቻሉ የኢንቨስትመንትና ቁጠባ ሚዛን መዛነፍ ተስተውሏል። ይህም በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የዋጋ ግሽበትን ማረጋጋት ፈታኝ መሆን

የዋጋ ግሽበት መንስኤዎች በርካታ ቢሆኑም ከፍተኛና ተከታታይነት ያለው የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚው ውስጥ መከሰት የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ምልክት ተድርጎ ይወሰዳል። ከዚህ አኳያ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የዋጋ ግሽበትን በአንድ አኃዝ የመገደብ የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫ የነበረ ቢሆንም በተግባር ግን ይህ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ከ2003 እስከ 2012 በነበሩት የበጀት ዓመታት የተመዘገበው ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት 14.4 በመቶ ሆኗል። ይህም በኢኮኖሚው ውስጥ በፍላጎት እና በአቅርቦት መካከል አለመጣጣም መኖሩን ከማሳየቱም በተጨማሪ የግብይት ሥርዓቱን የሚያዛንፉ ተቋማዊ ችግሮች መኖራቸውን ያመላክታል። ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት በዜጐች ላይ

ካስከተለው የኑሮ ውድነት በተጨማሪ ዘላቂ ኢንቨስትመንት እንዳይኖር በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጓል።

የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር

የሥራ ስምሪት ሁኔታ የማክሮ ኢኮኖሚውን ጤናማነት ከሚያሳዩ አመልካቾች አንዱ ነው። ከዚህ አኳያ በ2011 ዓ.ም በክልላችን ከ60 በመቶ የማያንሰው ሕዝብ እድሜው ከ50 ዓመት በታች እንዲሁም ከ28 በመቶ የሚሆነዉ ዕድሜው ለስራ የደረሰ (ከ30 ዓመት በታች) መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህን መሰሉ የሥነ ሕዝብ መረጃ በርካታ ወጣቶች መኖራቸውንና ሥራ ፈላጊ መሆናቸውን ይጠቁማል። ከዚህ በተጨማሪ የግብርናው ዘርፍ መጠነ ሰፊ ስውር ሥራ አጥነትን (disguised unemployment) እንዲሸከም ተገዷል። በአንጻሩ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙ ውስን እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። እስካሁን የተሞከሩ የተለያዩ የሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች የተወሰነ ውጤት ያስገኙ ቢሆንም በቀጣይነት የሥራ ዕድል ለማስፋፋት ተስፋ የሚጣልባቸው አይደሉም። በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለዜጐች በቂ የሥራ ዕድልም ሆነ አብዛኛው ዜጋ ሊደርስበት የሚችል የኑሮ ደረጃ መፍጠር አልቻለም።

አዝጋሚ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና ደካማ የዘርፎች ትስስር መኖር

ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አዝጋሚ በመሆኑ የኢኮኖሚው ምርታማነት ዝቅተኛ ከሆነው የግብርናው ዘርፍ ምርቶች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው የግብርና ምርቶች እንዲሁም ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የመሸጋገር ሂደቱ ደካማ ነበር። በዚህም በግብርናው ዘርፍ የተሰማራውንና ምርታማነቱ ዝቅተኛ የሆነውን እምቅ የሰው ኃይል ሊቀበል የሚችል የዳበረ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መገንባት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል። ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር በታቀደው ልክ እየሄደ አይደለም። በኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ የተመዘገበውም ዕድገት የመጣው ከማኑፋክቸሪንግ ሳይሆን በአመዛኙ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ነው። በተጨማሪም በዘርፎች መካከል ያለው ትስስር አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የማኑፋከቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል።

ክልላዊ ሀብት የማሰባሰብ አቅም ዝቅተኛ መሆን

ባለፉት ዓመታት የክልሉን ውስጥ የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከር ከታክስና ከሌሎች የውስጥ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን በአግባቡ ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የታክስ ገቢ የመሰብሰብ አቅማችን በየዓመቱ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በዕቅድ ተይዞ ከነበረው የታክስ ገቢ ግብ አኳያ ከፍተኛ ጉድለት ነበረበት። በዚህም ምንም እንኳ በክልሉ አመርቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ቢመዘገብም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የክልሉ

ሀብት ጋር ያለው ድርሻ ከተጣለው ግብ አንፃር ክፍተቶች ይታያል።የመንግሥት ወጪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ያስገኘውን ውጤት ለመገምገም ብሎም ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማስያዝ የተሰጠው ትኩረትም አነስተኛ ነበር።

የፋይናንስ ድርጅቶች ተደራሽነት

የባንክና የመድን ኩባንያዎች በተለመደው የፋይናንስ ተቋማት ጤንነት መመዘኛ ሲታዩ ደህና ቢመስሉም የአብዛኛዎቹ አቅም በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ካሉ ሃገራት የባንክና የመድን ኩባንያዎች አማካይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። የመንግስት ባንኮች መጠነ ሰፊ ብድሮችን ካለ በቂ አዋጭነት ጥናትና ክትትል የረዥም ጊዜ ብድር በመስጠታቸው የንግድ ባንኮችን የብድር ዓይነትና ጥራት አዛብቷል። የመድን ኩባንያዎችም በአብዛኛው በለመዱትና በሚቀላቸው አገልግሎት በመታጠር በሌሎች የመድን አገልግሎቶች ላይ በሰፊው ባለመሰማራታቸው የመድን ኢንዱስትሪው እንዳይሻሻል አድርጎታል። በአጠቃላይ የፋይናንስ መሠረተ ልማቱ ባለፉት ዓመታት ዕድገት እያሳየ ቢመጣም ኢኮኖሚው ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የማይመጣጠንና በየአካባቢው ያለው ተደራሽነትም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል።

የመሠረተ ልማት አቅርቦትና የጥራት ጉድለት መኖር

ባለፉት ዓመታት በመንገድ፣ በመጠጥ ውሃ እና በመስኖ ግንባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም አቅርቦቱ ካለው የመሠረተ ልማት ፍላጎት አኳያ ሲታይ ከፍተኛ የሆነ ጉድለት ይስተዋልበታል። ከጥራት አንጻርም ሰፊ ጉድለት የሚታይበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራ በታቀደና ክልላዊ አቅሞችን ከመጠቀም አንጻር በተቀናጀና ቅደም ተከተል በማስያዝ በአግባቡ ባለመከናወኑ ዋና ዋና የልማት ኮሪደሮችንና አካባቢዎችን ከማስተሳሰር አንጻር ጉድለቶች ተስተውለውበታል።

የማህበራዊ አገልግሎቶች የጥራት ውስንነት መኖር

ባለፉት ዓመታት በማህበራዊ አገልግሎቶች ዙሪያ በተለይም በጤናና በትምህርት ዘርፎች ከአገልግሎት ጥራት ጋር የተያያዙ የአፈጻጸም ጉድለቶች ታይተዋል። በትምህርቱ ዘርፍ በቅድመ መደበኛ፣ በተግባር ተኮር የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርትና የልዩ ፍላጎትና የአካል ጉዳተኞች ትምህርት አገልግሎትን በተመለከተ ተደራሽነቱም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ኤች.አይ. ቪ ኤድስን ከመከላከል አኳያ ቀድሞ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችን በነበሩበት ፍጥነት አጠናክሮ ያለማስቀጠል፣ ከሥነ ምግብ ጋር በተያያዘ በሕጻናት ላይ እየታየ ያለው የመቀንጨርና የመቀጨጭ ምጣኔ ትርጉም ባለው መልኩ አለመቀነሱ፣ የሕክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ሥርዓት ጠንካራ አለመሆን እያጋጠሙ ካሉ ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ከዚህ ባሻገር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነት በከተማና በገጠር ሰፊ የሆነ ልዩነት የሚታይበት ሲሆን ይህም ለዜጎች እኩል ዕድል ከመፍጠርና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯል።

የአቅም ውስንነትና ብልሹ አሠራር

ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡትን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር በተለያዩ ደረጃዎች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች ተስተውለዋል። በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት (በማቀድ፣ በመተግበር፣ በመከታተል፣ ኮንትራት በማስተዳደር) የአቅም ውስንነቶችና የቅንጅት ችግሮች ከመታየታቸውም በላይ የሀብት ብክነትና ሌብነትም ሰፍኖ የነበረ ሲሆን እነዚህን ሁኔታዎች የሚያስተካክልና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓትም በተገቢ መንገድ የተዘረጋ አልነበረም።

1.2. መልካም አጋጣሚዎች

የክልላችን ኢኮኖሚ በርካታ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ከነዚህ ችግሮች ተላቆ የዕድገትና ብልጽግና ጎዳናን ለመያዝ የሚያግዙ መልካም አጋጣሚዎች ባለፉት ሶስት ዓመታት ሀገሪቱ ብሎም በክልላችን ከተካሄደው ፖለቲካዊ ለውጥ ጋር ተያይዞ መፈጠራቸው ግልፅ ነው።

የሰላምና ፍትሕ መስፈን ለመልካም አስተዳደርና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር

የሰላምና ፍትሕ መስፈን ለመልካም አስተዳደርና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለኢኮኖሚና ማሕበራዊ ዕድገትና ብልጽግና እንዲሁም ለግሉ ዘርፍ ተሳትፎ መጠናከር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም በለውጡ ጊዜ የክልላችንን ሕዝቦች ለቅሬታና ለምሬት የዳረጉ በርካታ ጉድለቶችን ለማረም የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ክልላዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። የክልላችን ብሎም የሀገራችን የሰላም ግንባታ በተያዘው መንገድ እየተሻሻለ ከቀጠለ ሙሉ ትኩረትን ወደ ልማት በመመለስ የተስተዋሉ ጉድለቶችን በማረም በተሻለ የልማት ፍጥነት መንቀሳቀስ ይቻላል። እንዲሁም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ትውልድና ዜጋ በቀጣይ የተያዙ የልማት ግቦችን በተሻለ የመፈጸም አቅም ይኖረዋል።

ሕብረተሰቡ በክልሉ የፖለቲካና የልማት እንቅስቃሴ ያለው ተሳትፎ መጠናከሩ

ባለፉት ዓመታት ዜጎች በክልላችን የፖለቲካና የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩት ተሳትፎ እያደገ ስለመምጣቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ። እነዚህም ሀገራዊና ክልላዊ መግባባትን ለመፍጠር፣ የታክስ ገቢን ለማሳደግ፣ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ፍትሐዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው አግባብ እንዲሆን የመከታተልና የመጠየቅ ባህልን ለማዳበር በተደረጉ ለውጦች የሚገለጽ ነው። በቀጣይ የዜጎችን ተሳትፎ ማጠናከር የልማት ዕቅድን በባለቤትነት ከመፈጸምና ከማስፈጸም እንዲሁም አስፈላጊውን ሀብት ከማሰባሰብ አኳያ ዋናው የልማት አንቀሳቃሽ ዜጎች እንዲሆኑ ያስችላል።

ያለፉ ስህተቶችን በማረምና ከነሱ በመማር ተገቢ አቅጣጫን መከተል

ካለፉት ስህተቶች ተሞክሮ ለመውሰድና እነዚህንም ስህተቶች በማረም ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በመሆኑም በቀጣይ በተሻለ የግልፅነትና ተጠያቂነት መንፈስ ሥራዎችን በማከናወን ውጤታማ ልማትን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው የልማት ዕቅድን በሚፈለገው አግባብ ለመፈጸም የሚያስችል መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።

ምዕራፍ ሁለት

የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህርያት

2.1 የክልላችን የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ

በሀገራችን ደረጃ የልማት ዕቅድ የማዘጋጀት ልምድ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ በ1940ዎቹ መጀመሪያ ላይ የጀመረ ሲሆን በተመሳሳይ የደቡብ ብ/ብ/ክልል ከመደራጀቱ በፊት የክልሉ አከባቢዎች ሀገራዊ ዕቅዱን መነሻ ያደረገ የልማት ዕቅድ በማቀድ ሲተገበር ቆይ*ቷ*ል። ይህ እንዳለ ሆኖ ደቡብ/ብ/ብ/ሀ/ክልል ከተደራጀ በኋላ በተቀናጀ መልኩ የዕቅድ ሥራዎች መሰራት የተጀመረዉ ከ1988 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ነው።

ክልላችን ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት በዕቅድ ለመምራት የሚያስችሉ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይቷል። ከነዚህም ውስጥ ከ1988 -1992 ዓ.ም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እና ከ1993-1997 ዓ.ም የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ዕቅድ (Poverty eradication Plan) ተግባራዊ ተደርጓል። ከዚህ በኋላም ሁለት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች ማለትም ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ማስወገድ (Plan for Accelerated and Sustainable Development to End Poverty - PASDEP 1998-2002) እና የመጀመሪያውና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (GTP I (2003-2007) እና GTP II (2008-2012) ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ ተደርጓል።

በመቀጠልም በተመረጡ ዘርፎች ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች እንዲካሄዱ በማድረግና በግብዓትነት በመጠቀም "ኢትዮጵያ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት" ለማድረግ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካትና ክልላዊ ድርሻውን ለመወጣት የሚያስችል የ10 ዓመት (2013-2022) ክልላዊ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱ በዘርፎች መካከል እርስ በእርስ የጎንዮሽ ኢኮኖሚ (በግብዓት፣ በፋይናንስ፣ በመሠረተ ልማት፣ በቴክኖሎጅ፣ በሰው ኃይል፣ በገበያና በመሳሰሉት) እንዲሁም ከማክሮ ጋር ወደ ላይ እንዲተሳሰር ተደርጓል። በተጨማሪም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከልማት ዕቅዱ ጋር በማስተሳሰር የዕቅዱ አካል ሆነው እንዲተገበሩ ለማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራ የፋይናንስ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ጥናቱ የየዘርፉን የልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲመግብም ተደርጓል። በአጠቃላይ የልማት ዕቅዱ የጋራ መግባባትንና ፍላጎትን እንዲሁም የዜጎችን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቅና የህዝቦችን ተሳትፎ ያረጋገጠ የልማት ዕቅድ እንዲሆን ሰፊ የሕዝብ ምክክሮች ተካሂደዋል።

2.2 የአስር ዓመት ዕቅዱ አስፈላጊነት

ክልላዊ የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ሚና በዋናነት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በየምዕራፉ በሚኖሩ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች አማካይነት ሊተገበሩ የሚቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን፣ ዓላማዎችን፣ ግቦችንና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በማስቀመጥ የዕቅዶችን ተፈፃሚነት በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ለመከታተል የሚያስችል ነው። ይህም ማለት የልማት ዕቅዱ ለክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን በማስቀመጥ፣ ክልላዊ የኢኮኖሚ

ዕድገትንና ልማትን በረጅም ጊዜ ዕቅድ በመምራት፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የማምጣት ዓላማን ለማሳካት ብሎም ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በግልፅ በማስቀመጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና የጋራ ብልጽግናን ለማስፈን ያስችላል።

ከፍጹም ድህነት ወደ ማይቀለበስ ብልጽግና የሚደረግ ሽግግር የአንድና ከዚያ በላይ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል። በዚህም መሠረት በአንድ ትውልድ ዕድሜ ብልጽግናን በራዕይ ደረጃ ማመላከት የሚቻል ሲሆን ስኬቱ በትክክለኛ ጎዳና መሆኑን ለማመላከት በቂ ጊዜ ያስፈልገዋል። በተለይም በልማት ሂደት ውስጥ የዓመት፣ የአምስት ዓመት እና የአስር ወይም አስራ አምስት ዓመታት ዕቅዶች በእነዚህ ጊዚያት ሊፈጸሙ እንደሚገባቸዉ ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው።

በዝቅተኛ የድህነት ምጣኔ፣ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጽ የገቢ አቅም፣ በከፍተኛ የሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ፣ በዘላቂ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ በዘላቂ የከተማ ልማት፣ በኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ በፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና በመሳሰሉ ጉዳዮች የሚገለጹ ጥቅል የልማት ግቦች በአጭር ጊዜ የሚረጋገጡ ስላልሆኑ ከአስር ዓመት በማያንስ የጊዜ ሰሌዳ ይመላከታሉ። የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችም በረጅም ጊዜ ዕቅዱ የተመላከቱትን ግቦች ለማሳካት የሚተገበሩ ዝርዝር ዕቅዶች ናቸው።

የልማት ሂደትን የሀብት መፍጠሪያ አቅም መገንባት፣ ሀብት መፍጠር እና ሀብት በፍትሐዊነት መከፋፈሉን ማረጋገጥ በሚሉ ሦስት ደረጃዎች መከፋፈል ይቻላል። የሀብት መፍጠሪያ አቅም በኢንቨስትመንት ይረጋገጣል፤ ሀብት በኢኮኖሚ ዕድገት ይፈጠራል፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በፖሊሲ እውን ይሆናል። የእነዚህ ሂደቶች ትግበራም የተለያየ ጊዜ ይወስዳል። በአንድ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ስለኢንቨስትመንትና ተያያዥ ጉዳዮች፣ ስለ ዝርዝር የዘርፎች ተግባር እና በፖሊሲ ደረጃም ስለ ጥቅል ኢኮኖሚ መረጋጋት ሊታቀድ ይችላል። በአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ስለ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ስለ ፈጣን የመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊታቀድ ይችላል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ዘላቂ ልማት እና ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም መዋቅራዊ ለውጥ ከአስር ዓመት ባነሰ የጊዜ ሰሌዳ ማቀድ አይቻልም።

ከዚህ አንጻር አስርና ከዚያ በላይ ዓመታት የሚወስዱ የረጅም ዘመን ዕቅዶች አመላካችና አቅጣጫ ጠቋሚ ሲሆኑ የአምስት ዓመት ዓይነት የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች በረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ የተመላከቱ ዋና ዋና ግቦችን ለማስፈጸም የሚታቀዱ ዝርዝር ጉዳዮች ይሆናሉ። በአስር ዓመት ሊደረስባቸው የሚገባቸውንና የሚችሉትን ግቦች ግምት ውስጥ ያላስገባ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ በብዙ መልኩ ግቡን የሚያሳካ ዕቅድ ሊሆን አይችልም።

ይህን ጉዳይ በምሣሌ ለማስረዳት የቡና ልማት ችግኝ ከማፍላት እስከ ምርት ባለው ሂደት የአምስት ዓመት ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል። በአንድ ዓመት ውስጥ ሊታቀድ የሚችለው ችግኝ አፍልቶ ከመትከልና ችግኙ መጽደቁን ከማረጋገጥ አይዘልም። ቡና በመትከል ተጠቃሚነትን ግብ ላደረገ ገበሬ ግን ትልቁ ዕቅድ የአምሥት ዓመት ዕቅድ

ይሆናል። ገበሬው ስለሚኖረው የቡና ምርት መጠን፣ የቡናው ምርት ተሸጦ ስለሚገኘው ገቢና በገቢው ስለሚሟሉ ፍላጎቶች ከአምሥት ዓመታት ባነሱ ጊዚያት እንደሚሟሉ አድርጎ ማቀድ አይቻለውም። ይልቁንም እነዚህ ግቦች በአምሥት ዓመት ዕቅድ ከተመላከቱ በኋላ ዝርዝር አፈጻጸሞች የአምሥት ዓመት ግቦችን መሠረት አድርገው በአንድ ዓመት ተመጥነው ይታቀዳሉ።

2.3. የአስር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪያት

የልማት ዕቅድ ዝግጅቱ የዘርፎችን ትስስር ያማከለ እንዲሆን መደረጉ፦ የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አንዱ መለያ የዘርፎችን ትስስር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ነው። የዘመናዊ ግብርናን፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪንና የማዕድን ዘርፎችን አንዱ ለሌላው ግብዓትና ፍላጎት በመሆን እንዲደጋገፉ የንግድ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎችን በማሳለጥ ምርትን ከገበያ ጋር የማገናኘት ሚና እንዲወጡ በልማት ዕቅዱ ዝግጅት ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል። በተመሳሳይ መሠረተ ልማቶች (መንገድ፣ ኢነርጂ፣ መስኖ፣ ሌሎች የትራንስፖርት መንገዶች፣ መገናኛዎች) ለሌሎች ዘርፎች መልማት መሠረት እንዲሆኑ እንዲሁም የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ የምርታማነት ወሳኝ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው የሁሉንም ዘርፎች ልማት በሚያሳልጡበት አግባብ ታቅዷል።

የዘርፎች ትስስር ወሳኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ምርታማነት፣ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም እና ሌሎች ዘርፎችን የማነቃቃት አቅም ያላቸውና ለበርካታ ዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል መሠረት የሚሆኑ ዘርፎች በቀጣይ አስር ዓመታት የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ዘመናዊ ግብርና፣ የአምራች ኢንዱስትሪና የማዕድን ዘርፎች በአምራች ዘርፍነት የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን እነዚህ ዘርፎችም በግብዓትና በፍላጎት የእርስ በእርስና ውስጣዊ ትስስር በሚደጋገፉበት አኳያ ታቅደዋል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዱ ክልሉ ባለው የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች ምክንያት የቱሪዝም ዘርፍ ለአገልግሎት ዘርፎች መጠናከር እንዲሁም ለአምራች ዘርፎችና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ወሳኝ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በማስገኘት ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከግምት ያስገባ እንዲሆን ተደርጓል። በተመሳሳይ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት፣ የሥራ ዕድል ምንጭ እና የሰው ሀብት መገንቢያ ለማድረግ የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል። እነዚህን ዘርፎች ለማልማትም መሠረተ ልማቶች ቁልፍ ሚና ስለሚኖራቸው የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በአብዛኛው ከዘርፎች ትስስር ጋር የተቆራኘ ነው። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በዘርፍ ተቋማት እንደመሆኑ ተቋማቱ ስለዘርፎች የመልማት አቅም፣ መሠረታዊ ክፍተቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የተሻለ ግንዛቤ አላቸው። በመሆኑም የልማት ዕቅድ ከላይ ወደታች የሚወርድ ሳይሆን በዘርፎች ተሳትፎ እንዲታቀድ ተደርጓል።

አሳታፊና ክልላዊ የልማት ማዕከላትን የለየ መሆኑ፦ በክልሉ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የሚደረጉ የልማት ዕቅዶችን ክልላዊ የልማት ዕቅድ ጋር የሚያስተሳስር ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት መኖር ለልማት ዕቅዱ ውጤታማነት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በዞኖችና ከልዩ ወረዳዎች በታች ባሉ

የመንግሥት አካላት የልማት ዕቅድን የሚመራ አቅምና በቂ ፋይናንስ እንዲኖር ማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሠረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሰት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አካባቢዎች የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይልና አቅሞችን በአግባቡ በመጠቀም ለልማት ዕቅድ መሳካት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ክልላዊ የልማት ዕቅዱና የዞን መዋቅር የልማት ዕቅዶች ያላቸውን የመልማት እምቅ አቅም በመቃኘትና በማጣጣም እንዲሁም ክልላዊ የልማት ማዕከላትን በመለየት የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ከተመረጡ የልማት ማዕከላት ጋር የተቀናጁበትን አግባብ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ተደርጓል።

የሥርዓታትን ድክመቶች እንደ ዋና ተግዳሮት በመውሰድ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የሚደረግበት አቅጣጫ መያዙ፦ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በመዋቅራዊ ለውጥ ረገድ ለተስተዋለው ዝቅተኛ አፈጻጸም አንዱና ዋናው ምክንያት የሥርዓታት ድክመት እንደሆነ ታምኖበታል። የተቋማት ዝቅተኛ የማስፈጸም አቅም፣ የፕሮጄክት አስተዳደር እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መላላት፣ ተጠያቂነት አለመስፈን፣ በግሉ ዘርፍ ያልተገቡ ባሕርያት መታየትና ከመንግሥት ተቋማት ብልሹ አሠራሮች ጋር መቆራኘት፣ እንዲሁም ክልላዊ የጋራ ስምምነቶች ይልቅ የተናጠል ፍላጎቶች ልቀው መገኘትና ለሠላም መደፍረስ መንስኤ መሆን የሥርዓታት ድክመት መገለጫ ሆነዋል። የልማት ዕቅዱ እነዚህን ክፍተቶች ከግምት በማስገባት የሥርዓታት መሻሻልና ለውጥ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን የለየ ሲሆን በዚህም የተሻሉ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ እንደሚውሉ ታሳቢ አድርጓል።

የግሉ ዘርፍ ዋና የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተር መሆኑን መቀበል የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ ትብብር የሚያጠናክር መሆኑ፦ ባለፉት አሥራ አምሥት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ ነበር። የመንግሥት የልማት ስኬቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚና በማሕበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ የተንጸባረቁ ሲሆኑ ዋና የዕድገት ምንጮቹም ፍላጎትን የሚያበረታቱ እነዚህ ዘርፎች ነበሩ። ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት መረጋገጥ የሚችለው በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሲሆን በቀጣዮቹ አስር የልማት ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግሉ ዘርፍ በተለይም የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በወሰኝ አምራች ዘርፎች ላይ እንደሚሰማራ ትልቅ ተስፋ ተጥሏል። ይህ ዕቅድ ዳር እንዲደርስም የግሉ ዘርፍ የመንግሥትን የልማት አቅጣጫ እንዲረዳና በምክክር ሲዳብርም እንዲገዛው እና መንግሥትም የግሉ ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በተቀላጠፈ መንገድ እንዲፈታ የማድረግ ዓላማ ያለው ሲሆን በልማት ሂደቱ የመንግሥትና የግሉ ዘርፎች እውነተኛ ትብብር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት በሀገር ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ፣ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ማዕቀፍ፣ ሀገራዊ የተቀናጀ የልማት ማዕቀፍ እና የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ማዕቀፍ እየተዘጋጁ መሆኑ እንዲሁም በክልል ደረጃ ዘመናዊና ዲጂታል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ለመዘርጋት ትኩረት መሰጠቱ የልማት ዕቅዱን ልዩ ያደርገዋል።

ክፍል ሦስት

የአሥር ዓመት (2013-2022) የልማት ዕቅድ

ምዕራፍ አንድ

የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና ምሰሶዎች

1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች

1.1.1 ክልላዊ የረጅም ጊዜ የልማት ራዕይ

የቀጣይ 10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎችና ግቦች የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ክልላዊ ራዕይን ለማሳካት ወሰኝ በሆኑት የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በዚህ መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፤ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ፤ የኢኮኖሚውን የዕድገት ቀጣይነትና ዘላቂነት ማረጋግጥና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ናቸው።

1.1.2 የቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች

የክልሉ የቀጣይ 10 ዓመት የመሪ ፕላን ዕቅድ ዓላማዎች ኢትዮጵያ አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ሀገራዊ ራዕይን ታሳቢ በማድረግ የተጀመረውን የለውጥና የብልጽግና ጉዞ በላቀ ደረጃ ለመፈጸም ማስቻል ነው። በዚህም መሰረት ዋና ዋና ዓላማዎቹ የሚከተሉት ይሆናሉ።

- በቀጣይ አስር ዓመታት ክልላዊ ኢኮኖሚው በአማካይ 10.4 በመቶ በማሳደግ ሀገራዊና ክልላዊ ራዕይ መሳካት የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት ማድረግ፤
- አነስተኛና መካከለኛ ኢንደስትሪዎችን ማስፋፋት፣ የአምራች ዘርፉን ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል ተወዳዳሪነትን ማጎልበትና መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ፤
- የህዝቡን የማስፈጸም አቅም በመገንባት የልማት ተሳታፊነት፣ ባለቤትነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
- የግል ባለሀብቱን በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ድርሻና ተሳትፎ በላቀ ደረጃ ማጎልበት፤
- የክልሉን የአየር ንብረትና የአከባቢ ጥበቃን መሰረት በማድረግ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ መሰረት መጣል ነው።

1.2. የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎች (strategic pillars)

የልማት ዕቅዱ የተመረጡ ቁልፍ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (strategic pillars) ያሉት ሲሆን እነዚህም ፡-

- ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና የጋራ ብልጽግና ማረጋገጥ፤
- የኢኮኖሚ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፤
- የቴክኖሎጂ አቅም እና የዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት፤
- የዘላቂ የዕድገት እና የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ፤
- የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት ማረጋገጥ፤
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፤
- የሥርዓታት ለውጥን ማረጋገጥ፤

- የልማት ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ አካታችነትን ማረጋገጥ፤
- የፍትህ ተደራሽነት እና ውጤታማ የህዝብ አገልግሎት ማስፈን፤
- ዘላቂ የሰላም ግንባታ እና ጠንካራ ክልላዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ማረጋገጥ ናቸው።

1.3. የልማት ዕቅዱ የትኩረት መስኮች

በልማት ዕቅዱ የተካተቱ ሁሉም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ሌሎች ዘርፎች ለክልሉ የልማት ራዕይ መሳካት የማይተካ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ ክልሉ ቅድሚያ ሰጥቶ ሊፈታቸው ካሰባቸው ማነቆዎች፣ ዘርፎች ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና፣ በትንሽ ጥረት ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ያላቸው አቅም፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ባላቸው ትስስርና በእነዚህ ዘርፎች ላይ በሚያመጡት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ፣ ክልሉን ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ ያላቸው አቅም፣ እንዲሁም ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ ያላቸው የጎላ ድርሻ መሠረት በማድረግ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት

ፈጣን፣ ዘላቂና መሠረተ ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስመዝገብ የኢኮኖሚያዊ ብዝሃነት ዕሳቤ እንደ ስትራቴጂ ይተገበራል። ኢኮኖሚያዊ ብዝሃነት ከአንድ የገቢና የዕድገት ምንጭ ይልቅ ወደ ብዙ የዕድገት ምንጮች የማተኮር ሂደት ነው። በዚህም መሠረት ግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ጨምሮ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የከተማን ዕድገት መሠረት ያደረገ የአይ.ሲ. ቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጮች ተደርገው ተለይተዋል።

የግብርና ዘርፍ ልማት፦ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የግብርና ዘርፍ አፈጻጸም አበረታች የነበረ ቢሆንም ዘርፉን በአስተማማኝ ደረጃ ከማዘመን አንጻር ከፍተኛ ክፍተቶች ተስተውለዋል። በ2ኛዉ የዕ.ት. ዕ ትግበራ ዓመታት የግብርናው ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ በየዓመቱ በ9.4 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። ይህም በተመሳሳይ ወቅት ከተመዘገበው ከሕዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ በመሆኑ አስችጋሪ የአየር ንብረት በተከሰተባቸው ዓመታት ዘርፉ ከመፈተኑ በስተቀር በገጠር አማካይ የኑሮ መሻሻል እንዳለ ማስተዋል ይቻላል። ከዚህም በላይ ግብርናው ለሌሎች ዘርፎች ዕድገት መፋጠን የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል። ይሁን እንጂ ዘርፉ ውስጣዊ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና ከመዘመን አንጻር አሁንም ከዝናብ ጥገኝነት አለመላቀቅ፣ የዘርፉ አቅሞች ከበሬ እምብዛም ያልዘለሉ መሆን፣ ለአጠቃላይ መዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ ከማድረግ አኳያ በተለይም ለሌሎች ዘርፎች በቂ ምግብና አስተማማኝ ግብዓቶች ከማቅረብ እንዲሁም ገበያ ከመፍጠር አንጻር የግብርናው ዘርፍ ውስንነት አለበት። የክልሉን የምግብ ፍላጎት ማሟላት ካለመቻሉ በተጨማሪ የዘርፉ የሰው ኃይል ምርታማነትም ዝቅተኛ ነው።

የግብርናው ዘርፍ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ፈጣን እንዳይሆንና የግብርና ትራንስፎርሜሽን እንዳይረጋገጥ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የመዋቅራዊ ሽግግር የተሻለ አስተዋጽኦ አንዳያበረክት የሚገድቡ ማነቆዎች ከቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት፥ ከዝቅተኛ የግብርና ኢንቨስትመንት ብሎም ከዝቅተኛ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዙ በሦስት አበይት ጉዳዮች የሚጠቃለሉ ናቸው።

ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶችም የመስኖ ልማት በተገቢው መጠን አለመስፋፋትና በቴክኖሎጂ ያልታገዘ መሆን፣ የተቀናጀ የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት አለመኖር፣ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ማመንጨት፣ ብዜትና ስርፀት ሥርዓት አለመዳበር፣ የግብርና ፋይናንስ እንዲሁም ኢንሹራንስ እና ኢንቨስትመንት በበቂ ሁኔታ አለማደግ፣ የግብርና ግብይት ሥርዓት ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና ሕጋዊ ሆኖ ያለመገንባት፣ በግብርና መስክ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖርና የግብርና ዘርፍ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዘም የዕውቀት፣ ክህሎትና ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን፥ ወጥነት ያለውና የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር አለመኖር ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማሻሻልም የግብርና ዝመና አማራጭ የሌለው የዕቅዱ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል።

የግብርና ዝመና የክልሉን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማሳደግ በቀጣዮቹ አስር ዓመታት ድርብርብ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ መመገብ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የመዋቅራዊ ሽግግርን እውን ማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ምግብ፣ ግብዓትና የሰው ኃይል ማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት ማጎልበትና የሥራ ዕድል መፍጠር ከግብርናው ዘርፍ በቀጣይ የሚጠበቁ ሚናዎች ናቸው። በመሆኑም የግብርና ዝመናን ለመተግበር ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶች በወሳኝ መልኩ መፈታት ይኖርባቸዋል። አጠቃላይ የግብርና ልማት አቅጣጫው በባሕላዊው የአመራረት ሥርዓት ከሚካሄዱ የተለመዱና እነዚህንም ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን ለጎን ግብርናን እንደ ህይወት ማቆያ አድርጎ የሚወስድ ሳይሆን እንደ አንድ ትርፋማና አዋጭ ኢንዱስትሪ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት በማበረታታት በሂደት የባሕላዊውን የግብርና ዘይቤ መተካት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በልማት ዕቅዱ የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ፣ ከጉልበት አጠቃቀም እስከ ተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች የሚዘልቅ ሜካናይዜሽን በሁሉም የግብርና ንዑስ ዘርፎች ለማስፈን፣ በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ ገበሬዎችን የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው ማገዝና ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስተርነት ለማሳደግ፤ የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማጎልበት እና በዘርፉ የባለሀብቱን ተሳትፎ ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። ለዚህም የግብርና ሥነ ምህዳርን ማዕከል ያደረገ የግብርና እንቅስቃሴን መከተል፣ የአመራረት ሥርዓትን ማዘመን፤ በተለይም የኤክስቴሽን አገልግሎቱን የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት በማድረግ የክትትል ሥርዓትን ማዘመን፣ ሁለንተናዊ የግብርና አቅሞችን ማጎልበት፤ የምርምር፣ የሰው ኃይል፤ የግብርና መሠረተ ልማት፤ የቴክኖሎጂ ሥርፀትን ማሻሻል፣ በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ በሂደት አስቻይ ፖሊሲዎችን መተግበር፤ የግሉ ዘርፍ በአስተማማኝ የመሬት ይዞታ ላይ ግብርናውን

እንዲያዘምን ማድረግ በትኩረት ሊተገበሩ የሚገባቸው ዋና ዋና ርምጃዎች ይሆናሉ። በእንስሳት ሀብት ዙሪያም የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ፣ መኖ እና ጤና ላይ በትኩረት ለመሥራት ግቦች ተጥለዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፦ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት እና ለተለያዩ አሉታዊ ተጽዕኖዎች የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ጠንካራ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መኖር ወሳኝ ነው። በክልሉ ባለፉት ዓመታት ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት ቢኖርም ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከአጠቃላይ በክልሉ ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከ17.8 በመቶ ነዉ። ዘርፉ በአጠቃላይ ሲቃኝ በቀላል ማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች የተዋጠ ከመሆኑም በተጨማሪ አዝጋሚ ለውጥ የታየበት ዘርፍ ነው። ዘርፉ ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ያለው ተጽዕኖና ፋይዳ ደካማ ነው።

በተመሳሳይ የማኑፋክቸሪንግ የማምረት አቅም በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ፤ ያሉት ማኑፋክቸሪንግ ከሌሎች ላዕላይ ኢንዱስትሪዎች ጋር ያላቸው ቁርኝት ዝቅተኛ መሆኑ፣ የመሠረተ ልማት በተለይም የኃይል አቅርቦት መጓደል ብቁ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የተንዛዛና ገዳቢ የመንግስት ቢሮክራሲ እና ከግሉ ዘርፍ አቅም ውስንነት ጋር ተዳምሮ የዘርፉን የማምረት አቅም ከ50 በመቶ በታች አድርጎታል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ምርታማነትና ቅልጥፍናን በማሳደግ መዋቅራዊ ሽግግርን ዕውን ማድረግ ወሳኝ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል።

የማኑፋክቸሪንግ ልማት ወሳኝ ከሚሆንባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በከፍተኛ የዘርፎች ትስስር በሚፈጠር ሰፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አማራጭ ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ መቻሉ ነው። ከዚህ አንጻር የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት የሀገሪቱን የእንስሳት ሀብት፣ የቅባት እህሎች፣ የጭረትና የፍራፍሬ ሀብቶች በአግባቡ መጠቀምን ቅድሚያ ይሰጣል። የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ከግብርናው ዘርፍ ግብዓትና በቂ ምግብ በማግኘት ተጠቃሚ እንደሚሆን የመታሰቡን ያህል በአጸፋው ዘመናዊ ግብርና ግብዓቶችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን በመፈብረክ እንዲሁም ከግብርና ዘርፍ ለሚመረት ትርፍ ምርት ገበያ በመፍጠር በዘርፎች ትስስር የኢኮኖሚ ዕድገትንና መዋቅራዊ ለውጥን የማረጋገጥ አቅጣጫ ይከተላል።

የአምራችና የኮንስትራክሽን ዘርፎችም የማዕድን እንዲሁም ለኃይል ምንጭነት የሚውሉ ሀብቶችን በመጠቀምና ዙሪያ መለስ የዘርፎች ትስስርን በመፍጠር በማኑፋክቸሪንግ፥ በማዕድን፥ በውኃና በኤሌክትሪክ፥ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፎች የሚፈጠረውን ተጨማሪ እሴት በማሳደግ አጠቃላይ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ልማት እንዲያፋጥኑ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል። በእነዚህ ጥረቶች ከውጭ የሚገቡ መሠረታዊ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፣ በአዲስና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አዲስ ምርትና አዲስ ፍላጎት መፍጠር፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ በመሆን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ ሥራ አጥነትን በመቀነስ እና በሂደቱ የተስተካከለ የንግድ ሚዛን

ማረጋገጥ የዘርፉ ዋነኛ ግብ ነው። በተጨማሪም በመጪው አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ባለፉት ዓመታት ማኑፋክቸሪንግን ለማስፋፋት የተጣሉ መሠረተ ልማቶችን ታሳቢ በማድረግ ማኑፋክቸሪንግ ከሌሎች ዘርፎች የተነጠለ እንዳይሆን፣ የትስስር ሠንሠለቱን በጠበቀና ከሌሎች ዘርፎች ፍላጎት ጋር በማጣመር የአምራች ዘርፎችን ማፍጠን ያስፈልጋል። በተጨማሪም ማኑፋክቸሪንግን ተወዳዳሪ ለማድረግ አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በማሟላት ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል።

በተጨማሪም በቀጣይ አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ትግበራ የዕድገት ማዕከልን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ልማት ልዩ ትኩረት የሚያገኝ ይሆናል። መካከለኛና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የሥራ ዕድልን ከመፍጠር በተጨማሪ ለመካከለኛና ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ግብዓቶችን የማቅረብና በሌሎችም ጉዳዮች በማስተሳሰር በትብብር እንዲሰሩ ማድረግ ትኩረት ይሰጠዋል።

ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በጊዜ፣ በአይነትና በመጠን ስለሚለያይ የኢኮኖሚውን አጠቃላይ ገጽታ ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተፈላጊውን የሰው ኃይል ግብዓት ቀድመው በማቀድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል። በተጨማሪም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማቶችን በዕድገት ማዕከላት አማካይነት በማቅረብና ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በመጨመር የማኑፋክቸሪንግ ልማት ዕውን ይደረጋል።

የማዕድን ዘርፍ ልማት፡- ክልሉ ማዕድናትን ጨምሮ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያለዉ አከባቢ ሆኖ ሳለ፣ የተፈጥሮ ሀብት በተለይም ማዕድን በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ ነዉ። ለዚህም በዋነኝነት በዘርፉ ያለው ኢንቨስትመንት በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ዝቅተኛ መሆን፤ በክልሉ የማዕድን አለኝታ ሽፋን መረጃ በዝርዝርና በጥራት በበቂ ደረጃ አለመኖር፣ መረጃው በሚገኝበትም ጊዜ መረጃ ከማቅረብ፣ የተቀላጠፈና ፈጣን የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከማስፈን፣ ከማስተዋወቅና አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ከመሳብ ጀምሮ ዘርፉን የማስተዳደር አቅም ውስንነት፤ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ አቅም ደካማ መሆን፣ የዘርፉን ልማት ከሌሎች ዘርፎች ልማት ነጥሎ የማየት ችግር ወይም በተገቢው ደረጃ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የስልቶች ግልጽና ወጥ አለመሆን፣ ከማኅበረሰብ እስከ ፖሊሲ አውጪ ባሉ ተቋማት ስለማዕድን ሀብትና በዘርፉ ስለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የተያዙ ገንቢ ያልሆኑ ግንዛቤዎችና አመለካከቶች፣ የፌዴራል መንግሥትና የክልላችን መንግሥት የማዕድን አስተዳደር የዘርፉን ሕጎች ለመተግበር የአቅም ውስንነት መኖር ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ትግበራ ዘመን እነዚህም ተግዳሮቶች በማስወገድ የማዕድን ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። የማዕድን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ካለው ትስስር አኳያ የአሸዋና የባዛልት የመሳሰሉ ድንጋዮች፣ የዕምነ በረድ፣ የግራናይትና የኖራ ድንጋይ ማዕድናት ለኮንስትራክሽንና ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ጠቃሚ ግብዓቶች ናቸው። ከዚህም በላይ ክልላችን ብሎም ሀገራችን ለወጠነችው የመዋቅራዊ ሽግግር ዕቅድና የመካከለኛ

ገቢ ሀገር የመሆን ትልም መሳካት ወሳኝ እንደሆኑ የታመነባቸውን የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ዝመና ስትራቴጂዎች ከማፋጠን አንጻር ከማዕድን ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ሚና ይጠበቃል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ የተያዘው አቅጣጫ የማዕድን ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግርን በማፋጠን አጠቃላይ አቅም መፍጠር ሲሆን በተለይም የዘርፎች ትስስርን ማጠናከር፣ የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ዝመናን ለማፋጠን ከውጭ የሚገቡ የግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ግብዓቶችን በመተካት ማዕድናትን በግብዓትነት መጠቀም፣ ተጨማሪ እሴት በዘርፉ በመፍጠር ለኢኮኖሚው ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ፣ ለዘላቂ ማኅበራዊ ለውጥ አጋዥ ዘርፍ እንዲሆን በማድረግ የማኅበረሰብ የሀብትና የልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጫ መስክ እንዲሆን ማድረግ እና ተወዳዳሪ የማዕድን ኢንዱስትሪ በመፍጠር መዋቅራዊ ለውጥን ማምጣት ትኩረት ይሰጠዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ ልማት፦ የቱሪዝም ዘርፍ ለአንድ ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ በጣም ከፍ ያለ ነው። ክልላችን ታሪክ፣ በውብና ማራኪ የተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም በአስደናቂ የባህል ፀጋ የታደለ ነዉ። እነዚህ ብርቅቤ ሀብቶቿ ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነጻጸሩ በጣም ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ናቸው። ሆኖም ባለፉት ጊዜያት እነዚህን ሃብቶች በአግባቡ ከመጠቀም አንጻር ሰፊ ክፍተቶች ታይተዋል። በተለይም የቱሪስት መዳረሻዎች በተገቢው መልኩ በጥናት ተለይተውና ለምተው፣ ለሀገር ጥቅም ሊያስገኙ በሚችሉበት ቁመና ላይ አይገኙም። መስህቦቻችን ያላቸው ደረጃ እጅግ ከፍ ያለ ቢሆንም ለጎብኝዎች በሚመች፣ ተወዳዳሪና ሳቢ በሆነ ሁኔታ የለሙ አይደሉም። በቱሪስት መዳረሻዎቻችን በቂና የሁሉንም ፍላጎት ሊያስተናግድ በሚያስችል መጠን የመጓጓዣ፣ የመኝታ፣ የምግብ፣ የቴሌኮም፣ የባንክ፣ የመንገድ ዳር ማረፊያዎች፣ የመታጠቢያ ቤቶች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የእግር መንገዶች የተሟሉ አይደሉም። በተጨማሪም ማህበረሰቡም ከቱሪዝም ተጠቃሚ የሚሆንባቸው በቂ አሠራሮች አልተዘረጉም። በዘርፉ ለተሰማሩና መሰማራት ለሚፈልጉ በተለይም ከማዕከል ወጣ ባሉ የመስህብ ቦታዎቻችን መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ማበረታቻዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸውና የቱሪዝም ዘርፉን ተወዳዳሪ ሊያደርግ በሚችል መልኩ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለኢንዱስትሪው እየቀረበ አለመሆኑ በቱሪዝም ዘርፍ ያለውን ከፍተኛ የሆነ እምቅ አቅም ጥቅም ላይ እንዳይውል አድርገዋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች በመፍታት ከዘርፉ የሚጠበቀውን እምቅ አቅም ሀገራችን ብሎም ክልላችን በአግባቡ እንዲጠቀም ማስቻል ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል።

በቀጣይ አስር ዓመት የክልሉን የቱሪዝም አለኝታዎች በአግባቡ በመለየትና በማልማት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት በማጠናከር፣ በክልልሉ የሚገኙ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን በማልማት፣ ነባር መዳረሻዎችን በማጎልበትና የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነት በማስፋፋት የዘርፉን ተወዳዳሪነት በማሳደግ፤ ውጤታማ የገበያ ትስስር፣ የብራንዲንግና ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን መፍጠርና በነባር የቱሪስት አመንጪ ሀገራት ያለንን የገበያ ድርሻ በማሳደግ፤ በዘርፉ ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ በመፍጠር እና የማበረታቻ

ሥርዓቶችን በመዘርጋት የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት እንዲሁም በተወሰኑ ግብዓቶችና የመሠረተ ልማት ጥረቶች ሌሎች በርካታ ዘርፎችን በማነቃቃት ለክልሉ ኢኮኖሚ በሚኖረው ከፍተኛ ሚና ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል።

አይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ፡- ብዘሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕሳቤ ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ዘመኑን በሚመጥን ለፈጣን የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር ወሳኝ በሆኑ አይሲቲን በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ መሰማራት የግድ ነው። አይሲቲና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር ገብተው የሌሎች ዘርፎችን ልማት ከማሳለጥ ይልቅ እንደ አንድ የኢንዱስትሪ መስክ በማበልጸግ የኢኮኖሚ ዕድገትና የልማት ግስጋሴን እንዲያፋጥኑ በትኩረት ይሠራል። በተጨማሪም የዲጂታል ኢኮኖሚ መገንባት፤ በሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ኢገቨርናንስ ተግባራትን (e-governance) ፣ ወረዳ ኔት፤ የገጠር ኮኔክቲቪቲ ፕሮግራምና የገጠር መንግሥታዊ ኢንተርኔት አቅርቦት ማዕከል የመሳሰሉትን ማጎልበት) ፣ የቴክኖሎጂ ግብይት፣ ፋይናንስና ሎጂስቲክስ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የአይሲቲ ፓርክንና ኢኮሲስተምን ማበልጸግ፤ በአይሲቲ ዕውቀትን የሙያና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቶችን ማስፋፋት በትኩረት ተይዘው የሚሰሩባቸው ይሆናል። በተጨማሪም "ምርታማነት ከቴክኖሎጂ ጋር" የሚል ወሳኝ የዕድገት አቅጣጫ በትኩረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

2. ዘላቂ እና ተደራሽ የፋይናንስ ዘርፍ ልማት

ባለፉት ዓመታት የክልሉ የመንግስት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ሳይካሄድ በበጀት ውስጥ እንዲካተቱ መደረጉ አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደታቸውን አጠናቀው በወቅቱ ወደ ምርትና አገልግሎት ባለመግባታቸው ምክንያት ከተስተዋለው የልማት ፋይናንስ እጥረት በላይ በልማት ፕሮጀክቶች መጓተት፣ እንዲሁም ብልሹ አሠራሮች ምክንያት የተከሰተው ብክነትና ከዚህ ጋር የተያያዘው ዝቅተኛ የካፒታል ምርታማነት ነው።

የፋይናንስ አቅሞችን ከጊዜያዊ ወደ ዘላቂና ጥራት ወዳላቸው ምንጮች ማሸጋገር፣ የፋይናንስን ጥራትና ፋይዳ መጨመርና ብክነትን መቀነስ፣ ቅልጥፍናን ማሻሻል፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባን ከገጠር እስከ ከተማ ባሉ ተቋማት ማሳደግ እንዲሁም የክልሉን ውስጥ ገቢን በዘመናዊ የታክስ ሥርዓት መደገፍ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

3. የሥነ ሕዝብ ለውጥ ትሩፋት

የአንድ ሀገር ትልቁ ኃብት የሰው ኃይል ነው። ዘላቂ ልማትን እንዲሁም ብልጽግናን ለማረጋገጥም ዋናው መሠረት የሰው ኃይል ነው። በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለያዝነው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ ልማትና ማህበራዊ ልማት እንደ ጽኑ መሠረት የሚወሰድ ነው። በመሆኑም ለሰው ሀብት ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት የሥነ ሕዝብ ትሩፋትን ማረጋገጥ ወሳኝ ይሆናል። በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ ባለፉት ዓመታት በርካታ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ከጥራት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከተደራሽነት እንዲሁም ከተገቢነት አንጻር ሰፊ የአፈጻጸም ክፍተቶች ተመዝግበዋል። በትምህርት ዘርፍ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ፣ በአንደኛ ደረጃ

ሁለተኛ ዕርከን ንጥር ተሳትፎ፤ በሁለተኛ ደረጃ ጥቅልና ንጥር ተሳትፎ፤ በመሰናዶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥቅልና የንጥር ተሣትፎ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተደራሽነት ከሀገሪቱ ስታንዳርድ አንጻር አነስተኛ ነው። በተጨማሪም በመጠነ መድገምና በመጠነ ማቋረጥ የተመዘገቡት ዝቅተኛ የሆነ አፈጻጸም በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው። በተመሳሳይ በጤናው ዘርፍ ተግባራዊ የተደረገው በሽታን የመከላከል ስትራቴጂ የህብረተሰቡን የጤና ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት እንደሚያስችል በተጨባጭ ማየት ተችሏል። ከዚህ ስትራቴጂ በተጓዳኝ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ተደራሽና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ጥረቶች ተደርገዋል። ይህም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አፈጻጸም የተሻለ ውጤት እንዲኖራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት በመቆጣጠር የህጻናትን ሞት መቀነስ የተቻለ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል። በተጨማሪም ወደ ጤና ተቋም ሄደው የማይወልዱ እናቶችን ቁጥር በመቀነስ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶችን ምጣኔ መቀነስ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ሰፊ ክፍተቶች አሉበት። ባለፉት ዓመታት በዘርፉ በዋናነት የተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ጉድለት፤ የዘርፉ የቁጥጥር ሥርዓት ጠንካራ አለመሆን፤ የአገልግሎት ተቋማት ከስታንዳርድ በታች መሆን፤ ዘርፉ በሚገባው መልኩ በቴክኖሎጂ አለመደገፉ፤ የፋይናንስና የግብዓቶች በቂ አለመሆን፤ የማህበረሰቡና የባለድርሻ አካላት የዘርፉ ተሳትፎ፣ ዕውቀትና ክህሎት ውስንነት፤ ቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት አለመኖር፤ የአመራርና የአስተዳደር የብቃት ችግሮችና የተጠያቂነት አሠራር ደካማ መሆን እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አናሳ መሆን ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ናቸው።

የሰው ኃብት ልማት ዘርፍ በቀጣይ ጤናማ፣ በዕውቀትና በክህሎት የዳበረና ርዕቱ አመለካከት ያለው የሰው ኃይል በመፍጠር የኢኮኖሚ ዕድገትንና አስፈላጊውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በክልላችን በቀጣዮቹ ዓመታት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአምራች ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ የሰው ኃይል እንደሚኖራት ጥናቶች ያመለክታሉ። በመሆኑም ይህን አምራች የሰው ኃይል ጤንነቱን በመጠበቅ የዕድገት ምዕራፉ የሚፈልገውን ሙያና ክህሎት ማዳበር የሚያስችሉ አቅሞችና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሥነ ሕዝብ ለውጥ ትሩፋት ይረጋገጣል። ለዚህም የትምህርት አገልግሎት ተደራሽነትን፣ ጥራትንና ፍትሐዊነትን ማሳደግ ትኩረት ይሰጠዋል። በተጨማሪም የዘርፉን አገልግሎት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነትና ጥራት የሚያስጠብቁ ሥርዓታትን መዘርጋት፣ መከታተልና መቆጣጠር፤ ከሌሎች የዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በትብብር መሥራት፣ መደገፍ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳትና በማሸጋገር ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ከዚህም አኳያ በቀጣይ አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን በሁሉም ደረጃ ጥራት፣ ተገቢነትና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ ልዩ ትኩረት ያገኛሉ።

4. ጥራትን፣ ተደራሽነትንና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያገናዘበ መሠረተ ልማት

የልማት ዕቅዱን ራዕይ በተሟላ መልኩ ለማሳካት እና ዜጎችን በዘላቂነት ከልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ጥራት ያለው፣ ተደራሽ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያገናዘበ የመሠረተ ልማት ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ትኩረት

ከተሰጣቸው ቁልፍ መስኮች መካከል የትራንስፖርት መሠረተ ልማት፣ የኢነርጂ መሠረተ ልማትና የመስኖና የውኃ መሠረተ ልማት እና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የትራንስፖርት መሠረተ ልማት፡- በክልላችን የመንገድ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት መንግሥት ከፍተኛ ትኩረትና ቅድሚያ በመስጠት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ምክንያቱም መንገድ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደ ደም ሥር የሚቆጠር መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። በዚህም ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ በክልሉ መንገዶች ጠቅላላ ርዝመት በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ተችሏል። ሆኖም ከክልሉ የቆዳ ስፋት አንጻር ሲታይ ያለው የመንገድ አውታር በቂ ካለመሆኑም በላይ ተደራሽነቱም ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም የመንገድ አውታር በቂ አለመሆኑንና ተጨማሪ መንገድ በስፋት መሠራት እንዳለበት ያመለክታል።

በትራንስፖርት መሠረተ ልማት ረገድ ማነቆ ከሆኑት መካከል ግንባታው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑና እንዲሁም የማስፈጸም አቅም ውሱንነት በዋንኛነት ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም በግንባታው ሂደት የሚያጋጥሙ የወሰን ማስከበር፣ የካሣ ክፍያና የመሳሰሉት ችግሮች በመሠረተ ልማቱ ግንባታ ፍጥነትና ወጪ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይታወቃል። በተለይም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያስኬዱ የገጠር መንገዶች አማካይነት ከወረዳዎች ጋር ለማገናኘት ታቅዶ የተጀመረ ቢሆንም በፋይናንስ እጥረት፣ ተገቢውን ቅድሚያ ባለማግኘቱ እና በአጠቃላይም በማስፈጸም አቅም ውሱንነት ምክንያት አፈጻጸሙ እጅግ ደካማ ሆኖ ቆይቷል። በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ዘላቂነትና ፍትኃዊነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን ከፍተኛ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ከወዲሁ ታሳቢ ያደረገ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ ማፋጠን፣ የነባር መንገዶችን እንክብካቤና ወቅታዊ ጥገና ማጠናከር፣ እንዲሁም የመሠረተ ልማቱን ጥራት፣ ፍትኃዊነትና ተደራሽነት ማረጋገጥ የዘርፉ ቀዳሚ ተግባራት መሆኑና በቀጣይ በትኩረት የሚሰራ ተግባር ነዉ።

የኢነርጂ መሠረተ ልማት፡- በክልላችን ብሎም በሃገራችን እየተካሄደ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ የኢነርጂ ፍላጎት በፍጥነት እየጨመረ መጥቷል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገትም የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። የኢነርጂ መሠረተ ልማት ከሌሎች ልማቶች ቀድሞ መገኘት ያለበት፣ ሌሎች የልማት ሥራዎችን የሚያነቃቃና የሚስብ መሠረተ ልማት በመሆኑ በቂና አስተማማኝ የሆነ የኢነርጂ መሠረተ ልማት አቅርቦት ለዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ስለ ሀገራዊ ልማት ሲታሰብ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ክልላችን ከተለያዩ ምንጮች ለኢነርጂ ማመንጫ ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ እምቅ ሀብት ያላት ሲሆን እስከ አሁን በሥራ ላይ የዋለው እጅግ አነስተኛው ክፍል ነው።

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ በኢነርጂ ዘርፍ ያለው ሁኔታ ሲታይ ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት የኃይልአቅርቦትን በፍጥነት ለማሳደግና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ በፋይናንስ እጥረት፣ በሰለጠነና በሥነ ምግባር የታነፀ የሰው ኃይል እጥረትና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት በዕቅድ የተያዙ የኢነርጂ ምንጮች በወቅቱ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ታይተዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በቂና ጥራት ያለው የኃይል አገልግሎት ለማቅረብ ያለመቻል ችግሮች (ለምሳሌ የኃይል አቅርቦት መቆራረጥ እንዲሁም ከፍተኛ ብክነት) ሲያጋጥሙ ከመስተዋሉም በላይ በአገልግሎቱ ዝቅተኛ ተደራሽነትና ኢፍትኃዊነት ይንፀባረቅበታል። በልማት ዕቅዱ ዘመን የኢነርጂ መሠረተ ልማት ዋና ትኩረት ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያስፈልገውን መሠረተ ልማት በመገንባት ጥራት ያለው የኃይል አገልግሎት በወቅቱና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀርብ ይደረጋል።

የመስኖና ውኃ መሠረተ ልማት፡- የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የመስኖ ልማትን በተመለከተ ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በቀጣይ የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ እንዲሁም ለሌሎች ዘርፎች በበቂ ሁኔታ ግብዓት በሚሆን ደረጃ ለማድረስ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታን በማካሄድ የመስኖ ልማትን ማስፋፋትና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል። የመሠረተ ልማት አቅርቦትና ዝርጋታ በራሳቸው የሚኖራቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በአካባቢዎች ላይ ያለውን እምቅ የመልማት አቅም በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ለአካባቢውና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የሚኖረውን ፋይዳ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸውል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመት የሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶች የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ እና የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራርን እውን ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ለሁሉም ዜጎች እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ተቋማትና ለእንስሳት ለማዳረስ የመጠጥ ውኃ መሠረተ ልማት ግንባታ የሚካሄድ ይሆናል። ለዚህም የንጹህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሥራ ማስፋፋት፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ መሠረተ ልማቶች ዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ የታዳሽ ኃይል አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፣ የከተሞች ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ላይ ትኩረት ተሠጥቶ ይሠራል። በተጨማሪም በሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የንጹህ

የመጠጥ ውኃ፣ የሳኒቴሽንና ሃይጅን አቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት በማከናወንና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ዞኖችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ወጥና ዘላቂ ድጋፍ በማድረግ ይሠራል።

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፡- ግቦችን በአግባቡ የሚለካ የመለኪያ ውስንነት፣ ስራ ክፍሎች ዕቅዳቸውን ከተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር በትኩረት ያለማናበብ ችግር፣ እንደ ቴክኖሎጂ ተቋምነቱ የውስጥ አሰራሮች በሲስተም የታገዙ አለመሆንና ከጊዜው ጋር የሚራመድ እንዲሁም ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችሉ የዘመነ የአሰራር ስርአት በየዘርፉ አለመኖር፤ አገልግሎት አሰጣጡ በተቀመጠው በስታንዳርድ መሰረት የሚሰጡ አለመሆናቸው፤ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ቅድመ ሁኔታዎችን ኦን ላይን የማሳወቅ ስርዓት አለመኖርና አገልግሎት አሰጣጡ በራሱ አውቶሜትድ አለመሆናቸው፤ አገልግሎት ላይ የዋለ የኢኮቴ መሠረተ ልማት የጥራትና የብቃት ችግር ያለው መሆኑ፣ ከቴክኖሎጂዎች ፈጣን ዕድገት መለዋወጥ ጋር ተጣጥሞ አለመሄድ፤ የሳይበር ጥቃት እየጨመረ መምጣቱ በዘርፉ የታዩ ሲሆን በቀጣይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

5. ዘላቂ ከተሜነት (Sustainable Urbanization)

ክልላችን ከተሜነት በፍጥነት ከሚያድግባቸው ክልሎች ውስጥ አንዷ ናት። ሆኖም እየታየ ያለው የከተሜነት ዕድገት በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርና በምርታማነት ዕድገት የታገዘ ባለመሆኑ መልካም ዕድል ሳይሆን ስጋት ሊሆን ችሏል። የከተሞች መስፋፋት በዕቅድ ሊመራ የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ መልካም ዕድል የሚፈጥር ነው። በከተማ ልማት ዘርፍ ከተሜነትን በብቃት ለመምራት የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ አለመኖሩ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰውን የሰው ኃይል ወደ ሥራ ለማስገባት በቂ የሥራ ዕድል አለመኖርና የከተማ ፋይናንስ አቅም ውስንነት በዘርፉ የተስተዋሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

ከተሞች የሥራ ዕድልን በስፋት እንዲፈጠሩ በማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንዲሁም የብልጽግና ጉዞን ለማፋጠን ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተጨማሪም ከተሞችን ማልማት ለሥራና ለኑሮ ሳቢ በማድረግ ለመዋቅራዊ ሽግግሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከዚህ አኳያ በአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ዘመን ከዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የከተማ መሬትን ምርታማነት ለመጨመር የይዞታ ማረጋገጫ ሥርዓትን ማሻሻል፣ ለልማት የሚሆኑ የመሬት አቅርቦቶችን ማሻሻልና በመልሶ ማልማት ሂደት ዘላቂ የከተማ ልማትን ማረጋገጥ፣ ከተሞችን ከዙሪያቸው ካለ ልማት ጋር በማስተሳሰርና ከሌሎች የልማት ማዕከሎች ጋር በማቆራኘት ምርታማነትን ማሳደግ፣ የመንግስትና የግል አጋርነትን በመጠቀም የቤቶችን ዕጥረት መፍታት፣ ያልተማከለ የከተማ ልማትን ማጠናከር፣ የከተሞችን የመሠረተ ልማት ፍላጎት ማሟላት ይገኙበታል። በተጨማሪም ብቃትና የሥራ ተነሳሽነት ያለው የሰው ኃይል አቅርቦትና ቴክኖሎጂ በስፋት፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ወጪ የማቅረብና ቅንጅታዊ አሠራር የማዳበር እንዲሁም የመረጃ ልውውጥን ወደ ዲጂታል የማሳደግ ተግባራት ከቀጣይ የትኩረት መስከች ውስጥ ናቸው።

6. ሰላም፣ ፍትህና አካታች ሥርዓታት

ባለፉት ዓመታት በክልላችን የሰላም፣ የፍትሕ፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደር እና የአካታችነት ችግሮች ማጋጠማቸው ይታወቃል። የፍትሕ ዘርፍ ከመንግስት የለውጥ ፍጥነትና ከህዝቡ መሰረታዊ የፍትሕ እና በእኩል የመጠቀም ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አንጻር ሲመዘን ገና ጅምር ላይ መሆኑ፤ የዜጎች በመብትና ግዴታ፣ በነጻነትና ሃላፊነት መሃል ያለውን ሚዛን አለመጠበቅና የመብት ጥያቄን በኃይል ለማስፈፀም የሚያደርጉት የተደራጁ የሕገ ወጥ ተግባራትና የሥርዓት አልበኝነት አዝማሚያዎች መታየታቸው፤ በተለያዩ የክልሉ አከባቢዎች የተከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶችና በዚህ ውስጥ የተሳተፉ ወንጀል ፈፃሚዎችን በተሟላ መልኩ ለሕግ አለማቅረብ በፍትሕ ሥርዓት እና የሰላም ሁኔታ ላይ የተወሰኑ ክፍተቶችን ፈጥረው ቆይተዋል።

በቀጣይ አስር ዓመት ፍትሐዊ፣ ተደራሽ እና ጠንካራ የፍትሕ አገልግሎትን በማስፈን የኢኮኖሚ ዕድገቱንና ልማቱን ማገዝ፣ ብቃት ያለው የህዝብ አገልግሎት ሥርዓትን መገንባት፣ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ሥራ አመራር ሥርዓትን ማሻሻል፣ ክልላዊ ጉዳዮችንና ጥቅሞችን አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በብዙሃን ተሳትፎ መለየትና የጋራ መግባባትን መፍጠር፣ የህዝብ ሰራተኞች እሴት ግንባታና ሥነ ምግባርን ማሻሻል እንዲሁም የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናሉ። በዚህም ለኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ ሁኔታን ለመፍጠር እንቅፋት የሆኑ የሰላም፣ የሕግ፣ የፍትህ፣ የፖሊሲና የተቋም አሠራሮችን በማሻሻል ክልላችን ለንግድ ምቹ ከባቢ ደረጃ ማሻሻልና በዚያውም ሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ይሠራል።

ምዕራፍ ሁለት

የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ

2.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

- **የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ**

በክልሉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ በተሰሩ ስራዎች ክልሉ ባለፉት አምስት ዓመታት 9.3 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከዚህም በመነሳት በሚቀጥሉት አስር ዓመታት (ከ2013 እስከ 2022) የክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ የ10.4 በመቶ ዕድገት እንዲመዘገብ ለማስቻል ይሰራል። የኢኮኖሚ ዕድገቱ በክፍላተ ኢኮኖሚ ሲታይ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ በየዓመቱ የ5.8፣ የ18.7 እና የ8.6 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግቡ ታቅዷል።

ሠንጠረዥ 5፡ የዘርፎች የዕድገት ምጣኔ (ከ2013-2022 በጀት ዓመት)

የኢኮኖሚ ዘርፎች	አፈጻጸም		ግብ
	2003-07	2008-12 አማካይ	2913-22 አማካይ
ግብርናና ተዛማጅ	8.7	9.4	5.8
ኢንዱስትሪ	14.4	8.9	18.7
አምራች ኢንዱስትሪ	20.6	8.5	19.2
አገልግሎት	11.3	9.4	8.6
ክልላዊ ጠቅላላ ምርት	**10.4**	**9.3**	**10.4**

- **ስራ ዕድል ፈጠራና ድህነት ቅነሳ**

የድህነት ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7 በመቶ መቀነስን፤ የተገነቡና ሊገነቡ የታሰቡ ጥቅል ሀገራዊ አቅሞችን፤ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲሁም በእያንዳንዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ያሉ አቅሞችንና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ የምርታማነት መነሻዎች ታሳቢ በማድረግ ኢኮኖሚው ከ2013 እስከ 2022 ባሉት አስር ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ በ10.4 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል።

በከተሞች የስራ ዕድል በመፍጠር የስራ አጥነቱን ምጣኔ አሁን ካለበት 16.1% በየዓመቱ 1% ለመቀነስ የሚያስችል ስራ በመስራት ለ2,572,310 ስራ ፈላጊ ዜጎች በቋሚና በጊዜያዊ የስራ ዕድል ይፈጠራል። ይህም በኢንዱስትሪ (50%) በከተማ ግብርና (13%) እና በአገልግሎት (37%) ድርሻ እንዲኖራቸው ይደረጋል። የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራና ልማት አንጻር በስትራቴጅክ ዕቅድ ዘመኑ ለ2,606,280 የስራ ፈላጊ ዜጎችን በግብርና እና ከግብርና ውጪ ባሉ ዘርፎች የስራ

ዕድል የሚፈጠር ይሆናል። በአጠቃላይ በክልላችን በከተማና በገጠር ለ5,178,590 ስራ ፈላጊ ዜጎች በቋሚና በጊዜያዊ የስራ ዕድል ይፈጠራል።

በክልሉ ከድህነት ወለል በታች የሚገኘውን ሕዝብ በ2012 ከሚገመተው 19 በመቶ በ2022 ወደ 7 በመቶ ለመቀነስ የሚሰራ ይሆናል።

2.2. የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 58.8 በመቶ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 42.0 በመቶ እንደሚቀንስ ታቅዷል። በአንጻሩ በዚሁ ጊዜ የኢንዱስትሪ ድርሻ ከ17.8 በመቶ ወደ 36.5 በመቶ ሲያድግ በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ ከ23.4 በመቶ ወደ 21.5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል። ከኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተናጠል ሲታይ ከጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 4.2 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6.6 በመቶ እንደሚያድግ ታቅዷል።

ሠንጠረዥ 6፡ መዋቅራዊ ለውጥ

	የኢኮኖሚ ዘርፎች	አፈጻጸም		ግብ
		2008	2012	2022
1	ግብርና	58.5	58.8	**42.0**
2	ኢንዱስትሪ	18.2	17.8	**36.5**
	አምራች ኢንዱስትሪ	*4.3*	*4.2*	***6.6***
3	አገልግሎት	23.3	23.4	**21.5**

2.3 የፊስካል ፖሊሲ (ገቢና ወጪ)

ለፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የፊስካል ማዕቀፍ ትልቅ ትርጉም እንዳለዉ ይታወቃል። ባለፉት ዓመታት ተፈጻሚ የሆነዉ የፊስካል ማዕቀፍ ያሉትን የገቢ ዕቅዶችን በዉጤታማነት ከማስተዳደር፣ ገቢን ከማሳደግ እና የወጪ አመዳደብ በካፒታል እና ዕድገት ተኮር ዘርፎች ድህነትን በመዋጋት ረገድ ቁልፍ በሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነበር። የፊስካል ማዕቀፉ ዓላማ የክልሉን የወጪ በጀትን በክልሉ ዉስጥ በሚሰበሰበዉ ገቢ በአጭር ጊዜ መሸፈን የሚከብድ ቢሆንም ከዓመት ወደ

ዓመት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ፣ የፌዴራል ድጎማ እና የዉጭ ብድርና እርዳታ በሂደት በቅናሽ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ የክልሉ መንግስት ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት። ሆኖም ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና ከዓመት ዓመት በጀትን ከማሳደግ አንጻር ፈታኝ እየሆነ የሚሄድ በመሆኑ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል። ይህም በየፋይናንስ ምንጩ በክልሉ የሚቀጥሉት የ10 ዓመታት ፊስካል ማዕቀፍ አማካይ ዕድገት ትንበያዉ ያሳያል።

በልማት ዕቅዱ ዘመን የመንግስት ገቢና ወጪን ጤናማና ዘላቂ ለማድረግ ጠቅላላ የክልሉን ውስጥ ገቢን የሚያሳድግ አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት በታክስ ፖሊሲና ሕጎች ዙሪያ ማሻሻያ በማካሄድ፤ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን በማዘመን፤ የታክስ መዋቅሩን በማሻሻልና ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴን በመከላከል ገቢን የማሳድግ ስራዎች ይሰራሉ።

የክልሉን የመደበኛ ገቢ የመሰብሰብ አቅም አሁን ካለበት 8.666 ቢሊዮን ብር ወደ 33.592 ቢሊዮን ብር እና የማዘጋጃ ቤት ገቢን ከ1.442 ቢሊዮን ብር ወደ 4.866 ቢሊዮን ብር በማሳደግ የክልሉ አጠቃላይ ገቢ በ2012 ዓ.ም 10.108 ቢሊዮን ብር የነበረውን በ2022 ዓ.ም ወደ 38.458 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ታቅዷል።

ክልላዊ ገቢ ለክልላዊ ምርት ያለው ጥምርታ አሁን ካለበት ከ6.10 በመቶኛ በ2022 ዓ.ም ወደ 11.66 በመቶ እንዲያድግ የሚደረግ ሲሆን ክልላዊ ገቢ ለወጪ ያለው ድርሻ ከ25.21 በመቶኛ ወደ 34.32 በመቶኛ ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል።

ከመንግስት በጀት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ የበጀት ዕድገት በአማካይ በየዓመቱ 21 በመቶ እንዲያድግ ለማድረግ ግብ የተጣለ ሲሆን ጠቅላላ በጀት (ዕርዳታን ጨምሮ) በ2012 ከነበረበት ብር 40,056.9 (ቢልዮን) በቀጣይ 10 ዓመት መሪ ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (በ2022) ወደ ብር 226,276.7 (ቢሊዮን) ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

ከመንግስት ወጪ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመሠረተ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሕና የዘላቂ ሰላም ግንባታ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 214,962.8 (ቢሊዮን) የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ መደበኛ ወጪ ብር 144,833.1 (ቢሊዮን) እና የካፒታል ወጪ ብር 70,129.7 (ቢሊዮን) ይሆናል።

ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ለማስወገድ የሚረዱ የመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወጪ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 132,371.9 (ቢሊዮን) የሚደርስ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ 62 በመቶ ድርሻ እንደሚይዝ ትንበያዉ ያሳያል። ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ድርሻ በመቶኛ ማየት ይቻላል።

ምዕራፍ ሶስት

የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

3.1. የግብርና ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፡- የክልላችን የእርሻ ምርት በዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ለምርታማነት ዝቅተኛነት የተጋለጠ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የምርት መጠን ከዝናብ መጠን መለያየት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ልዩነቶች ይታዩበታል። ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንፎርሜሽን ለማምጣት በቂ ስላልሆነ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለበት። ይህም ያሉንን የምርት ወቅቶች ከ3 እና 4 ጊዜ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ ለኢንዱስትሪና ለውጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያመጣል። የምንከተለው የመስኖ ልማት አካሄድ የጥቃቅንና የአነስተኛ መስኖ ልማት ሲሆን በአርሶአደር ደረጃ የሚከናወን ይሆናል። በአጠቃላይ ለመስኖ ሥራ ትኩረት በመስጠት በቤተሰብ ደረጃ የውሃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋጽዖ ያደርጋል።
- **ክላስተር የተከተለ (Commodity based commercialization cluster approach) የአመራረት ዘይቤ ማጠናከር፡-** በክልላችን ልዩ ልዩ ሥነ ምህዳር ዞኖች መኖራቸው በአንድ ሥነ ምህዳር ዞን በላቀ ደረጃ ሊመረት የሚችለው ምርት በሌላ አካባቢ በፍጹም ሊመረት የማይችል ቢመረትም የላቀ ውጤት ሊያስገኝ የማይችል ይሆናል። በመሆኑም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች እንደየአካባቢያቸው ሥነ ምህዳር የላቀ ውጤት በሚያስገኝላቸው የግብርና ምርት ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግና ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂ ፓኬጅ በመጠቀም የየአካባቢው ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል። በስፔሻላይዜሽን ወይም በክላስተር አሰራር አ/አደሩ ወደ ኮሜርሻላይዜሽን ወይም በገበያ የተመራና ገበያ በሚፈለገው standard መጠን እንዲያመርት ይደረጋል። ስለሆነም ይህን ለማሳካት አሰራርና አደራጃጀቶችን ማስተካከል የዚሁ commodity-based commercialization cluster approach አካል ይሆናል ነው። በክላስተር የሚመረጠው ምርት የገቢ ምርት የሚተካ መሆኑ (import substitution) እንዲሁም የገበያ ሰብል አምርቶ ወደ ዓለም ገበያ ለመግባት በሚያስችል ጥራት ከፍተኛ ምርታማነት ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ይጠናከራል።
- **ሆርቲካልቸር ልማት፡-** የሆርቲካልቸር ልማት ዋና ምሶሶዎች የሚሆኑት በክላስተር የተደራጁ አነስተኛ አርሶ አደሮችና ትላልቅ የግል አምራቾች ይሆናሉ ተብለው ይጠበቃል። በዘርፉ የምርት ስፔሺያላዜሽን ቢበረታታም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን መሰረተ ያደረገና የዋጋ ግሽበትን የሚያረጋጋ ስትራቴጂ የምንከተል ይሆናል። የሆርቲካልቸር ዋና ስትራቴጂ የሚሆነው ግብዓት አቅርቦት ስርዓቱን ማዘመን ሲሆን ይህም ማለት ገበያ ተኮር የሆነና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟሉና ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዝርያዎችን ማፍለቅና ማሰራጨት እና

የግሉ ዘርፍ ተሳታፊነቱን አሁን ካለበት ማስፋፋት፣ የዘመናዊ ነርሰሪ ልማት ስትራቲጂያዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማጠናከር፣ የግብይት ማዕከላትን ለአርሶ አደሩ ቅርበት ባለባቸው አከባቢዎች ማደራጀት፣ የኮልድ ቼይን መሰረተ ልማት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማመቻቸት ትኩረት ይሰጥበታል።

- **የከተማ ግብርና ስራዎችን ማጠናከር፡-** የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥና በዙሪያው በአነስተኛ ቦታ ለምግብነትና ለሌሎች ጠቀሜታዎች ሊውሉ የሚችሉ እፅዋት ልማት እና እንስሳት እርባታ ስራን በማስፋፋት ምርት ማምረት፤ ምርት ውጤቶችን የማቀነባበር እና ለተጠቃሚው የማቅረብ ስራዎች ይሰራል። በተለይም በቤተሰብ ደረጃ በአነስተኛ ከሚከናወኑ የማምረትና ማቀነባበር/ እሴት ጭመራ እሰከ ሰፋፊ የማምረትና ማቀነባበር ያስፈልጋል።
- **የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፡-** የሜካናይዜሽን አግልግሎት ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ለክልላችን መልከዓ ምድርና አግሮ ኢኮሎጂ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነትን ለአርሶ/አርብቶ አደር በማረጋገጥና አጠቃቀም ላይ የተመሰረተና የአርሶ አደሩን አቅም ያገናዘበ ሀገር-በቀል የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ፣ ማኑፋክቸሪንግና ስርጭት ስርዓት በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ አደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል። ዘርፉ የሚጠቀማቸውን ማናቸውም የቴክኖሎጂ ግብዓትና ማሽነሪዎች ከግብር ነጻ በማድረግና የሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ስርዓት በመገንባት ግብርናን ለማዘመን በትኩረት ይሰራል። በዚህም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለማቋቋም ከፍተኛ ዕገዛ ይኖረዋል። በተጨማሪም ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና ለመሳብ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዋና ምሰሶ የግሉ ዘርፍ መሆኑ ቢታወቅም የግብርና ዘርፍ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የቁጥጥርና ፍተሻ እንዲሁም ክትትል ሥራዎችን ይሰራል። የግሉን ዘርፍ ለማሳተፍ በሚደረገው ጥረት መንግስት የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን ይጠቀማል። በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮችን የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው በማገዝ ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስተርነት የማሳደግ ሥራ በልማት ዕቅዱ ዘመን በስፋት ይሰራል።
- **የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ፡-** በሁሉም ደረጃ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን በተለይም የማዳበሪያ መጠንና ጥምርታ እንዲሁም የሰብል ምርጥ ዘር አቀባበልና አፈጻጸም በሚፈለገው መጠን ለውጥ ያለመምጣቱ ሲታይ ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ለማሻሻል የቴክኖሎጂ አቀባበልና አጠቃቀም ለማሻሻል በተደራጀ መልኩ የግብርና አካላት ተቀናጅተው የአርሶ አደሩ ገቢ እንዲያድግ ትርጉም ያለው ሥራ መሰራት እንደሚገባ አቅጣጫ ተይዟል።
- **የቅድመና ድህረ ምርት አያያዝ እና አጠቃቀም ማሻሻል፡-** በቅድመና ድህረ ምርት አያያዝ በተመለከተ በተለይም ትራክተር፣ ምርት ማጨጃ፣ መውቂያ፣ ማከማቻ፣ ወዘተ... የአ/አደሩ ፍላጎት እየጨመረ የመጣ

ቢሆንም የሚመለከተው ክፍል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከሚሰሩ ውስን ስራዎች ባሻገር በድህረ ምርት ላይ በቂ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አይደለም። በቅድመና ድህረ ምርት የቴክኖሎጂ አቅርቦት በበቂ አለመኖር እና አለመስፋፋት የተነሳ በብዙ ድካም የተመረተውን የሰብል ምርት አርሶ አደሩ ሳይጠቀምበት ሲባክን ይታያል፡ ፡ ሰለዚህ በቀጣይ አስር ዓመት በቂ የሆነ ማረሻ ትራክተር፣ የማጨጃና የመውቂያ መሳሪያዎችንና በክልሉ በተቋቋሙ የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላት የሚወጡ አነሰተኛ ማሽነሪዎች አርሶ አደሩን አቅምና ሥነ ምህዳርን መሰረት በማድረግ የማቅረብ ሥራ በተለየ ሁኔታ በቅንጅት በመስራት መፍታት እንደ አቅጣጫ ተይዟል።

- **የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት፣ መኖ ልማትና ጤና ማሻሻል፡-** የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ስርዓትን፣ ዝርያን ከማሻሻልና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል። በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ሲሆኑ የውጪ ንግዳችንን የሚያነቃቁና ወደ አዳዲስ ገበያዎች እንድንገባ የሚያደርጉ ዘመናዊ የምርት ዱካ ስርዓት መተግበር፣ እንዲሁም የአርሶ/አርብቶ አደር አካባቢዎችን ከበሽታዎች የፀዱ ማድረግና ህገወጥ ንግድን ትርጉም ባለው መልኩ መቆጣጠር በሰፊው የሚሰራባቸው ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የእሴት ጭመራን ለማቀላጠፍ ከኤክስፖርት ቄራዎች ጋር የአርቢዎችን የምርት-ግብዓት ግንኙነቶችን ማጠናከር ትኩረት ይደረግበታል።
- **ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት ማካሄድ፡-** በክልላችን እየተስፋፉ የሚገኙ ዋና ዋና ተባዮች (የበረሃ አንበጣ፣ የአሜሪካን መጤ ተምች፣ የበቆሎ ገዳይ የቫይረስ በሽታ፣ የማንጎ ነጭ ስኬል፣ የቡና ፣ የድንች፣ ዝንጅብልና እንሰት አጠውላጊ የባክቴሪያ በሽታዎች፤ የስንዴ ዋግ፣ መጤ ወራሪ አረሞችና ሌሎች) ከምርምር በሚገኙ አዳዲስና ነባር የተቀናጀ ተባይ መከላከል ቴክኖለጂዎችን በመጠቀም የመከላከል ሥራ እንዲስፋፋ ይደረጋል። የተባይ ክስተት ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሠራር ሥርዓት የመዘርጋት እና በክልላችን የተስፋፉትን ወራሪ መጤ አረሞችን ለመከላከል የሥነ-ሕይወታዊ የተባይ መከላከያ ዘዴን (Biological Control) ትኩረት ሰጥቶ ማስፋትና ሌሎች የተባይ መከላከያ ዘዴዎችን በመጠቀም በተባዮቹ የሚደርሰውን የምርት ብክነት ለመቀነስ በስፋት ይሰራል። የአየር ንብረት ለውጥ በእንስሳት ምርትና ምርታማነት ላይ በሚያስከትለው ተፅእኖ የተነሳ በአርሶ/አርብቶ አደሮች ህይወት ላይ የጎላ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝና የእድገት ማነቆ በመሆኑ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ከማካሄድ አንፃር የአመንዣኪ እንስሳት (Ruminant animal) የሚለቁትን የሙቀት አማቂ ጋዝ (Methane Gas) ለመቀነስ ከተቻለም ለማስወገድ የሚያስችል በጥራት ላይ የተመረኮዘ ዘመናዊ የእንስሳት የአረባብ ዘዴ በመጠቀም ማለትም የዝርያ ማሻሻል ስራ ላይ በማተኮር የእንስሳት ቁጥር መቀነስ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ በምርትና ምርታማነት ላይ ከሚያመጣው ከፍተኛ ጠቀሜታ በተጨማሪ ወደ አየር የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ጥቅም የሚያስገኝ በመሆኑ በትኩረት ይሰራል።

- **የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ማጠናከር፡-** የግብርና ኤክስቴንሽ አገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓቱ ከአመራረት ተኮር (Production oriented) ወደ ገበያ ተኮር (Market oriented) የአመራረት ዘይቤ እንዲሸጋገር ለማድረግ ለአርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር የሚሰጠውን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓት ከመንግስት በተጨማሪ ሌሎች የልማት ተዋንያንን (ማህበራት፣ የግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ያሳተፈ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- **የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት (አማማ) አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ማሻሻል፡- አማማ** የሚጠበቅባቸውን ተግባር መወጣት እንዲችሉ እንደ ሌሎች የመንግስት ተቋማት የራሳቸው የሆነ ዓመታዊ የመደበኛ ሥራ ማስኬጃና ካፒታል በጀት (Block grant or Seed money) እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የተገኘውን ሀብት በአግባቡ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ነሐሴ 2010 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሴክተር አውቆት የማዕከላትን ገንዘብ፣ ንብረትና ሠነድ እንዲያስተዳድርና እንዲቆጣጠር ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡
- **በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፡-** ባለሃብቱ በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርት፣ በግብይት መሰረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፍና ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉ ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከሀገር በቀልና አለማቀፍ ባለሃብቶች ጋር በጥምረት የሚሰራ ይሆናል። በተጨማሪም ባለሃብቱን የእሴት ጭመራ ስራዎች ላይ ለማሳተፍ በተለይም አግሮ ኢንዱስትሪዎችን መሰረት ያደረገ የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር ስራ የሚሰራ ይሆናል።
- **የሥራ ዕድል መፍጠር፡-** በገጠር የሚኖሩ ስራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሃዊ፣ ዘላቂና ውጤታማ የስራ እድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በመሆን በ2022 ለሃገር እድገት እና ትራንስፎርሜሽን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡
- **ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፡-** በዘርፉ የማስፈፀም አቅምና ክህሎት ለማሳደግ በሀገር ደረጃ ስር-ነቀል የሰው ሃብት ሪፎርም እየተሰራ ይገኛል። ይህ ስራ የአገልግሎት ጥራትና ጊዜን የሚያፋጥን እና የውሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፍ ነው። ይህ ጅማሮ በክልል፣ በዞንና በወረዳ የማውረድ ስራ የሚሰራ ሲሆን የተቋማዊ መሰተጋብሩም ጎን ለጎን እንዲቀናጅ ይደረጋል። በየደረጃው የሚገኙ ግብርና ባለሙያዎች በአመለካከት፣ በዕውቀትና በክህሎት የሚታይባቸውን የአቅም ውስንነት ለመቅረፍ ተከታታይነት ያለውና ችግር ፈቺ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ ጥቅል ዓላማዎች ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፣ ለኢኮኖሚዉ መዋቅራዊ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ በተለይም ግብርናን በማዘመን የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፍላጎትን ማሟላት፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለውጪ ንግድ በቂ ምርት ማቅረብ፣ እሴት መጨመርና በገጠር በቂ የሥራ ዕድል መፍጠር ናቸው።
- እነዚህን ጥቅል ዓላማዎች ዕውን ለማድረግም ዋና ዋና ስትራቴጂክ ዓላማዎች የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ገበያ ተኮር የእንሰሳትና የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ እንዲሁም ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ማሻሻል ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- **የሰብል ምርትና ምርታማትን ማሳደግ፡-** በሁሉም የአመራረት ስርዓቶችና የሰብል ዓይነቶች የሰብል ምርትን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት ከ234.58 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 466.76 ሚሊዮን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ 10% ዕድገት) ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን የአዝርዕት ምርትን ከ38.4 ወደ 54.5 ሚሊዮን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ 4.19% ዕድገት) ፣ የሆርቲካልቸር ምርትን ከ196.14 ወደ 394.7 ሚሊዮን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ 10.1% ዕድገት) ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።
- **የአዝርዕት ሰብል ምርትና ምርታማነት፡-** ከአመራረት ሥርዓቶች በአነስተኛ ይዞታ የሚመረተው ምርት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፣ የአዝርዕት ምርት በመኽር ከ19.7 ሚሊየን ኩንታል ወደ 28.78 ሚሊየን ኩንታል እና በበልግ ከ18.7 ሚሊየን ኩንታል ወደ 25.73 25.73 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በአስር ዓመቱ መጨረሻ ከተገኘው ከአጠቃላይ ምርት መኽር የ52.79 በመቶ እና በልግ የ47.2 በመቶ የምርት ድርሻ ይኖራቸዋል።
- ከአጠቃላይ የአዝዕርት ሰብሎች የአገዳ ሰብል ምርትን ከ18,330,927 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ3.48% በማሳደግ ወደ 24,714,976 ኩ/ል፣ የብርዕ ሰብል ምርት ከ13,714,609 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ 5.75% በማሳደግ ወደ 21,597,871 ኩ/ል፣ የጥራጥሬ ሰብል ምርት ከ6,081,292 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ2.66% በማሳደግ ወደ 7,700,792 ኩ/ል፣ የቅባት ሰብል ምርት ከ270,427 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ6.32% በማሳደግ ወደ 441,460 ኩ/ል እና የጮረት ሰብል ምርት ከ39,894 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ8.54% በማሳደግ ወደ 73,965 ኩ/ል ለማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ ግብ ተይዟል።
- በክላስተር/ኩታ ገጠም (commodity based commercialization cluster) በሁሉም አመራረት ሰርዓቶች በልዩ ትኩረት የሚመረቱ ሰብሎች ሲሆኑ በሁሉም አመራረት ሰርዓቶች (በልግና መኽር) በአዝርዕት ሰብሎች

አሁን ከሚመረተው 12,977,591 ኩ/ል ምርት በየዓመቱ በ 31.2% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ 40,563,969 ኩ/ል ለማድረስና የመሬት ሽፋኑን ከነበረበት 390,161 ሄ/ር በ2022 ዓ/ም ወደ 1.3 ሚሊዬን ሄ/ር መሬት በክላስተር ሰብልችን ለመሸፈን ታቅዷል። በዚህም (Zonal/Special Woreda Crop Commodities specialization) በማድረስ የሰንዴ ፣የጤፍ፣ የገብስ፣ የበቆሎ፣ የፍራፍሬ ፣ የቦሎቄ ፣የሥራሥር አምራች ክላስተር አከባቢዎች የሚፈጠሩ ይሆናሉ።

- **ከምርታማነት አንጻር** የአገዳ ሰብል ከ47 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 77 ኩ/ል በሄ/ር፣ የብርዕ ሰብሎች ከ25 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 40ኩ/ል በሄ/ር፣ የጥራጥሬ ሰብል ከ15 ኩ/ል /ሄ/ር ወደ 23 ኩ/ል በሄ/ር፣ የቅባት ሰብሎች ከ7 ኩ/ል ሄ/ር ወደ 12 ኩ/ል በሄ/ር፣ የጭረት ሰብሎች 19 ኩ/ል ሄ/ር ወደ 30 ኩ/ል በሄ/ር ምርታማነት ለማድረስ ታቅዷል።
- የተለየ ትኩረት ከሚሹ አዝርዕት ሰብል ውስጥ አነስተኛ ይዞታ እርሻ በመስኖ የሚመረተው የስንዴ ምርትን ከ450 ኩ/ል ወደ 2 ሚሊዬን ከንታል፣ ጥጥ ምርትን ከ0.040 ሚሊየን ኩንታል ወደ 0.073 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ በዕቅድ ተይዟል።
- **የሆርቲካልቸር ምርትና ምርታማነት፦** የአነስተኛ ይዞታ አርሶአደሮች የሆርቲከልቸር ሰብሎች አጠቃላይ ምርት አንጻር የአትክልት ሰብል ምርት መስኖን ጨምሮ ከ59,556,218 ኩ/ል ወደ 103,104,177 ኩ/ል፣ በፍራፍሬ ሰብል ምርት መስኖን ጨምሮ ከ24,466,594 ኩ/ል ወደ 41,644,131 ኩ/ል፣ የስራስር ሰብል ምርት ከ77,314,856 ኩ/ል ወደ 132,165,549 ኩ/ል እና በእንሰት ሰብል ምርት ከ33,251,243 ኩ/ል ወደ 41,580,591 እና ሌሎች የመስኖ ሰብሎች በመነሻ ዓመት (2012) ከነበረበት 400,830 ኩ/ል ወደ 784,007 ኩ/ል በማድረስ አጠቃላይ የሆርቲካልቸር ሰብሎች መስኖን ጨምሮ ምርቱን ከ 194,989,741 ኩ/ል ወደ 319,278,456 ኩ/ል ለማድረስ ዒላማ ተይዟል።
- የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርታማነት አንጻር አትክልት ከ180 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 306 ኩ/ል በሄ/ር፣ ማሳደግ፣ ስራስር ሰብሎች ከ238 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 389 ኩ/ል በሄ/ር፣ ፍራፍሬ ሰብሎች ከ258 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 444 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ይሰራል።
- **አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን የቴክኖሎጂ ማፍለቂያና ማሸጋገሪያ ማድረግ፦- በ**10 ዓመታት ውስጥ ግንባታ በሌላቸው 100 ቀበሌያት በሁሉም ግንባታ ማካሄድና ወደ ጀማሪ ደረጃ በማሸጋገር ሙሉ በሙሉ ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ይደረጋል፣ በ Pre Basic ደረጃ ከሚገኙ 1,008 አማማዎች በየዓመቱ 12% ወደ መሠረታዊ ደረጃ በማሸጋገር በ2022 ዓም መጨረሻ ሽግግሩን 100% ወደ Basic ደረጃ ማድረስ፤ በBasic ደረጃ የሚገኙ 944 አማማዎች በየዓመቱ 112(12%) አማማዎችን ወደ መካከለኛ ደረጃ በማሸጋገር በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ሽግግሩን 100% ወደ Intermediate ደረጃ ማድረስ፤ በIntermediate ደረጃ የሚገኙ 338 አማማዎችን በየዓመቱ 40(12%) አማማዎችን ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማሸጋገር በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ሽግግሩን 100% ወደ Advance ደረጃ በማድረስ የአርሶ አደሩ የሜካናይዜሽን አጠቃቀም ምርታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እና የተሻሻለ

የአግሮኖሚ ተግባራቶችን ዕውቀትና ክህሎት በመማር በሚኖርበት ሥነ ምህዳር በአንድ ሰብል ኮሜርሻላይዝድ በማድረግ ለገቢያ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

- **ቡናና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማትን ማሳደግ፡-** የአመራረት ስርዓታችን በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ላይ ያተኮረ ሆኖ በተወሰነ ደረጃ በመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎችንም የመደገፍ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን በበልግ፣ በመኸር፣ በመስኖና የተለያዩ የእርጥበት ማቆያ ዘዴዎችን በመተግበር የቡናና የቅመማ ቅመም ሰብሎች እንዲለሙ ይደረጋል። የቡና ሰብል ምርት ከ172,077.6 ቶን ወደ 415,675.2 ቶን ለማሳደግ እና ምርታማነትን ከ8.5 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 11.8 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ይሰራል።
- በዋና ዋና እና በአነስተኛ ቅመማ ቅመም ሰብሎች ምርት 463,270.81 ቶን ወደ 880,099.62 ቶን ለማድረስ እና ምርታማነትን ከ45.69 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 67.35 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ እቅድ ተይዟል።
- **የተሻሻለ ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ፡-** የግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥርና ኪረንቲን አገልግሎት በማጠናከር የምርጥ ዘር አቅርቦትን ከ109,287 ኩ/ል በየምርት ዘመኑ 10.67 በመቶ በማሳደግ ወደ 335,018 ኩ/ል ለማድረስ እና የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት ከ1,562,842 ኩንታል በየዓመቱ በአማካይ 9.8 በመቶ በማሳደግ ወደ 4,219,947 ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል። የፀረ-ተባይ ኬሚካል ከ 71,874 ሊትር አቅርቦት በየዓመቱ በአማካይ 11 በመቶ በማሳደግ ወደ 170,149 ሊትር ለማቅረብ ታቀደ ሲሆን የአረም መከላከያ ኬሚካል ከ20,218 ሊትር ወደ 47,864 ሊትር፣ የበሽታ መከላከያ ኬሚካል ከ42,834 ሊትር ወደ 101,403 ሊትር እና የተባይ መከላከያ ኬሚካል ከ8,822 ሊትር ወደ 20,882 ሊትር አግሮ-ኬሚካል ለማቅረብ ታቅዷል። ከዚህ ጎን ለጎን የአፈር ጤንነትና ለምነት ለማሻሻያ የተጎዱ መሬቶችን በኖራ፣ በህያው ማዳበሪያና በአይባር ቢቢም በማከም፣ እንዲሁም እንደ ኮምፖስት ያሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና ዘላቂ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በማሻሻል የኬሚካል ማዳበሪያ ፍላጐትን ለመቀነስ መጠነ ሰፊ ጥረት ይደረጋል።
- **የኅብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ማደራጀትና ማጠናከር በተመለከተ፡-** መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች 9,302 ከነበረበት በ2022 ወደ 12,134 በማድረስ የአባላት ቁጥርም በ75% በማሳደግ 1.9 ሚሊዬን ግለሰቦችን (50 በመቶ ሴት እና 30 በመቶ ወጣቶችን) አባል ለማድረግ ይሰራል።
- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 0.517 ቢሊዮን ወደ ብር 2.356 ቢሊዮን ለማድረስ የሚሰራ ሲሆን ከዚህ ቁጠባም ኢንቨስትመንትን በማሳደግ የስራ እድል ይፈጠራል። የኅብረት ሥራ ማህበራት በአገር ውስጥ ደረጃ የግብርና ምርቶች የግብይት ተሳትፎ እና ድርሻ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 12 በመቶ ወደ 32 በመቶ ለማድረስ እና የውጭ ግብይት ድርሻ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት በመጠን 5 በመቶ ወደ 50 ከመቶ እና በገቢ ደግሞ ከ19 በመቶ ወደ 39 በመቶ በማድረስ የአባላትንና የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ ይሠራል።

- የግብርና ምርቶችን በጥሬ ከመገበያየት ባሻገር የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ውጤታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ ዓይነት ነባርና አዳዲስ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማቋቋም እንዲሁም ምርቶችን በማቀነባበር፣ እሴት በመጨመር እና አባላት ምርታቸውን ገበያ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት ይሰራል።

- አርሶ/አርብቶ አደሩን የግብርና ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ በማድረግ፣ የግብርና ምርምር ውጤቶች በማበልጸግ፣ በማፍለቅ እና በማላመድ ለተጠቃሚዉ በማቅረብ፣ የአደጋ ስጋቶችን በማጥናት፣ በመለየትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት የመቀነስ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ክስተት የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ በማጠናከር፣ በአደጋ የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን በዘላቂነት የማቋቋም፣ እንዲሁም የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አገልግሎቶች በማጠናከር የግብርና ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራዎች ይሰራሉ። በዚህም መሰረት በየዓመቱ በሰብል 12፣ በእንስሳት 9፣ በተፈጥሮ ሃብት 5፣ በግብርና ኢኮኖሚክስና ሥርዓተ-ፆታ 2 ተክኖሎጂዎችንና አሰራር ዘዴዎችን ለማቅረብ የታቀደ ሲሆን፤ በቴክኖሎጂ ሽግግር 18 ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም መነሻ ዘር ብዜት በአዝርዕት 1642.5 ኩንታል እና በሥራስርና በፍራፍሬ በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ለማባዛት ዕቅድ ተይዟል። በሚቀጥለው አስር ዓመታት የኤክስቴንሽን ስርዓቱ ለ2,700,000 በእንሳሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ተጠቃሚዎች ያደርጋል። ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ውስጥ 80 በመቶ (2,158,873) የሙሉ ፓኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ። በተመሳሳይ መልኩ ካሉት የሙሉ ፓኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ውስጥ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ እንዲሁም ለሌሎች አርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ 30 በመቶ (647,660) ሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮችን መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጐ ይሰራል። ከተጠቃሚዎች ውስጥ በእንስሳትና ዓሳ ሥራ ከተሰማሩ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 30 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የእንስሳትና ዓሳ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ይደረጋሉ።

- **የተፈጥሮ ሀብትና** የተፋሰስ ልማት ስራዎች በማስፋፋት የግብርና ልማት ስራዎች ዘላቂነት ለማረጋገጥ በመነሻ ዓመቱ የነበረው የልማት ዕቅድ የተዘጋጀላቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች በቁጥር 11,337 ይህም 2,691,215 ሄክታር ሲሆን በ2022 የማህበረሰብ ተፋሰሶች በየዓመቱ በአማካይ 16% በመጨመር በቁጥር 13,151 ሲሆን በሄክታር 6,575,500 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በየዓመቱ በክልሉ ቀበሌ ብዛት 2,510 ተፋሰስ በመያዝ 753,000 ሄ/ር እየለማ ይሄዳል። የተለያዩ የፊዚካል አፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች የተካሄደባቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት አሁን ከተደረሰበት 2,691,215 ሄክታር መነሻ በማድረግ በየዓመቱ 2% ጭማሪ አፈጻጸም ኖሮ በ2022 የዓመቱ ዕቅድ 318,360 ሄክታር በመሆን አጠቃላይ አፈጻጸም በመጨረሻ ዓመት ወደ 6,138,880 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል። ከዚህም በተጨማሪ በስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ዘዴ የተሸፈኑና

ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሰጡ የሚደረጉ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት በመነሻ ዓመቱ ከነበረበት 1,466,920 ሄ/ር መነሻ በማድረግ በየዓመቱ 5% ጭማሪ አፈጻጸም ኖሮ በ2022 የዓመቱ ዕቅድ 429,321 ሄክታር በመሆን አጠቃላይ አፈጻጸም በመጨረሻ ዓመት ወደ 5,383,511 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል። ከዚህም በተጨማሪ የተጎዱ ቦታዎችን (Hot spot areas) በመለየትና ከንክኪ ነጻ በማድረግ እንዲለሙና በቀጣይም ለህብረተሰቡ (ሴቶችና ወጣቶች) ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

- የመስኖ ውሃ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ሥራዎች ውጤታማነት ጉልህ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በዚህም መሰረት የውሃ አማራጮች ከማዘጋጀት አንፃር አነስተኛ ወንዝ ጠለፋ በመነሻ ዓመቱ ከነበረበት 3,678 ወደ 5,993 ፣ የእጅ ጉድጓድ ከ8,599 ወደ 4,461.4 ፣ ምንጭ ማጎልበት ከ3,012 ወደ 4,907 ፣ የቤተሰብ ገንዳ ከ372 ወደ 967 ፣ የማህበረሰብ ገንዳ ከ382 ወደ 466 ፣ እና ፓምፕ ከ874 ወደ 10,652 ለማድረስ ግብ ተጥሏል።
- **ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፡-** ዘላቂ የመሬት አሰተዳደር ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ በቀጣይ አሥር ዓመት የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ልኬት አሁን ከደረሰበት 4.37 ሚሊዮን ማሳ በቀጣይ ተጨማሪ 1.37 ሚሊዮን ማሳ በመለካት ከቀጣይ አሥር ዓመት በመጀመሪያው አምሰት ዓመት ሁሉም የክልሉ ማሳ በመለካትና በማጠናቀቅ ወደ 5.74 ሚሊዮን ማሳ የማድረስ ተግባር ይከናወናል። የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሥርጭት ሁሉም የገጠር ባለይዞታ ባለው ማሳ መጠን የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኝ ይደረጋል። በዚህም አሁን ከተደረሰበት 3.36 ሚሊዮን ማሳ በተጨማሪ 1.41 ማሳ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት በቀጣይ አሥር በዓመት 4.77 ሚሊዮን ማሳ በማድረስ ሁሉም ባለይዞታ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኝ ይደረጋል። ዘላቂ የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት ለማጠናከር በሁሉም ወረዳዎች በቀጣይ አሥር ዓመት የገጠር መሬት ዘላቂና አሰተማማኝ ለማድረግ የመረጃ ሥርዓት ማዘመን አሰፈላጊ ይሆናል። በዚሁ መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የገጠር መሬት አሰተዳደር መረጃ ሥርዓቱ በክልሉ በሁሉም የአርሶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ወቅታዊ በማድረግ 110 ወረዳዎች ዘመናዊ የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል በተመሳሳይ መልኩ የመረጃ ሥርዓቱን በየደረጃው ማስተሳሰር ሰለሚያስፈልግ በ11 ዞኖች ዘመናዊ የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል ።
- **የእንሰሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት፡-** የእንስሳት ምርት እድገት ለግብርና አጠቃላይ ምርት አሁን ያለውን 28 በመቶ ድርሻ በ2022 መጨረሻ ወደ 38 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው ለማስቻል ዕቅድ ተቀምጧል።
- **የወተት ምርትና ምርታማነት፡-** የወተት ምርትን ከዳልጋ ከብት ከ967,879 ቶን ሊትር በየዓመቱ በአማካይ 12% በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ወደ 2,108,541 ሊትር ማድረስ፣ የግመል ወተት ምርት ከ152 ቶን በየዓመቱ በአማካይ በ4% በማሳደግ ወደ 225 ቶን ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ከወተት ምርታማነት አንጻር ከአንድ የሀገር በቀል የወተት ላም የሚገኝ ወተት በቀን ከ2 ሊትር በአማካይ በ6% በማሳደግ 2022 ዓ.ም መጨረሻ 3.4 ሊትር

ማድረስ፣ እንዲሁም ከአንድ ግመል የሚገኝ ወተት በቀን ከ2.93 ሊትር በአማካይ በ2% በማሳደግ ወደ 3.57 ሊትር ለማሳደግ ታቅዷል። በአነስተኛ ስፔሻላይዝድ ወተት ከብት እርባታ የቀን አማካይ ወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 8 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 20.9 ሊትር (6%) ለማሳደግ እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት መጠን በዚሁ ጊዜ ከ2,160 ሊትር ወደ 3,651 ሊትር (5%) ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል። በተጨማሪም በመካከለኛ ስፔሻላይዝድ የቀን አማካይ ወተት ምርት አሁን ከሚገኘው 16 ሊትር ወደ 23.68 ሊትር (4%) እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት ከ4,800 ሊትር ወደ 7,104 ሊትር (4%) ለማሳደግ ታቅዷል።

- **የሥጋ ምርትና ምርታማነት፡-** የሥጋ ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 380,403 ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 834,383 ቶን ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። በተጨማሪም ስነ ምህዳርን መሠረት ያደረገ የሥጋ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም የዳልጋ ከብት፣ የበግ፣ የፍየልና የግመል ሥጋ ምርታማነት በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 130፣ 15፣ 14 እና 250 ኪ/ግ የቁም (ካርካስ) ክብደት በዓመት በአማካይ በ1.4%፣ 1.3%፣ 1.6% እና 0.14% በማሳደግ በቅደም ተከተል በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 144፣ 16፣15.7 እና 252.8 ኪ. ግ ኪ. ግ ለማድረስ ይሰራል።
- **የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት፡-** የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን በማሟላት የውጪ ንግድን ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮዎች አያያዝ የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስፔሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚያዙትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ማሳደግን መሠረት ያደረገ ሥራ በልማት ዕቅድ ዘመን ይሰራል። በዚህ ረገድ የእንቁላል ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 27,293 ቶን እንቁላል በ2022 ወደ 40,589 ቶን እንቁላል የማሳደግ ግብ ተቀምጧል። ይህን ለማሳካት ከስፔሻላይዝድ የእንቁላል ዶሮ እርባታ የሚኖረው የእንቁላል ምርት ከ2,729 ቶን ወደ 3,490 ቶን፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት ከ8,188 ቶን ወደ 16,203 ቶን እና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት ከ16,376 ቶን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገር በማድረግ በ2022 ዓ.ም ወደ 205ቶን ለማሳደግ ይሰራል። የዶሮ እንቁላል ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በዓመት የሚገኘዉን የእንቁላል ምርታማነት ከስፔሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 185፣185 እና 48 ሲሆን ይህም በዓመት በአማካይ በ2.5፣1.4 እና 1.2 በሞቶ በቅደም ተከተል በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ዘመኑ መጨረሻ 237፣213 እና 54 ማድረስ ይሆናል።
- የዶሮ ስጋ ምርትን በተመለከተም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 8,992 ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 14,657 ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። ይህን ለማሳካት ከስፔሻላይዝድ የስጋ ዶሮ እርባታ የሚኖረው የስጋ ምርት ከ10 ቶን ወደ 11.4 ቶን፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የዶሮ ስጋ ምርት ከ2,695 ቶን ወደ 4,072 ቶን እና

ከባህላዊ የዶሮ እርባታ የሚገኘው የስጋ ምርት መጠን ከ6,287 ቶን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገሩ በማድረግ በ2022 ዓ.ም ወደ 12,925 ቶን በማድረግ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ የዶሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በዓመት የሚገኘዉን የዶሮ ስጋ ምርታማነት ከስቴሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 2፣2 እና 0.8 ኪሎ ግራም ሲሆን ይህም በዓመት በአማካይ በ1.9፣3.4 እና 5.1 በመቶ በቅደም ተከተል በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2022) 2.4፣2.6 እና 1.3 ኪሎ ግራም ማድረስ ይሆናል።

- **የዓሳ ምርት፡-** የዓሳ ምርትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትናንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት ከ20,906 ቶን በየአመቱ በአማካይ በ12% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 62,208 ቶን ለማድረስ ታቅዷል።
- **የማርና ሰም ምርትና ምርታማነት፡-** የማር ምርት በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 12,015ቶን በአማካይ በዓመት 5% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 20,090 ቶን ለማሳደግ ታቅዷል።
- የንብን ምርታማነት ለማሳደግ አሁን ያለዉን የባህላዊ ቀፎ ቁጥር በየዓመቱ በአማካኝ በ5% እንዲቀንስ በማድረግ ወደ ሽግግር ቀፎና ዘመናዊ ቀፎ ለማሸጋገር የታቀደ ሲሆን በልማት ዕቅድ ዘመን አሁን ያለውን 1,268,468 ባህላዊ ቀፎ ቁጥር በየአመቱ በአማካይ 5% እንዲቀንስ በማድረግ ወደ 243,033 ዝቅ እንድል፣ የጨፈቃ ቀፎ አሁን ያለውን 130,869 በየአመቱ በአማካይ 15% በማሳደግ ወደ 217,068 የማሳደግ፣ የሽግግር ቀፎ አሁን ያለውን 23,053 በየአመቱ በአማካይ 15% በማሳደግ ወደ 37,305 እንዲያድግ ይሰራል። እንዲሁም የዘመናዊ ፍሬም ቀፎ አጠቃቀም አሁን ያለውን 13,582 በየአመቱ በአማካይ 12% በማሳደግ ወደ 16,874 የማድረስ ስራ ይሰራል።
- ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጋጠመ ያለውን የህብረንብ ቁጥር መቀነስ ችግርን ለማቃለል እንዲሁም በምርታማነታቸው የተሻሉ የንብ ቤተሰብን ለማባዛት እንዲቻል የንግስት ንብ ብዜት ቴክኖሎጂ በሰለጠኑ አ/አደሮች 2012 ከተደረሰበት 12,707 ዓመታዊ የንግስት ንብ ብዜት በአማካይ 11% በየዓመቱ በማሳደግ በ2022 12,989 ኩ/ል ለማድረስ እየተሰራ ይገኛል።
- የሰም ምርትን ደግሞ ከ1,201 ቶን በአማካይ በዓመት 5% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 2,009 ቶን ለማድረስ ታቅዷል።
- **የሐር ኩብኩባ ምርትና ምርታማነት፡-** ይህ ዘርፍ ቀደም ሲል በስፋት ያልተሰራበትና ትኩረት ያልተሰጠው ሲሆን ለእንዱስትሪ በጥሬ እቃነትና በውጪ ገበያ ያለው ተፈላጊነት፣ ልማቱ በአነስተኛ መሬት፣ ጉልበትና መነሻ ካፒታል የሚሰራ በመሆኑ፣ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ምርት በመስጠት የህብረተሰቡን ገቢ በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ 10 አመታት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት የደረቅ በ2012 ዓም

ከተደረሰበት 123 ኩ/ል የሐር ኩኩባ ምርትን በአማካይ በዓመት 12% በማሳደግ በእቅድ ዓመቱ መጨረሻ 381ኩ/ል ለማድረስ ይሰራል።

- **የቆዳና ሌጦ ምርት፡-** በቀጣይ 10 ዓመታት በአማካይ በዓመት 2% በማሳደግ የዳልጋ ከብት ቆዳ ከ1,639,198 ወደ 1,494,209 ፣ የበግ ሌጦ ከ2,080,976 ወደ 2,078,485 እና የፍየል ሌጦ ከ1,188,454 ወደ 1,113,045 ለማሳደግ ይሰራል።
- **የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፡-** የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት አቅርቦት እና በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ዙሪያ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ እንዲጠናከር በማድረግ የእዉቀት፣ የክህሎትና የአደረጃጀት ችግሮች ተለይቶ ለማስተካከል ይሰራል። በቀጣይ 10 ዓመታት የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል በሰው ሰራሽ ዘዴ (በመደበኛና ሲንክሮናይዜሽን) እና በተሻሻለ ኮርማ የሚካሄደውን የማዳቀል አገልግሎት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 214,684 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 506,487 ማሳደግ፣ በመደበኛ የሰው ሰራሽ የማዳቀል አገልግሎትን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 148,255 በየአመቱ በአማካይ 10% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 302512 ማድረስ፣ በበሆርሞን ማድራት ቴክኖሎጂ የሚካሄደውን የማዳቀል በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 36,788 በየአመቱ በአማካይ 15% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 131165 ማድረስ፣ በተሸሻሻለ ኮርማ የሚካሄደዉን የማዳቀል አገልግሎት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 29,641 በየአመቱ በአማካይ 8% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 72,810 ማድረስ፣የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል (በመደበኛና ሲንክሮናይዜሽን) እና በተሻሻለ ኮርማ የሚካሄደውን የማዳቀል አገልግሎት የተወለዱ ጥጆች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 115,689 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 260,758 ማሳደግ፣ በመደበኛ የሰው ሰራሽ የማዳቀል አገልግሎትን የተወለዱ ጥጆች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 70,654 በየዓመቱ በአማካይ 10% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 145078 ማድረስ፣ በበሆርሞን ማድራት ቴክኖሎጂ የሚካሄደውን የማዳቀል አገልግሎት የተወለዱ ጥጆች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 14,004 በየዓመቱ በአማካይ 15% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 56654 ማሳደግ፤በተሻሻለ ኮርማ የሚካሄደዉን የማዳቀል አገልግሎት የተወለዱ ጥጆች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 20,030 በየዓመቱ በአማካይ 15% በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 59026 ማሳደግ
- በቀጣይ 10 ዓመታት የተሻሻሉ ሐገረሰብ የወተት ዳልጋ ከብቶች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 3 ሚሊዮን በየዓመቱ በአማካይ 6% በመቀነስ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 1.7 ሚሊዮን ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም የተሻሻሉ ዲቃላ የወተት ዳልጋ ላሞች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 210,060 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ በ21% በማሳደግ ወደ 1,308,066 ለማድረስ ይሰራል።
- ሐገረሰብ የወተት ዳልጋ ከብቶች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 3 ሚሊዮን በየዓመቱ በአማካይ 6% በመቀነስ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 1.7 ሚሊዮን ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም የተሻሻሉ ዲቃላ ላሞች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 210,060 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ በ21% በማሳደግ ወደ 1,308,066 ለማድረስ ይሰራል።

በተመሳሳይ መልኩ ዝርያቸው የተሻሻሉ ዲቃላ የሥጋ ዳልጋ ከብቶች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 43,181 በየዓመቱ በአማካይ 10% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 82,453 ለማድረስ ይሰራል።

- ዝርያቸው የተሻሻሉ ዲቃላ በጎች ከ518,767 ወደ 1,934,741 ለማድረስ እና ዲቃላ ፍየሎች ከ101,260 ወደ 390,136 ለማድረስ ይሰራል።
- ለተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የሚውሉ ዝርያቸው የተሻሻሉ ዶሮዎች ብዛት በየዓመቱ በአማካይ 10% በማሳደግ በ2012 ዓ.ም 1,750,000 ከነበረበት በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 3,676,630 ለማሳደግ፣ ለስፔሻላይዝድ የእንቁላል ደሮ ከ70,500 በየዓመቱ በአማካይ 5% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 93,018 እንዲሁም ለስፔሻላይዝድ የስጋ ደሮ 5,000 በየዓመቱ በአማካይ 10% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 9,078 ሚሊዮን ለማድረስ ይሰራል።
- በአጠቃላይ በክልሉ የሚገኙ የእንቁላል ጣይ ዶሮች ቁጥር በ2012 ከነበረበት 775,500 በአማካይ በዓመት 8 በመቶ በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ላይ ወደ 1,356,140 ለማድረስ እና የእንቁላል ምርት በ2012 ከነበረበት 27,293 ቶን በአማካይ በዓመት 7% በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ላይ ወደ 40,589 ቶን ያድጋል።
- **የእንስሳት መኖ ሀብት ልማትና አጠቃቀም፡-** የመኖ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ለማሻሻል የመኖ ማባዣ ጣቢያን ከ200 በአማካይ 7 በመቶ በማሳደግ ወደ 336 ማባዣ ጣቢያ የማሳደግ እና የመኖ ዘር አባዥ ባለሀብቶች ከ15 በአማካይ 7 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 22 የመኖ ዘር አባዥ ባለሀብቶች ለማድረስ የሚሰራ ይሆናል። የእንስሳት መኖ አቅርቦት ሽፋንን በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 82.1% በየዓመቱ በአማካይ 1.5 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ሽፋኑን 95.3% ለማድረስ ይሠራል። በዚህም መሰረት በአጠቃላይ ዓመታዊ የድርቆ መኖ ምርት በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 19.79 ሚሊዮን ቶን በየዓመቱ በአማካይ 3.5 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 20.7 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ ይሰራል። የተዘራና የተተከለ የመኖ ዘር ከ3,077 ኩ/ል መኖ ዘር በአማካይ 16.90 በመቶ በማሳደግ ወደ 12,081 ኩ/ል ለመዝራት፣ እንዲሁም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 3.13 ቢሊዮን መኖ ቁጥርራጭና ግንጣይ እና 7.174 ቢሊዮን እንዲሁም የመኖ ችግኝን ከነበረበት 275 ሚሊዮን 12 በመቶ በማሳደግ 802 ሚሊዮን ችግኝ ለማድረስና ለመትከል ይሰራል።
- **የእንስሳት ጤና አገልግሎት፡-** መከላከልን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ጤና አገልግሎት በመስጠት የእንስሳት በሽታዎችን በመቆጣጠርና በመከላከል የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ ድንበር ዘለልና መደበኛ ክትባቶችን ከመስጠት አንጻር በ2012 ከተደረሰበት 34,563,862 ዶዝ አመታዊ የክትባት መጠን በየዓመቱ በ5 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም 55,078,772 ዶዝ ለማድረስ ታቅዷል። በዚህም የክትባት አገልግሎት ሽፋኑን ከ82 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ይሰራል። የእንስሳት ህክምና አገልግሎትን በ2012 ከተደረሰበት 10,021,207 እንስሳትን የማከም ስራ በየዓመቱ በ5 በመቶ በማሳደግ በ2022 የህክምና አገልግሎት የሚያገኘውን እንስሳ ቁጥር ወደ 18,219,528 ለማድረስ ይሰራል።

- በክሊኒክ የሚሰጡ የእንስሳት ጤና አገልግሎቶች በ2012 ከተደረሰበት በአመት ለ 1,535,553 እንስሳት የክሊኒክ አገልግሎት ከመስጠት በመነሳት በየአመቱ በ10 በመቶ በማሳደግ በ2022 የክሊኒክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንስሳትን ቁጥር በአመት ወደ 3,766,491 ለማድረስ ይሰራል።
- ደረጃቸዉን የጠበቁ የእንስሳት ጤና መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት አሁን በክልሉ ዉስጥ ያሉንን 91ክሊኒኮች በቀጣይ 10 አመታት ተጨማሪ 54 ክሊኒኮችን በመገንባት ወደ 145 ክሊኒኮች ለማሳደግ ይሰራል። እንዲሁም ያሉንን 468 ጤና ኬላዎች ታሳቢ በማድረግና ካሉን 2,877 ቀበሌዎች በመነሳት በየቀበሌዉ 1 የጤና ኬላ በመገንባት የጤና ኬላ የሌላቸው 2,409 ቀበሌዎች ላይ 2,877 የጤና ኬላዎች እና በየቀበሌዉ 2 ደረጃቸዉን የጠበቁ የህክምናና የክትባት በረቶች በአጠቃላይ 5,754 በረቶች በቀጣይ 10 አመት የሚገነቡ ይሆናል።
- **የእንስሳትና ዓሣ ግብዓት አቅርቦት፡-** የአባለዘር አቅርቦትን በ2012 ከደረሰበት 258,659 ሺህ ዶዝ ዓመታዊ ምርት በየዓመቱ በአማካይ 13% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 770,632 ሺህ ዶዝ ለማድረስ ይሰራል። የፈሳሽ ናይትሮጂን አቅርቦትን ዓመታዊ ምርት በ2012 ከደረሰበት 47,882 ሊትር በአማካይ በየዓመት በ8% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 116,461 ሊትር ለማድረስ ይሰራል። ዝርያቸው የተሻሻሉ ጊደሮችን በ2012 ከደረሰበት 252 በአማካይ በየዓመት በ12% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም 621 ማድረስ እንዲሁም ለጥቂ የሚሆኑ ኮርማዎችን በ2012 ከደረሰበት በቁጥር 99 በአማካይ በየዓመት በ14% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም መጨረሻ 262 ዝርያቸው እና ጥራታቸው የተረጋገጡ የጥቂ ኮርማዎችን በየዓመቱ ማቅረብ። እንዲሁም የተሻሻለ የበግ አውራዎችን በ2012 ከደረሰበት 13,157 በአማካይ በየዓመቱ በ15% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም መጨራሻ ላይ በቁጥር 35,641 እንዲሁም ለፍየል ዝርያ ማሻሻል ተግባር የሚውሉ በደቡብ በምርምር ትክክለኛ መረጃ ያላቸውን የኮንሶ ፍየል አውራዎችን በ2012 ዓ/ም ከደረሰበት 2,760 በአማካይ በየዓመት በ14% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም መጨራሻ 14,919 እንዲቀርብና እንዲሰራጭ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፥

- **ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን፡- ለግብርናው ዘርፍ** የግብርና ልማት ቢሮ በአዋጅ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በዘርፉ ለማሳካት ያቀዳቸውን ተግባራት ለመፈፀም የሚችል ተቋማዊ መዋቅር፣ የሰው ሃብትና ክህሎት እንዲኖረው ይደረጋል። በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳና ወረዳ ደረጃ መልሶ ማቋቋም ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምዘናና የማበረታቻ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር (ለአርሶ/አርብቶ አደሩና ለግሉ ባለሃብቱ፣ ለማህበራት፣ ለመንግስት ባለሙያዎች) ስትራቴጂ በመንደፍ ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል።

- **የግብርና ልማትን ዲጅታላይዝ ማድረግ፡-** የግብርና ልማትን በቴክኖሎጅ የተደገፈ ለማድረግ የግብርና ባለድርሻ አካላት የሚጠቀሙበት የግብርና መረጃ መረብ መሰረተ ልማት (AgriNet) በመዘርጋት የግብርና ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በመደገፍ ጥራት ያለውና ቀልጣፋ አገልግሎት ለደንበኞቹ መስጠት እንዲችል ይደረጋል፡ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የግብርና ምክር አግልግሎት፣ የግብዓት ማሰባሰቢያና ስርጭት ክትትል ስርዓት፣ የግብርና በሽታና አደጋ ክትትልና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት፣ የግብርና ገበያ መረጃ ስርዓት፣ የግብርና ምርቶች አመራረት ዱካ ስርዓት፣ የተቀናጀ የግብርና መረጃ ስርዓት፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት እና የተሞክሮና እውቀት አስተዳደር ስርዓት ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናሉ።
- **የፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች፡-** በሀገር ደረጃ እየተሰራ ያለውን አገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያን መሰረት በማድረግ ግብርናም በዘርፍ ደረጃ የፖሊሲ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በጥናት በመለየት የዘርፉን ስትራቴጃዊ ማነቆዎች ሊፈቱ የሚችሉና ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ስምንት ጉዳዮች እንዲለዩ ተደርጓል። እንደተለዩት ጉዳዮች ባህሪ የአሠራር ማሻሻያ፣ የስትራቴጂ ለውጥ፣ የፖሊሲና የሕግ ለውጦችና ማሻሻያዎች በማድረግ የግብርናን ትራንስፎሜሽን ለማረጋገጥና ዘርፉ ለጥቅል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ያለውን አስተዋፆ በተገቢው መንገድ እንዲወጣ በአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ ማዕቀፍ ውስጥ የአጭር፣ የመካከለኛና ረጅም ጊዜ የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት የሚፈፀሙ ይሆናል። በተጨማሪም የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ ቴክኖሎጅና ግብዓት አቅርቦት፣ ግብርና ፋይናንስና ኢንሹራንስ፣ ሀገር ውስጥና የወጪ ንግድ ግብይት፣ አዋጪ የመስኖ ልማትና ውሃ አጠቃቀም፣ አዋጪ የግብርና አገልግሎት መሰረት ልማት፣ የግል ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የግብርና ዘርፍ የማስፈፀም አቅም ማጠናከር የፖሊሲ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ይሆናሉ።
- **የገጠርና ከተማ ትስስር፡-** የግብርና ልማት በማፋጠን አገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ የገጠርና ከተማ ትስስር ወሳኝ በመሆኑ የተሟላና ዉጤታማ የግብርናና ገጠር ልማት ላይ በትኩረት ይሰራል። በመሆኑም የተቀናጀ ቤተሰብ ተኮር አሰራሮች በሙከራ ደረጃ መፈተሽና በሚቀጥሉት አስር አመታት በስፋት ለመተግበር አቅጣጫ ተቀምጧል። በተለይም በሙከራ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የዘርፈ ብዙ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን ውጥን ማስፋት ላይ በትኩረት ይሰራል። ለዚህም የመንግስት ተቋማትን፣ የህብረተሰቡን፣ የግሉን ዘርፍና መንግሰታዊ ያልሆኑ አጋር አካላትን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችል አሰራርን በዘላቂነት ለመዘርጋት የሚያስችል ሲሆን የመንግስት ተቋማት ተናቦና ተቀራርቦ መሥራትን በሁሉም ደረጃ በተለይም ለህብረተሰቡ ቅርበት ባላቸው አካላት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራትን ቅድሚያ የሚሰጥ አሰራር ነው።
- በዚህ የልማት ስልት ተመጋጋቢ የገጠርና የከተማ መስተጋብርን ለመፍጠር የተሻሻለ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፤ አማራጭ የሥራ ዕድል ፈጠራ፤ የተሻሻለ መሰረታዊ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፤ የተጠናከሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ቁልፍ ተግባራት ናቸው። ይህ የልማት ሥርዓት

የገጠርና የከተማ መስተጋብር ምርታማነትን በማሻሻል፤ የገበያ አማራጮችን በማስፋት፤ አገልግሎትን በማሳለጥና አመጋገብን በማሻሻል ጤናማና ዘላቂነት ያለው ዕድገት አንዲመዘገብ የራሱን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ አሰራር በተጨማሪም የህብረተሰቡን እምቅ የልማት ኃይልና የማደግ ፍላጎትን አዋህዶ የቤተሰብ ለውጥን በማሳለጥ፣ የቀበሌ፣ወረዳ፣ ክልል እና ሀገራዊ እምርታዊ ለውጥን በአጭር ጊዜ በማምጣት የዘላቂ ልማት ግቦችን አካታች በሆነ መልኩ ለማሳካት የሚያስችል እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።

3.2. የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች

የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ከክልል እስከ ቀበሌ የተዘረጉ መዋቅሮች በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በሰው ኃይል ተጠናክረው በራሳቸው አቅም የሚፈጽሙ እንዲሆኑ በማድረግ በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የተጀመረውን ሁለገብ ልማትን ማስቀጠል እና ብልጽግናን ማረጋገጥ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል።
- የአርብቶና ከፍል አርብቶ አደርን የአኗኗር ዘይቤ ማዕከል ያደረገ የመሰረተ ልማት ስራዎችን በማስፋፋት ተደራሽነትና ጥራታቸውን ማረጋገጥ፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራምን ማጠናቀቅ፤ መንደሮች በፕላን የሚመሩ፣ ጽዱ፣ ለኑሮ ምቹና አረንጓዴ እንዲሆኑ መሥራትና ወደ ፊት የከተማ ማዕከል እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው።
- በአርብቶና ከፍል አርብቶ አደሩ እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የእንስሳትንና የሰብልን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግሉ ባለሀብት በራሱና ከመንግስት ጋር በቅንጅት በግብርናውና በአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፍ ማድረግ እና የገበያ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤
- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ በቂ የፋይናንስ አገልግሎት አንዲኖር በማድረግ የባንክና ኢንሹራንስ እንዲሁም የገጠር ማይክሮ-ፋይናስ እንዲስፋፋ ማድረግና ህብረተሰቡ እንስሳቱን በዋስትና አስይዞ የሚበደርበትን ሁኔታ እንዲመቻች፣ ሕዝቡ በብድርና ቁጠባ ህብረት ሥራ ማህበራት እየተደራጀ ብድር የሚያገኝበትና የቁጠባ ባህል እንዲዳብር ይደራጋል።
- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የውሃ አቅርቦት፣ የጤና እና የትምህርት ፍትሃዊነትና ተደራሽነት በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል።
- የህዝቡን ምርታማነት ለማሳደግ አዳዲስ ቴክኖሎጆዎችና ግብአቶች የማቅረብ፣ የድርቅ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘላቂ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ ማላመድ ሥራዎች በሁሉም ተግባራት ትኩረት አግኝቶ እንዲታቀዱና እንዲፈፀሙ ይደረጋል።

- የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ማህበራዊ ሃብት በመገንባት፣ የሰላም አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በማጠናከር አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድና በራሳቸው አቅም የሚፈቱበትን ስርአት በመዘርጋት፣ ተጎራባች ማህበረሰቦችን በልማትና መልካም አስተዳደር በማስተሳሰርና በመካከላቸው ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማ እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በአርብቶ አደርና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ በመተግበር የህዝቡን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- በአርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ግንዛቤዉ ያደገ፣ ልማትን ማፋጠን የሚችል ማህበረሰብ እና የሰለጠነ የሰዉ ሀብት በማፍራት የማስፈጸም አቅም ችግርን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ በአማካይ ከ40% በታች የሆነዉን የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ወደ 85% የማሳደግ፣ በአካባቢዉ የሚታየዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀይል እጥረት ለመቀነስ የአጭር ጊዜ ሥልጠና በመነሻ 1,738 የነበረ ሲሆን 1,500 ማሰልጠን፤ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ስልጠና ለ790 የመስጠት፣ በአካባቢዉ ያለዉን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ በሆስቴል ማህበራዊ አገልግሎት በመነሻ 18,140 የነበረዉን በ2022 ለ9,498 ተገልጋዮች ለመስጠት ታቅዷል።
- በመነሻ ከነበረዉ 780 የተለያዩ የመጠጥ ዉሀ ተቋማት አዳዲስ 59 የውሃ ተቋማትን በቅንጅት በመገንባት ወደ 839 በማሳደግ የንጹህ መጠጥ ውሀ ተደራሽነት ይረጋገጣል
- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ ወደ መንደር መዳረሻ 190 ኪ/ሜ መንገድ በመገንባት ተደራሽነትን ለማሳደግ ይሰራል
- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ የተመሰረቱ አዳዲስና ነባር የመንደር ማሰባሰብ ማዕከላት ሙሉ በሙሉ ዘመናዊ፣ ፅዱ፣ ለኑሮ ምቹና አረንጓዴ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመንደር ማሰባሰብ በመነሻ 20,695 ከነበረዉ በተጨማሪ 8,750 የቤተሰብ ታላፊዎችን በአዲስ መልክ በማሰባሰብ ወደ 29,445 የቤተሰብ ታላፊዎች በማድረስ የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ግንባታን በ2022 ወደ 120 በማድረስ በመንደር ተሰብስበው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል።
- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች የሰላም አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በማጠናከር፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግጭት እንዲቀንሱና እንዲወገዱ 116,602 ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በማሳደግ፣ ተጎራባች ማህበረሰቦችን በልማትና መልካም አስተዳደር በማስተሳሰር፣ በመካከላቸው ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር

በማድረግ እና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድና በራሳቸው አቅም እንዲፈቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ የሰላም አደረጃጀቶችን የመፍጠርና የማጠናከር ስራ ይሰራል።

- አርብቶ አደሩ ከእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን የሰብል ልማትን በማካሄድ በዓመት ሁለት ጊዜና ከዚያ በላይ በማምረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ነባርና አዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች የዉሀ አማራጮችን በመጠቀም በየዓመቱ 22,460 ሄ/ር ማሳ በመስኖ እንዲለማ ይደረጋል።
- አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ከእንስሳት ሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ከሚመለከተዉ ሴክተርና ከልማት አጋሮች ጋር በመቀናጀት የእንሰሳቱን ጤና እና መኖ በማሻሻል፣ እንዲሁም ምርታማነቱን በማሳደግ ከዚህ ጋር በተያያዘ የገበያ መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ይደረጋል።
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ ስራዎች በግጦሽ 564 ሄ/ር መሬት መከለል፤ 1,128 ሄ/ር የግጦሽ መሬትን ተበይ ካልሆኑ ዕፀዋቶች ወይም ከወራሪ ዕፅዋት ማፅዳት፤ 648 ሄ/ር የግጦሽ መሬት ስነ ህይወታዊና አካላዊ ስራዎችን በመስራት፣ 48ሄ/ር ስነህይወታዊ ሥራዎች መስራት፣ 4ሚሊዮን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ችግኞች መትከል በአየር ንብረት ለውጥ ላይ አዎንታዊ ሚና እንዲኖራቸው ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመሆን አርብቶ አደሩ ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ተግባራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት ይሰራል።
- የአርብቶ አደሩ የእንሰሳቱን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እና በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ድርቅን ለመቋቋም እንዲያስችል ዘላቂ 28 የእንስሳት መኖ /ድርቆሽ/ ማከማቻ ባንኮች አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ 50 ኩ/ል የእንሰሳት መኖ ዘር በማቅረብ 500ሄ/ር መሬት የእንስሳት መኖ ባንክ እና 450,000 እስር ሳር ቤል ማዘጋጀት፤ በስድስቱም የአርብቶአደር ወረዳዎች 6,200 እንስሳቶችን ማዳቀልና 8,000 እንስሳቶችን በማስከተብ ማህበረሰቡ ከእንስሳት ሀብት ይበልጡን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- አርብቶ አደሮችና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካቢዎች በመንደር ማሰባሰብ ጠቀሜታ፤ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አወጋገድ፣ ከዘላቂ ሠላም ግንባታ፣ በእንስሳት ዝሪያ ማሻሻል፣ በመስኖ ልማት፣ በእንስሳት መኖ ልማት፣ በሰብል ልማትና በተለያዩ ዘርፎች የተሻለ ተሞክሮ ባለባቸዉ ወረዳዎችና ክልሎች ምርጥ ተሞክሮ ላይ ልምድ ልውውጥ ቀስመው እንዲተገብሩት ተገቢው ድጋፍና ክትትል ይደረጋል።
- አርብቶና ከፊል አርብቶ አደር በየአካባቢያቸው የሚያስመዘግቡትን መልካም ተሞክሮዎች በጋራ ተገናኝተው መለዋወጥ እንዲችሉ እና ለመንግስት አስፈጻሚ አካት ያላቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ 1 የሀገር አቀፍ በዓል እና 5 ክልላዊ የአርብቶ አደር ቀን በዓል ይዘጋጃል።

- በመንደር ማሰባሰብ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትና ግጭት መከላከል ዙሪያ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሰፊ የሞብላይዜሽን ተግባራት በየደረጃዉ ለማካሄድ፣ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮችን በግብዓትነት ለመጠቀም፣ ከሚመለከታቸዉ ባድርሻ አካት ጋር በቁርኝነትና በቅንጅት ለመስራት፣ በክልልና በዞን ስትሪንግ እና ቴክኒክ ኮሚቴ ዕቅዱ እንዲመራ ለማድረግ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት የተሰጡት የትምህርትና ስልጠናዎች ያስገኙትን ውጤቶችንና የነበረበትን ክፍተት በዳሰሳ ጥናት የመለየት ስራ ይሰራል።

3.3. የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ ድርሻ በፍጥነት ማሳደግ እንዲቻል ነባር ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማሻሻል የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ እንዲሁም ከአምራች ዘርፉ ውጭ ያሉ ባለሀብቶችን ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ በማድረግ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና የምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት፣ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት እንዲፈጠሩ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎች መካከል የገበያ፣ የቴክኖሎጂና የማኔጅመንት ዕውቀት ሽግግር መፍጠር የሚያስችል ትስስር እንዲኖር በትኩረት ይሰራል።
- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት የሁሉንም ህብረተሰብ በተለይም ወጣቶች፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትን (equitable and inclusive growth) ማረጋገጥ ትኩረት ይሰጠዋል።
- ነጻ ውድድርን የሚያሰፍን፣ ማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽእኖን የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን የሚያረጋገጥ፣ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመሩበት የድጋፍ ማዕቀፎች የልማቱ እድገትና ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር ተጣጥሞ እንዲሻሻል ይደረጋል።
- የክልሉ ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን በመለየት በተለያዩ ገቢ ማስገኛ መስኮች በማሰማራት በሀገሪቱ እየተመገዘገበ ያለውን ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል ድህነትን በመቀነስ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።
- የቢዝነስ መፈልፈያ ማዕከል (BIC) በማደራጀት የስራ ፈጣሪነትን ባህል በማዳበር ዘርፉ የአዳዲስ ስራ ፈጠራ ማፍለቂያ እንዲሆን የማድረግ፣ ሰፊ የስራ ዕድል ለሚፈጥሩ ተቋማት የማበረታቻ ስርዓት የመፍጠር፣ የቁጠባ ባህላቸው የሚዳብርበትን፣ የጥ/አ/መ/ኢንተርፕራይዞች ባንክ ማቋቋም እና የአነስተኛ ብድር ተቋማትን የሚዘምንበት አቅጣጫ ለመከተል ታቅዷል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- የኢንዱስትሪ ልማት ምርታማነት፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፣ የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪው መሠረቱን በማስፋት በሂደት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መሠረት እንዲጥል በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱ

ከኢንዱስትሪና ግብርና ጋር በማስተሳሰር የክልሉ ህዝቦች ብልፅግናን ማረጋገጥ፤

- በገጠር አካባቢዎች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁና ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችን መጠነኛ ቁጠባ በመነሻነት እንዲቆጥቡ በማድረግና ከመንግስትና አበዳሪ ተቋማት የብድር አገልግሎት በማቅረብ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የሥራ ዕድል እንዲያገኙና ሀብት ፈጥረው ለራሳቸውም ሆነ ለአገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው፡፡
- የስራ ፈጠራ ክህሎትና የስራ ፈጣሪነት አመለካከትን በማጎልበት፣በከተሞች ሰፊ የስራ አማራጮችን በመፍጠርና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ለኢንዱስትሪ መሰረት የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች በማፍራት ስራ አጥነትን በመቀነስ ለክልላችን ብሎም ለሀገራችን ብልፅግና ዘርፉ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፣

- በክልሉ የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪው አሁን ከሚገኝበት 16.6 በመቶ አማካይ የምርት ዕድገት ወደ 20.6 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት በማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪው በ2012 በጀት ዓመት 4.2 በመቶ ከነበረበት የምርት ድርሻ በየዓመቱ 1.3 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 19.2 በመቶ ከፍ እንዲል የሚደረግ ሲሆን ይህንን ለማሳካት በዕቅድ ዘመኑ 3,900 ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም እና አዲስ ወደ ዘርፉ የሚቀላቀሉ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 9,605 ነባር ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር ለ167,419 ዜጎች የስራ ዕድል ይፈጠራል፡፡
- የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪ በ2ኛው የዕ.ት.ዕ ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገቱ መዋቅራዊ ለውጥ በተፈለገው ፍጥነትና አቅጣጫ መሄድ ባለመቻሉ በቀጣይ 10 ዓመት ዕቅድ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማፋጠን ይሰራል፡፡ በዞንና ልዩ ወረዳ ከተሞች የሚገኙ ኢንዱስትሪ መንደሮችን ማልማት፣ በተለያዩ ከተሞች የተጀመሩ የክላስተር ማዕከላትን ማጠናከር፣ አምስት መለስተኛ የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥናት በማድረግ ሁለት ፓርኮች ይለማሉ፡፡ የነባር ማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም በማሳደግ 777 ኢንዱስትሪዎች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና 61 ኢንዱስትሪዎች ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ በክልሉ የአርሶና አርብቶ አደሩ ምርቶች ከኢንዱስትሪ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር የአግሮ ኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት እና አገር ውስጥ ገበያ ድርሻ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ የገጠርና ከተማ እና የግብርናና ኢንዱስትሪ ትስስር እንዲሳለጥ ይሰራል፡፡
- የዩኒቨርሲቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር በማጠናከር የማንፋክቸርንግ ዘርፉን በምርምር የተደረገ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ዘርፉን ለማጠናከር ይሰራል፡፡ በአምራች ኢንዱስትሪው የሚገጥመውን የካፒታልና ማሽነሪ ችግር ለመቅረፍ የሚሰራ ሲሆን በካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ 2,123

ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 2.26 ቢሊየን የማምረቻ መሳሪያ እና የብር 2.38 ቢሊየን የስራ ማስኬጃ ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 7735 ሺህ ሄክታር የለማ የኢንዳስትሪ መንደር በማዘጋጀት በማምረቻ ኢንዱስትሪ ለሚሰማሩ ባለሃብቶችና ለኢንተርፕራይዞች ለማምረቻ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸርንግ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚሆን የመሰረተ ልማት የተሟላላቸው 233 የምርት ማሳያ እና መሸጫ ህንጻዎች ተገንብተዉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ስኬታማ ሽግግር እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- አምራች ኢንዳስትሪዎች በራሳቸው ጥረት ገበያ ውስጥ መግባት ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የብር 2.5 ቢሊየን የሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር የሚፈጠር ሲሆን ኢንዱስትሪዎች 6,763,876 ኪ.ግ የማኑፋክቸሪንግ ምርት ለውጪ ሃገር ገበያ በማቅረብ 13.7 ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ ይሰራል፡፡ 38,760 ኢንዱስትሪዎች 961 ባዛሮችና ኤግዚቢሽን ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 176,347,453 ሽያጭ የገበያ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡
- የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራና ልማት፡- በገጠር ስራ አጥ ወጣቶች ስምርት በዋናነት በአማራጭ የግብርናና ከግብርና ውጪ ባሉ የስራ መስኮች ሆኖ በተለየ ሁኔታ የግብርና ፓኬጅ በተሟላ ቴክኖሎጂና በተሻሻለ አሠራር በመፈፀም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በግብርና ምርቶች ዕሴት መጨመር (አግሮ ፕሮሰስንግ) ስራዎችና ግብዓት ማምረት ላይ ተገቢው ትኩረት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም የገጠርና ከተማ ትስስር አንዱ ማዕከል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
- በ10 ዓመቱ ለቋሚ ስራ ዕድል ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን በ5 ዓመቱ በአማካይ የተፈጠረው የስራ ዕድል መነሻ በማድረግና በየዓመቱ 15 በመቶ በማሳደግ በአጠቃላይ ለ2,606,280 የሥራ እድል የሚፈጠር ሲሆን አስፈላጊውን የኤክስቴንሽን ድጋፍ በማድረግ 2,085,024 (80%) ቋሚ ፓኬጅና በቅጥር ሲሆን 521,256 በጊዜያዊ የስራ ዘርፎችና ቅጥር የስራ ዕድል እንዲሆን ይሰራል፡፡ በሁሉም የስራ ዘርፎች 50 በመቶ ሴቶች ተጠቃሚ አረንዲሆኑ የሚደረግ ይደረጋል፡፡
- በአዲስ ከሚደራጁ ኢንተርኘራይዞች ውስጥ ለ249,302 ኢንተርፕራይዞች የመስሪያና መሸጫ ቦታ የሚሆን 104,522 ሄ/ር መሬት እንዲቀርብላቸው ይደረጋል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ለወጣቶች ስምርት ከሚያስፈልገው ካፒታል ውስጥ የመንግስት ድርሻ በአማካይ በአንድ ወጣት አስር ሺህ ብር ታሳቢ በማድረግ የብድር ገንዘብ 19,049,810,364 ብር ይቀርባል፡፡ ይህም በየደረጃው ባለው የመንግስት መዋቅር፣ ከወጣቶችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጠባና ከብድር ተመላሽ የሚሸፈን ሲሆን ከክልል መንግስት 30 በመቶ 5,714,943,109 ብር፤ ከዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎችና ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች 20 በመቶ 3,809,962,073 ብር፣ እንዲሁም ከቅድመ-ቁጠባና ሌሎች ቁጠባዎችና ከብድር ተመላሽ ብር 9,434,961,729 የሚሸፈን ነው፡፡

- በገጠር ነባርና በአዲስ የሚደራጁ ወጣቶች ምርትና አገልግሎታቸውን በሀገር ውስጥ ከመንግስትና ከግል ተቋማት፣ ከግለሰቦች፣ ከባዛርና ኤግዝብሽን የብር 15.6 ብሊየን የገበያ ትስስር ለኢንተርፕራይዞች ይፈጠራል።
- በዕቅድ ዘመኑ ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ 12,148፣ ከመስራች ወደ ታዳጊ 5,734፣ ከታዳጊ ወደ መብቃት 2,717 ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ይደረጋል። የኢንተርፕራይዞች ድህረ-ቁጠባ ብር 4,520,514,056፣ ብድር አመላለስ ብር 7,259,901,695 እንዲሁም ሂሳብ አያያዝ ለ261,285 አደረጃጀቶች፣ ኦዲት አገልግሎት ለ130,637 አደረጃጀቶችና የባዛር ኤግዝብሽን ለ381 ኢንተርፕራይዞችን የምርት ማስተዋወቂያ ድጋፍ ይደረጋል።
- **የከተማ ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና፡-** በከተሞች የስራ ዕድል በመፍጠር የስራ አጥነቱን ምጣኔ አሁን ካለበት 16.1% በየዓመቱ 1% ለመቀነስ ይሰራል። ያለውን የገበያ ክፍተት መነሻ በማድረግ አዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋምና በመደገፍ ለ2,572,310 ስራ ፈላጊ ዜጎች በቋሚና በጊዜያዊ የስራ ዕድል ይፈጠራል። ባለፉት አስር ዓመታት የስራ እድል ፈጠራ አፈጻጸማችን 55% ከነበረበት ወደ 80% ከፍ እንዲል እና በኢንዱስትሪ (50%)፣ በከተማ ግብርና (13%) እና በአገልግሎት (37%) ድርሻ እንዲኖራቸው ይደረጋል።
- በዕቅድ ዘመኑ ብር 22,024,039,680 እንዲቆጠብ እና ብር 27,530,049,600 ብድር የሚሰራጭ ሲሆን ከተሰራጨው ብድር የዘመኑንና እና ውዝፍ ዕዳ ሙሉ በሙሉ የማስመለስ ሥራ የሚሰራ ይሆናል።
- የማምረቻና መሸጫ ቦታ ችግር ለመቅረፍ ለኢንተርፕራይዞች የለማ መሬት የማምረቻና መሸጫ ቦታ ድጋፍ እንዲሁም ሼድ ይቀርባል። በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙና አዲስ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ ዝርጋታ የሚደረግላቸው ሲሆን ነባር ኢንተርፕራይዞች ሂሳባቸው እንዲያስመረምሩ ይደረጋል።
- አዲስ የስራ ዕድል ለሚፈጠርላቸዉና ለነባር የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የብር 17,785,268,000 የገበያ እድል በማመቻቸት 210,944 ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ያደረገ የገበያ ድጋፍ ይመቻቻል።
- የኢንተርፕራይዞችን እድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ድጋፍ በመስጠት ከሚፈጠሩ ኢንተርፕራይዞች 30 በመቶ ወደ አነስተኛ ደረጃና 2 በመቶ ኢንተርፕራይዞችን ወደ መካከለኛ ደረጃ በማሸጋገር ለኢንዱስትሪው ልማት ያለውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ይሰራል።
- የተሟላና ተደራሽ የአንድ ማዕከል አገልግሎትና መንግስታዊ ድጋፎችን በመስጠት የኢንተርፕራይዞች ምርታማነት እንዲያድግ ይደረጋል። ነባር 555 እና አዳዲስ 253 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በግብዓትና በቴክኖሎጂ ብቁ ይደረጋል።
- በክልላችን በ137 ከተሞች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉትን ቤተሰቦች እና ግለሰቦች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት 121,016 እና በምግብ ዋስትና ፈንድ 196,230 ዜጎች በአጠቃላይ 317,246 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች፣ በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ እና 2,900 በማህበራዊ ሴፍቲኔት አማካኝነት ተጠቃሚ በማድረግ በከተሞች ያለውን ድህነት ለመቀነስ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፥

- የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታቱ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ተግባራዊ ይደረጋል። የስራ እድል ፈጠራ በተሻለ ብቃት መምራትና መተግበር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም በመፍጠር በሁሉም የአስተዳደር እርከን ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።
- የሥራ ዕድል ፈጠራን በተጠናከረ መንገድ ለመተግበር ሁለንተናዊና የተቀናጀ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል። በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሳተፉ ዜጐች በግል፣ በማህበር በኢንተርኘራይዞችና ሌሎች አደረጃጀቶችና ስራዎች ተሰማርተው ውጤታማ ለማድረግ ቀጣይነት ያላቸው ዘርፈ-ብዙ የአንድ ማእከል አገልግሎትና በከላስተር ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።
- የሥራ ዕድል አማራጮችን የማስፋት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል፣ ከአነስተኛ ካፒታል እና የቴክሎጂ አቅም በመነሳት በልማታዊ ጥረት እያደገ የሚሄድ የካፒታልና የቴክኖሎጂ አቅም እንዲገነባ፣ እንዲሁም ለተዋናዮች አስፈላጊው የግብዓት አቅርቦት የማመቻቸትና የገበያ ትስስር እንዲጎለብ ይደረጋል።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ከአጭር ጊዜ አኳያ ካፒታልን ቆጥቦ ፈጣን እድገት በማረጋገጥ ከልማቱ ሕዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን፣ ከመካከለኛና ረዥም ጊዜ አኳያ ልማታዊ ባለሀብት የሚፈራባቸው ምንጮች ሆነው ከማገልገላቸው ባሻገር ሀገራችን ባላት ውስን ካፒታልና ቴክኖሎጂ በመጀመር ደረጃ በደረጃ የካፒታልና ቴክኖሎጂ አቅምን በማጠናከር በማያቋርጥ የፈጠነ እድገት ኡደት ውስጥ ለመግባት የሚያስችል እንዲሆን ይደረጋል።
- አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥና በውጪ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የማያቋርጥ የኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ አሟጦ እንዲጠቀሙ የተለያዩ አማራጮች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የመሸጫ ማዕከላትን በተመጣጣኝ ኪራይ እንዲጠቀሙ ገንብቶ የማቅረብ፣ የማምረቻ ማሽንና ስራ ማስኬጃ ብድር ለማቅረብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል።
- በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ተደራጅተውም ሆነ በግላቸው የሴቶችንና ወጣቶችን ተጠቃሚነት አሁን ካለበት ደረጃ በዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ 50 በመቶ ማድረስ እና የአካል ጉዳተኞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

3.4. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፥

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለመምራት የሚችል አቅምና የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ ለኮንስትራክሽን ኢንዳስትሪ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን የመፈተሽ፣ የማላመድና የማስረጽ ሥራዎች በስፋት በማከናወን፣የፕላን ስምምነትና ይዞታ ማጣራት ስራዎችን በማገናዘብ እና ዲዛይን በመገምገም በልዩ ትኩረት ይፈጸማል። ለግንባታ ፕሮጀክቶች የቅደመ ዲዛይን ጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ ከአካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋዊያን ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ እና ግንባታዎች ደረጃቸውን ጠብቀው በጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ማስቻል የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል።
- ክልላዊ ፈጣን እድገትን ተከትሎ የሚፈጠሩ የገጠር አገልግሎት ማዕከላት እድገታቸውን በስኬች ፕላን በመምራት ሀገራዊ ሰውነት በመስጠት እና ከተሞች ከደረሱበት እድገት አኳያ በመስፈርት ላይ በተመሰረተ አግባብ በመፈረጅ ከነዋሪው አዳጊ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አገልግሎት በማቅረብ ያልተማከለ፣ የተመጣጠነ እና ፍትሃዊ የአከታተም ሥርዓት የመገንባት አቅጣጫ መከተል፣ እንዲሁም ክልል አቀፍ ስፓሻል ፕላን ጋር የተቀናጀ የተለያየ ዓይነት የከተማ ፕላን ጥራቱን የጠበቀ በማዘጋጀት የከተማ-ከተማ እና የከተማ-ገጠር ትስስርን በማጠናከር እና የዕቅድ ትግበራ ክትትልና ግብረመልስ ስርዓቱን በማዘመን ነዋሪው ንቁ ተሳታፊና ባለቤት የማድረግ አቅጣጫ መከተል ነው።
- አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩን በከተሞች መስፋፋት ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግና በከተሞች መሬትን በቁጠባ መጠቀምን የሚያጠናክር በቂ የካሳና መልሶ ማቋቋም ድጋፍ በመስጠት ለልማቱ መሬት በበቂ መጠን በቀጣይነት የሚቀርብበት አቅጣጫ መከተል በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን በመረጃ ላይ የተመሠረተና ዘመናዊነትን የተላበሰ የመሬት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት በመሬት ዙሪያ ያሉ የሌብነት ምንጮችን የመለየትና የማድረቅ ስራ መስራት ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው።
- በከተሞች የመኖሪያ ቤት ፍላጎት መጨመርና የአቅርቦት ማነስ ችግርን ለመቅረፍ የተለያዩ የቤት ልማት አማራጮች መጠቀም፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ለዜጎች ሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ ቅንጅታዊ አሰራር በመከተል፣ የቁጠባ ባህል በማሳደግ፣ የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ እና በገጠር የልማት ማዕከላት የተሻሻሉ መኖሪያ የቤቶች ግንባታ ፕሮግራሞች በማስቀጠል ደረጃ ማስጠበቅ፣ የቤት አቅርቦትን ከባለቤትነት በተጓዳኝ የኪራይ አማራጭንም እንዲያድግ መስራት፣ በቤት ልማት የግል ዘርፉ ሚና ማጎልበት፣ የቤቶች መረጃና አስተዳደር በማዘመን ህገወጥነትን መከላከል እና የመንግሥት ቤቶች የይዞታ ዋስትና በማረጋገጥ የቤት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ቀጣይነት ማረጋገጥ ይሆናል።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በክልሉ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽ ኢንዱስትሪ በመገንባት ኢንዱስትሪው በክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትንና መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የሚኖረውን ሚና ከፍ ለማድረግ እና በየምዕራፉ ለሚዘጋጁት የኮንስትራክሽ ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች ዝግጅትና ትግበራ አቅጣጫ ቀያሽ ወይም ፍኖተ ካርታ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል።
- በክልሉ እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ሊሸከሙ የሚችሉ ተወዳዳሪ እና በጥላን የሚመሩ ከተሞችን መፍጠር። በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ አዳጊ፣ተናባቢና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ ካዳስተር ሲስተም በማስደገፍ፣ የመሬት ይዞታ ምዝገባውን በሃገር አቀፍ ስታንዳርድ መምራት እና በዕቅድ ዘመን ዘርፉ የዜጎችን የንብረት ዋስትና በማረጋገጥ የከተሞችን የኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያግዝ ማድረግ።
- ፍላጎትን መሰረት ያደረገ፣ ልማትን የሚያፋጥን፣ ወጪን የሚያስመልስና ፍትሀዊነትን የሚያሰፍን የመሬት ዝግጅትና አቅርቦትን ማረጋገጥ።
- በክልሉ በሚገኙ ከተሞችና የገጠር ማዕከላት እያደገ የመጣውን የቤት ፍላጎት ደረጃውን የጠበቀና ተደራሽነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓትና አቅም በመፍጠር ዘላቂነት ያለው የመኖሪያና መስሪያ ቤት አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀርብ ማድረግ።
- በተደራጀና በነቃ የከተማ ህዝብ ተሳትፎ የከተሞች የአካባቢ ልማት፣ የመሰረተ ልማትና አስተዳደር፣ የቆሻሻ አስተዳደር፣ የአረንጓዴ መሰረተ ልማትና አስተዳደር እና የከተማ ውበት በማሻሻል፣ እንዲሁም በከተማ ነክ ሙያዎች የሰው ሃይል ልማትን በማጠናከር ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን በማዘመን የተገልጋይ እርካታ ማረጋገጥ ነው።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎችን የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

የኮንስትራክሽን ስራዎች፡-

- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ተቋማት የ9793 ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲጠኑ የተፈጥሮ አካባቢ ተፅዕኖን ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ክትትል ይደረጋል። በአማካሪ የማይሸፈኑ 9395 መካከለኛና አነስተኛ ግንባታዎች የተፈጥሮ አካባቢ ተፅዕኖን ግምት ውስጥ ያስገቡና 100% ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋዊያን ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው የተሟላ ዲዛይን የማዘጋጀት ስራ ይሰራል። 401 ከፍተኛ ደረጃ ላላቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች የአማካሪ ግዥ የሚሆን ሰነድ በማዘጋጀት የከፍተኛ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ዝግጅትና ጥራት ክትትል ስራዎች በቅንጅት በማድረግ በግንባታዎቹ ለሚሳተፉ የግንባታ ሰራተኞች ደህንነት መጠበቂያና መከላከያ አልባሳትና መሳሪያዎች እንዲሟሉ ይደረጋል። በተለያዩ ምክንያቶች ተጀምረው ሳይጠናቀቁ የቀሩ እና የግንባታ ሂደታቸው የተጓተቱ ፕሮጀክቶች የውለታ አስተዳደር ተግባር 100% በአዲስ መልክ ውለታ በመግባት ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል።

- የክልሉ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአከባቢ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት 80 በመቶ የሚሆነው በክልል ውስጥ ምርት እንዲሸፈን ይደረጋል። የክልሉን የአካባቢ የግንባታ ግብዓት ክምችት የሚያሳይ 10 የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት እና በክልሉ ውስጥ የሚለሙ 672 የካባ ቦታዎች ለግንባታ ተስማሚነታቸው በላብራቶሪ ፍተሻ ይረጋገጣል። በተጨማሪም በተመረጡ 16 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የኮንስትራክሽን ኦዲት በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው ውጤታማነቱ ይረጋገጣል።
- ለ13,927 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ባለሙያዎች፣ 4,895 ተቋራጮች እና 53 አማካሪዎች አዲስ ፈቃድ በመስጠት በዘርፉ የሚኖራቸው ሚና ከፍ እንዲል እና በክልሉ በሚለሙ የግልና የመንግስት ግንባታዎች 82,000 ለሚሆኑ ዜጎች (27,701 ሴት) የሥራ እድል እንዲያገኙ ይደረጋል።

የከተሞች ፕላን ስራዎች፡-

- አንድ ክልል አቀፍ የልማት ፕላን ነዋሪውን እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ይዘጋጃል። የከተሞችን ፈርጅ መሠረት ያደረገ የተለያየ ዓይነት 442 ፕላን በሕብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት የመሬት አጠቃቀም ምጣኔ ተከትሎ የሚዘጋጅ ሲሆን ፕላኑን ለመተግበር እንዲያመች 122 የሰፈር ልማት ፕላን፣ በ20 ከተሞች አርባን ዲዛይን እና የገቢ መሠረታቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ለ383 ከተሞች የቦታ ደረጃ ፕላን ጥናት ይዘጋጃል። የገጠር አገልግሎት ማዕከላት በጅምሩ እድገታቸውን በፕላን ለመምራት የሚያስችል 907 ስኬች ፕላን ይዘጋጃል። የተዘጋጁ ፕላኖች በአግባቡ መውረዳቸውን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል።
- ክልላዊ የከተሜነት ደረጃ ቀደም ሲል ከነበረበት 25 ከመቶ ወደ 31 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል። ለ200 የገጠር አገልግሎት ማዕከላት የከተማነት እውቅና ጥናት፣ ለ174 ከተሞች የፈርጅ ለውጥ ጥናት፣ ለ50 ከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ጥናት (Urban Base Line Study) እና ለ100 ከተሞች መሠረታዊ መረጃ ፕሮፋይል ጥናት ይዘጋጃል። በተጨማሪ ለ50 ከተሞች እህትማማች ግንኙነት እንዲፈጥሩ ይደረጋል፤ እንዲሁም 100 አዲስ ከተሞች የማደራጀትና የማዋቀር ሥራ እና 6 የሕግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋል።

መሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎች ፡-

- የመሬት ፍላጎቱን ቢያንስ 75 በመቶ እንዲዘጋጅና እንዲቀርብ በማድረግ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚዉል 24,473 ሄ/ር የለማ የከተማ መሬት እና 3,906 ሄ/ር መሬት ለተለያያዩ አገልግሎቶች እና በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለሚነሱ ባለመብቶች ምትክ ቦታ ባንክ የሚደረግ በድምሩ 28,379 ሄ/ር መሬት ተዘጋጅቶ 24,886 ሄ/ር መሬት ለልማት ይተላለፋል።
- በሁሉም ከተሞች ሽንሻኖ አልባ (ቅርጽ የሌላቸዉ)፣ ከደረጃ በታችና በላይ የሆኑ ይዞታዎችን በየከተማዉ በጥናት በመለየትና የጥናት ሰነድ ዉጤት መረጃዎችን በማጠቃለል ይዞታዎች ላይ LDP/በሰጥቶ መቀበል መርህ/

የማስተካከያ ዉሳኔ እየተሰጠ በከተማዉ ፕላን ስታንዳርድ መሰረት ማሰተካከያ እርምጃ ተወስዶ ወደ ልማት እንዲገቡ ይደረጋል።

መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ስራዎች፡-

- የካዳስተር እና የመሬት ይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተናባቢ፣ ወጥና ተመጋጋቢ ሆኖ እንዲገነባ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን 58 ከተማ አስተዳደር ከተሞችን ወደ ካዳስተር ሥርዓት ለማስገባት የሚያስችሉ የኦርቶፎቶ ዝግጅት እና የጂኦደቲክ መረብ ማስፋፊያ ስራዎች ይሰራሉ።
- በ58 ከተማ አስተዳደር ከተሞች 600,000 ቁራሽ መሬቶች በተቀመጠው ሀገራዊ ስታንዳርድ መሠረት ይረጋገጣሉ። ከተረጋገጡት ቁራሽ መሬቶች ውስጥ 520,000 ይዞታዎች በሃርድ ኮፒና በለማው ሃገራዊ ሶፍትዌር በመታገዝ ተመዝግቦ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል። በ18 ነባር የከተማ አስተዳደር ከተሞች 100,000 ይዞታዎች በለማው ሃገራዊ ሶፍትዌርና በሃርድ ኮፒ በመታገዝ የሚመዘገብ ሲሆን ቀሪ 40 ከተማ አስተዳደር ከተሞች 420,000 ቁራሽ መሬቶች በሃርድ ኮፒ ይመዘገባል። እንዲሁም በ18 ነባር ከተማ አስተዳደር ከተሞች ዘመናዊ የአድራሻ ሥርዓት ይዘረጋል።

ቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች፡-

- በከተሞች የቤት አቅርቦት መጠን አሁን ካለበት ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ 221,467 ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል። በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 22 በመቶ (48,386) ፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ወጪ ቆጣቢ 4 በመቶ (8,757) ፣ በግለሰቦች 68 በመቶ (150,005) ፣ በሪል ስቴት ገንቢ ባለሀብት 2 በመቶ (5,007) ፣ በመንግስትና በግል ባለሀብት አጋርነት 1 በመቶ (2,474) ፣ በተቋማት ፍላጎትና ፋይናስ 1 በመቶ (2,285) እና የደሃ ደሃ ቤት አቅርቦት 2 በመቶ (4,553) ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል።
- በከተማና በገጠር ማዕከላት 258,935 ቤቶች ግንባታ ለ53,400 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና 82,041,000 ብር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል።
- በከተሞች 20,417 የመንግስት ቤቶች መረጃ የማደራጀት፣ለ4,586 የመንግስት ቤቶች ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው የማድረግና እና 5,251 የመንግስት ቤቶች ጥገና ይደረጋል።

የማስፈጸም አቅም ግንባታና አካባቢ ልማት ስራዎች፡-

- በ50 ከተሞች ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ እንዲዘምን በማድረግ የነዋሪው እርካታ አሁን ካለበት 50 በመቶ ወደ 85 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል። በዘርፉ ለተሰማሩ 5,500 ኢንተርፕራይዝ አባላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ይደረጋል።

- የከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ፣መንግስትና አጋዥ ድርጅቶች በገንዘብ፣ በጉልበትና በእውቀት የሚሳተፉበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የነዋሪው የልማት ተሳትፎ አደረጃጀት በሁሉም ከተሞች የሚከናወን ሲሆን ለመሰረተ ልማትና አካባቢ ልማት የሚያስፈልገው በጀት በየአመቱ 35% በህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡
- የ171.26 ኪ.ሜ የአዲስ አስፋልት መንገድ ግንባታ፣የ1,252.30 ኪ.ሜ የኮብልስቶን ንጣፍ መንገድ ግንባታ፣ 16,046.63 ኪሜ አዲስ መንገድ ከፈታና ጠረጋ እንዲሁም የ6,490.44 ኪ.ሜ የአዲስ ጠጠር መንገድ ግንባታ ይከናወናል፡፡ የ100.87 ኪ.ሜ የነባር አስፋልት መንገድ ጥገና፣194.69 ኪሜ ኮብልቶን መንገድ ጥገና፣ የ4222.74 ኪ.ሜ የነባር ጠጠር መንገድ ጥገና፣የ1275 ኪ.ሜ የጎርፍ መከላከያ ክትር፣ የ 5,015 ኪ.ሜ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ግንባታ እና 1,280 ድልድይና ካልቨርት ይገነባል፡፡ 10,826.44 ኪሜ የመንገድ መብራት፣ 11852.33 ኪሜ የውሀ መስመር ዝርጋታና እና በቁጥር 1,169 የውሀ ቦኖ ይገነባል፡፡
- በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሽፋንን ካለበት 19 ከመቶ ወደ 30 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል፣ በከተሞች 692,112,347 ችግኞች ተከላና እንክብካቤ ይደረጋል፡፡የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሽፋን ከነበረበት 64% ወደ 90%፣ የኦርጋኒክ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ከነበረበት 28 ከመቶ ወደ 50%፣ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ 8 የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች /land fill/ ግንባታ ይከናወናል፡፡

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፥

- ምቹ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሁኔታ ለመፍጠርና ለማጠናከር የተሳለጠ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ የአሰራርና ሥነ ምግባር ኮድ የማዘጋጀት፣ ተቋማዊ አደረጃጀትና የኮንትራት አስተዳደርን የማጠናከር፣ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሰራርን የማስፈን እንዲሁም የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭነት የመቀነስ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።
- ከዲዛይን ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፕሮጀክቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን የቁጥጥር ሥርዓት የሚያጠናክር የኮንትራት አስተዳደርና የፕሮጀክት ማኔጅመንት አሰራርን የማዘመን ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል። የአቅም ግንባታና የመንግስትና የግል አጋርነትን በማጠናከር የግሉን ዘርፍ ሚና የማሳደግ ጥረቶች በስፋት ይከናወናሉ።
- በከተማና በገጠር ማዕከላት ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለማሳደግ የሚያስችል የቤት ልማት የፋይናንስ ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት አቅርቦት አማራጮችን የማስፋት ሥራ በአዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ይደረጋል። የመንግሥት ቤቶች መረጃን በአግባቡ ከቴክኖሎጂ አንጻር የቤቶች መረጃና አስተዳደር የማዘመን፣የመንግሥት ቤቶች መረጃ የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ተጠናክሮ የሚከናወን ይሆናል፡

- ከመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ አንፃር የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። በዘርፉ የሚታየውን የባለሙያ ዕጥረት ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች የትም/ት ተቋማት ጋር በቅንጂት በመስራት እንዲፈታ ይደረጋል። የፈጻሚው የክህሎት ክፍተት በሥልጠና እንዲሟላ ይደረጋል።

3.5. የማዕድን ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የማዕድን ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የክልሉን የማዕድን ሀብት አለኝታ ጥናት በወርቅ፣ በኢንዱስትሪ እና በጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ ትኩረት በመስጠት ጥናት የሚደረግ ሲሆን የማዕድን ዘርፉን መሰረት አድርገው ለሚቋቋሙ የማኑፋክቸሪንግ አንዱስትሪዎች እና የግብርና ግብዓት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ለወደፊት ኢንቨስትመንት አቅጣጫ አመላካች የሆነ ፍኖተ ካርታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።
- በከበሩና በከፊል በከበሩ በማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር የውጭ ምንዛሪ አቅምን ለማሳደግ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያሥችሉ ስልጠናዎችንና እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን ለማመቻቸት፣ ለዜጐች በተለይም ደግሞ ለወጣቶች የሥራ ዕድል የሚፈጠርበትን አሠራር የመዘርጋትና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይሰራል።
- በባህላዊ ደረጃ ለተሰማሩ ህጋዊ አምራቾች የአነስተኛ ማምረቻ ቴክኖሎጂ እና የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ ወደ አነስተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣ ከዘርፉ ልማት ህብረተሰቡ (በተለይም ሴቶች፣ ህጻናትና አካል ጉዳተኞች) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።
- ዘላቂ የሆነ የማዕድን ሃብት ልማት ለማስፈን የማዕድን ሥራው የአካባቢ ጥበቃን ያገናዘበ እንዲሆን እና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የማዕድን ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የማዕድን ዘርፍ ዋና ዓላማዎች የክልላችንን የማዕድን ሀብታችንን በተገቢው ደረጃ በማወቅ ለማልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የክልሉን ብሎም የሀገራችንን ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጡን ለማፋጠን ዘርፉ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማስቻል ነው። ይህን ጥቅል ዓላማ ዕውን ለማድረግም ዋና ዋና ስትራቴጂክ ዓላማዎች የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም የክልሉ የማዕድን ሀብት በጥናት መለየት፣ በዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪና የሃገር ውስጥ ገቢ ማሳደግ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለግብርና እና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ምርት አቅርቦትን እንዲሻሻል ማድረግ፣ በዘርፉ ኢንቨስትመንት ማሳደግ፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ከማረጋገጥ አንጻር የበኩሉን እንዲወጣ ማድረግ እና ተቋማዊ አቅም ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የማዕድን ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የጌጣጌጥ ማዕድናት ምርት አሁን ከደረሰበት 32 ቶን ወደ 763 ቶን ከፍ እንዲል ለማድረግ እና የክልሉን የማዕድን ሃብት አለኝታ አመላካች ሽፋን አሁን ካለበት 45.4% ወደ 70% ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም በማዕድን ፍለጋ እና ማምረት ሥራ ላይ እንቨስት የሚያደርጉ ባለሃብቶች ቁጥር አሁን ከደረሰበት 115 ወደ 196 ለማሳደግ ታቅዷል።
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ የግንባታ ማዕድናት ምርት አቅርቦትን አሁን ከደረሰበት 21.59 ሚሊዮን ሜ. ኩብ ወደ 89 ሚሊዮን ሜ. ኩብ፣ እንዲሁም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ማዕድናት አቅርቦቱን አሁን ካለበት 111,833 ቶን ወደ 465,652 ቶን ለማሳደግ ታቅዷል።
- የማዕድኑ ዘርፍ ለሥራ አጥ ወጣቶች የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል አሁን ካለበት 107,305 (ሴት 17,225) ወደ 307,000 (ሴት 36,217) የማሳደግ እና ከማዕድኑ ዘርፍ ለክልሉ የሚሰበሰበውን የውስጥ ገቢ አሁን ከደረሰበት 203 ሚሊዮን ብር ወደ 0.5 ቢሊዮን ብር ከፍ እንዲል የማድረግ ስራ ይሰራል። እንዲሁም የዘርፉን የሰው ሃይል አሁን ካለበት 38% ወደ 95% ለማድረስና የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የማዕድን ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- የማዕድን ኢንቨስትመንት ሥራ ከአካባቢ ብክለት የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግና በሚለማው ማዕድን አካባቢ የሚገኘውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ ይደረጋል
- ከከፍተኛ ትምህርትና ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር ለዘርፉ ጥናት፣ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ባለሙያዎችን የማፍራት እንዲሁም ብቁና በቂ ባለሙያዎችን በዘርፉ ማቆየት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል

3.6. የንግድና ገበያ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ገበያ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የህግ ማዕቀፎችን ከወቅታዊ ተለዋዋችጭ ሁኔታዎች ጋር በማሻሻል የመቅረጽ፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የማዘመን ስራ አጠናክሮ በመቀጠል አገልግሎት አሰጣጥን ግልጽና ቀልጣፋ የማድረግ፣ የንግድና የግብይት ህጎችን በማስከበር ህጋዊ የንግድ ውድድርን በማጎልበት ለኢኮኖሚ ዕድገት ዘርፉ የበኩሉን እንዲያበረክት የማድረግ፣ በህጉ መስረት የሸማቾችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል የሚመለከታቸውን አካላት ግንዛቤ፣ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራል።

- የንግድ ግብይትና የገበያ መረጃ ለማዘመን መሰረተ-ልማት አቅርቦቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ የግብርና ምርት ግብይት የውጭ ምንዛር እንዲያስገኙ በብዛት፣ በዓይነትና በጥራት ለገበያ እንዲቀርቡ ገበያ የማመቻቸት፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስራዎች፣ እንዲሁም ህገ-ወጥ ንግድንና ግብይት መከላከል የሚያስፈልግ የክትትል፣ መረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲሰሩ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ገበያ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በንግድና በግብይት ዘርፍ ህጋዊና ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ምቹ የንግድ ስርዓት እና ጤናማ የገበያ ዉድድርን በመፍጠር የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን፤
- ዘመናዊ የግብርና ምርት ግብይት መሰረተ-ልማት በማስፋፋት የከተማና የገጠር እና የከተሞች የእርስ በርስ ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ እንዲሁም ለውስጥና ለውጭ የገበያ ትስስርን በመፍጠር የግብርና ምርቶችን በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣
- መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች አቅርቦትና ስርጭት ፍትሃዊና ወቅታዊ በማድረግ የሸማች ህብረተሰብ ተጠቀሚ እንዲሆኑ ማስቻል እና በሕግ መሰረት ለሸማቹ ጥበቃ ማድረግ እና
- የንግዱ ማህበረሰብንና የሸማቹን ኅብረተሰብ አደረጃጀቶችን በመደገፍና በማጠናከር የህዝቡንና የነጋዴውን ተሳትፎ በማሳደግ ለዘርፉ ዕድገት አጋዥነታቸውን እንዲረጋገጥ ማድረግ የተቀመጡ የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ገበያ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ህግ መሰረት የንግዱ ማህበረሰብ መሥራት እንዲችሉ ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ከማጠናከር አንጻር በክልሉ በሚገኙ 110 ከነበረበት አዲስ 94 በመጨመር ወደ 204 አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የኦን ላይን ስርዓትን ለመዘርጋት፤ በክልሉ 391,078 አዲስ ንግድ ምዝገባና 420,122 አዲስ ንግድ ፈቃድ በመስጠት እና 2,874,757 ንግድ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት የመስጠት ሥራ የሚሰራ ሲሆን የንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች 102 ከነበሩበት 50 በመጨመር 152 ማድረስ እና የነጋዴ ሴቶች ማህበራት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ የሚደረግ ሲሆን 84 አዳዲስ ማህበራትን በመጨመር አሁን ካለበት 85 ወደ 169 ማህበራት የማሳደግ ሥራ ይሰራል። በተጨማሪም በክልሉ ለሚቀርቡ ድርጅቶች የካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ለማካሄድና መረጃቸውን ለማደራጀት በታቀደው መሠረት በየዓመቱ በ2.5% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 3,611 ካፒታል ዕቃዎች የመመዝገብና መረጃ የማደራጀት ስራ ይከናወናል።
- የንግድና ግብይት ሕጎች የማስከበር ሥራዎችን ከማጠናከር አኳያ የንግድና የግብይት ሕጎችን የማስከበር ሥራዎች ከማጠናከር አንጻር የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ በሀገሪቱ ህግ መስፈርቶች መሰረት ስለመከናወኑ 3,324,533 ፋይሎች በ10 ዙር ኢንስፔክት በማድረግ ስህተት የሚገኝባቸው ፋይሎች ወደ 0% ለማድረስ፣

በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች በሀገሪቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሕግ እና በሌሎች የንግድና ግብይት ህጎች መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው በ40 ዙር የውጪ ኢንስፔክሽን በማድረግ 3,331,406 የንግድ ድርጅቶች በመቆጣጠርና እርምጃ በመውሰድ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን 16% ከነበረበት ወደ 6% እንዲቀንስ ለማድረግ፣ እንዲሁም የንግድ ስነ-ልክ መሳሪያዎችን ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ በ40 ዙር በ1,019,578 የስነ-ልክ መሳሪያዎች ላይ ምርመራ በማካሄድና እርምጃ በመውሰድ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን 20% ከነበረበት ወደ 5% እንዲቀንስ ለማድረግ ታቅዷል።

- **በንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግብይት ላይ የዋጋ ፍትሃዊነት የማስጠበቅ ሥራዎችን** ከማጠናከር አኳያ፡- ከመሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 3,485,765 ኩ/ል ስኳር፣ 2,345,737 ኩ/ል ስንዴ እና 427,015,482 ሊትር የምግብ ዘይት እንዲቀርብና እንዲሰራጭ የሚደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ 7,035 አሰራጮችን ክትትል በማድረግ ቅሬታ በሚቀርብባቸው ላይ 100% እርምጃ ይወሰዳል።
- ህግን በተፃረረ መልኩ በንግድ ዕቃዎች ላይ ግብይት በሚፈጽሙና አስገዳጅ የኢትዮጵያ የጥራት ደረጃ ምልክት ያላቸው ምርቶች መሆናቸውን በማረጋገጥ በየዓመቱ 5% በማሳደግ በዕቅዱ ዘመኑ መጨረሻ 1,357,314 ንግድ ድርጅቶችን ክትትል በማድረግ ከደረጃ በታች በተገኙ ምርቶችና ድርጅቶች ላይ 100% እርምጃ ይወሰዳል።
- **የሸማቾች ጥበቃ ሥራዎችን ከማጠናከር አንፃር፡-** በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅና ደንብ ላይ በየዓመቱ በ20% የሸማች ህ/ሰብና የንግዱ ማ/ሰብ፣ በ2% የባለድርሻ አካላትና የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት አመራር አካላት ግንዛቤ በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 3,763,479 ሸማች ህ/ሰብ ፣ 907,793 ንግዱ ማ/ሰብ፣ 34,175 ባለድርሻ አካላት እና 11,489 ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት አመራር አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፤ እንዲሁም የሸማች ሲቪክ ማህበራትና ክበባት እንዲቋቋሙ ግንዛቤ ለመፍጠርና ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በየዓመቱ በ10% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 81 ሲቪክ ማህበራት እና 818 ሸማች ክበባት እንዲቋቋሙ ይደረጋል።
- ዘመናዊ የንግድ ግብይት ማዕከላትን በማስፋፋትና በማጠናከር የገበያ መረጃ አቅርቦትና ስርጭት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የግብርና ምርት ግብይት ማዕከላት በታቀደው መሠረት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 5 ሁለተኛ እና 16 አንደኛ ደረጃ የግብርና ምርት ግብይት ማዕከላት እንዲቋቋሙ ይደረጋል። በከተሞች ዘመናዊ የንግድ ግብይት ማዕከላት በግሉ ባለሀብት እንዲገነቡና እንዲጠናከሩ ቴክንካዊ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በየዓመቱ 5% አዲስ እና 10% ነባር ዘመናዊ ግብይት ማዕከላትን በማጠናከር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 221 አዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ እና 1,686 ነባር ማዕከላት እንዲጠናከሩ ይደረጋል።
- በከተሞች ነባር ዘልማድ ገበያ ማዕከላት ለንግድ ግብይት ምቹ እንዲሆኑ የህግ ማዕቀፍና ቴክንካዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ 20%ቱን ደረጃ በማሻሻል በየዓመቱ 10% በማሳደግ 1,020 አዲስ ዘልማድ ገበያ ማዕከላት

በማቋቋምና 1,767 ነባር ዘልማድ ገበያ ማዕከላት በማጠናከር እንዲሁም ከነባሩ 20% ደረጃቸውን በማሻሻል በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 353 ማዕከላት ደረጃ እንዲሻሻል ይደረጋል።

- ከንግድና ግብይት ማዕከላት የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ወቅታዊ የገበያ መረጃ በዘመናዊ መንገድ ለግብይት ተዋናያን በዙር ለማቅረብ በታቀደው መሠረት በየዓመቱ በ2% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ከ1,682 ግብይት ማዕከላት 477 ዙር መረጃዎችን በመሰብሰብ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲሰራጩ ይደረጋል፤ እንዲሁም በከተሞች የባዛርና ኤግዝቢሽን ዝግጅቶች የሚካሄዱበት ማዕከላት የሚለሙበት የህግ ማዕቀፍና ቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 9 ማዕከላትን ለማደራጀት የባዛርና ኤግዝቢሽን ዝግጅቶችና ፕሮሞተሮች ምዝገባ በየዓመቱ በ5% በማሳደግ 408 ዝግጅቶች ፈቃድ የመስጠትና 161 ፕሮሞተሮች የመመዝገብ ስራ ይከናወናል።
- **የሰብል ምርቶችን** በጥራትና በመጠን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ ትስስር ከመፍጠር አንፃር የአገዳ፣ የብርዕ፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት፣ የጥጥ፣ የእጣንና ሙጫ እና የጫት ምርቶችን በየዓመቱ በ1.5% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1,975,174ቶን የአገዳ፣ 3,433,575ቶን የብርዕ፣ 1,999,485ቶን የጥራጥሬ፣ 103,407ቶን የቅባት፣ 149,193ቶን የጥጥ፣ 1,161ቶን የእጣንና ሙጫ እና 76,473 ቶን የጫት ምርት፣ በየዓመቱ በ1.75% በማሳደግ 1,621,623ቶን የፍራፍሬ፣ 1,842,498ቶን የአትክልት፣ 2,985,014ቶን የስራስር እና 256,985ቶን የእንሰት ምርቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን የቅባትና ጥራጥሬ ምርቶችን በየዓመቱ በ1.5% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 49,990 ቶን ሰሊጥ፣ 2,771ቶን ዱባ ፍሬ፣ 164,078ቶን ቀይ ቦለቄ፣ 427ቶን ነጭ ቦለቄ፣ 64,751ቶን ዝንጉርጉር ቦለቄ፣ 38,860ቶን የእርግብ አተር እና 40,005ቶን ማሾ ምርቶች እንዲሁም በየዓመቱ በ1.75% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 61,868ቶን የሙዝ ምርት ለውጭ ሀገር ገበያ ትስስር ይፈጠራል።
- **እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን** በጥራትና በመጠን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ ትስስር መፍጠር አንፃር የቁም እንስሳት ገበያ ትስስር በየዓመቱ በ10% በጥራትና በመጠን በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ የዳልጋ ከብት በቁጥር 6,781,235፣ ጋማ ከብት 540,035 እና በግና ፍየል 12,488,608 ለሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር የሚፈጠር ሲሆን የዶሮ ትስስር በየዓመቱ በ10% እና የዓሳ ምርት ትስስር በ5% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 12,380,005 ዶሮ እና 90,587ቶን ዓሳ ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር ይፈጠራል። የማርና ሰም ምርት በ5%፣ የወተት ምርት በ20% እና ቅቤ በ10% በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 52,290 ቶን ማርና ሰም፣ 15,294,176ሊትር ወተት እና 67,464ቶን ቅቤ ለሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር ይፈጠራል። እንዲሁም በ2.5% የዳልጋ ከብት፣ 5% በግና ፍየል፣ 2.5% ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ በ3% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በቁጥር 252,577 ዳልጋ ከብት፣ 2,318,052 በግና ፍየል፣ 6,714,406 ጥሬ ቆዳ እና 16,575,089 ሌጦ ለኤክስፖርት ቄራዎችና ለተለያዩ ላኪ ድርጅቶች የውጭ ሀገር ገበያ ትስስር እንዲፈጠር የሚደረግ ሲሆን በሀገር

ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ በእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርቶች የግብይት ተዋንያንን በገበያ ትስስሩ ተጠቃሚ ለማድረግ በየዓመቱ በ10% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 315,148 ግብይት ተዋናንያን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ገበያ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- የንግዱ ዘርፍ በአሠራር፣ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት እንዲጠናከር ይደረጋል። ከዚህም አንጻር ቅንጅታዊ አሰራርን የማጎልበት፤ የሥራ አመራርና የቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባትና የንግድ አሠራር ምቹነትና የሪፎርም ሥራዎችን ውጤታማ የማድረግ ሥራዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ። በተጨማሪም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን የማዘመንና በጥናት ላይ የተመሠረተ የግብይት ሰንሰለትና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ይካሄዳሉ። ህገ ወጥ ንግድን በተጠናከረ መልኩ ለመቀነስ የተሻሻለ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል። አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድና ገበያ መረጃ ሥርዓት ይገነባል።
- ንግድን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች እንዲዘምኑ፣ ዲጂታል መር የሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍንና መሰረታዊ የሆኑና ለንግድ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ አስፈላጊው ፋይናንስ እንዲቀርብ፣ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጠናከር ይደረጋል።

3.7. የኢንቨስትመንት ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢንቨስትመንት ስራዎች የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የክልሉን ተወዳዳሪና ተነጻጻሪ የኢንቨስትመንት ሀብት በጥናት በመለየት የክልሉን እምቅ ሀብትና ምቹ ሁኔታዎች በማስተዋወቅ እና የተለያዩ የኢንቨስትመንት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት እንዲሁም የተዘጋጁ መድረኮችን በመጠቀም የማህበረሰቡን፣ የአስፈጻሚውን እና ፈጻሚውን ብሎም የባለሀብቱን ግንዛቤ በማዳበር የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር እና እንዲስፋፋ በማድረግ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወት ይደረጋል።
- ተወዳዳሪ የሆኑና ለኢኮኖሚው አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ልማታዊ ባለሀብቶች አንዲያብቡ ልዩ ድጋፍ በማድረግ በክልሉ ብሎም በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።
- የክልሉን አማራጭ የኢንቨስትመንት ዕድሎችና ንፅፅራዊ ጠቀሜታ ላይ መሰረት ያደረገ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ለልማታዊ ባለሀብቶች የሚሰጡ ድጋፎችና ማበረታቻዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል።
- የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በብዛት በመሳብ የካፒታል ክምችት መፍጠር፣ የክልሉን አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠንና የህብረተሰቡን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

- በወጪና ተኪ ምርቶች ላይ የሚሰማሩ ልማታዊ የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ ማጎልበት፣ በግብርናና አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ነባርና አዲስ ባለሀብቶች ወደ አምራች ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ በማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመደገፍና በመከታተል ወደ ሙሉ ትግበራ ማሸጋገር እንደ ዋና ትኩረት አቅጣጫ ተወስደዋል፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢንቨስትመንት ስራዎች ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በክልሉ የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድሎችና ንጽጽራዊ ጠቀሜታ ላይ ያነጣጠረ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት በማስፋፋት የተፈጥሮ ሀብታችንን ጥቅም ላይ በማዋልና በማልማት፣ የወጪ ምርቶች ገበያን በማዳበር፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር በማድረግ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር የክልሉን ህዝቦች የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ ዋና ዓላማ ተደርጎ ተለይቷል፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢንቨስትመንት ስራዎች ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የክልሉን ተወዳዳሪና ተነጻጻሪ የኢንቨስትመንት ሀብት በጥናት በመለየትና መረጃ ተደራሽ በማድረግ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር 353 ባለሀብቶችን በቀጥታ በግንባር በመገናኘት፣ 4,582 የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም የፕሮሞሽን ስራ በመስራት በጠቅላላው 4,935 ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ይሠራል፡፡
- በተለያዩ ዘርፎች ለባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት እና ከማሰማራት አንፃር፡- በግብርና 1,419፣ በኢንዱስትሪ 1,460 እና በአገልግሎት 2,056 በጠቅላላው 4,935 ባለሀብቶች በ10 አመት ውስጥ ፈቃድ በማውጣት ወደ ኢንቨስትመንት ይሰማራሉ፡፡ ለ256 ባለሀብቶች የማስፋፊያ ፈቃድ በመስጠት ብር 161.18 ቢሊዮን ካፒታል በመመዝገብ ለ783,107 የስራ እድል ይፈጠራል፡፡
- አዲስ ፈቃድ ያወጡ 4,945 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በመረጃ ቋት ማደራጀት እና የፕሮጀክቶችን መረጃ 43,539 ጊዜ ወቅታዊ የማድረግ ስራ በመስራት 3,260 የተተነተነ መረጃ ለተጠቃሚ የመስጠት ስራ ይሰራል፡፡
- በጋይድ ማፕ ተደግፎ የተዘጋጀ 43,424 ሄ/ር አዲስ የገጠር የኢንቨስትመንት መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን 82,700 ሄ/ር መሬት በመለካት ከይዞታ ማረጋገጫ ካርታና ከምስክር ወረቅት ጋር የማሰረከብ ስራ ይከናወናል፡፡

- በዕቅድ ዘመኑ የክልሉን የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል በተመለከተ 10 ጥናቶች የሚደረጉ ሲሆን የተገኘውን የጥናት ውጤት ተግባራዊ በማድረግ አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎችን የማስፋትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- በክልሉ በኢንቨስትመንት በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ተሰማርተው ለሚገኙ በግብርና 1,258፣ በኢንዱስትሪ 1,707 እና በአገልግሎት ሰጪ 1,584 በድምሩ 4,549 ፕሮጀክቶች ላይ 23,545 ዙር ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 2,775 ያህሉ ሙሉ በሙሉ ወደ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል።
- በፕሮጀክቶች አካባቢ የሚገኙ 60,601 የህብረተሰብ ክፍሎች (በዋናነት በግብርና) የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢንቨስትመንት ስራዎች ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- የልማት ሠራዊት ግንባታን ማስቀጠል፣ ዘመናዊ የመረጃና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የኢንቨስትመንት መማክርትና ምክክር መድረኮችን ማጠናከር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ግንዛቤ ማስጨበጥ እና የፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል እንዲጠናከር ይደረጋል።
- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጠት፣ የክትትልና ድጋፍ ተግባርን ቁልፍ ሥራ አድርጎ መረባረብ፣ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፣ የማስፋት ስትራቴጂን መከተል እና የኢንቨስትመንት ስራዎችን በልማታዊ ኮሚኒኬሽን መደገፍ እንደማስፈጸሚያ ስልት ተለይተዋል።

3.8 የባህልና ቱሪዝም ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባት በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በዕውቀት እና በክህሎት ማብቃት፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ ሕዝባዊ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ ዘመናዊና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መተግበሪያዎችን የማልማት ሥራ በትኩረት ይሰራል።
- የመሠረተ ልማት አቅርቦቶችን ለማስፋፋት የባህል ማዕከላት፣ የዕደ-ጥበባት መንደር፣ የቴአትርና ሙዚቃ ሥፍራዎች፣ የቱሪስት መረጃ ማዕከል፣የቱሪስት መዳረሻዎች (መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት አገልግሎት) ፣ ሀጋዊ በማድረግና በማዘመን፣ በማልማትና ለሥራ ምቹ ለማድረግ በትኩረት ይሰራል።
- በመሠረተ-ልማት አቅርቦ፣ በሰው ኃብት ልማት፣ በአማራጭ የፋይናንስ አቅም ማስፋት፣ በቴክኖሎጂ ማልማትና መጠቀም፣ ጥናትና ምርምር እና በህግ ማዕቀፍ ዝግጅት ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ

አሠራሮችን ማጠናከር የሚያስችል አቅጣጫ ተግባራዊ ይደረጋል።

- በዘርፉ ልማት ውስጥ የግል ዘርፍ ሚና ለማሳደግ የባለሀብቱን ተሳትፎ ማጎልበት፣ አማራጭ የሥራ ዘርፎችን መለየትና እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፣ የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር ትኩረት ይሰጣቸዋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- ዘርፉ ለክልሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ብልጽግና የሚኖረውን ጉልህ አስተዋጽኦ በማጎልበት የብሔሮች ብሔረሰቦችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ዋና ዓላማ ሲሆን የብሔሮችና ብሔረሰቦችን ቋንቋ፣ ሥነ ጥበብ፣ ባህል፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን ማጥናት፣ በዘለቄታዊነት መጠበቅ፣መሰነድ፣ ማልማትና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ፣ የህዝቦችን የእርስ በርስ ትስስርና አብሮነትን ማጠናከር፣ የሥራ ዕድልን ማስፋፋትና የቱሪስት ፍሰትንና ገቢን ማሳደግ፣ ለሰላም፣ ለአንድነትና ለብልጽግና የሚኖረውን ፋይዳ ማጎልበት ዝርዝር ዓላማዎች ናቸው።

የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ሀብቶች ልማትና ጥበቃ፡-

- ባህላዊ ቅርሶች በዩኔስኮ ከማስመዝገብ አንጻር 2 ቋሚ እና 2 የማይዳሰሱ በድምሩ 4 ቅርሶች እንዲመዘገቡ ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የጥናትና ምርምር፣ ዘለቄታዊ ጥበቃና እንክብካቤ፣ የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት እንዲሁም የተሟላ የምዝገባ ሠነድ የማዘጋጀት ሥራ ለማከናወን ታቅዷል። 112 የብሔሮችና ብሔረሰቦች መገለጫ የሆኑ የተሰበሰቡ የተደራጁና ለጉብኝት፣ለጥናትና ምርምር የበቁ ወካይ የኢትኖግራፊ ቅርሶችን በሙዚዬሞች በአግባቡ ማደራጀት፣ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ዘርፍን በዕውቀትና በክህሎት በማጎልበት የጥበቃና እንክበካቤ ሥራዎችን በማሳደግ በቁጥር 15 ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ቅርሶች ከሚመለከታቸዉ የባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለመመዝገብ ይሰራል።
- በክልሉ የሚገኙ 13,500 ቋሚ፣ ተንቀሳቃሽና የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን በአግባቡ በመመዝገብ መረጃውን በዳታ ቤዝ የማደራጀት ሥራ ለማከናወን እና በየደረጃዉ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለጉብኝት እና ለምርምር ለማብቃትና ለማስተዋወቅ በታችኛዉ መዋቅር በቁጥር 15 የሚሆኑ አነስተኛ ሙዝየሞችን ለማደራጀት፣ እንዲሁም በክልል ደረጃ አንድ ሁለገብ ክልላዊ ሙዝየም ለመገንባትና ለማደራጀት ታቅዷል።
- ከሚመለከታቸዉ የባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በየደረጃዉ 5000 ቋሚ ቅርሶችን፣ 10,766 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን እና 7,500 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን የመመዝገብ ፣ 1,450 ቋሚ ቅርሶችን፣ 5,000 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን እና 1,500 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ እንዲሁም 250 ቋሚ ቅርሶችን፣ 1,500 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን እና 300 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን የማልማት ስራ ይሰራል።

- የሀገር በቀል ዕውቀትና ሙያ እንዲሁም ባለሀብቶችን በማስተባበር 200 የሚሆኑ ጉዳት የደረሰባቸዉን ባህላዊ ቅርሶችን በመለየት በውስጥ እና በዉጭ አቅም እንዲጠገኑ የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን በክልሉ የሚገኙ ዓለም አቀፍ ቅርሶች ዘለቄታዊ የጥበቃና እንክብካቤ ስራዎችን ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተደራጀ መንገድ ለማከናወን ታቅዷል።
- በክልሉ በየደረጃው 100 የሚሆኑ ባህላዊ ቅርሶች ህጋዊ ሰዉነት እንዲያገኙ የማድረግ እና 25 በሚሆኑ ጥንታዊ ገዳማት እና መስጊዶች ውስጥ የሚገኙ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶችን የመጠበቅ ስራ የሚሰራ ሲሆን 30 ጥንታዊ የቋጥኝና የዋሻ ውስጥ ስዕሎች በአግባቡ ተለይተው እንዲታወቁና እንዲጠበቁ ይደረጋል።
- በመጥፋት አደጋ ላይ ያሉ 2 (ሙሩሌ እና ኦንጐታ) ቋንቋዎች እንዲያገግሙ በዘርፉ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት፣ ፕሮጀክት በመቅረፅና ፈንድ በማፈላለግ ለቋንቋዎቹ ቅድመ ልማትና መልሶ ማገገሚያ የሚሆኑ ሥራዎችን በማከናወን ያገገሙና ከመጥፋት የተታደጉ ቋንቋዎች ቁጥር ከ0 ወደ 2 ለማድረስ ታቅዷል።
- ሥርዓተ-ጽህፈት የተዘጋጀላቸውን የክልል ቋንቋዎች ከ33 ወደ 43፣ ሰዋሰው (Grammar) የተዘጋጀላቸው ቋንቋዎች ከ16 ወደ 26፣ ባህላዊ መዝገበ ቃላት የተዘጋጀላቸውን ቋንቋዎች ከ11 ወደ 20 እና ተጠንተው የታተሙ ቃላዊ ተረቶች፣ ስነ-ቃሎችና ወጎች በሰነድ አሁን ካለበት 62 ወደ 120 ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን አንድ የቋንቋ ምክር ቤት ለመመስረት እና አንድ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የቋንቋ ፕሮፋይል ለማዘጋጀት ታቅዷል።
- በየአመቱ በየደረጃዉ 24 የባህል ሳምንታት፣ ፌስቲቫልና ዓዉደ-ርዕይ በማዘጋጀትና በማክበር የባህል እሴቶችንና ሀብቶችን በተደራጀ መንገድ ለማስተዋወቅና ለማበልጸግ የታቀደ ሲሆን 10 የሚሆኑ ባህላዊ ክብረ በዓላትን በተደራጀ መልኩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የማልማትና የማበልፀግ ስራ ይሰራል።
- በየደረጃዉ የተለያዩ የጥናት፣ የንቅናቄና የማስተዋወቅ ሥራዎች በመስራት የሀገር በቀል ዕዉቀቶች አጠቃቀምን በቁጥር 25 የማሳደግና በክልል ደረጃ የክልሉን ብ/ብ/ሕዝቦች የሀገር በቀል እዉቀቶችን ፕሮፋይል የማዘጋጀት እንዲሁም በየደረጃዉ 1,000 የሚሆኑ ባህላዊ ተምሳሌቶች እንድለዩና እንዲመዘገቡ ይደረጋል።
- በየደረጃው 15 የባህል ማዕከል፣ በክልል ደረጃ 1 ሁለገብ የባህል ማዕከል፣ በታችኛዉ መዋቅር 50ና በክልል ደረጃ 1 ሁለገብ የህዝብ ቤተ- መፅሀፍት ቤቶች፣ በቀበሌያት 2500 የህዝብ ንባብ ቤቶች፣ በትምህርት ቤትና በተለያዩ ተቋማት100 የንባብ ክበባት እና 100 የባህልና ቅርስ ክበባትን ለማደራጀት፣ ለማጠናከር፣ ለመገንባት እና ለማቋቋም ታቅዷል።
- ለህዝብ እይታ የቀረቡ የትውን ጥበባት ከ371 ወደ 742፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን ለህብረተሰቡ ማቅረብ ከ2,049 ወደ 4,098፣ የሥነ ጥበብ አማተር ክበባት ከ107 ወደ 214፣ ክልላዊ የሙዚቃ ፌስቲቫል ከ6 ወደ 16 እና የስዕል፣ ፎቶግራፍ፣ ኤግዚብሽንና የሥነ ጥበብ ውድድር 147 ወደ 294 ለማሳደግ ታቅዷል።
- የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ማህበራት ከ79 ወደ 379፣ የተደራጁ የሥነ ጥበብ አማተር ክበባትን ከ107 ወደ 150 እና በየአስተዳደር እርከኑ የተዘጋጁ የባህል፣ የቱሪዝምና የኪነጥበብ

ፌሲቲቫሎችን ከ105 ወደ 150 ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን የቅጂና ተዛማጅ መብቶችን ለማስከበር ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት እና በየዓመቱ የባህል ምርት አምራቾችና አቅራቢዎች የማበረታቻ ሽልማት የማዘጋጀት ስራዎች ይሰራሉ።

- የኪነ ጥበብ አገልግሎት ያገኘ የሕብረተሰብ ብዛት ከ15,891,725 ወደ 45,892,000 (ሴት 22,946,000) እና የንባብ አገልግሎት ያገኘ የሕብረተሰብ ክፍል ብዛት ከ6,975,872 ወደ 18,976,000 (ሴት 8,976,000) ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን የማህበረሰብ ቱሪዝም የተጀመረባቸው ቦታዎችን ከ4 ወደ 8 ለማሳደግ ይሰራል።
- በየአመቱ የህዝቦችን አብሮነት እና ክልላዊና አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ 2 መድረኮች፣ የህዝቦችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠናክና የሚያቀራርቡ 24 የባህል ጉባዔና ስምፖዚየም እንዲሁም የህዝብ ለህዝብ መድረኮችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በተባበር የማካሄድ ስራ ይሰራል። በተጨማሪም በየአመቱ በክልል ደረጃ 1 የህዝቦች የጋራ ባህላዊ ዕሴቶች በመለየት፣ በመሰነድና በማስተዋወቅ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብርን ለማጠናከር ታቅዷል።

የቱሪዝም ሀብት ልማት፡-

- የተፈጥሮ መስህቦችና የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ጥበቃና ልማት በተመለከተ የተመዘገቡ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎችን አሁን ካለበት 396 ወደ 500፣ የተጠበቁ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች አሁን ካለበት 326 ወደ 376፣ የተቋቋሙ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች ብዛት አሁን ካለበት 10 ወደ 12፣ የማካለልና ዳግም ማካለል በማካሄድ ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አሁን ካለበት 6 ወደ 10፣ ዓመታዊ የአዞ ቆዳ አቅርቦት መጠን አሁን ካለበት 1,500 ወደ 3,000 እና የጫጩት ቅበላ መጠን አሁን ካለበት 1,200 ወደ 4,000 ለማሳደግ ታቅዷል።
- የአገር ውስጥ ቱሪዝምን በማስተዋወቅና የጉብኝት ባህል እንዲዳብር በማድረግ የጎብኚዎችን አሁን ካለበት 34,309,610 ወደ 90,000,000፣ የአገርህን እወቅ ክበባት አሁን ካለበት 1,000 ወደ 1,500 እና ክትትልና ድጋፍ ተደርጎላቸው የተጠናከሩ ነባር የአገርህን እወቅ ክበባት 728 ወደ 1200 እንዲያድግ ይደረጋል። የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚያስችል በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በዓመት አንድ ጊዜ የሀገር ውስጥ የጉብኝት ጉዞዎችን እና የንቅናቄ መድረኮች ለማዘጋጀት ታቅዷል።
- የዘርፉን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት አሁን ካለበት 30,303 ወደ 40,303፣ የጎብኝዎችን እርካታ መጠን ከ50% ወደ 90%፣ የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸውን የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ከ32 ወደ 70፣ ማድረስ፣ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውና የታደሰላቸው የዘርፉን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት ከ22,500 ወደ 30,000 ለማሳደግ ታቅዷል።

- በከተማና በገጠር ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ 10 ቦታዎችን በጥናት በመለየት እንዲከለሉና ጋይድ ማፕ እንዲዘጋጅላቸው፣ ከከተማ ወጣ ባሉ መዳረሻዎች በሎጅና በሌሎች ሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ማበረታቻዎችን በጥናት በመለየት ማጸደቅና ሥራ ላይ እንዲውል፣ የተፈጥሮ ሀብትና ፓርኮች አካባቢ ከግል ባለሃብቱ ጋር በመቀናጀት የመዳረሻ ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በቁጥር 5 ለማከናወን ይሰራል።
- የመዳረሻና መስህብ ልማት በተመለከተ 5 አዳዲስ የቱሪዝም ምርቶችን ለማልማት፣በ10 ነባር መዳረሻዎች ላይ ዕሴቶች ለመጨመር፣በቁጥር 5 ነባርና አዳዲስ የቱሪስት መስመሮችንና የለሙ መስህቦች በማስተዋወቅ ወደ ቱሪዝም ገበያ ለማስገባት፣ እንዲሁም ክልላዊ የቱሪዝም ፍኖተ ካርታ ሰነድ እና ክልላዊ የቱሪስት ደህንነት ክትትል ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዷል።
- የግብይትና ፕሮሞሽን ስራ በየዓመቱ በተመረጡ 2 አለም ዓቀፍ ትሬድፌር መድረኮች ላይ መሳተፍና 1 የትዉዉቅ ጉዞዎችን በማካሄድ የገፅታ ግንባታ ስራዎችን ለመስራት፣ አንድ ክልላዊ የቱሪዝም ማርኬትንግ ብራንድ በማዘጋጀት ለማስተዋወቅ፣ የክልሉን የቱሪዝም ሀብቶች ተደራሽነት ባላቸው የማስተዋወቂያ መንገዶች በመጠቀም ለማስተዋወቅ፣ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ የውጪ ጎብኚዎችን ቁጥር ከ253,288 ወደ 746,713 ለማሳደግ እና የኦንላይንና የዲጂታል ማርኬቲንግ ስርዓት ለመዘርጋት ይሰራል።
- የኪነ ጥበብ አገልግሎት ያገኘ የሕብረተሰብ ብዛት ከ15,891,725 ወደ 45,892,000 (ሴት 22,946,000) እና የንባብ አገልግሎት ያገኘ የሕብረተሰብ ክፍል ብዛት ከ6,975,872 ወደ 18,976,000 (ሴት 8,976,000) ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም በማህበረሰብ ቱሪዝም የተጀመረባቸው 4 ቦታዎችን በማጠናከር ወደ 8 ለማሳደግ ይሰራል።
- የስራ እድልና ገቢን በተመለከተ ዘርፉን በማልማትና በማሳደግ ለዜጎች የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከ314,216 ወደ 814,200 (ሴት 439,200) ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን በባህል ኢንዱስትሪዎች የሚሰበሰበውን ገቢ 2,000,000,000 ብር፣ ከቱሪዝምና ከባህል የሚገኘዉን ገቢ ከ155,315,480 ብር ወደ 641,900,000 ብር፣ ከጥበቃ ቦታዎች በደረሰኝ የሚሰበሰበዉ ገቢ 31, 799,900 ብር ወደ 79,060,400 ብር ለማድረስ ታቅዷል። እንዲሁም ዘርፉ ለክልላዊ GDP ያለውን ድርሻ ከ6.1% ወደ 10% ለማሳደግ እና የቱሪስት ቆይታ ጊዜ ከ6 ቀን ወደ 8 ቀን ከፍ እንዲል ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፥

- በአሥር ዓመቱ የዘርፍ ዕቅድ ላይ ከአመራር፣ ከሰራተኛ፣ ከባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ ካሉ ማህበራት፣ ፌዴሬሽኖችና ከግል ባለሃብቶች ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር እና ዕቅዱን በየደረጃው ማውረድ፣ እንዲሁም እቅዱን መሰረት ያደረገ የለውጥ አስተዳደር በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

- የዘርፉ የሰው ሀብት ልማት ፣ የገበያና ፕሮሞሽን፣ የቱሪዝም አገልግሎቶችና መረጃ ስርጭት፣ የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ በቱሪዝም ልማት የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት፣ ፍትሃዊ የቱሪዝም ንግድን ማረጋገጥ፤ የቱሪስት ደህንነትና ጥበቃ ማቋቋም፤ ቱሪዝም ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው የሚያስችሉ ሥራዎች የሚከናወኑ ሲሆን የማስፈፀሚያ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማስተካከያዎችን ማውጣትና መተግበር እንዲሁም በዘርፉ የሚካሄዱ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች የማስፈፀሚያ ስልት ይሆናሉ።

ምዕራፍ አራት

የመሠረተ ልማት ዕቅድ

4.1. የትራንስፖርትና መንገድ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፥

- የማስፈፀም አቅም በማሳደግ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ አገልግሎት መስጠት፣ የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ-ልማት አቅርቦቱን ማሻሻል፤ ደህንነቱ የተጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥን ማስፈን፤ በሥራ ዕድል ፈጠራ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ (የመንገድ ልማት ዲዛይን አቅርቦትን ማሳደግ፣ የመንገድ ልማት ግንባታ አቅርቦትን ማሳደግ፤ የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ማሳደግ፣ የመንገድ ልማት ደረጃን ማሻሻል)፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣ የመፈጸም አቅም መገንባት የዘርፉ ውጤታማነትን ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዋና ዋና ግቦች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ-ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡- በ5 ዞኖች አምስት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና መስጫ /ትራፊክ ኮምፕሌክስ/ መገንባት እና ከጋራዦች የሚወጣውን አከባቢ በካይ ጋዝ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመከላከል በ4 ዞኖች የሚገኙ ጋራዦችን በኢንደስትሪ ዞን የማደራጀት ስራ ይሰራል።
- የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን በመገንባት አሁን ካለበት 138 ወደ 166 ለማድረስ፣ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን 4ቱን ከደረጃ 2 ወደ ደረጃ 1 እና 25ቱን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 2 በማሻሻል የደረጃ 2 መናኸያዎችን ከ79 ወደ 104 ለማሳደግ ታቅዷል። እንዲሁም በከተሞች 52 የከተማ ታክሲ መናኸሪያዎች መለየትና 6 መገንባት፣ በ60 ከተሞች የስምሪት መስመሮች ላይ የተሳፋሪ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎችን በመለየት ከ502 ወደ 582 ማድረስ፣ በከተሞች ውስጥ የስምሪት መሰመሮች ላይ ሼዶችን በመገንባት ከ8 ወደ 45 ሼዶች ማድረስ፣ 48 የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንግ እና በ7 ከተሞች ላይ የሳይክል መንገድ ለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል። የጭነት ትራንስፖርት መናኸሪያ ግንባታ አሁን ካለበት ከ2 ወደ 24 ለማድረስ ታቅዷል።
- መንገድ ልማትን በተመለከተ የመንገድ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት ካለበት 15,798.66 ኪ.ሜ ወደ 36,067.66 ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛው መንገድ ግንባታ ፕሮግራም አሁን ከነበረበት 2,646 ኪ.ሜ. ወደ 12,915 ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ13,152.66 ኪ.ሜ ወደ 23,152.66 ኪ.ሜ. ለማሳደግ ይሰራል።

- የድልድይ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት 525 ወደ 1,746 ለማሳደግ በመደበኛው ፕሮግራም ከ207 ወደ 428 ድልድዮች እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ318 ወደ 1,318 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡
- የመንገድ ግንባታ 12,934 ኪ.ሜ ወደ 30,968.62 ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛው ፕሮግራም አሁን ካለበት 6,884 ኪ.ሜ ወደ 14,918 ኪ.ሜ በማሳደግ የመንገድ ጥግግት ኪ.ሜ/1000 ኪ.ሜ^2 አሁን ካለበት 68.40 ወደ 176.42 ለማድረስ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 6,050.62 ኪ.ሜ ወደ 16,050.62 ኪ.ሜ በማሳደግ በአማካይ ክረምት እና በጋ ወደሚያገለግል መንገድ ለመድረስ የሚወስደው ሰዓት ከ1፡49 ወደ 0፡42 ደቂቃ የማድረስ ስራ ይሰራል፡፡
- የመንገድ ጥገናና ደህንነት አሁን ካለበት 22,704 ኪ.ሜ ወደ 55,215 ኪ.ሜ ለማሳደግ በመደበኛ ፕሮግራም ከ22,704 ኪ.ሜ ወደ 47,013 ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ0 ወደ 8,202 ኪ.ሜ መጠገን ስራ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የመንገድ ደረጃን ለማሻሻልና መልሶ ግንባታ ከ930 ኪ.ሜ ወደ 6,492 ኪ.ሜ. ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ዘርፍ ከ0 ወደ 3,000 ኪ.ሜ. ለማሳደግ ይሰራል፡፡ በመደበኛው ፕሮግራም የመንገድ መልሶ ግንባታ 930 ኪ.ሜ. ወደ 3,492 ኪ.ሜ እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም የመንገድ ደረጃን ማሻሻል ከ0 ወደ 2,878 ኪ.ሜ. መንገድ ለማሻሻል ይሰራል፡፡
- የትራንስፖርት አገልግሎት የተቀናጀ፣ ፍትሃዊና ተደራሽነትን በተመለከተ፡- ክልሉን ከአጎራባች ክልሎች የሚያገናኘውን የስምሪት መስመር ከ135 ወደ 139 ለማሳደግ፣ የከተማና የገጠር የስምሪት መስመሮችን 1,334 ወደ 1,629 ለማድረስ፣ በክልሉ አሁን ላሉና ወደ ፊት ለሚከፈቱ የትራንስፖርት ስምሪት መስመሮች የጉዞ መስመሮችን የሚያሳይ 1 ካርታ /Route map/ ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡
- አማራጭ የከተማ ትራንስፖርትን ለማስፋፋት በ14 ከተሞች የከተማ አውቶቢስ፣ በ56 ከተሞች ሚኒ ባስ የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት በኤሌክትሪክ እና በታዳሽ ሀይል ድብልቅ የሚሰሩ አውቶብሶች 45 ወደ ሥራ ለማስገባት፣ በተለየ መስመር የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ተግባራዊ የተደረገባቸው ከ50 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች ብዛትን ወደ 6 ለማድረስ፣ በወንዞችና ሀይቆች ላይ የሚሰሩ ባለሞተር ጀልባ ኦፕሬተሮችን አሁን ካለበት 11 ወደ 27 ለማድረስ፣ እንዲሁም የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶቡስ አቅርቦት ብዛት ወደ 141 በማሳደግ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት ከ10,000 ወደ 73,998 ለማድረስ ይሰራል፡፡
- በክልሉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ከ5,091 ወደ 7,966 ለማድረስ፣ የተጓዘ ተሳፋሪ ከ71,234,981 ወደ 81,334,981 እና የሥምሪት ምልልስ ከ1,063,676 ወደ 1,725,000 በማድረስ የኪሎ ሜትር ሽፋን 222,782,684 ወደ 580,270,125 ለማድረስ ይሰራል፡፡
- የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር፡- በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት

የሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋማትን ድርሻ ከ65% ወደ 100%፣ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የሚሰጡ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ድርሻ ከ25% ወደ 100%፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ቁጥር ከ66 ወደ 92፣ አለም አቀፍ ደረጃ የጠበቁ የአሽከርካሪ ሞዴል ማሰልጠኛ ተቋማት ብዛት 80%፣ በሲሙሌተር የተደገፈ የአሽከርካሪዎች እና የቴክኒሽያኖች የተግባር ስልጠና 5% ከነበረበት ወደ 100%፣ ጥገና መስጫ ጋራዦች ከ62 ወደ 124፣ ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ 30,779 ከነበረበት ወደ 69,809 ለማድረስ ይሰራል።

- የትራፊክ አደጋን በ2012 የነበረውን 1,098 የአደጋ መጠን በ5% በየዓመቱ በመቀነስ በ2022 ወደ 611፣ ሞት የሚያስከትል አደጋ ከ478 በየዓመቱ 5% በመቀነስ ወደ 319፣ የንብረት ዉድመት ከብር 26,677,568 በየዓመቱ 5% በመቀነስ ወደ ብር 15,712,642.1፣ በሰው ህይወት ላይ በ10 ሺህ ተሽከርካሪ ይደርስ የነበረውን 38 ሞት ወደ 9 ዝቅ ለማድረግ ይሰራል።
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ 1,000,000 ችግኝ ህብረተሰብን በማስተባበር የመትከል እና በ9 ከተሞች ላይ የብስክሌት ትራንስፖርትን ለማስፋፋት ይሰራል። የተሽከርካሪዎች ማጠቢያ/ላቢያጆ/ በመገንባት በወንዞችና ሀይቆች ላይ የሚደርሰውን ብክለት ለመቀነስ 20 ከነበረበት ወደ 80 ለማድረስ ታቅዷል።
- 107 መናኸሪያዎችን በዋይድ ኤሪያ ኔት ወርክ ማገናኘትና የመረጃ አያያዝ፣ ትንተናና ሥርጭት ዘዴውን ዘመናዊ ለማድረግ፣ የትራፊክ ቁጥጥሩን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማገዝ በክልል ደረጃ 2 ተሽከርካሪና በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠም እና 20 በእጅ የሚያዝ የፍጥነት መቆጣጠሪያ (ራዳር) የመግዛትና የማሰራጨት ስራ ይሰራል።
- በትራንስፖርት ዘርፍ ለዜጎች የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል ከ47,521 ወደ 76,461 ለማድረስ፣ በመንገድ ዘርፍ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር አሁን ከነበረበት 150,000 ቋሚና ጊዜያዊ ወደ 528,676 ለማድረስ፣ በመደበኛ የመንገድ ፕሮግራም ከ50,000 ወደ 156,120 እና በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ100,000 ወደ ለ372,556 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- ሞተር አልባ መካከለኛ ትራንስፖርት ዘዴ አፈፃፀም መመሪያ፣ የብዙሃን ትራንስፖርት ማስፋፊያ ስትራቴጂ፣ የትራፊክ ፍሰት ቁጥጥር ስትራቴጂ፣ ፐብሊክ ትራንስፖርት ደንብ፣ የዘርፉን የአደረጃጀት ማሻሻያዎች፣ የወርሃዊ ድርጊት መረሃ-ግብርና መናኸሪያ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ማሻሻል፤ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ፣ ሁሉ አቀፍ መንገድ ግንባታ አተገባበር መመሪያና ደንብ እና የትራንስፖርት ኢንፎርሜሽን ሶፍትዌር ግንባታ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

4.2. የኢነርጂ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት ኢነርጂ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፥

- ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችን በማልማት በቤተሰብ ደረጃም ሆነ በተቋማት (በጤና፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በትምህርት እና በግብርና ምርምር) የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል። አዳዲስ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ላይ ጥናት በማድረግ፣ በማፍለቅ፣ በማላማድና በማሻሻል ማሰራጨት እንዲቻል በክልል ደረጃ የሚገኘውን የምርምር ማዕከል እንዲጠናከር ይደረጋል።
- የግል ባለሃብቶችን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን እና የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን በማስተባበር በዘርፉ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።
- የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች በህብረተሰቡ ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና ያለብድር እራሱን አስችሎ ማሰራጨት እንዲቻል የማስተዋወቅ ሥራ በትኩረት ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት ኢነርጂ ዘርፍ ዓላማ እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- የክልሉ አማራጭ ኢነርጂ ሀብት በጥናት በመለየት የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ለህ/ሰቡ ተደራሽ በማድረግ ኑሮው እንዲሻሻል ማድረግ፤ ዘርፉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ከማረጋገጥ አንጻር የበኩሉን እንዲወጣ ማድረግ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢነርጂ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- ኢነርጂ ልማት ዘርፍን ማሳደግን በተመለከተ፡- በቀጣይ አስር ዓመት የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ቤተሰብ ከ1,256,527 ወደ 2,734,787፣ የባዮጋዝ ተጠቃሚ ቤተሰብ ከ4,363 ወደ 8,398 እና ባዮጋዝ በተቋማት ከ7 ወደ 22 ለማሳደግ ይሰራል። እንዲሁም 17 የብሪኬት ማዕከላትን በመገንባት ከ10 ወደ 27 ለማሳደግ ታቅዷል።
- የሶላር ተጠቃሚ ቤተሰብ ከ565,733 ወደ 1,380,498፣ የሶላር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ተቋማትን ከ2,813 ወደ 5,110 እና 10 በንፋስ ውሃ መሳቢያ ቴክኖሎጂዎች ግንባታ በማካሄድ ተቋማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። እንዲሁም ከፒኮ/ማይክሮ ሀይድሮ ፓወር ሀይል ተጠቃሚ ቤተሰብ ከ3,300 ወደ 3,548 ለማሳደግ (10 በማጥናትና 5 በመገንባት) ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የኢነርጂ ዘርፍ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- አስተማማኝና ዘመናዊ የኃይል መሠረተ ልማት መገንባት፣ በዘርፉ ዘለቄታዊ ኢንቨስትመንት ማረጋገጥና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማስፋፋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው

4.3. የውሃ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የውሃ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማስፋፋት፣ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማትን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማስቻል፣ የታዳሽ ኃይል የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፤ የከተሞች ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ማሳደግ በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን የአቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት ማከናወን፣ ልዩ ድጋፍ በሚሹ የክልሉ አካባቢዎች ወጥነትና ዘላቂነት ያለውን ድጋፍ ማድረግ በቀጣይ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የውሃ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የክልሉን የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦቱን በማስፋፋት የአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ፤ንፁህ፣ አስተማማኝና በቂ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት የልማት ዕቅዱ ማጠናቀቂያ ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ፤ የከተሞችና ገጠር ሳኒቴሽን አገልግሎት አቅርቦትን ማሳደግ፤ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፤ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የውኃ ጥራት ደረጃ ማስጠበቂያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ የመጠጥ ውኃ ጥራትን ማረጋገጥ፤ የዋሸና የተፋሰስ ዘመናዊ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፤ በዘርፉ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ አለመኖሩን ማረጋገጥና የውኃ ሀብት አስተዳደርን ማስፋፋትና ማጠናከር ዋና ዋና አላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የውሃ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- **የመጠጥ ውሃ ዘርፍ፡-** የመጠጥ ውሃ ተቋማት በገጠር 18,948 እና በከተማ 325 ጥናትና ዲዛይን፣ አፕሬዛልና ይሁንታ ስራዎችን ማከናወን ለ5,622,009 የገጠር ነዋሪ ህዝብ በ1 ኪ/ሜ ክልል ውስጥ በነፍስ ወከፍ በቀን 25 ሊትር ውሃ በማቅረብ የገጠር ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን ከ40.62% ወደ 75% ማሳደግ፣ ለ1,841,445 የከተማ ነዋሪ ህዝብ በነፍስ ወከፍ በቀን ለደረጃ 1 ከተሞች 100 ሊትር፣ ለደረጃ 2 ከተሞች 80 ሊትር፣ ለደረጃ 3 ከተሞች 60 ሊትር፣ ለደረጃ 4 ከተሞች 50 ሊትር እና ለደረጃ 5 ከተሞች 40 ሊትር ውሃ በማቅረብ በ2012 ዓ/ም ከነበረበት 55.39% በ2022 ዓ/ም ወደ 90% ለማሳደግ ይሰራል፡፡

- ለ7,463,454 የክልሉ የከተማና ገጠር ነዋሪ ህዝብ በተቀመጠው መለኪያ ንፁህ መጠጥ ውሃ በማቅረብ የክልሉን አማካይ ሽፋን በ2012 ዓ/ም ከነበረበት 42% በ2022 ዓ/ም ወደ 78% ማሳደግ፣ አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሃ ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት የመጠጥ ውሃ ተቋማትን የብልሽት መጠን በ2012 ዓ/ም ከነበረበት በአዲሱ ስታንደርድ 21% በ2022 ዓ/ም ወደ 5% መቀነስ።
- የከርሰ ምድር ውሃ አለኝታ ጥናት መረጃን በ2012 ዓ/ም ከነበረበት 22% ወደ 100% ማድረስ እና ገጸ ምድር ውሃ አለኝታ ጥናት መረጃን በ2012 ዓ/ም ከነበረበት 22% ወደ 100% ለማድረስ ታቅዷል። የውሃ ሀብት አጠቃቀም በሀጋዊ ስርዓት ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና ፍትሃዊና የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር ስርዓት ማስፈን፣ የውሃ ብክለትና ብክነት መቀነስ እና የውሃ አቅርቦት ጥራትን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ሃይጅን መረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና ስርጭት ሥርዓት ለመፍጠር ይሰራል።
- **የገጠርና የከተማ መጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን**፡- በገጠር 5,264 የቤተሰብ የእጅ ጉድጓድ (በአማካይ 1 ቤተሰብ ወይም 6 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 611 የህብረተሰብ የእጅ ጉድጓድ ፓምፕ የተገጠመለት (በአማካይ 15 ሜትር ጥልቀት ያለውና 160 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 5,758 ምንጭ በቦታው (በአማካይ 200 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 5,832 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ የዕጅ ፓምፕ የተገጠመለት (በአማካይ 250 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 468 ምንጭ ከነማከፋፈያው (በአማካይ 3,000 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ) እና 1,014 ጥልቅ ጉድጓድ ከነማከፋፈያው (በአማካይ 2,000 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ) ለመስራት ታቅዷል። በከተማ 72 ምንጭና 144 ጥልቅ ጉድጓድ ከነማከፋፈያው እና 9 ወንዝ ጠለፋ ለመስራት ታቅዷል።
- **የገጠርና የከተማ መጠጥ ውሃ ግንባታ**፡- በገጠር 4,785 የቤተሰብ የእጅ ጉድጓድ (በአማካይ 1 ቤተሰብ ወይም 6 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 556 የህብረተሰብ የእጅ ጉድጓድ ፓምፕ የተገጠመለት (በአማካይ 15 ሜትር ጥልቀት ያለውና 160 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 5,285 ምንጭ በቦታው (በአማካይ 200 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 5,302 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ የዕጅ ፓምፕ የተገጠመለት (በአማካይ 250 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ)፣ 425 ምንጭ ከነማከፋፈያው (በአማካይ 3000 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ) እና 922 ጥልቅ ጉድጓድ ከነማከፋፈያው (በአማካይ 2000 ሰው ተጠቃሚ የሚያደርግ) በድምሩ 17,225 ተቋማት ለመገንባት ታቅዷል። እንዲሁም በከተማ 156 ምንጭ ከነማከፋፈያው፣ 131 ጥልቅ ጉድጓድ ከነማከፋፈያው እና 8 ወንዝ ጠለፋ በድምሩ 295 ተቋማት ለመገንባት ይሰራል።
- **የውሃ ሀብት ጥናትና አስተዳደርን በተመለከተ፡-** በ15 ንዑስ ተፋሰሶች የውሃ ሀብት አጠቃቀም ጥናት ማካሄድና ዋና ዋና የውሃ ተጠቃሚዎችንና ባለድርሻ አካላትን በማካተት የውሃ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ የጋራ ጥምረት ለመፍጠር፣ 20 የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎችን ለመገንባት፣ የፍሎራይድ ችግር ያለባቸው የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች አማራጭ ውሃ እንዲያገኙ ለማድረግ ይሰራል።

- በ76 የውሃ አካላት ላይ የፊዚኮ ኬሚካልና ሌሎች ከባቢያዊ ምርመራዎች በማካሄድ የጥራት ደረጃቸውን ማረጋገጥና በተገኘው ውጤት መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ በ24,816 አዳዲስ የገጠርና ከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ተቋማት የፊዚኮ ኬሚካልና የባክቴሪዎሎጂካል የውሃ ጥራት ምርመራ በማካሄድ የጥራት ደረጃቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል።
- በ530 ሀጋዊ የውሃ ሃብት ተጠቃሚዎችን በውሃ ሀብት የመጠቀም ፈቃድ እንዲኖራቸው፣ 1,300 በማማከር፣ በግንባታ እና በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋጫ፣ 732 በውሃ ነክ ሥራዎች በማማከር በግንባታ፣ እና በጉድጓድ ቁፋሮ ለሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ይሰጣል።
- ለ200 ከተሞች የሚቀርብ የመጠጥ ውሃ ጥራት እና በ40 ኢንዱስትሪዎች በውሃ አካላት ላይ የሚለቁትን ፍሳሽ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር በማድረግ የፍሳሹን የጥራት ደረጃ አረጋግጦ የመልቀቅ ፈቃድ ይሰጣል።
- **የመጠጥ ውሃ ጥገናና ተቋማት አስተዳደር** ቀደም ሲል የተገነቡ 10,152 ተቋማትንና በቀጣይ አስር ዓመታት የሚገነቡ 17,225 በድምሩ 27,377 የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ወቅታዊ የቅድመ መከላከል ጥገና በማከናወን ተቋማት አገልግሎት አንዳያቋርጡ ይደረጋል። ቀደም ሲል የተገነቡ 412 ተቋማትንና በቀጣይ የሚገነቡ 294 በድምሩ 706 የከተማ መጠጥ ውሃ ተቋማት አገልግሎት አንዳያቋርጡ የማድረግ ስራ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የውሃ ልማት ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በሚመለከት ፍላጎትን፣ አቅምንና ቁጠባን መሠረት በማድረግ ውጤታማ፣ አስተማማኝና ዘላቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፤ ለገጠሩ ህብረተሰብ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲስፋፋ ለማድረግ በአነስተኛ ወጪ ሊገነቡ የሚችሉ አማራጭ ዲዛይኖችን ዘላቂና አዋጭ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።
- በነባር ውሃ ተቋማት ውስጥ የበቃ አስተዳደርና አሠራር እውን በማድረግ አዳዲስ የውሃ ልማት ፕሮጀክቶች ከመገንባታቸው በፊት ቁጠባን መሠረት ያደረጉ እርምጃዎች ለመውሰድ ሚያስችሉ ሥልቶች ይመቻቻሉ፣ ነባር የውሃ ተቋማትን መንከባከብና ውሃን በቁጠባ መጠቀም፣ በቤተሰብ ደረጃ መሠረታዊ የውሃ ፍላጎቶችን ማሟላትና ከመሰረታዊ ፍላጎቶች ባሻገር የሚኖረው ውሃ ክፍፍልና አጠቃቀም ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በሚያመጡ መመዘኛዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ ባልተማከለና በዝቅተኛ ደረጃ ያሉትን ተቋማት የውሃ ሀብት አስተዳደር አቅም ግንባታ ማካሄድ፣ በከተሞች ዋጋ ማስመለስ መርህን መሰረት ባደረገ መልኩ በአነስተኛ ወጪ በብድር ለሚገነቡ ውሃ ተቋማት ቅድሚያ መስጠት።

4.4. የመስኖ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የመስኖ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ ዋነኛ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚተገበር ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በክልሉ በተመሳሳይ ተግባር የተሰማሩት ተቋማትን አቅም አሟጦ መጠቀም ፤ጥናትና ዲዛይን፤ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ላይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችን በማህበር በማደራጀት ወደ ስራ ማሰማራት፤ በዘርፉ ልምድና ብቃት ያላቸዉን የግል ተቋራጮች በመለየትና በማሳተፍ የመስኖ ግንባታ ስራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤ የመስኖ ተቋማት አስተዳደር የአሰራር ስርአት መዘርጋትና አቅም መፍጠር።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ማካሄድ በተመለከተ፡- 17,234 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 194 አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን፣ 37,719 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 76 መካከለኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን እና 74,643 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 28 ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን የሚከናወን ሲሆን 4,581 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ የ34 የጥልቅ የከርሰ ምድር መስኖ ጥናትና ጉድጓድ ቁፋሮ ለማከናወን ታቅዷል። እንዲሁም 6,844 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸው 80 የመስኖ ተቋማት መልሶ ግንባታና ማስፋፊያ ጥናት ይካሄዳል።
- የመስኖ ፕሮጄክቶች ግንባታ ስራዎች ከማካሄድ አንጻር 13,751 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸው 130 አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች፣ 21,926 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 53 መካከለኛ መስኖ ፕሮጀክቶችና 51,254 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 18 የግድብ መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ የማካሄድ፣ 3,241 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ የ24 የጥልቅ ከርሰ ምድር የመስኖ አወታር ዝርጋታ የማከናወን እና 4,447 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸዉ 40 ነባር የመስኖ ተቋማት መልሶ ግንባታና ማስፋፊያ ስራ ይሰራል።
- በክልሉ የመስኖ ፖቴንሽያል መሬት በተመለከተ በአነስተኛ፣ በመካከለኛ እና በሰፋፊ መስኖ መልማት የሚችል 700,000 ሄ/ር መሬት (በአዲስ የተደራጁት ሁለቱ ክልሎች ተቀንሶ) በጥናት የተለየ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከዘመናዊ የመስኖ ፖቴንሻል አንጻር የለማ መሬት 40,548.83 ሄ/ር (5.8 %) ከነበረበት ወደ 135,198 ሄ/ር (19%) ለማልማት በዕቅድ ተይዟል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉተወ የማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- ከክልል ጀምሮ እስከ ዞን፤ልዩ ወረዳና ወረዳ ያለዉን የመስኖ መዋቅር የሎጂስቲክስና የሰዉ ሀይል አቅም በመገንባትና የሰዉ ሀይል በማሟላት በራስ ሀይል የሚከናወኑ ስራዎች በስፋት እንዲተገበሩ ማድረግ፤
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚሰሩትን ስራ በኮንትራት አስተዳድር ህግ እንዲፈጸም በማድረግ የስራ ጥራትና ጊዜ እንዲጠበቅ ማድረግ፣ የግል አማካሪዎችና ተቋራጮችን በስፋት በማሳተፍ ተገቢዉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፣ በዘርፉ ካሉ የከፍተኛ ትምርት ተቋማትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋራ በቅንጅት መስራት፣ የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች የተጠቃሚውን ባህላዊ እሴቶች ጠብቀው ለማከናወን እንዲቻልና ህብረተሰቡ ችግሩን ከመለየት ጀምሮ እስከ ግንባታና ምርት ሂደት ጉልህ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማስቻል፣ ይህንንም በተሳትፎአዊ መስኖ ልማትና አስተዳደር አሰራር/PIDM/ መሰረት መፈጸም፤
- የመስኖ መልሶ ግንባታና ማስፋፊያ ሥራዎች በዞን/በልዩ ወረዳ እና በወረዳዎች ባለቤትነት እንዲካሄዱ ማድረግና ከአቅም በላይ ለሆኑ ጥገናዎች የበጀትና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ።

4.5. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሳይንስ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እና ዘርፈ ብዙ ትብብሮችን ከማጠናከር አንጻር፡- የተለያዩ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ሥራዎችን በመለየት የማቴሪያል፣ የፋይናንስ እና ቴክኒካል እገዛዎችን ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ክልላዊና ሀገራዊ ትስስርና ትብብር የሚፈጠር ከመሆኑም በላይ የተለያዩ አቅም ግንባታ ሥራዎች በየደረጃው ትኩረት አግኝተው እንዲፈጸሙ የሚሰራ ይሆናል።
- የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ከማሳደግ ረገድ፡- ቴክኖሎጂዎችን ለማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ በመስራት በቴክኖሎጂ ላይ የሚታዩ የግንዛቤ ችግሮችን በመቅረፍና አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት ተለይተው እንዲፈጸሙ የሚደረግ ይሆናል።
- የዲጂታል ኢኮኖሚ ስርዓት ግንባታና ሁሉ አቀፍ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የተለያዩ ሶፍትዌሮችና ሲስተሞችን በማልማት፣ በማላመድና በማስተግበር ምርቶችና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃ ስለማሟላታቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር በመስራት እንዲሁም በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የሚደገፉ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን መሰረት ያደረጉ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የክልሉ ህብረተሰብ ወደ ዘመናዊ አሰራር እንዲመጣ የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በክልሉ ዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችና ፈጠራ ሥራዎች በማበረታታትና አቅም በመገነባት ዘርፉ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጉልህ ሚና እንዲጫወት በማድረግ ምርትና ምርታማነት በመጨመር የተወዳዳሪነት አቅም እንዲሻሻል ማስቻል ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ከማረጋገጥ አንጻር፡- የለሙ ሲስተሞችና ሶፍተዌሮችን ለማስተዳደር የሚያስችል የዳታ ማዕከል አቅም ለመገንባት ከ60% ወደ 100%፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ፣ ፈቃድና ዕድሳት ያገኙ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን ከ375 ወደ 3,577 ለማሳደግ ታቅዷል።
- ምቹ የምርምርና የፈጠራ ስራ ምህዳር በመፍጠር የተመራማሪዎችንና የፈጠራ ባለሙያዎችን ውጤታማነት ከማሳደግ አንጻር፡- 309 የፈጠራና የምርምር ውጤቶች የተለያዩ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፎች ተደርጎ ወደስራ የማስገባት፤ በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች 136 ጊዜ የፈጠራ ስራዎች ውድድርና የሽልማት ስነ ስርዓት ማካሄድ እና 10 ዙር ክልላዊ የፈጠራ ስራዎች ውድድርና ሽልማት ስነ-ስርዓት የሚካሄድ ይሆናል።
- ብቁና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን ከመፍጠር አኳያ በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች 79 ስልጠና ማዕከላትን ከ14 ወደ 93፣ የጥገና ማዕከላትን ከ5 ወደ 88፣ እድሳት ማዕከላትን ከ1 ወደ 17፣ ኢንኩቤሽን ማዕከላትን ከ1 ወደ 17፣ 1 የሳይንስ ቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ምርምር ማዕከል ግንባታ፣ 167 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበባት እና 1 የዲማኑፋክቸሪንግና ኢ-ቄስት ማዕከላት በስታንዳርዱ መሰረት ለማቋቋም ታቅዷል።
- ውጤታማ የትብብር ስርዓትን ለማረጋገጥ የተጣለውን ግብ ለማሳካት የመግቢያ ሰነድ ተፈራርመው ቅንጅታዊ ትስስር የፈጠሩ ተቋማትን ከ10 ወደ 33 ማድረስ፣ በኢንዱስትሪው ተገቢውን የተግባር ለምምድ ያደረጉ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ከ525 ወደ 3090 የማድረስ ስራ ይሰራል።
- የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አኳያ፡- የዲጂታል ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች አጠቃቀምንና አቅርቦት በማሳደግ ከክልል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የሲስተሞችን ቁጥር ከ3 ወደ 42፣ ከስተማይዝ የተደረጉ ሲስተሞችን ከ5 ወደ 58፣ የለሙ ዌብሳይቶችን ከ71 ወደ 213 እና ለመረጃ ልውውጥ የለማ ፖርታል ቁጥር ከ1 ወደ 5 ለማሳደግ ታቅዷል። የኔትወርክ መሰረተ ልማትና ዲዛይን ሰነድ የተዘጋጀላቸው ተቋማትን ከ40 ወደ 424 የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- የዲጂታል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ቁጥር ከማሳደግ አንጻር የ(WAN) ዝርጋታ የተከናወነላቸው የመንግስት መ/ቤቶች ከ6 ወደ 31፣ የአካባቢያዊ ኔትዎርክ(LAN) ዝርጋታ የተከናወነላቸው የመንግስት መ/ቤቶችን ከ436 ወደ 1293፣ ለመረጃ ልውውጥ በለማ ፖርታል ውስጥ የተካተቱ ተቋማት ቁጥር ወደ 68 ለማሳደግ ታቅዷል።

- ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሀርድዌርና ሶፍትዌሮች ተደራሽነትን ከማሳደግ አንጻር፡- ታድሰው ለአገልግሎት ዝግጁ የተደረጉ የኢ.ኮ.ቴ መሳሪያዎችን ከ8 ወደ 433፣ 28,000 የኢ.ኮ.ቴ መሣሪያዎች የሶፍትዌር ጥገና፣ 20,500 የሀርድዌር ጥገና በማድረግ 29.2 ሚሊየን ብር ከመንግስት ሊወጣ የነበረ የመንግስት ሀብት ለማዳን፣ የሶፍትዌር ልማት ሲስተም ሪኪየርመንት ስፔስፊኬሽን ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሲስተሞች ቁጥር ከ10 ወደ 79 ማድረስና የኢ.ኮ.ቴ መሰረተ ልማቶችንና ሲስተሞችን አዲት ስርዓት የተገበሩ ተቋማትን ቁጥር ከ1 ወደ 143 ለማድረስ ታቅዷል፡፡
- በተማከለ የዲጂታል መሰረተ ልማት የተቋማትን የመረጃ ልውውጥ ውጤታማነትን ከማሳደግ አንጻር፡- የወረዳኔት መሰረተ ልመት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማትን ከ42 ወደ 116፣ የኤክስቼንጅ ሜይል አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማትን ቁጥር ከ42 ወደ 116 ማድረስ፣ የክልሉን ቪድዮ ኮንፍራንስ ስቱዲዩ በመጠቀም የቪድዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ማከናወን የቻሉ ተቋማትን ከ9 ወደ 77፣ ተቋማትን የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ ከ45.5 ወደ 135.9 ሚሊዮን ብር በቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ከመንግስት ሊወጣ የሚችል ሀብት ለማዳን ታቅዷል፡፡
- በግል በቴክኖሎጂ ዘርፍ ተደራጅተው ወደ ስራ የሚገቡ ኢንትርፕራይዞች ከ18 ወደ 252 በማሳደግ በኢንኩቤሽን ማዕከላት ከ75 ወደ 1,350 ለሚደርሱ ወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር፣
- የጨረር አመንጪ መሣሪያዎች ጉዳት በመከላከል የህብረተሰቡን ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር፡- ለ60 ተቋማት የጨረራ አመንጪ መሣሪያ የመጠቀም ፈቃድ እና 596 ተቋማት የጨረራ አመንጪ መሣሪያ የመጠቀም የፈቃድ ዕድሳት እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን 10 ዙር ድንገተኛ የጨረር አመንጪ መሳሪያዎች ፍተሻ ማካሄድ፣ ለ103 ምርቶች አስገዳጅ ምዘና እና ለ20 ምርቶች አስገዳጅ ያልሆነ ምዘና ተካሂዶላቸው ማረጋገጫ መስጠት፣ በትብብር የፋብሪካ ውጤት ለሆኑ ምርቶች የምርት ጥራት ደረጃ ከመስጠት አንጻር ለ135 ምርት ዓይነቶች ምርመራ በማድረግ ደረጃ መስጠትና 120 ምርቶች በዳታ ቤዝ ለመመዝገብ ታቅዷል፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈፀሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- ከዘርፎችና ከሚመለከታቸዉ እስከ ፈፃሚ ድረስ የስራ ክፍፍል በማድረግ የስራ ውል መግባቢያ መፈራረም፣ ከባለድርሻ አካላት ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከሴክተር መ/ቤቶች እና ከፌዴራል ከሚኒስቴር መስሪያቤቶችና ኤጀንሲዎች ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችል ግንኙነት መፍጠር፣ የተቋሙን ስራዎች ውጤታማ ሊያደርጉ የሚያስችሉ የተለያዩ ልምድ ልውውጦችን ማድረግ፣ ጠንካራ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም የሰው ሀይል ልማትና አስተዳደር ላይ ትኩረት የማድረግ ስልቶች ጥቅም ላይ ማዋል ናቸዉ፡፡

ምዕራፍ አምስት

የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

5.1 የሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት

5.1.1 የሥነ-ሕዝብ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መኖር፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ውስንነት መኖር፣ የምርትና ምርታማነት ማነስና የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ያለመረጋገጥ፣ የትምህርት ፍትሀዊነት፣ ጥራትና ተደራሽነት ችግር መኖር፣ የሕብረተሰብ የተዋልዶ ጤና እና አጠቃላይ የጤና ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት፣ የሴቶች፣ የአረጋዊያን፣የአካል ጉዳተኞችንና ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማህ/ሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ተሣታፊነትና ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆን፣ ዋና ዋና የሥነ-ህዝብና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማ እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን ከክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ምጣኔና የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ጋር በማጣጣም በሂደት የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ለዚህም በሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም አማካይ ክልላዊ የውልደት ምጣኔና የሞት ምጣኔ እንዲቀንሱ በማድረግ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔንና በክልሉ የሚታየውን የሥራ አጥነት ምጣኔን መቀነስ፣ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን በሚመለከታቸው ሴክተሮች፣ የሐይማኖት ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት የልማት ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግና ተግባራዊነታቸውን መከታተል የቀጣይ አሥር ዓመት መሪ የሥነ ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ዓላማ ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የሕዝብ ዕድገት ምጣኔን ከክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ጋር ማጣጣም፣ የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎችን ምጣኔ ከ45% ወደ 80%፣ አንዲት በመውለድ የዕድሜ ክልል (15-49) ያለች እናት የምትወልዳቸው ልጆች መጠን /TFR/ በአማካይ 4.4 ልጆች ወደ 3.1 ልጆች በማድረስ አጠቃላይ የክልሉ ህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ከ2.9% ወደ 2.3% ለማድረስ ታቅዷል።
- በክልሉ ዲሞግራፊያዊ ባህሪያት ዙሪያ ልዩ ልዩ ጥናቶችን በማድረግ ለሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ማሻሻያ የሚረዱ ሃሳቦችን ማቅረብና የፖሊሲውን ዓላማና ግቦች ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ፕሮግራምና ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤ የተፈጥሮ አካባቢን በመጠበቅና በማልማት፣ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፤ የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ አጠቃላይ የሕብረተሰቡ ጤና እንዲሻሻል የግንዛቤ ሥራዎችን በልዩ ትኩረት መስራት፣ በክልሉ ፍትሀዊና ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ እንዲሆንና በተለይ የሴት ልጆች መማር ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስፋፋት ከፍተኛና የማይተካ ሚና

ስላለው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ተሳትፎአቸውን ማሳደግ፣ ሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካልጉ ዳተኞችንና በአጠቃላይ ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማህ/ሰብ ክፍሎች ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸውና በክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግንዛቤ ሥራዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለመስራት ታቅዷል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማና ዋና ዋና ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት ማስፈጸሚያ ስልቶች ተለይተዋል፥

- የሥነ-ሕዝብና ልማት ችግሮችንና መፍትሔዎችን እንዲሁም የሥነ-ህዝብ ሥራዎች ዓላማን ለሕ/ሰቡ ለማስተዋወቅ፣ ለማስተማር፣ ለማስረፅና ለመቀስቀስ እንዲሁም የአመራር አካላትን የማሳመን /IEC/BCC and Advocacy ሥራዎችን የማከናወን እና የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በየደረጃው ባሉ ሴክተር መ/ቤቶች ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችና ስትራቴጂክ ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፤
- በትምህርት ቤቶች የሥነ-ህዝብ ክበባትን በማቋቋምና በማጠናከር የሥነ-ህዝብ መልዕክቶችን ለተማሪ ወጣቶችና ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲያደርጉ የመደገፍ እና የሴቶች መማር ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስፋፋት የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ የሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ እንዲያድግ የግንዛቤና የቅስቀሳ ሥራዎችን መስራት፤
- የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ከክልል እስከ ወረዳ እንዲዘጋጅና በየወቅቱ አፈፃፀሙ እንዲገመገም በማገዝ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የስነ ህዝብ የስራ ሂደቶች የቴክኒክ፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ አቅም መገንባት።
- የስነ-ተዋልዶ ጤና እና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነትን በመብት መርህ መሰረት ማስፋፋት፤
- ማሕበረሰቡን በማንቀሳቀስ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በማፋጠን ለጥቃት፣ ለመገለል፣ ለመድልዎና ለበደል ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሕግ ጥበቃ እና የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማጠናከር ይሆናል።

5.1.2 የትምህርት ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የትምህርት ልማቱ በሰባት ትኩረት መስክክ የሚሰራ ሲሆን ሀገራዊ እሴቶች እና ብዝሃነት ለብሔራዊ አንድነት ማጠናከር፣ የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ለገበያ ተወዳዳሪነት፣ የትምህርት ዘርፉን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ፣ የአጠቃላይ የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነትና ውስጣዊ ብቃት መርሃ-ግብር፣ መደበኛ ያልሆነ የወጣቶች እና የጎልማሶች ትምህርት መርሃ-ግብር፣ የትምህርት ሥርዓት፣ አስተዳደርና ተጠያቂነትን ማጠናከር፣ የትምህርት ጥራት ማጠናከር ላይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ የግዴታ ትምህርት፣ ሁለተኛ ደረጃን የነፃ ትምህርት በሳይንስና ተስማሚ ቴክኖሎጂ የተደገፈና በብቁ አመራር የሚመራ ትምህርት በማድረግ ለሁሉም በፍትሀዊነት በማዳረስ የዜጎችን አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እንዲሁም መልካም እሴቶችን በማጐልበት ለሀገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡና ግብርናውን ወደ ላቀ ደረጃ በማሻገር ኢኮሚኖሚውን የሚያሳድጉ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጐችን ማፍራት ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የሥርዓተ-ትምህርቱን አካታች እና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ከማድረግ አንጻር፡- በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሁም በአንደኛ፣ በሁለተኛና በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍት ጥምርታ በ2012 ዓ.ም 1፡2 ከነበረበት በ2022 ዓ.ም 1፡1 የማድረስ ስራ ይሰራል።
- የመምህራንና የትምህርት አመራሩን አቅርቦት፣ ተነሳሽነትና ብቃትን ከማሳደግ አንፃር፡- ለደረጃው የሰለጠኑ ቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን ሽፋን በ2012 ዓ.ም 33.3% ከነበረበት በ2022 ዓ.ም 100% ለማድረስ፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን ሽፋን ከ12% ወደ 50% ማድረስ፣ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሽፋን ከ12.7% ወደ 50% የማሳደግ ስራ እንዲሁም የመምህራን ከስራ የመልቀቅ ምጣኔ ከ2.6% ወደ 0.5% ዝቅ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- የሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን የመማር ማስተማር ሂደት በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል በተመለከተ፡- ለSTEAM ፕሮግራም የሳይንስ ላብራቶሪ የተሟላላቸው አንደኛና መካከለኛ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ75% ወደ 100% የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- የት/ት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል የመማር ማስተማር ሂደቱን ምቹ ከማድረግ አንፃር፡- ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ከ10.28% ወደ 70 በመቶ፣ ደረጃ 3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ 26.60 ወደ 80 በመቶ፣ ደረጃ 4 የደረሱ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ 0.09 ወደ 30 በመቶ፣ ደረጃ 4 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከ0.20% ወደ 20 በመቶ ከፍ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- ዲጂታል ቴክኖሎጂን መጠቀምና የትምህርት ስርአቱን ከማሻሻል አንፃር፡- ፈጣን በሆነ የብሮድባንድ ኔትዎርክ መሰረተ ልማት ተሳስረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በቴክኖሎጂ ተደግፎ በጥራትና በወቅቱ የተሰበሰበ፣ የተተነተነና ጥቅም ላይ የዋለ የትምህርት አስተዳደር መረጃ ሥርዓት ትግበራ 100% ይሰራል።

- የትምህርት ተደራሽነትና ውስጣዊ ብቃትን ማሳደግ በተመለከተ፡- የጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ቅበላ ከ56.3 ወደ 100%፣ የጥቅል የ1ኛ ክፍል ተሳትፎ ከ124.4 ወደ 100% እና ንጥር የ1ኛ ክፍል ተሳትፎ ከ83.5 ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዷል። ጥቅል ተሳትፎ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል አማራጭን ጨምሮ ከ116.3 ወደ 99.98% እና ንጥር ተሳትፎ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል አማራጭን ጨምሮ ከ91.1 ወደ 100% ለማሳደግ ይሰራል። ጥቅል ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል ቅበላ ከ70.7 ወደ 100% እና ንጥር ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል ቅበላ 50 ወደ 100% ለማድረስ ይሰራል። ጥቅል ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ከ34.9 ወደ 76% እና ንጥር ከ9ኛ-12ኛ ክፍል 27.1 ወደ 75% ለማድረስ ይሰራል።
- መጠነ መድገም ከ1-6ኛ ከ8.8 ወደ 2%፣ ከ7-8ኛ ከ11 ወደ 3% እና ከ9-12ኛ ከ6.4 ወደ 2% ዝቅ የማደረግ ስራ ይሰራል። በመጠነ ማቋረጥ ከ1-6ኛ ከ9.7 ወደ 5% ፣ ከ7-8ኛ ከ10.5 ወደ 3%፣ ከ9-12ኛ ከ10.1 ወደ 2% ዝቅ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- የአርብቶ አደር ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት ከ38.2 ወደ 95%፣ ጥቅል ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ከ96.1 ወደ 100%፣ንጥር ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ከ68.5 ወደ 95%፣ ጥቅል ከ7ኛ- 8ኛ ክፍል ከ51 ወደ 85%፣ ንጥር ከ7ኛ- 8ኛ ክፍል ከ19.6 ወደ 75%፣ ጥቅል ከ9-12 ክፍል ከ13.1 ወደ 70% እንዲሁም ንጥር ከ9-12 ክፍል ትምህርት ተሳትፎ ከ6.1 ወደ 65% የማድረስ ስራ ይሰራል።
- የትምህርት ፍትሀዊነትና አካታችነትን ከማሻሻል አንፃር ፡- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሥርዓተ ጾታ ምጥጥን ከ0.93 ወደ 1፣ ከ1-6ኛ ክፍል ከ0.9 ወደ 1፣ ከ7-8ኛ ክፍል ከ0.91 ወደ 1 እና ከ9-12ኛ ክፍል ከ0.86 ወደ 1 የሥርዓተ ጾታ ምጥጥን ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህት ተሳትፎ ከ9.2 ወደ 30% ፣ ጥቅል ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ከ31.5 ወደ 50፣ ጥቅል ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ከ18.1 ወደ 50፣ ጥቅል ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ከ6.2 ወደ 30 የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ ከፍ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መርሀ ግብሮችን ተደራሽነት ማሳደግ፡- የተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት ተጠቃሚ የሆኑ ጎልማሶች ከ81.65 ወደ 100%፣ እና የሰለጠኑ አመቻቾች ከ7,831 ወደ 9,079 ከፍ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- የትምህርት ሥርዓቱ በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራቱን ማረጋገጥ፡- በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከ79.3 ወደ 100%፣ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 65.4 በመቶ ወደ 100%፣ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከ50.5 በመቶ ወደ 100% የሚሰራ ይሆናል። እንዲሁም የሙያ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና የወሰዱ እጩ መምህራን ከ99.4 ወደ 100%፣ የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤት መምህራን 100%፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ከ99.1 ወደ 100%፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ከ32.7 ወደ 100% የሙያ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲወስዱ የማድረግ ስራ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፥

- የግብረ-ገብ እና የዜግነት ትምህርትን በሚፈለገዉ ደረጃ እንዲተገበር ማድረግ፣ ተማሪዎችና መምህራን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢውን አደረጃጀት በመፍጠር የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ማጠናከር በስፋት የሚከናወን ይሆናል። የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ የትምህርት ዓይነቱ የይዘት ፍሰት፣ አጥጋቢ የመማር ብቃትና መርሀ ትምህርትን ለመጽሐፍት ዝግጅት ስራ በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ፣ የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ምልመላ፣ አሰለጣጠንና ስምሪት በተመለከተ የፖሊሲ፣ የትምህርት ህግ ማዕቀፍና ሌሎች ማዕቀፎች፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮፋይል፣ የምልመላ፣ የስራ ላይ ስልጠና፣ የማትጊያ ሥርዓትና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ።
- STEAM መምህራንን የፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ የትምህርት ህግ ማዕቀፍ፣ መመሪያዎችን ክልላዊ በማድረግ መተግበር፣ በየደረጃው ላሉ የትምህርት ተቋማት ሊተገበሩ የሚችሉ እና አግባብነት ያላቸው የትምህርት ቴክኖሎጂ መረጣ የሚካሄድበት ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር።
- ትምህርትን ተደራሽ ማድረግና ውስጣዊ ብቃትን ለማሻሻል የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ ስልቶችና ስርዓቶችን መንደፍ፣ የትምህርት ቤቶችን ስርጭት (School Mapping) መሠረት በማድረግ ፍትሃዊና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለሁሉም ዜጎች ትምህርትን በፍትሀዊነት ለማዳረስ የሚያስችሉ ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፣ የሴቶች፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹና፣ የአርብቶ አደርና ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአዎንታዊ ድጋፍ ስርዓት መዘርጋትና በግብዓትና በሰው ኃይል የማደራጀት ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ።
- በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጡ ትምህርቶች ከአካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞና ተለማጭ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ፤ መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ፕሮግራም ወጣቶችን እና ጎልማሶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲና ስትራቴጂ መዘርጋት፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞችን ተደራሽ ለማድረግ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን ማስፋፋት፣የትምህርት ዘርፉን ያልተማከለ ሥርዓት ለማዘመን የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች እና የአሠራርና የአደረጃጀት ሰነዶችን ክልላዊ በማድረግ በየጊዜው እየፈተሹ ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

5.1.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አግባብነት፣ ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ ተቋማዊ አቅምና ብቃት ማጎልበት፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የሳይንስ ባህል ግንባታ

ማጠናከር፣ ኢኖቬሽን፣ ጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፣ መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ ማሳደግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለው፣ ተነሳሽነትን የተላበሰና ከሥራ ፍላጎት ጋር ራሱን የሚያስማማ፣ ስራ ፈጣሪ በመሆን የኢኮኖሚውን ዕድገትና ልማት የሚያራምድ የሰው ኃይል መፍጠርና አዋጭ ቴክኖሎጂ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማሸጋገር የክልላችንና የሀገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና አስተዋጽኦ ማድረግ ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- **የሰው ኃይል ልማት ማፍራት፡-** የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ዓመታዊ የመደበኛ ሰልጣኝ ቅበላ አሁን/2012 ዓ.ም ካለው 44,371 በ2022 ወደ 90,095.49 ለማሳደግ፣ የገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠና ዓመታዊ ስልጠና ከ40,531 ወደ 66,847 ለማሳደግ ታቅዷል። በትብብር ስልጠና የሚሳተፉ ኢንዱስትሪዎች፣ የልማት ድርጅቶችና ጥ/አ/ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ11,926 ወደ 18,026 በማሳደግ ጥራቱ የተጠበቀ የትብብር ሥልጠና ሽፋንን አሁን ካለበት ከ66 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በትኩረት ዘርፎች የበቃ የኢንዱስትሪና የተቋማት አሰልጣኞችን አሁን ከሚታየው እጥረት በበቂ ደረጃ ለመቅረፍ በA ደረጃ ከ102 ወደ 898፣ በB ደረጃ ከ1,738 ወደ 2,459 ለማድረስ ይሰራል። ቴክኖሎጂን የመቅዳትና የማሻሻል አቅም የተረጋገጠላቸው 2,252 የተቋም ዉስጥ አሰልጣኞች ወደ 3,668 ለማድረስ ይሰራል።
- **ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ ማድረግ፡-** በወረዳዎች ተደራሽነቱ የተረጋገጠ የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ከ55 ወረዳዎች (45%) ወደ ሁሉም ወረዳዎች (100%) ለማዳረስ ይሠራል እንዲሁም ዕውቅና አግኝተው ወደ ፖሊ-ቴክኒክ ያደጉ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከ9 ፖሊ ተቋማት በየዓመቱ 1 በስታንዳርዱ መሰረት ወደ 18 ፖሊ ተቋማት እንዲደርሱ ይደረጋል።
- ለመንግስት የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት የተለያዩ የስልጠና ፕሮግራሞች አሁን ካለበት 47 ከአካባቢ የልማት ኮሪደር እና ወቅቱ ከሚፈልገው የገበያ ፍላጎት አንጻር በ2022 ዓ.ም ለ79 የስልጠና ፕሮግራሞች በተጨማሪም የፕሮግራም ምዝገባ፣ እውቅናና የእውቅና እድሳት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዷል። እንዲሁም ለግልና እና ለመያድ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት የተለያዩ የስልጠና ፕሮግራሞች አሁን ካለበት 25 ከአካባቢ የልማት ኮሪደር እና ወቅቱ ከሚፈልገው የገበያ ፍላጎት አንጻር በ2022 ዓ.ም ለ49 የስልጠና ፕሮግራሞች በተጨማሪም የፕሮግራም ምዝገባ፣ እውቅና የእውቅና እድሳት ፈቃድ ይሰጣል።
- **የቴክኖሎጂ ሽግግርና ኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን በተመለከተ፡-** ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከምርምር ተቋማትና

ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበር አዲስ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና መቅዳት አሁን ካለበት 103 ወደ 175 ለማሳደግ እና የተለዩና የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ላይ አብዝ ኢንተርፕራይዞችን ማብቃት አሁን ካለበት ከ234 ወደ 654 ለማድረስ ይሰራል።

- ለነባርና በአዲስ ተደራጅቶ ወደ ሥራ ለሚገቡ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች የሚሠጥ የኢንዳስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የሚደረግላቸው ነባር የኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች ከ64,547 ወደ 290,648 ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም ድጋፍ የሚደረግላቸው አዲስ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች ከ46,660 ወደ 360,248 ለማድረስ ይሰራል። በተሰጠ ኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍና በተሸጋገረ ቴክኖሎጂ የተፈጠረ ሀብት ከ23 ሚሊዮን ብር ወደ 66 ሚሊዮን ብር እንዲደርስ ይደረጋል።
- ኢንተርፕራዝ አንቀሳቃሾችን፣ አሰልጣኞችን፣ ሰልጣኞችን እና አካል ጉዳተኞችን በክህሎት፣ በተግባራዊ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በቴክሎሎጂ ውድድር እና ኤግዚቢሽን በዓመት አንድ ጊዜ በማካሄድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን ማረጋገጥና በውድድሩ ክልላዊ ገፅታ ለመገንባት ታቅዷል።
- **የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጥ፡-** የምዘና መሳሪያ አዘጋጅ ባለሙያዎችን ከ126 ወደ 2,105 ለማድረስ፣ የምዘና መሳሪያ (ተጨማር አዳዲስ ቨርሽን) ዝግጅት ከ362 ወደ 2,167 ለማሳደግ፣ የድህረ ምዘና ጥናትን ምርምር ሰነድ ከ7 ወደ 76 ለማሳደግ እና በአዲስ ዕውቅና ያገኙ የኢንዱስትሪ ምዘና ማዕከላት ከ 243 ወደ 2,330 ለማድረስ ይሰራል።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከ122 ወደ 1,674 ፣ የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ከ 19 ወደ 292፣ የቴ/ሙ/ት/ስ/ማ/ተቋማት ከ102 ወደ 365፣ እውቅና የታደሰላቸው ነባር የኢንዱስትሪ የምዘና ማዕከላት ከ582 ወደ 5,543 ፣የኢንደስትሪ መዛኞች የማፍራት ስራ ከ698 ወደ 9,616፣ የመዛኝ እውቅና ዕድሳት የተደረገላቸው መዛኞችን ከ778 ወደ 7,245 ለማድረስ ይሰራል።
- በስምንቱ የትኩረት ዘርፎች በዝቅተኛና መካከለኛ የኢንደስትሪ ባለሙያዎችን ብቃት ዓመታዊ ምዘና መጠን ከ42,607 ወደ 102,638 ፣ መደበኛና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ሠልጣኞችን ብቃት በምዘና ከ86,115 ወደ 396,173፣ ገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃት በምዘና ከ4,304 ወደ 283,362፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸው በምዘና የተረጋገጠ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች አሁን ካለበት 22,569 ወደ 92,722 ለማድረስ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የውጤት ተኮር ስርዓቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአመራርና አሰልጣኝ ልማት፣ የተቋማት አቅም ግንባታ ስልጠና ኮሌጆችን በሁሉም ወረዳዎች በማዳረስ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የትምህርት መሳሪያዎች አቅርቦት

ከመንግስት ግምጃ ቤት ከሚመደበው በተጨማሪ በተለያዩ ተቋማት/መ/ቤቶች፣ የህብረተሰብ ንቅናቄ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር፣

- የሰልጣኝ ልማት (መደበኛ እና ገበያ-ተኮር አጭጭር ስልጠና) ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት ብቃት ያለው ሙያተኛ ማፍራት፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ከ4ቱ የድጋፍ ማዕቀፎች (በቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት፣ ኢኮኖሚ መሰረተ ልማት፣ ፋይናንስ መሰረተ ልማትና ገበያ ትስስር) አንጻር ያሉባቸውን ክፍተቶች በማሟላት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣ የህብረተሰብ እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ማሰደግ፤
- ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት /Scaling up/ ከክልሎችና ከተቋማት የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት ሂደት በየደረጃው በዘርፉ ግቦች አፈፃጸም ላይ የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች በማስተላለፍ በስፋት እንዲተገበር ይደረጋል።
- የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማስጠበቅና ለማጠናከር የንድፈ ሀሳብና የተግባር ሥልጠናን በጠበቀ መልኩ Curriculum እና TTLM ይሰራል። የአካባቢ ጥበቃ (Green TVET) ተቋማቱ የተፈጥሮ አካባቢ ብክለትን ለማስወገድ ካይዘንን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ። እንዲሁም በትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ የዲጅታል ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል።

5.1.4. የደቡብ አመራር አካዳሚ ሥራዎች

የቀጣይ አሥር ዓመታት የደበብ አመራር አካዳሚ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- አካዳሚው በሰው ኃይል፣ በአሰራር እና በአደረጃጀት ተቋማዊ አቅም ማሳደግ፣ ከክልል እስከ ቀበሌ በየደረጃው ላሉ አመራሮች የስልጠና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ስልጠናዎችን በስፋት መስጠት፣ የሥራ አመራር ሥልጠና ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና ስልጠና መስጠት፣ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ማካሔድ እንዲሁም ተቋማትን የማማከር ሥራዎችን መስራት።
- በሀገር ውስጥ አቻ ተቋማት እንዲሁም ከሀገር ውጭ ካሉ የስልጠናና የምርምር ተቋማት ጋር ስትራቴጂያዊ ግንኙነት መፍጠር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ በመቀመር እና ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ አሰራር በተከታታይ የማሻሻል ስራ የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመት የደቡብ አመራር አካዳሚ ዓላማ እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የተቋማት አመራርና የፈጻሚዎችን አቅም በመገንባት የክልሉን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት እንዲፋጠን ማድረግ።

የቀጣይ አሥር ዓመት የደቡብ አመራር አካዳሚ ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የአገልግሎት ፍትሃዊነት፣ ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግን በተመለከተ፡- ተቋማዊ አቅምን በማጎልበት፣ አሠራሮችን በማዘመን፣ የሰው ኃይል መጠን እና ብቃትን ከተቋማዊ ተልዕኮ አፈጻጸም ጋር በማመጣጠን፣ አደረጃጀቶችን ለሥራ ፍሰት ምቹ በማድረግ፣ ግብዓቶችን በማሟላት፣ የደንበኛ ተቋማትን እና የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ፍላጎት በሳይንሳዊ ጥናት በመለየት የሚሰራ ይሆናል።
- ለአመራርና ፈጻሚዎች አግባብና ጥራት ያለው ስልጠና በመስጠት የህዝቡን የመልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን መመለስ፣ የሥልጠና ፍላጎትን መለየት የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናቶች ማካሄድ፣ 27 ነባር የሥልጠና ሞጁሎችን መከለስና 50 አዳዲስ የሥልጠና ሞጁሎችን በመቅረጽ ከክልለ እስከ ወረዳ ባሉ እርከኖች ላይ የሚገኙ 40,000 አመራሮች፣ ለ36,000 የቀበሌ አመራሮች ስልጠና የመስጠት እንዲሁም በሥራ አመራር እና በልዩ ሥልጠና ዘርፍ 50,000 ሰልጣኞችን የማሰልጠን ስራ ይሰራል።
- የምርምር እና የዕውቀት ሽግግርን ማጎልበት በተመለከተ፡- የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ከመስራት አንጻር እስከ 2022 ዓ/ም 70 የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በመስራት የአመራርና የፈጻሚዎች ስልጠና ውጤታማነት ከማረጋገጥ ባሻገር በጥናት ላይ ተመስርተን ተቋማትን በማማከር የተቋማት የመፈጸም ብቃት ከፍ እንዲል ይደረጋል። እንዲሁም በጥናትና ምርምር ግኝቶች ላይ 8 ሀገራዊና ክልላዊ አውደ ጥናቶች ይደረጋሉ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የደቡብ ሥራ አመራር አካዳሚ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተቀምጠዋል፥

- የታቀዱ የስልጠናና የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ከከፍተኛ ትምርትና ከአቻ ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል።
- አካዳሚውን በተገቢው ማስተዋወቅና በሙሉ አቅሙ ህዝቡ ጋር ተደራሽ መሆን እንዲችልና የመንግስትና የግል ተቋማት የአፈጻጸም ክፍተት በስልጠና እና በጥናትና ምርምር እንዲሞላላቸው ማድረግ እና ተቋማትም መርጠው እንዲጠቀሙት ለማስቻል የማስተዋወቅ ሥራዎች ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተገበሩ ይሆናል።
- በተጨማሪም በስትራቴጂክ ዘመኑ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ ጥናት በማድረግና ፍላጎታቸውን በመለየት እንዲሁም የሚስተዋሉ ጉድለቶችን በማረም፣ የሚሰጠው የስልጠናና የምርምር አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ በማገዝ ቅልጣፌ እንዲኖረው በማድረግ፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራትም ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋፋት፣ተቋማዊ የሰው ኃይል ልማት ሥራዎችን በማከናወን እንዲሁም የውስጥ ገቢ በማሳደግ ተልከዎችን ለመፈጸም ይሰራል።

5.1.5 የጤና ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ውጤታማ፣ ጥራት ያለውና ፍትሐዊ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦትና ሽፋንን ለማረጋገጥ የሚሰራ ሲሆን የጤና አገልግሎት ወጪም የፋይናንስ ስጋትን ለመቅረፍ የሚደረገውን ትግበራ ማፋጠን ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል እንዲሁም የጤናውን ሥርዓት በየግዜው ለሚቀያየረው የህብረተሰቡ ጤና ፍላጎት ምላሽ ሰጪ የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ። በተጨማሪም በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የተሃድሶና የህመም ማስታገስ የጤና አገልግሎቶች ዜጎችን ለፋይናንስ ችግር ሳያጋልጡ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋንን ማሻሻል ትኩረት ይሰጠዋል።
- በተመሳሳይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በማህበረሰብ ግጭቶች፣ ባልተጠበቁ የበሽታ ወረርሽኞች እና በአዳዲስ የጤና ስጋቶች ምክንያት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን በፍጥነት በመለየት፣ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጭነትን በማጠናከር የዜጎችን የጤና ደህንነት መጠበቅ አፅኖት ይሰጣቸዋል። የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ አካታችነት እና ባለቤትነትን በማጠናከርና በማሻሻል በጋራ ጤና ነክ ችግሮችን እየለዩ መፍትሄ በመስጠት የተሻለ የጤና ስኬት እና ፋይዳ የማምጣት ሥራዎች ይሰራሉ። ቤተሰቦች በጤና ፕሮግራሞች ዙሪያ በተለይም በሃይጅንና አካባቢ ጤና ሥራዎች፣ የእናቶች እና ህጻናት ጤና አገልግሎቶች የአጠቃቀም ሽፋን እና የጤና መድን ሽፋን ላይ የሚያድርጉትን ተሳትፎ ለማሳደግ ትኩረት ይደረጋል። የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት በማሻሻል ጥራት ያላቸውን መድሃኒቶችን፣ የላቦራቶሪና የምርመራ መሳሪያዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ ትኩረት ይሰጠዋል። የጤናው ዘርፍ የቁጥጥር ሥርዓትን በማሻሻል ለህብረተሰቡ የሚቀርበውን ጤና ነክ ምርት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሻሻል የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ።
- የሥራ አመራር እና መልካም አስተዳደርን በማሻሻል ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው የአመራር እና የአስተዳደር ሥርዓት በየደረጃው የመዘርጋት ሥራ ይሠራል።
- የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሻሻል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ይህም የግሉ ዘርፍ በጤናው ላይ ያለውን ተሳተፎ በተለይም ደግሞ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት በመስጠት እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ላይ ያተኮረ የማይበገር የጤና ሥርዓት በመገንባት የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጸኦ ማበርከት፣ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ማረጋገጥ፤ ዜጎች በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ ሳይዳረጉ የጤና አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች የሚደርሱ የእናቶችና ህጻናት ሞትን መግታት፤ ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ሳቢያ

የሚደርሱ ህመምና ሞትን መከላከልና መቀነስ፣ ዜጎችን ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች መጠበቅ፣ የወረዳ ትራንስፎርሜሽንን ማምጣት እና ተገልጋይ ተኮር እና ተዓማኒነት ያለው የጤና ሥርዓትን መፍጠር የዘርፉ የልማት ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- **ሁሉንም የጤና ዓላማዎች የሚመለከት የውጤት ዒላማዎች፡-** ከወሊድ በኋላ በህይወት የመኖር የእድሜ ጣሪያን አሁን ከደረሰበት 65 ወደ 70 እድሜ ለማድረስ፣ ሁሉ አቀፍ የጤና ሽፋን ጠቋሚን (UHC Index) ከ0.43 ወደ 0.7 ማሳደግ፣ በመጨረሻው የጤና አገልግሎት ጉብኝታቸው (የደንበኛ እርካታ መጠን) በአገልግሎቱ መርካታቸውን የገለጹ ደንበኞች ምጣኔን ከ46% ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዷል።
- **የእናቶች ጤና አገልግሎት /MCH-MNH፡-** የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ401/100,000 ወደ 140/100,000 ዝቅ እንዲል፣ በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ50.2% ወደ 95%፣ የድህረ ወሊድ እንክብካቤ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ34% ወደ 95%፣ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምጣኔን (CPR) ከ44.6% ወደ 60% የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- **የጨቅላ ህጻናትና ህጻናት ጤና አጠቃላይ /MCH Overall፡-** እድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ሞት ምጣኔ ከ55/1000 ወደ 35/1000፣ እድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ43/1000 ወደ 20/1000፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ30/1000 ወደ 15/1000 ዝቅ እንዲል ይሰራል። እንዲሁም ከ5 ዓመት እድሜ በታች ያሉ ህፃናትን የመቀጨጭ ምጣኔ ከ6.30% ወደ 3% እና ከ5 ዓመት እድሜ በታች ያሉ ህፃናትን የመቀንጨር ምጣኔ ከ36% ወደ 18% ዝቅ እንዲል ይሰራል። በተጨማሪም ሁሉንም ክትባቶች ጨርሰው የወሰዱ ህጻናት ሽፋንን ከ38% ወደ 95% ማሳደግና ኤች.አይ.ቪን ከእናት ወደ ጽንስ/ልጅ የመተላለፍ መጠንን ከ13.4% ወደ 5% የመቀነስ ስራ ይሰራል።
- **ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች፡-** የቲቢ ልየታ መጠንን ከ60.2% ወደ 90% ማሳደግ፣ አዲስ በተለዩ የስጋ ደዌ ህሙማን ላይ የደረጃ 2 የጉዳት መጠንን ከ12% ወደ 4% መቀነስ፣ አዲስ በኤች.አይ.ቪ የመያዝ መጠንን ከ0.03 ወደ 0.01% መቀነስ እና የወባ በሽታ ክስተት መጠንን ከ15/1000 ወደ 0 መቀነስ። እንዲሁም በወባ ምክንያት የሚከሰተውን የሞት መጠን ከ0.2/100,000 ወደ 0 የማውረድ ስራ ይሰራል።
- **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች /DPC-NCD፡-** በዋና ዋና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች አማካኝነት የሚከሰት ያለዕድሜ ሞት መጠንን ከ18% ወደ 10% ለመቀነስ፣ የማህጸን ጫፍ ካንሰር ልየታ የተደረገላቸው እድሜያቸው ከ30-49 ከሆኑ ሴቶች ሽፋንን ከ4.6% ወደ 65% ለማሳደግ፣ የደም ግፊት ከፍ ካለባቸው እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች መካከል የደም ግፊት ልኬታቸውን መቆጣጠር የተቻለ ታካሚዎች

መጠን ከ26% ወደ 80% ለማሳደግ እና በደማቸው የስኳር መጠን ካለባቸው ሰዎች መካከል በደማቸው የስኳር መጠንን መቆጣጠር የተቻለ ታካሚዎች መጠን ከ24% ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዷል።

- **የህክምና አገልግሎቶች፡-** ዓመታዊ አማካይ የተመላላሽ ህክምና ጉብኝት/የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት መጠንን ከ1.05% ወደ 3% ለማሳደግ፣ በጤና ተቋማት የመሞት ምጣኔን (ከጠቅላላ ሞት) ከ2.2% ወደ 0.8% ለመቀነስ፣ ከጠቅላላ ከተሰበሰበ የደም መጠን የደም ተዋጽኦ የተሰራላቸው መጠን ከ5.5% ወደ 100% ለማሳደግ እና የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን የአባ/እማወራ የአባላት ምጣኔን 35% ወደ 100% ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተቀምጠዋል፥

- በጤና ማጎልበት፣ በሽታ መከላከል እና ተገቢ የፈውስ ህክምና አገልግሎት ላይ ያተኮረ ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ የስነ-ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት፣ የልጆች፣ የወጣቶች እና የአፍላ ወጣቶች ጤና፣ ኤች አይ ቪ፣ ወባ፣ ቲቢ፣ ስጋ ደዌ እና ሄፖታይተስ ያሉ ተላላፊ በሽታዎች የመከላከል ስራ የጤና ሴክተር በቂ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን እንዲሁም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች (NCDs) መከላከልና መቆጣጠር፣ የጤና ኤክስቴንሽን እና የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፉ ይደረጋል።
- የጤና ድንገተኛ እና የአደጋ ስጋት አስተዳደርን ማሻሻል፣ የማህበረሰቡን የጤና ባለቤትናትንና ተሳትፎን ማሳደግ፣ የፋርማስትካልና የህክምና ቁሳቁሶች አስተዳደር ማጠናከር፣ የቁጥጥር ስርዓቶችን ማሻሻል፣ የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደርን ማሻሻል፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥን ማሻሻል (መረጃ፣ ምርምር እና የእውቀት አስተዳደር)፣ የጤና ፋይናንስ ማሻሻል፣ የጤና አመራርና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፣ የጤና መሠረተ-ልማት ማሻሻል፣ ዲጂታል ጤናንና ፈጠራዎችን ማሻሻል እና የባህል ህክምናን ማሻሻል ተጠናክሮ ይሰራል።
- ጤናን በሁሉም ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ውስጥ ማካተት፣ የጤና እና ከጤና ጋር የተዛመዱ እይታዎችን በሁሉም የሚመለከታቸው የዘርፍ ፖሊሲዎች እና ህገ ደንብ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣ ለጤና መጠበቅ እና በማህበራዊ የጤና ጠንቅ በሆኑ ጉዳዮች የህዝብ ንቅናቄ ማድረግ፣ የግሉን ዘርፍ የጤና ተሳትፎን ማሻሻል፣ በጤናው ዘርፍ የግሉን ሴክተር ተሳትፎ ለማጠናከር ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን እንደገና ማሻሻል፣ የመንግሥት-የግል ሽርክና/አጋርነት ማጠናከር፣ የህክምና ምርቶችን እና አቅርቦቶችን ማምረት እና ስርጭት ውስጥ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ማጎልበት፣ በጤና እና ከጤና ጋር በተዛመዱ አገልግሎቶች እና ምርቶች የቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ በማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

5.2 የሴቶችና የሕጻናት ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶችና የሕጻናት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፍ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲያድግ ማድረግ፤ የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ ተቋማዊነት እንዲጎለብት ማድረግ፤ የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ የተመለከቱ አሉታዊ የስርዓተ-ጾታ ወግ /አመለካከቶችና ተግባራት በመቀየር የአመለካከት ለውጥ ማምጣት፤ የሕጻናት ስብዕና ልማት ማጎልበት፤ የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን መገንባት።
- ሴክተር መ/ቤቶችን በማስተባበር፣ እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ንቅናቄ በመፍጠር፣ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት፣ የአስፈጻሚ አካላትን አቅም በመገንባት፣ ተግባርና ሃላፊነትን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ፣ ሊያሰሩ የሚችሉ ደንቦች፤ መመሪያዎችንና የአሰራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀትና አፈጻጸማቸውን ማጎልበት፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በአግባቡ የልየታ ሥራ በመስራት ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 50 በመቶ ሴቶችን የማድረግ ስራ ይሰራል።
- ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን ህይወት ለመታደግ አማራጭ የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ በተለይም ለአካል ጉዳተኛ፣ ለስደተኛና ተፈናቃይ ህፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት መብቶቻቸውን ማስጠበቅ፣ የተሀድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት (One Stop Center)፣ የአደጋ ጊዜ የስልክ ጥሪ አገልግሎት (Hot line)፣ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት ቤተሰብ ለማጠናከር የሚያስችሉ የኢኮኖሚ፣ የስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች የማስፋፋት ሥራዎች ይሰራሉ።
- የአስፈፃሚ አካላት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን አንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ በመከታተል የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ማሻሻያ እንዲደረግባቸው በማድረግ፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ የቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት ማድረግ፣ ለሁሉም ህፃናት የቀዳማይ ልጅነት ዘመን አገልግሎቶች ማነቃቂያ፣ የመማርና የመጫወት ዕድልን በማስፋፋት፣ የትምህርት ቤቶች ምቹነትና ተስማሚነት ማረጋገጥ፣ ህፃናት በእውቀት እንዲጎለብቱና በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ይሰራል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በክልላችን ሴቶችና ህፃናት በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና በባህል መስኮች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት፣የህፃናት መብትና ደህንነት የተከበረባት፣ የህፃናትና መልካም ስብዕና የጎለበተባት እና የስርአተ-ጾታ እኩልነት የሚሰፍንበት ይሆናል ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶችና የሕጻናት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

የሴቶችና ህፃናት ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-

- የሚመለከታቸውን ሴክተር መ/ቤቶችን በማስተባበር እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ንቅናቄ በመፍጠር ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ የስራ እድል እንዲፈጠር በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ የሴቶች ተጠቃሚነት 35% ወደ 50% ለማድረስ እና የሴቶች የስራ ክፍያ ልዩነት ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በፋብሪካ፤ በግንባታና በኮንስትራክሽን ዘርፍ በአማካይ 60% ከነበረበት ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት በመስራት ልዩነቱን ለመቀነስ ታቅዷል፡፡ እንዲሁም ተከታታይ የአቅም ግንባተ ስራዎችን በመስራት 533 ሴቶችን ለአመራር ብቁ ለማድረግ ታቅዷል፡፡
- በገጠር የሴቶች የመሬት ባለቤትነት ተጠቃሚነት ሰርተፊኬት ያገኙ ሴቶች ከ446,624 ወደ 710,000 ለማድረስ እና ባልና ሚስት በጥምር ከ2,196,593 ወደ 2,840,000 ሴቶች በማድረስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል፡፡
- ሴቶች በግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲቻል እማወራ ሴት አርሶ አደሮች 100% በግብርና ፓኬጅ (በእርሻና እንስሳት ልማት) ተጠቃሚ እንዲሆኑና ባለትዳር ሴቶች 50 በመቶ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል፡፡
- ሴቶች ለብቻቸው በህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ተጠቀሚ ለማድረግ በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌዎች 1,657 አዲስ በማደራጀት 1,843 ከነበረበት ወደ 3,500 ለማድረስ የሚሰራ ሲሆን በዚህም የገንዘብ ቁጠባና ብድር የሕብረት ሥራ ማህበራት የሴቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን በማሳደግ አሁን ካለበት 572,912 ወደ 888,636 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በአካባቢ ጥበቃ የሴቶችን ተሳትፎ ከ2,408,393 ወደ 5,623,200 ለማድረስ ታቅዷል፡፡
- የተለያዩ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ 897,222 ከነበረበት ወደ 1,707,924 የሆኑ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡
- የተለያዩ የአቅም ግንበታ ፕሮገራሞች በማካሄድ 4,502 ሴቶች የህይወት ክህሎታቸውን አንዲያዳብሩ የማስቻል ተግባር ለማካሄድ እቅድ ተይዟል፡፡
- የሴቶችን የገበያ ትስስር ተጠቃሚነት ከ137,640 ወደ 195,448 በማሳደግ በአነስተኛ ግብርና ምርቶች ማቀነባበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡ እንዲሁም 1 የሴቶች የገበያ ማዕከል በመገንባት የሴቶችን የግብይት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል፡፡
- የሴቶች የማምረቻና ኢንቨስትመንት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር የትብብርና የቅንጅት ስራዎችን በማጠናከር፣ በማንፋክቸሪንግ ዘርፍ የሴቶችን ባለቤትነት ከ6 በመቶ ወደ 30 በመቶ እና በኢንቨስትመንት ዘርፍ ደግሞ ከ9.4 በመቶ ወደ 40 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

- በሁሉም ዘርፍ የሴቶችን ተሳታፊትና ተጠቀሚነት ለማሳደግ በልማት ቡድን ከማደራጀት አንጻር በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌዎች 25336 አዲስ የሴቶች ልማት ቡድን በማደራጀት 63,340 ከነበረበት ወደ 88,676 በማድረስና የተደራጁትንም በማጠናከር መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጂቶች ዕቅዳቸውን ከሴቶች ልማት ቡድን ጋር በማስተሳሰር እንዲያቅዱና እንዲተገብሩ ለማድረግ ታቅዷል።
- የሴቶች የቁጠባና ብድር ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማጎልበት ዙሪያ በሀሉም አካባቢ ለሚገኙ ሴቶች የግንዛቤና ንቅናቄ ስራ በመስራት እንዲሁም ከፋይናንስ ተቋማት ጋር አጋርነት በመፍጠር 1,619,500 ሴቶች በቁጠባ እዲሳተፉ በማድረግና የመቆጠብ አቅማቸውን ከ6,405,280,926 ብር ወደ 8,669,143,916 ብር የማሳደግ እና እንዲሁም የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን መጠን ከ1,546,972 ወደ 2,956,000 ከፍ በማድረግ የብድር አገልግሎቱን ምጣኔ 1,139,865,481 የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ታቅዷል።
- የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግና ከማነኛውም ጥቃት ለመከላከል በተቋቋሙ አዳሪ ትምህርት ቤቶች/ሆስቴሎች/ ለሚማሩ 5,475 ሴት ተማሪዎች ድጋፍ ለማድረግ እና በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሴቶችን ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 1,996,760 ወደ 3,332,750 ለማሳደግ ይሰራል። በተጨማሪም የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመስራት ታቅዷል።
- የሴቶች ጤና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎች በመስራትና በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና አደረጃጀቶች ዘንድ የትብብርና የቅንጅት ስራዎችን በማጠናከር፣ የማህፀን በር ካንሰር ታላሚ (ዕድሜያቸው ከ30-49) ከሆኑ 2,671,711 ሴቶች መካከል ምርመራ የተደረገላቸዉ ሴቶች በ2012ዓ/ም 125,096 (4.6%) ከነበረበት በ2022 ዓ/ም ወደ 2,671,711 (100%) ሴቶች ልየ,ታና ምርመራ በማድረግ ይሰራል፤ በተለያዩ ምክንያቶች የማህፀን መውጣትና የፊስቱላ ችግር ክስተት የሚያጋጥማቸው ሴቶች 0.4 በመቶ ከነበረበት 0.05 በመቶ ዝቅ የማድረግ እና የሴቶች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ከ44.6 በመቶ ወደ 54 በመቶ ለማድረስ፣ እንዲሁም በህክምና ተቋማት የሚወልዱ ሴቶችን ከ73.3 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በአመጋገብና ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ትምህርት ያገኙ ነፍሰጡርና የሚያጠቡ ሴቶች ከ327,937 ወደ 393,709 ለማድረስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመስራት ታቅዷል።
- ለችግር ለተጋለጡ ሴቶች ምላሽ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማስፋፋትን በተመለከተ 2 የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት/one stop) በሁሉም መዋቅሮቻችን እንዲቋቋሙና አገልግሎት እንዲሰጡ በማመቻቸት 250 ለማድረስ ታቅዷል። እንዲሁም ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ማገገሚያ ማዕከላትን በማቋቋምና በቁሳቁሶች በማሟላት የተሀድሶ አገልግሎት ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግና በቀጣይ አሥር አመት 22 ለማቋቋም የታቀደ ሲሆን በእነዚህም ተቋማት 4,365 ሴቶች የተሀድሶ ማዕከላት አገልግሎት አንዲያገኙ ለማድረግ፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ችግር ለደረሰባቸው 10,000 ሴቶች ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

- ለ141,324 ሴቶችና ህፃናት የህግ ድጋፍና ምክር አገልግሎት፣ 89,500 የተለያዩ ማህበራዊና አስተዳደራዊ በደሎችና ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት፣ 16,550 የተለያዩ ጥቃት ለደረሰባቸውና ድጋፍ ለሚሹ ሴቶችና ህፃናት በፍርድ ቤት ጉዳዮቻቸውን የመከታተል፣ 15,892 ድጋፍ ተደርጎላቸው የፍርድ ቤት ውሳኔ ላገኙ ሴቶችና ህፃናት እንደፍርድ እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ክስ ማዘጋጀትና ውጤቱንም የመከታተል እና ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት የነጻ ጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- በክብር መዝገብ ላይ የተመዘገበ የሕጻናት ልደት ምዝገባን 75 በመቶ የማድረስ፣ በአማራጭ ፕሮግራሞች ድጋፍ በማግኘት ላይ ያሉ የህፃናት ቁጥር ከ541,064 ወደ 1,298,558 የማሳደግ፣ ጥቃት ደርሶባቸው የተቀናጀ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት 90 በመቶ፣ እንዲሁም 90 በመቶ ጥቃት የደረሳባቸው ህፃናት እና 100 በመቶ ከጎዳና የተነሱና ህግን ተላልፈው የተገኙ ህጻናት የተሃድሶ አገልገሎት እንዲያገኙ ይደረጋል። በተጨማሪም 5,000 ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትና ቤተሰቦቻቸው የኢኮኖሚ ድጋፍ እና 35,500 ህፃናት ጎዳና ለወጡባቸው ቤተሰቦች የስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ጎዳና የሚወጡ ህፃናትን 100% ለመቀነስ ይሰራል።
- በህፃናት መብት፣ አያያዝና አስተዳደግ የሰለጠኑ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራንና አመቻቾች ወደ 100%፣ ትምህርታቸውን በትክክለኛ እድሜ የጀመሩ ህፃናት ምጣኔ 100%፣ ት/ቤታቸው ከየትኛውም ጥቃትና መድልዎ ነፃ ነው ብለው የሚያምኑ ህፃናት 100%፣ ለትምህርታቸው አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ህፃናት ምጣኔ 100%፣ በክልሉ ከሚገኙ ት/ቤቶች ውስጥ 80 በመቶ ለህፃናት ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።
- በጤና ተቋማት የተወለዱ ህፃናት ምጣኔ 90 በመቶ፣ በምቹና ተስማሚ የህፃናት የቀን ማቆያ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት 100 በመቶ፣ በተመጣጠነ የህፃናት አመጋገብ ግንዛቤ ያላቸው ወላጆችና ተንከባካቢዎች 90 በመቶ፣ በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ብቁና ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት 95 በመቶ፣ ህፃናት በአልኮልና በተለያዩ አደንዛዥ እጾች በሱስ የመያዝ ምጣኔን ዜሮ እዲደርስ ይሰራል።
- የህፃናት ጥቃትና ህገ-ወጥ ዝውውር 10 በመቶ፣ የህፃናት የጉልበት ብዝበዛ 5 በመቶ የመቀነስና በተስማሚ የህፃናት ችሎት ለችሎት የቀረቡ ህጻናት 100 በመቶ ተጠቃሚ በማድረግ ጥቃትን የመከላከልና የመቀነስ ስራዎች ይሰራሉ። 25 የሚሆኑ ተስማሚ የህጻናት ችሎት እንዲደርስ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ በመልካም የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት 80 በመቶ፣ ለብዝሃነት በጎ አመለካከት ያላቸው ህፃናት ምጣኔ 75 በመቶ፣ ለራሳቸው አዎንታዊ ማንነትና እምነት ያላቸው ህፃናት 75 በመቶ፣ ለህይወት ከፍተኛ እርካታ ያላቸው ህፃናት 50 በመቶ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ጤናማ ግንኙነት ያላቸው ህፃናት ማፍራት 75 በመቶ፣ በተፈጠሩ የስብዕና ማዕከላት ህጻናትን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል 50 በመቶ ለማድረስ የሚያስችሉ ስራዎች ይከናወናሉ።

- ጥቃት ለደረሰባቸው 4,450 ሴቶችና ህፃናት የነጻ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት እና 1,000 የሚሆኑ ህጻናት በህግ አባትነን የማወቅ መብት እነዲረጋገጥ የማስቻል ስራ ይሰራል።
- በህፃናት ተሳትፎ ጥቅም አዎንታዊ አመለካከት ያለው ማህበረሰብ 80 በመቶ ማድረስ፣ በልማት እቅድና ፕሮግረሞች ህፃናትን ያሳተፉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት 90 በመቶ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ማስቻል፣ ትርጉም ባለው መንገድ መብታቸውን የመጠየቅ ብቃት ያላቸው ህፃናት 100% የማድረስ እንዲሁም አካባቢያዊና ሀገራዊ ህጎችና ፖሊሲዎች ላይ ተሳታፊነታቸው የጎለበተ ህጻናት 80 ከመቶ እንዲሆን የማስቻልና በመብቶቻቸው ተጠቃሚ የሆኑ ህጻናት 90 በመቶ ለማድረስ እቅድ ተይዟል።
- በሴቶችና ህፃናት ዙሪያ የሕብረተሰቡን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሀይል ጥቃቶች እንዲሁም ህገወጥ ዝውውር እንዲወገዱ/እንዲቀንሱ በሴቶች እና በአጠቃላይ 4,000,000 ህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የማያቋርጥና ተከታታይነት ያለው የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ ስራዎች ይከናወናሉ።
- ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት የመብቶቻቸው ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ፡- እድሜያቸው ለጋብቻ ያልደረሱ ህጻናት ጋብቻን አሁን ካለበት 24.7 በመቶ ወደ 0 ከመቶ እንዲደርስ እና የሴት ልጅ ግርዛትንና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ታቅዷል። እንዲሁም የሴቶች አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊና የቤት ውስጥ ጥቃቶችን በቀጣይ አስር አመት ውስጥ ሙለሙሉ ለማስወገድ ይሰራል።
- የሴቶችንና ህፃናትን ጥቃት ለመከላከል እና ፍትህዊ ምላሽ እንዲያገኙ ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የሴቶችና ህፃናት የፍትህ አካላት የጋራ ፎረም የማጠናከር ስራ ይሰራል።
- በሚደረግላቸው ሁለገብ ድጋፍ 50 በመቶ ሴቶች በመደራጀት መብትና ጥቅማቸውን ማስጠበቅ እንዲችሉ ይደረጋል። ከዚህ በተጓዳኝ ብዛታቸው 702,900 ሴቶች በቀጣይ አስር አመት በበጎ ፈቃድ የአገልግሎት መስኮች ላይ ተሰማርተው ለማህበረሰቡ አገልግሎት መሰጠት እንዲችሉ የማድረግ አቅድ ተይዟል።
- በህፃናት ፓርላማ በንቃት የሚሳተፉ ህፃናት 100 በመቶ፣ በህፃናት መብት ክበባት የሚሳተፉ 80 በመቶ፣ ትርጉም ባለው መንገድ መብታቸውን የመጠየቅ ብቃት ያላቸው ህፃናት 100 በመቶ፣ ሀሳባቸውን በነፃነት መግለጽ የሚችሉ ህፃናት 80 በመቶ፣ የህፃናት ተሳትፎን ለማጎልበት በሚካሄዱ ኩነቶችና ፌስቲቫሎች 4,432,158 ህጻናት እንዲሳተፉ ይደረጋል።
- አካባቢያዊና ሀገራዊ ህጎች እንዲሁም ፖሊሲዎች ላይ ተሳታፊነታቸው የጎለበተ ህፃናት 80 በመቶ፣ ማህበራዊ ተሳትፏቸውን ያሳደጉ ህፃናት 70 በመቶ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ ህፃናት 50 በመቶና ተስማሚ የህፃናት ችሎቶችን ከ15 ወደ 25 ለማድረስ ታቅዷል። በተጨማሪም ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ የህፃናት መብት ኮሚቴዎች(CRC) እና ግብረ ሀይሎች ለማቋቋምና ለማጠናከር ይሰራል።

- **የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር** በተለያዩ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የሴቶችን አቅም በመገንባት በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች፣ አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ አካላት 50 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በምርጫ ዙሪያ በመራጭነት ሁሉም ሴቶች እንዲሳተፉ፣ በአስመራጭነት 50 በመቶ እንዲሁም በተመራጭነት ወይም በእጩነት 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በተጨማሪም የሴቶችን የቤት ውስጥ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ጥናት በማድረግና በጥናቱ ግኝቶች ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶችና የሕጻናት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- በየደረጃው ከላይኛው እስከ ታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን ያለውን የሴቶችና ህጻናት ተቋማዊ አቅም በመገንባት በአደረጃጀት፣ በአስራር እና በስው ሃይል አቅሙን በተሻለ መልኩ በማሻሻል የልማት እቅዱ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸም ይደረጋል። በዚህም መስረት በሁለቱም ዘርፎች የተቀመጡ የመፈጸምና የማስፈጸም የአቅም ግንባታ ግቦች አፈጻጸሞችን በማስተሳስርና በማቀናጀት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸሙ ይደረጋል።
- የሴቶች የልማት ፍላጎት ለማሟላት በራሳቸው በሴቶች የተቋቋሙ አደረጃጀቶችን ያለባቸውን የአደረጃጀት፣ የአስራርና የስው ሃይል አቅማቸውን ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ የእቅዱ ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ እቅዱን በተቀላጠፈና በተናበበ መልኩ የተፈጻሚነቱ ዋና ሃይሎች እንዲሆኑ ይደረጋል። ልዩ ልዩ የማህበረሰብ አደረጃጀቶችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በመገንባት በሁሉም ዘርፎች ሚናቸውን እንዲወጡ በማስቻል ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው የሚረጋገጥ ይሆናል።
- የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ የሁሉንም አካላት ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚሻ እንደመሆኑ መጠን የልማት እቅዱ ዋና ፈጻሚዎች ሴክተር መ/ቤቶችና በተዋረድም የሚገኙ የዞን፤ የወረዳና የከተማ መስተዳደር አስፈጻሚ መ/ቤቶች እንደመሆናቸው መጠን የትብብር፣ ቅንጅት እና ህብረ- ታይልን የማጠናከር ስራ የሚከናወን ሲሆን የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር የሚያስችሉ ፎረሞችን፣ ኔትዎርከችን፣ ጥምረቶችና አደረጃጀቶች እንዲሁም የሁለትዮሽና ባለ ብዙ የትብብር ስምምነቶች የመመስረትና የማጠናከር ስራዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል።

5.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ለዜጎች ምቹ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ፣ አሠሪዎችና ሠራተኞች በሕግ የተደነገጉ መብቶችና ግዴታዎችን አክብረው የጋራ ራዕይ በመሰነቅ ለክልሉ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ፣ መሠረታዊ የሥራ ላይ መብቶች እንዲከበሩ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ተወዳዳሪነት እንዲጨምር፣ የኢንዱስትሪ ሰላም በዘላቂነት እንዲሰፍን፣ ከሚኒስተር መ/ቤት፣ ከልማት አጋሮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ለእነዚህ ጉዳዮች ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ፍትሃዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል።
- የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የትኩረት መስኮች (ልማታዊ ሴፍቲኔትን ማስፋፋት፤ የሥራ ዕድልን ማስፋፋት እና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል፤ የማህበራዊ መድንን ማሰፋፋት፤ የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እና ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የሕግ ጥበቃ እና ድጋፍ መስጠት) ላይ ርብርብ ይደረጋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ሠላማዊ የኢንደስትሪ ግንኙነትን በዘላቂነት ማሻሻልና በመከላከል መርህ የተቃኘ የሕግ ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ፤ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፤ፍትሃዊና ዘመናዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተካታችነት፣ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- **የአሠሪዎችና ሠራተኞች የመደራጀት ምጣኔን ማሳደግ፣** የአሠሪዎች በማህበር የመደራጅት ምጣኔን ከ3.3% ወደ 32% እና የሠራተኞች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን ከ14% ወደ 35% ለማድረስ ይሰራል። እንዲሁም በማህበር የመደራጀት መብታቸውን እንዲጠቀሙ ግንዛቤ በመፍጠር የአሠሪ ማህበር አሁን ካለበት 5 ወደ 36 እና የሠራተኛ ማህበራትን አሁን ካለበት 197 ወደ 368 ለማድረስ ታቅዷል።
- አሰሪዎች እና ሰራተኞች በማህበር የመደራጀት መብታቸው እንዲከበርና ማህበር ባልተደራጀባቸው ድርጅቶች ዉስጥ የህግ ተፈጻሚነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አሁን ካለበት 1,361 ድርጅት ወደ 17,263 ለማድረስ ታቅዷል።
- የማህበራዊ ምክክርና የሥራ ቦታ ትብብር ሥርዓትን ማጠናከርና ማስፋፋት፡- በድርጅት ደረጃ የሁለትዮሽ የሥራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት መዘርጋት አሁን ካለበት ከ197 ድርጅቶች ወደ 368

ለማድረስ፣ አንድ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድን የማቋቋም፣ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶችን ከ4 ማዕከላት ወደ 8 የማድረስ ስራ ይሰራል።

- ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከሚቀርቡ የሥራ ክርክሮች መካከል በስምምነት የተፈቱ አሁን ካለበት 40% ወደ 90%፣ ለአስማሚ ቀርበው በስምምነት የተፈቱ የሥራ ክርክሮችን ከ63% ወደ 100%፣ በአሠሪዎችና በሠራተኛ ማህበራት መካከል የተደረጉ የህብረት ስምምነት ሽፋን ከ35% ወደ 100% የማድረስ ስራ ይሰራል። እንዲሁም በክልሉ በአማካይ 4 ቦታዎች ጊዚያዊ አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የማቋቋም ስራ ይሰራል።
- **የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎት ማስፋፋትና ማሳደግ፡-** በሥራ ላይ የሚደርስ የሞት አደጋዎችን አሁን ካሉበት 52 /100,000 ሠራተኞች በመቀነስ ወደ 35 /100,000 ሠራተኞች ለማድረስ፣ በሥራ ላይ ሞት ያላደረሱ አደጋዎች አሁን ካሉበት 25,000/100,000 ሠራተኞች በመቀነስ ወደ 7,600/100,000 ሠራተኞች ለማድረስ፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎት ሽፋንን በድርጅት አሁን ካለበት ከ12,582 በማሳደግ 80,390 ላይ ለማድረስ እና የሙያ ደህንነትና ጤንነት ቁጥጥር አገልግሎት ላይ 100% የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ዕድሳት ለመሥጠት ይሰራል።
- **የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን መከላከልና መቆጣጠር ፡-** ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል በሥራ ቦታ ቁጥጥር በማድረግ አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን አሁን ካለበት 321,000 በመቀነስ 80,520 ማድረስ፣ አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲያስችል በክልሉ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአቻ ለአቻ ውይይት አሁን ካለበት 84 ወደ 4,085 ትምህርት ቤቶች ማድረስ፣ አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል የማህበረሰብ ውይይት ማካሄድን አሁን ካለበት 42 ቀበሌዎች ወደ 2,686 ቀበሌዎችን ማድረስ፣ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጥን አሁን ካለበት 61,900 (ሴት 28,800) በማሳደግ 4,556,298 (ሴት 1,888,179) ላይ ማድረስ ነው።
- **የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ማጠናከርና ማስፋፋት፡-** ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎትን በ255 ድርጅቶች ሥርዓት በመዘርጋት የሥራ ሁኔታዎች ማሻሻል፣ የቁጥጥር አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል የሚያግዝ አንድ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ላቦራቶሪ ማቋቋም ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 50% ተደራሽ ለማድረግ እና በሥራ ቦታዎች የአመራረትና የአገልግሎት አቅርቦት ዘዴዎች ከብክነትና ከብክለት የፀዱ የአሰራር ሥርዓቶች እንዲዘረጉ ለድርጅቶች የሚሰጡ የቴክኒክና የምክር ድጋፎችን ሽፋን አሁን ካለበት 25 ድርጅት ወደ 189 ድርጅት ለማድረስ ይሰራል።
- **የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፡-** አንድ የሥራ ገበያ መረጃ ቋት በማዘጋጀት እና በየደረጃዉ ጥቅም ላይ በማዋል የሥራ ገበያ መረጃዎችን ጥራት እና የቅብብሎሽ ስርዓት ለማሻሻል ፣የሥራ

ገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በመተንተን 10 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ፣ ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር የትብብር አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ክፍት የሥራ ቦታዎችን የሚያሳዉቁ ድርጅቶችን ቁጥር ወደ 2,050 በማድረስ ጥቅም ላይ እንድዉል ለማድረግ እና በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል አስመልክቶ 2 ክልላዊ ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዷል።

- **የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን በማስፋፋት የዜጎች ተጠቃሚነትን ማሳደግ፡-** ሞዴል የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማመቻቻ ማዕከላትን በ2 ማዕከላት ላይ በማቋቋም አገልግሎቱን ለማሳደግ፣ ለ2,927,278 ሥራ ፈላጊዎች የሙያ ምክር እና የሥራ አመራር አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት የሥራ ሥምሪት ግንኙነቶችን ለማጠናከር እና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የሥራ ባህል ለማሳደግ የሚያግዙ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለ6,750,000 (50% ሴቶች) የህ/ክፍሎች በመስጠት የስራ ስምሪት ተጠቃሚነትን ለማሻሻል ታቅዷል።
- በአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ድጋፍ አግኝተው በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎች ቁጥር አሁን ከደረሰበት 585,371 ወደ 2,145,716 በማሳደግ ሥራ አጥነትን የመቀነስ እና በዉጭ አገር ስራ ስምሪት ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ያሟሉ ሥራ ፈላጊዎችን 100% ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በመደገፍ በዉጭ አገር የስራ ስምሪት ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል።
- መስፈርቱን አሟልተዉ ለሚቀርቡ የአገር ዉስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች 100% ፍቃድ በመስጠት በስራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት ላይ እንዲሰማሩ እና የዉጭ ሀገር ስራ ስምሪት አገልግሎቶች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበል 90% በማስማማት ለመፍታት ይሰራል። እንዲሁም ህገወጥ የሰራተኛ ምልመላ እና ስምሪት የሚሰጡ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የመዉሰድ ምጣኔን ከ80% ወደ 90% በማድረስ ህገ-ወጥነትን ለመከላከል ታቅዷል።
- **መደበኛ ያልሆነ የሰዎች ዝውውር በመከላከል ተጋላጭነትን መቀነስ**፡- የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ፍልሰትን ለመከላከል የሚያስችል ግንዛቤ ያገኙ ዜጎችን ቁጥር ከ16 ሚሊዬን ወደ 17,230,584 ለማድረስ፣ የፍልሰት መረጃ መስጫ ማዕከላትን 1 ከነበረበት ተጨማሪ ሁለት ማዕከል በማቋቋም ወቅታዊ እና ትክክለኛ የፍልሰት መረጃዎችን አቅርቦት እና ተደራሽነትን ለማስፋት እና ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር 80% የሚሆኑት ከስደት ተመላሾች የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙና 60% የሚሆኑ ስደት ተመላሾች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማመቻቸት በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ ታቅዷል።
- **የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ**፡- የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎችን መረጃዎች አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ስርዓት አሁን ካለበት 2 የወረዳ መዋቅር ወደ 101 በማድረስ ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አስተማማኝና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ

ለማድረግ የሚያስችል አንድ ክልላዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ በማቋቋም የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል።

- የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አቀናጅቶ እና አስተባብሮ ለመምራት የሚያስችል በክልል ደረጃና በተዋረድ ባሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች 126 የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶችን በማቋቋም የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነትንና ሽፋንን ማሳደግ፣ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 637,319 የቤተሰብ ተቋም ተገቢ ሚናውን የሚወጣበት አደረጃጀትና አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቀነስ ይሰራል።
- የሀብት ማሰባሰብ ስርዓትን በማጎልበት ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ 1,946,271 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ ለድጋፍ የሚውል ሀብት አሰባሰብ አሁን ካለበት 34,000,000 ወደ 295,274,181 በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ፣1,380 በቀበሌ ደረጃ የማህበራዊ ጥበቃ ባለሙያ በማሰልጠንና በመቅጠር ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ።
- **የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነትና እና ተደራሽነት ማሳደግ፡-** ለ69,582 አካል, ጉዳተኞች የሥነ ልቦና እና ማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማመቻቸት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እና በመምራት የተሃድሶ አገልግሎት ከ30,741 ወደ 246,831 ለማድረስ፣ እንዲሁም 399,195 ለሚሆኑት አካል ጉዳተኞች የመሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ተደራሽነትን እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ታቅዷል። በተጨማሪም ለ272,991 አካል ጉዳተኞች የስራ ዕድል የማስፋት፣ በስራ ቦታ የሚደርስባቸውን መገለልና መድሎ የማስቀረት እና በስራ ቦታ ተመጣጣኝ ማመቻቸትን ለማሳደግ ይሰራል።
- በገጠርና በከተማ የሚኖሩ የመስራት አቅም የሌላቸውና እና የድሃ ድሃ የሆኑ አካል ጉዳተኞች የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እና የሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ተጠቃሚነት ሽፋንን አሁን ካለበት 11,327 ወደ 59,038 ለማድረስ ታቅዷል።
- በአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ላይ ለመስራት ከመንግስት ፈቃድ የወሰዱ 100% መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተገቢ ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችል የክትትል፣ የድጋፍና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ የአካል ጉተኞችና አረጋዊያን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- **የአረጋዊያንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-** ለ109,040 አረጋውያን የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማድረግ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ አረጋውያን መካከል 124,819 የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት እንዲያገኙ የማድረግ፣ እንዲሁም 8 አዲስ አረጋዊያን ማዕከላትን በመገንባት የአረጋዊያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነታቸውን ማሳደግ ፣አረጋዊያን ላይ የሚደርሱ የመብቶች ጥሰቶችን 100% በማስከበር የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል።

- **የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ**፡- በክልሉ ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ ከሚገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 99,138 በማሳደግ ለ224,412 የሥነ-ልቦና እና ማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ እና የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር በዋና ዋና ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ ከሚገኙት የህብተረሰብ ክፍሎች ውስጥ 32,597 የመሰረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል፡፡
- ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ካደረጉ ዜጎች መካከል ለ10,289 የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠትና በማቋቋም እንደዚሁም 10,039 ዜጎችን የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል ።
- የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ ከሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ለ20,489 ለሚሆኑት የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት እና በማቋቋም የችግሩን ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ለመስራት ከመንግስት ፈቃድ የወሰዱ 100% መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተገቢ ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችል የክትትል፣ የድጋፍና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ይሰራል፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አዋጆች፣ፖሊሲዎችና የተለያዩ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ።ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ሳይንሳዊ መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ መንገድ ተሰብሰበው፣ተደራጅተውና ተተንትነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል።

- በሁሉም ተቋማት በፕሮግራሞቻቸውና በእቅዳቻቸው ውስጥ የሴቶችን፣ የወጣቶች፣ የአረንጓዴ ልማት፣ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን፣ በሥራ ቦታዎች ኤች አይ ቪ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር፣ በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎቱን ተደራሽ እንዲያደርጉ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡
- የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ተግባራዊነት ለማሳለጥ የተቋቋሙ ፕላት ፎርሞች፣የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ በማቋቋም፣ አቅማቸውን በመገንባት ከህብረተሰቡ ሀብት በማሰባሰብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ይደረጋል፤ በህብረተሰቡ ዘንድም መረዳዳት ባህል እንዲጎለብት ቤተሰብ ተኮር ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

- በሥራ ቦታ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በአማራጭ የመፍቻ መንገዶች (የሁለትዮሽና የሶስትዮሽ ሥርዓት) እንዲዘረጉ ይደረጋል። እንዲሁም ሠራተኛው በተገቢው ሁኔታ የመደራጀት መብቱን እንዲጠቀም የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተከታታይነት ባለው መንገድ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲከናወኑ ይደረጋል።
- የሴክተሩ ተግባርና ኃላፊነት ዘርፈ-ብዙና ሴክተር ዘለል እንደመሆናቸው መጠን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ የግሉ ዘርፍ፣ አለም-አቀፍና ሀገራዊ የልማት አጋሮችና ማህበራዊ ተጓዳኞች ለዘርፉ ልማት የሚጠበቅባቸውን የጋራና የተናጠል ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉበት የትብብርና የቅንጅት አሰራሮች በየደረጃው እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል።

5.4. የወጣቶችና ስፖርት ልማት

የቀጣይ አስር አመታት የወጣቶችና ስፖርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በቀጣይ 10 ዓመታት መንግስታዊ የአደረጃጀቶችን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ፖሊሲውን ከማሻሻል ጀምሮ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችንና የአሠራር ስርዓቶችን ተግባር ላይ በማዋል፣ የአመራሩን እና የባለሙያዎችን አቅም በትምህርና ስልጠና ፕሮግራሞች በመገንባት እንዲሁም ሕዝባዊ አደረጃጀቶችን በአለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ስታንዳርዶች መሠረት በማደራጀት በፋይናንስ ከመንግስት ድጎማ የሚላቀቁበት የተለያዩ ቋሚ የገቢ ማመንጫ ስልቶች ተነድፈው ተግባር ላይ ይውላሉ።
- **መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት**፡- የወጣት ማዕከላትና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት ተደራሽነት፣ ህጋዊነት እና የጥራት ደረጃ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱን ተከትሎ የወጣት ማዕከላት፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እና የማሰልጠኛ ማዕከላት ከሕብረተሰቡ ቁጥር አንፃር ቁጥራቸውን በማሳደግ እና በህጋዊ አሰራር መሠረት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው በማድረግ በአለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ስታንዳርዶችን መሠረት የሚገነቡበት እና የሚስፋፉበት ስልት ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፣
- **የሕብረተሰብ ተሳትፎን ማጎልበት፡-** በክልላችን በርካታ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ሱሶችና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የመጠቃት ዕድላቸው እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ ጤናማ፣ ንቁ እና አምራች ዜጎችን ለመፍጠር በቀጣይ አስር ዓመታት ልዩ ልዩ የስብዕና ግንባታ አማራጮችና የማህበረሰብ ስፖርት እንቅስቃሴ ፕሮግራሞችን ተግባር ላይ በማዋል የነቃ ማህበረሰብ መፍጠር ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል።
- **የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ማጠናከር፡-** በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ የውድድር መስኮች ሀገራችንን የሚወክሉ ወጣቶችንና ተተኪ ስፖርተኞችን በተፈጥሮ ብቃት ላይ በተመሠረተ ሳይንሳዊ ስልጠናዎች ማፍራት እና ባለሙያዎችን ወጥ በሆነ የስልጠና ስርዓት በማብቃት በቀጣይ አስር ዓመታት አሸናፊ ሀገርና ተወዳዳሪ ክልል መፍጠር ትኩረት የሚሠጠው ጉዳይ ይሆናል፣

- **የግል ዘርፉን ተሳትፎ ማጎልበት**፡- የቢሮውን ካፒታል ፕሮጀክቶች ቀስ በቀስ ከመንግስት ድጎማ ለማላቀቅ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና ሊጫወት የሚችለውን የግሉን ዘርፍ በስፋት ለማሳተፍ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ የሚውሉ ይሆናል።
- **ስፖርትን ለማህበራዊ ልማትና ለሀገር ብልፅግና ማዋል፡-** ስፖርትን ለልማት ለማዋል የሚያስችል አደረጃጀትና ስርዓት በመፍጠር፣ስፖርትን በዘላቂነት ችግሮችን በመፍታት ስፖርት ለማህበራዊ ልማትና ለአገር ብልጽግና፣ ህዝቦችን ለማቀራረብ፣ ለክልላዊ ገጽታ ግንባታ እና ለስፖርት ቱሪዝም ዕድገት፣ እንዲሁም ከአጎራባች ክልሎች ጋር አንድነትን ለማምጣት መሳሪያ ሆኖ እንድያገለግል ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አስር አመታት የወጣቶችና ስፖርት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በመገንባት ብቁና ተወዳደደሪ ዜጋ ሆነው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥና የስፖርት ዘርፍ ልማትን በማስፋፋት ንቁ ህብረተሰብንና ውጤታማ ዜጎችን በማፍራት በሀገር አቀፍ መድረኮች ተፎካካሪ ክልልን በመፍጠር ለክልልና ለሀገር ብልጽግና ያለውን ሚና ማሳደግ ነው።

የቀጣይ አስር አመታት የወጣቶችና ስፖርት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

የወጣቶች ልማት፡-

- የወጣቶችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ ዙሪያ ለ4,889 ወጣት አደረጃቶች የፋይናንስ የቴክኒክና የግብዓት ድጋፎችን መደገፍ፣ ለ68,296 የወጣት አደረጃጀቶች አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት እና 80% የወጣት አደረጃጀቶችን ተቋማዊ ብቃት በማሻሻል የወጣት አደረጃጀቶችን አቅም የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የመገንባት እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥና አረንጓዴ ልማት ዙሪያ ለ4,656,372 ወጣቶችን ግንዛቤ የማስጨበጥና በተጨማሪም ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በመከላከልና ወጣቶች ሰልጥነውና ህጋዊ ሆነው ውጭ አገር ሄደው እንዲሰሩ በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችና በስራ ዕድል ፈጠራ ለ1,192,485 የተለያዩ የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ የሚሰራ ይሆናል ።
- የወጣቶች የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭነት ከመቀነስ አኳያ ከከተማ መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰትን ከ43% ወደ 13% እንዲሁም ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ወደ 1.5% መቀነስ፣ በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ለ1,475,927 ወጣቶች ግንዛቤ በማስጨበጥ የህገ-ወጥ የወጣቶችን ዝውውርን ከሀገር ውጪ ያለውን ወደ 1.5% እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰትን ከ43% ወደ 13% ለመቀነስ የሚሰራ ይሆናል።

- የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ በተመለከተ ለ4,183,630 ወጣቶች በመደበኛ የክረምትና የበጋ የበጎ ፈቃድ የአገልግሎት በ14 መስኮች በብሔራዊ አገልግሎት /Non- military/ አገራዊና ክልላዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች በስፋት እንዲሳተፉ የማድረግ እና 12,550,893 ወጣቶች የክልላችንን ህ/ሰብ በሚሰጧቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲጠቅሙ በማድረግ በመንግስትና በህ/ሰቡ ሊወጡ የሚችሉ 3,503,661,391.00 ብር የማዳን ተግባራት በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት የሚሰሩ ይሆናል።
- የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በከተማና በገጠር የሚገኙ 2,725,682 ወጣቶች እና በ20 ከተሞች የሚገኙ 10,917 ልዩ ትኩረት የሚሹ ተጋላጭ ወጣቶች በተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮች በሚፈጠሩ የስራ አማራጮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።
- ለወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ የወጣቶች የልማት ፈንዶችን በማቋቋም ለ1,873,906 ወጣቶች በቁጠባ ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ 5,061,406,490.00 ብር በማስቆጠብ የቁጠባ ባህልን የማጎልበት ስራዎችን የመስራት እና 3,566,537 ወጣቶች ገበያ ተኮርና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉ የክህሎት ስልጠናዎችን የማመቻቸት እንዲሁም 10,311,133,570.00 ብር የተዘዋዋሪ የብድር ገንዘብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይመቻቻል። በተጨማሪም ለ1,662,154 ወጣቶች የብድር አገልግሎት እና ለ786,046 ወጣቶች የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማመቻቸት እንዲሁም ለ899,475 ወጣቶች የማምረቻና መሸጫ ቦታ አቅርቦትንና በገጠር የመሬት አቅርቦትን በማሻሻል የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- በወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲ፣ የዕድገትና የለውጥ ፓኬጅ፣ በስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በኤች አይቪ/ኤድስና በኮቪድ-19 ወረርሽን መከላከል፣ በኢንተርፕረነርሺፕ፣ በህይወት ክህሎትና በወጣቶች ስብዕና ልማት 8,060 (ሴት 4,030) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችና 32,240 (ሴት 16,120) አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ወጣቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት እና 2 የተሃድሶና የማገገሚያ ማዕከላት የሚገነቡበት ሁኔታዎችን በማመቻቸት የወጣቶች የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭነት የመቀነስና ልዩ ትኩረት የሚሹ ወጣቶችን ግንዛቤ የሚያጎለብቱ ተግባራት ለማከናወን ታቅዷል።
- በክልል አቀፍ ደረጃ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን በማሳደግ የአንደኛ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃ፣ የመሰናዶና የቴክኒክ ሙያ ስልጠና፣ የመምህራንና የጤና ትምህርት ተቋማት የሴት ወጣቶችን ድርሻ ከ20% ወደ 50% ማሳደግ፣ ከትም/ት ሴክተር ጋር በመቀናጀት በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት 1,537,822 ወጣቶች ተሳትፎ ማሻሻል፣ የአካል ጉዳተኛ ወጣቶች የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምጣኔን 7% በማድረስና አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ትምህርት ተሳትፎን በማሻሻል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ወጣቶች ለመፍጠር ቅንጅታዊ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ይከናወናሉ።

- የወጣቶችን ስብዕናና አመለካከት ማጎልበት በተመለከተ ለ2,555,326 ወጣቶች በህይወት ክህሎት /Life Skill/ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ከአሉታዊ የአቻ ግፊቶች ራሳቸውን በመከላከልና ዕለት ዕለት በህይወታቸው የሚገጥማቸውን ፈተናዎች በአሸናፊነት እንዲወጡ ለማስቻል፣ በአዕምሮ ውቅር /Mind Set / ዙሪያ 3,974,952 ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ እና በክልሉ ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የወጣቶችን አሉታዊ መጤ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከላለከል ግብረ-ሀይል ከቀበሌ እስከ ክልል እንዲቋቋም በማድረግ የመከላከል ስራ ይከናወናል።
- የወጣቶችን አመለካከት ለመለወጥ የሚያስችል ግንዛቤ ከመፍጠር አንፃር ለ3,236,747 ወጣቶች የጠባቂነት አመለካከት በመለወጥ የዳበረ የስራ ባህል እንዲኖራቸው፣ ለ4,542,802 ወጣቶች በሠላም፤መቻቻልና አገር ግንባታ በሚኖራቸው ሚና፣ ለ2,271,789 ወጣቶች በባህላዊ ዕሴቶች፣ በመልካም አስተዳደር፣ በፌዴራሊዝም ፅንሰ-ሀሳብና በፀረ-ሙስና መከላከል፣ ለ2,555,326 ወጣቶች በወጣቶች ፖሊሲ፣ በወጣቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅ፣ በአሉታዊ የወጣቶች መጤ ጎጂ ባህሎችን መከላከል በፓኬጁ ስትራቴጂ ፣ በበጎ ፈቃድ /አገልግሎትና በማካተቻ ጋይድ ላይኑ ላይ እና ለ5,678,503 የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በወጣቶች ፖሊሲ፣ ፓኬጁና ስትራቴጂውና በወጣቶች ዙሪያ በተዘጋጁ ሌሎች ሰነዶች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል።
- እንዲሁም 350 ምክንያታዊ የውይይትና የክርክር መድረኮችን በማመቻቸት 3,974,952 ወጣቶች እንዲሳተፉ እና በየደረጃው የወጣቶች የንቅናቄና ተሳትፎ ኮንፈረንስ መድረኮችን በማዘጋጀት 4,997,083 ወጣቶች በችግሮቻቸው ዙሪያ ከከፍተኛ አመራሮች ጋር እንዲወያዩ የማድረግ ስራ ይሰራል። በተጨማሪም ህብረተሰቡ ብቁ ዜጋን ለማፍራት በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ለ3,179,961 የተለያዩ ህ/ሰብ ክፍሎች በወጣቶች ልማት እንዲሳተፉ በማድረግ እና የተለያዩ የግንዛቤና የአመለካከት ማጎልበቻ ተግባራት በማከናወን የጎለበተ የወጣቶች ስብዕናና ያደገ የወጣቶችና የህብረተሰቡ አመለካከት መፍጠር ስራ ይሰራል።

የስፖርት ልማት፡-

- የህዝባዊ እና መንግስታዊ ስፖርት አደረጃጀቶችን ከማጠናከር አንፃር መንግስታዊ የስፖርት ተቋማትን ከ261 ወደ 2,952፣ የስፖርት ፌዴሬሽኖች ከ175 ወደ 414 የማሳደግና 2,952 የስፖርት ም/ቤቶች የማጠናከር ስራ ይሰራል። እንዲሁም 12 ስታንዳርዱን አሟልተዉ የተደራጁ ክልል አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች ፤ 68 የስፖርት ክለቦችን እና 28,604 የስፖርት ቡድኖች የማሳደግ ስራ ይሰራል።
- የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎችና ማዕከላት ከማስፋፋት አንፃር የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎች ተደራሽነት ሽፋን 30 በመቶ ማድረስ፣ 5 በግል የተገነቡ ስፍራዎችን ፣ 3 አለም ዓቀፍ ስታንዳርድ ያሟሉ እንዲሁም 77 በሀገር አቀፍ ስታንዳርድ የሚያሟሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የማሳደግ ስራ ይሰራል። በከፍተኛ ትምህርት

ተቋማት ስር ያሉ የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎች 22 የማድረስ፣ በገጠር የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸው ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ወደ 2,378 ማድረስ፣ በከተማ ካርታና ፕላን ያላቸው ማዘውተሪያ ስፍራዎችን 415 ማድረስ፣ የተገነቡ 1ኛ ደረጃ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን 2 ማድረስ፣ የተገነቡ 2ኛ ደረጃ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን 38 ማድረስ፣ የተገነቡ 3ኛ ደረጃ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን 213 ማድረስ፣ የተዘጋጁ ጥርጊያ ሜዳዎች 2,951 ማሳደግ፣ አንድ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ማፒንግ በማዘጋጀት ሀገዊ እና ደረጃቸዉን በጠበቁ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች ተደራሽና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በትኩረት ይሰራል፡፡

- የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትና ተቋማትን በ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ደረጃ ቁጥራቸውን በማሳደግ፣ 3 የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ፣ 1 የህክምና ማዕከል በመገንባት፣ 4 በስታንዳርዱ መሰረት የስፖርት ትጥቆችንና ቁሳቁሶችን የሚያመርቱ ተቋማት በመፍጠር በአጠቃላይ የተቋማትን ቁጥር ወደ 97 በማሳደግ ዘመናዊና ሳይንሳዊ የስፖርት ትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡
- በየደረጃዉ የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትን በማስፋፋት በት/ቤቶች 2,099,747፣ በመስሪያ ቤቶች ሠራተኞችን 166,801፣ በፋብሪካዎች ሠራተኞችን 200,000፣ በመኖሪያ ስፍራዎች በጤና ቡድኖች 1,751,253፣ ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት በጤናና በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ተሳትፈ የህብረተሰብ ብዛት 14,059,338 ውስጥ 30 ፐርሰንት በማድረስና በማሳተፍ በስፖርት አካሉ የዳበረ ጤናማና አምራች ዜጋ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡
- በስፖርት ለሁሉም መዝናኛና ባህል ስፖርቶች የህብረተሰቡን ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር 10 ኩነቶች /መድረኮች/ በማዘጋጀት፣ 192 የስፖርት ለሁሉም ፌስቲቫል ፕሮግራሞች ማካሄድ፣ 3,370 የባህል ስፖርት ፌስቲቫሎች ማዘጋጀት፣ 2,195,558 በስፖርታዊ ፌስቲቫሎች ህብረተሰብ ማሳተፍ፣ 656,735 ህብረተሰብ በስፖርት ኩነቶች ማሳተፍ እና ለ11 ባህላዊ ስፖርቶች ደንቦችና ጨዋታዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚሳተፍ የህብረተሰብ ቁጥር የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡
- በታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ልማት ፕሮግራም በግለሰብ የማበልፀጊያ ማዕከላት የተያዙ ሰልጣኞች 480 ማድረስ፣ መንግስት ማበልፀጊያ ማዕከላት የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች 860፣ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮጀክት ጣቢያዎችን 398፣ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮጀክት አሰልጣኞችን 796፣ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮጀክት ሰልጣኞችን 9,950 በማድረስ ተተኪ ስፖርተኞችን ማፍራት፡፡
- የኤሊት (የአዋቂ እና የላቁ) ስፖርተኞችን ቁጥር በዋና ክለብ ላይ በተከታታይነት መሳተፍ የቻሉ ኤሊቶች ወደ 1,443፣ በአዋቂ ብሄራዊ ቡድን የተሳተፉ ኤሊቶች 369፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሳተፉና ዉጤታማ የሆኑ ኤሊቶች ብዛት 369፣ በክልል በስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላት የሚሰለጥኑትን ወደ 860፣ በክለብ የሚሰለጥኑ ስፖርተኞችን ወደ 1,219፣ በብሄራዊ ቡድን የሚሰልጥኑ ስፖርተኞችን ወደ 369፣ በሀገር አቀፍ አካዳሚዎች

የሚሰለጥኑ ብዛት ወደ 558 ማሳደግ እና በክልሉ በሚገነባው አካዳሚ የሚሰለጥኑትን ሰልጣኞች ወደ 232 በማሳደግ ሀገራችንን የሚወክሉ ዉጤታማ ስፖርተኞች የማፍራት ስራ በትኩረት ይሰራል።

- በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በ21 የስፖርት አይነቶች ስፖርተኞችን በማሳተፍ ዉጤት ለማስመዝገብ ተሳትፎና ዉጤት የተመዘገበባቸዉ የስፖርት አይነቶች ወደ 23፣ በባህል ስፖርት ውድድር 1,944,112፣ በሴቶች ጨዋታ 965,958፣ በአካል ጉዳተኞች ጨዋታ 40,668፣ በአርሶ አደር ጨዋታ 1,376,458፣ በአርብቶ አደር ጨዋታ 130,840፣ በጤና ቡድኖች ዉድድር 119,573፣ በት/ቤቶች ወድድር 134,452 እና በመላ ጨዋታ 1,937,889 ስፖርተኞች እንዲሳተፉ ይደረጋል።
- በደቡብ ክልል ልዩ ልዩ ሻምፒዮና 1,937,889፣ በታዳጊ ወጣቶች ምዘና ፕሮግራም 4,975 እና በተለያዩ ሻምፒዮናዎች ላይ 31,544 ስፖርተኞችን የማሳተፍ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ዉድድሮች /ሻምፒዮናዎች/ 5ቱን በክልሉ አስተናጋጅነት እንዲካሄዱ ማድረግ ደረጃዉን የጠበቀ የስፖርት ዉድድር መርሃ-ግብር የማዘጋጀት ልምድ በማሳደግ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት ስራ ይሰራል። በተጨማሪም 14 ክልል አቀፍ የውድድር መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤዉ ያደገ ሁለንተናዊ ጤንነትና ብቃት ያለዉን አትሌት የማፍራት ስራ ይሰራል።
- በስፖርት ህክምናና በጸረ - አበረታች ቅመሞች ዙሪያ ለ2,285 ህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለ1,658 ስፖርተኞች የዕድሜ ምርመራና ቁጥጥር ማድረግ፣ ለ219 ኤሊት ስፖርተኞች የጸረ-ዶፒንግ እና የስፖርት ህክምና አገልግሎት እና ለ9,477 ለዳኞችና ለአሰልጣኞች የፀረ - ዶፒንግ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የመስጠት ስራ ይከናወናል። እንዲሁም ለዳኞችና ለአሰልጣኞች የተለያዩ የስፖርት ህክምና ዓይነቶች ስልጠና በመስጠት ስፖርት ለሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ማበርከቱን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል።
- የስፖርት ኢንዱስትሪዉን በማስፋፋት አንፃር የባለሀብት ተሳትፎን ለማሳደግ 37 በስፖርት ኢንዱስትሪዉ/ኮሜርሻላይዜሽን ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ በስፖርት ኢንቨስትመንት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ባለሀብቶች ወደ 5 ማድረስ፣ በግል ባለሀብቶችና ድርጅቶች የተያዙ ክለቦች ወደ 18 ማድረስ፣ በስፖርት ስራ ፈጠራና ኢንተርፕሪነርሽፕ የገቡ ኢንተርፕራይዞች ወደ 4 ማድረስ፣ በስፖርት ኢንቨትመንት የሚሰማሩ የቴክ/ምክ/አገ/ ያገኙ ባለሀብቶች ወደ 5 ማድረስ፣ እስታንዳርዱን የጠበቀ መሠረተ ልማት ግንባታ፣ በትጥቅና መሳሪያዎች ማምረት የተሠማሩ ባለሀብቶች ወደ 2 ማሳደግ፣ በተዘጋጀ የትጥቅ /መሳሪያዎች/ ስታንዳርድ 2 ባለሀብቶች እንዲሰማሩ በማድረግ በስፖርት ኢንቨትመንት የካፒታል መጠን እስከ 18,480,260 ብር ኢንቬስት እንዲያደርጉ የማድረግ ስራ ይሰራል።
- የስፖርት ማህበራዊ ልማትና ህዝብ ለህዝብ ትስስር ለማሳደግ ስፖርትን ለማህበራዊ ልማት የሚጠቀሙ ተቋማት ወደ 10 ማሳደግ፣ ከ5 የስፖርት ማህበራዊ ልማት የተሰማሩ የሲቪክ ማህበራት ጋር በቅንጅት መስራት፣ በስፖርት ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞች ወደ 40,668 ማሳደግ፣ በስፖርት ልማት

ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ቁጥር ወደ 965,958 ማሳደግ፣ በስፖርት በጎ ፍቃድ አገልግሎት የተሰማራ ህብረተሰብን ወደ 36,956 ማድረስ፣ ለክልልና ለሀገር ገፅታ ግንባታና ለቱሪዝም ዕድገት ተልዕኮ የተሰጣቸዉ ስመጥር አትሌቶች ወደ 37 በማድረስ በስፖርት ማህበራዊ ልማትን የማሳደግ ስራ ይሰራል።

የቀጣይ አስር አመታት የወጣቶችና ስፖርት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- በሴክተሩ መሪ ልማት ዕቅድ ዙሪያ የጋራ መግባባት በመፍጠር የተቋሙ አመራር፣ ሰራተኛች፣ ከባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ ካሉ ማህበራት፣ ፌዴሬሽኖችና ከግል ባለሃብቱ ጋር መግባባት መፍጠርና መፈጸም።
- በሴክተሩ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤ የቅንጅትና ትብብር ሥርዓትን ማሳደግ፤ የተለያዩ የወጣትና ስፖርት አደረጃጀቶችን መፍጠርና ማጠናከር፣ የአሠራር ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ የተጠያቂነትና ውጤታማ የተግባቦት ሥርዓትን መዘርጋት በዘርፉ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ ይደረጋል።
- የስፖርት ፖሊሲ እና የስፖርት ሕግ እንዲሁም የስፖርት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ፣ የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያ ፕሮግራም እና የፀረ አበረታች ቅመሞች ስትራቴጂ እና ልዩ ልዩ ሰነዶች ይተገበራሉ።
- በእቅድ ዘመኑ የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠናዎችን የመስጠት ስራ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።
- የድጋፍ፣ የክትትል እና ግምገማ ስርአቶችን በመተግበር የዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ የማሰፈጸሚያ ስልት ሆኖ ተወስዷል።

ምዕራፍ ስድስት

የሕዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕቅድ

6.1. የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ነፃ፣ ገለልተኛና ብቃት ያለዉ የመንግስት አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት፣ የሰዉ ሃብት ሥራ አመራርና ዘመናዊ የሰዉ ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት በማሻሻል፣ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥና የአፈፃፀም ሥራ አመራር ሥርዓት በማጠናከር፣ ሥነ-ምግባር ዕሴት ግንባታና መልካም አስተዳደርን በማሻሻል በፐብሊክ ሰርቪሱ ዘርፍ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት በክልሉ የልማት ጉዞ ጉልህ ሚና መጫወት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ተልዕኮውን በውጤታማነት መፈጸም የቻለ፣ በሥነ-ምግባሩ የተመሰገነ ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃት ያለው የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ በመፍጠር የተገልጋዩን እርካታ ማረጋገጥ ነዉ።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የመንግስት ተቋማት የአደረጃጀት ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 60% በ2022 ወደ 100% ማሳደግ፣ በየደረጃው የሚገኝውን አመራር የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በ2012 በጀት ዓመት 35 በመቶ ከነበረበት በ2022 ዓ/ም ወደ 100 % ማሳደግ እንድሁም የአፈጻጸም ሥራ አመራር ሥርዓትን በማጠናከር የመንግስት ተቋማት የዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት 60 በመቶ ከነበረበት በመሪ ዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 85 % እንዲያሳድጉ ለመደገፍ ታቅዷል።
- የሰው ሀብት ሕጎች አተገባበር ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት 60 በመቶ ከነበረበት በ2022 ዓ/ም ወደ 100% ለማሳደግ፣ በ2012 በጀት ዓመት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት 60 በመቶ ከነበረበት በ2022 ወደ 100% ለማሳደግ፣ የሰው ሀብት ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ትግበራን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 100 % ተግባራዊ ለማድረግ፣ ተቋማዊ የተደረገ የሰው ሀብት ሥራ አመራር የአሰራር ስርዓት በ2012 በጀት ዓመት ከሚገኝበት 60% በ 2022 መጨረሻ ወደ 100 % ለማሳደግ፣ የሰው ሀብት አቅም ማሳደግ ተደራሽነት በ2012 በጀት ዓመት 30 በመቶ ከነበረበት በ2022 ወደ 100 % ለማሳደግ፣ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 47% በ2022 ወደ 100 % ለማሳደግ፣ ሂደት ተኮር አደረጃጀት ትግበራ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 90% ወደ 100 % ለማሳደግ፣ በመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የዜጎችን እርካታ በ2012 ከነበረበት 79.5 በመቶ በ 2022 በጀት ዓመት ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዷል።
- ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ ሥርዓት ተደራሽነት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት ከ 45 በመቶ ወደ 100% ለማሳደግ፣ የመንግሥት ሠራተኞችን ሥነ-ምግባርና እሴት ግንባታ በማሳደግ በ2012 በጀት ዓመት

የመንግስት ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት 35 በመቶ ከነበረበት ወደ 100 % ለማሳደግ፣ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት የመልካም አስተዳደር ችግሮች በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበሩበት 40 በመቶ በዚህ መሪ ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 5 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- በክልል ደረጃ በቢሮውና በዞንና ልዩ ወረዳዎች የመንግስት አገልግሎት ዘርፍ መካከል የጠበቀ የመደጋገፍ የመመካከር፣ መረጃዎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን በጋራ የመንደፍ ግንኙነቶች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል። ሴክተሩን በተመለከተ ወጥ አሰራር በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ዕቅድ መንደፍና አተገባበሩ የተናበበ እንዲሆን ማድረግ፣ ወቅታዊ የአፈጻጸም መረጃዎችንና ሪፖርቶችን መለዋወጥ የነዚሁ ግንኙነቶች አካል ናቸው። በሌላ በኩልም ከክልል ሴክተር አስፈጻሚ ተቋማት ጋር ያለው በህግ የተደገፈ ግንኙነትም የበለጠ የሚጠናከር ይሆናል። ከዚህ ውጪ የሴክተሩን አፈጻጸም ለማጎልበትና የሚጠበቅበትን ሚና ለመወጣት ከሲቪል ማህበራት፣ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች የባለድርሻ አካላትም ጋር በቅርበትና በመመካከር የሚሰራ ይሆናል።
- ለዕቅዱ ተግባራዊነት የተቋማትና ዜጎች ዕርካታ ጥናት፣ የመንግስት ተቋማት ማዘዳደሪያ/ሽልማት ስርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፣ የካይዘን ትግበራ፣ የነፃ ገለልተኛና ብቁ ተቋማት መዋቅር እና አሰራር ጥናትና ትግበራ ፕሮጀክት፣ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ ስርዓት /ICSMIS/ ፕሮጀክት፣ የሰው ሀብት ብቃት ማረጋገጫ ፕሮጀከት፣ የአፈጻጸም ሥራ አመራር ማዕቀፍ ዝርጋታና በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የመደገፍ ፕሮጀክት፣ የአመራር እና ባለሙያዎች ልማት ፕሮግራም፣ ሴቶችን በልዩ የማብቃት ፕሮግራሞች፣ እንደ መሪ ዕቅዱ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች/ስልቶች ተግበራዊ ይደረጋሉ።

6.2. የፍትህና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥራዎች

6.2.1 የፍትህ ሥራዎች

የቀጣይ አሥር ዓመታት ፍትህ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ፣ የመንግስትና ህዝብን ጥቅም ማስከበር፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማሳደግ፣ የህግ የበላይነትን ማስከበር፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ማረጋገጥ፣ የህግ ታራሚዎች የታረሙና የታነጹ በማድረግ በተቋማቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊ እና ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሠጥባቸው ይሆናሉ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት ፍትህ ዓላማዎች እንደሚከተለው ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የተቋማቱ የመፈፀም አቅም በማሳደግ የመንግስትና የህዝብን ጥቅሞችን በማስከበር የበኩሉን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል እንዲሁም የህግ የበላይነትን በማክበርና ማስከበር የሕብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ ሀገራዊና ክልላዊ የፍትህ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት ያደረጉ ተግባራትን ማከናወን፡፡
- የዜጎች ሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር፣ የህግ ታራሚዎች በአግባቡ የታረሙና የታነጹ በማድረግ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- በህግ የበላይነት፣ በግልጸኝነትና ተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሰረት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽና ጥራታቸውን የጠበቁ ለማድረግ በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ በቀጣይ ዘርፉ ተልዕኮዉን በአግባቡ መወጣት እንዲችል ለማድረግ ያለመ ነው፡፡

የቀጣይ አስር ዓመታት ፍትህ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የወንጀል ጉዳዮች አስተዳደር ጥራትና ውጤታማነት ለማሳደግ ከፖሊስ ጋር በጋራ ሊጣሩ በሚገቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ ምጣኔ 95.8% ወደ 99%፣ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን ከ97% ወደ 99.75%፣ የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን ከ4.23% ወደ 1% መቀነስ፣ የማስቀጣት ምጣኔን በመዝገብ ከ92.5% ወደ 99% በተከሳሽ ደግሞ 95%፣ ዐ/ህግ ይግባኝ የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር ምጣኔ ከ83.2% ወደ 99% እንዲሁም ሰበር ደግሞ ከ76.6% ወደ 99% እና ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና የማድረግ ምጣኔ ከ94% ወደ 99% እንዲሁም ሰበር ደግሞ ከ90.7% ወደ 99% ለማድረስ በትኩረት ይሰራል፡፡
- በሴቶችና ህጻናት አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የተፈጸሙ የወንጀል መዝገቦች የማጥራት ምጣኔን ከ96.6% ወደ 100%፣ የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን ከ3.15% ወደ 0.5% መቀነስ፣ የማስቀጣት ምጣኔን በመዝገብ ከ94.6% ወደ 99% በተከሳሽ ደግሞ 97%፣ ዐ/ህግ ይግባኝ የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር ምጣኔ ከ96% ወደ 99% እንዲሁም ሰበር ደግሞ ከ96% ወደ 99% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና የማድረግ ምጣኔ ከ97% ወደ 99%፣ ሰበር ደግሞ ከ97% ወደ 99% ለማድረስ በትኩረት ይሰራል፡፡ በዕርቅ ማለቅ የሚገባቸው ቀላል የወንጀል መዝገቦች አሁን ካለበት 43.1% ወደ 95% ለማድረስ እና በጠቋሚዎችና በምስክሮች የሚቀርቡ የከለላ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት አቅም 100% ለማሳካት ይሰራል፡፡

- የዐቃቤ ህግ መዝገቦች የወንጀልና የፍትሐብሔር መዝገቦች ውጤታማነታቸው ለማረጋገጥ በዕቅድ ዘመኑ በናሙናነት በተመረጡ 27,500 ላይ የህግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ስራ ይሰራል፡፡
- የመንግስትና የህዝብ የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ውጤታማነት ለማሳደግ የመንግስት የግዥ ውል ምርመራ ሽፋን ምጣኔን ወደ 100%፣ መንግስት ከሳሽና ተከሳሽ በሆነበት ፍትሐብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔን 96%፣ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተወሰኑ የፍትሀብሄር ጉዳዮች በአፈጻጸም ክስ ለመንግስት የማስመለስ ምጣኔ ከ91.22% ወደ 96%፣ የፍትሐብሔር ጉዳይ ከክስ በፊት በድርድር የማስመለስ አቅም ወደ 20%፣ በሙስና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ ከ66.2% ወደ 99%፣ በታክስ ማጭበርበር የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ 100% ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል፡፡ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ እና ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር/የማሻሻል/ ምጣኔ 99% እንዲሁም ተከሳሾች ይግባኝና ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ ምጣኔ 95% ለማሳደግ ትኩረት ይደረጋል፡፡
- የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር ፈጻሚ ሴክተር መ/ቤቶች ሰብዓዊ መብትን በዕቅዳቸው ሜንስትም እንዲያደርጉ በመከታተልና ድጋፍ በማድረግ በየሩብ ዓመቱ የእቅድ አፈጻጸማቸው ድጋፍና ክትትል የማድረግ፣ በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ለፈጻሚ ተቋማት አመራሮችና ፈጻሚዎች በየበጀት ዓመቱ 1 ጊዜ እና በሰብዓዊ መብት ህግጋት ዙሪያ የተለያዩ የሲቪክ ማህበራትን እና ተቋማትን በማስተባበር 20 የግንዛቤ መፍጠር መድረክ የማዘጋጀት ስራ ይሰራል::
- የተጠርጣሪዎች እና የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት ለማስከበር በፖሊስ ማቆያ/ማረፊያ/ ቤት በሳምንት 2 ጊዜ እና በማረሚያ ቤቶች ደግሞ በወር 1 ጊዜ ጉብኝት የማድረግ ስራ በመስራት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈፀሙ አካላት ላይ 100% በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፡፡
- የህግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ ምልመላና መረጣ አፈፃፀም ጥራት 99% እንዲሁም በይቅርታ እንዲፈቱ የሚሰጠው የውሳኔ አስተያየት ጥራት 98% ለማድረስ ይሰራል፤ በተጨማሪም ከህፃን ጋር ያሉ እናቶች፣ አረጋውያንና የማይድን በሽታ ታማሚ የሆኑ የህግ ታራሚዎች 100% በልዩ ሁኔታ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የአመክሮ ጊዜያቸው የደረሰ የህግ ታራሚዎች ጥያቄ በማጣራት ፍ/ቤት በማቅረብ እንዲፈቱ የሚደረግ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ በይቅርታና አመክሮ አሰጣጥ ፋይዳ ዙሪያ 5 የዳሰሳ ጥናት ይደረጋል፡፡
- የህግ ማርቀቅና ምክር አገልግሎት ውጤታማነትን ለማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ እንዲረቀቁና አስተያየት እንዲሰጥባቸው የሚቀርቡ ሕጎች 100% የህግ ማርቀቅና ቅርጽ የማስያዝ እና ወደ እንግሊዘኛ የመተርጎም ስራ የሚሰራ ሲሆን በስራ ላይ በሚገኙ 10 ህጎች ላይ የፋይዳ ጥናትም ይደረጋል፡፡ ለክልሉ መንገስት፣ ለሴክተር መ/ቤችና የልማት ድርጅቶች በህግ ጉዳይ የማማከር ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡

- የጠበቆችና የህግ ጉዳይ ፀኃፊዎች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥነታቸውን ለማጠናከር ለጠበቆችና ለህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ፈቃድ የመስጠትና የማደስ አገልግሎት ቀልጣፋ በማድረግ በየበጀት ዓመቱ የስልጠና እና የመወያያ መድረክ የማዘጋጀት እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆኑ ይደረጋል። ለጠበቃ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት 100% እንዲያገኙ ይደረጋል።በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በማጣትና ክስ በመመስረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ምጣኔ ከ89.2% ወደ 98% ለማሳደግ ይሰራል።
- ዜጎች በሲቪል ማህበራት የመደራጀት መብታቸውን ለማረጋገጥ የፌደራሉን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅን መነሻ በማድረግ ክልላዊ የሲቪል ማህበራት አዋጅ የማጸደቅ ስራ ሲሆን የሲቪል ማህበራት ፈቃዳቸው የማደስና በተቋቋሙበት ዓላማ መሰረት ስለመንቀሳቀሳቸው ቁጥጥር ይደረጋል። እንዲሆም በማህበራቱ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማጣራት 100% ምላሽ ይሰጣል።
- ታራሚዎች ተሀድሶ ልማት ግንባታ ለመስጠት በቀለም ትምህርት 63,113፣ በቴክኒክና ሙያ የዕደ ጥበብ ስልጠና 69,004፣ በምክክር አገልግሎት 60,912 እና በሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት 12,159 የህግ ታራሚዎች የተሀድሶ ልማት ይሰራል። በዕቅድ ዘመኑ 1 ዘመናዊ የግብርና ማዕከላት እና 1 የወጣት ጥፋተኞች የተሀድሶ ማዕከል የማቋቋም ስራ ይሰራል።
- የታራሚዎች መሰረታዊ ፍላጐት ማሟላት የምግብ አቅርቦት በሚኒማ መሠረት፣ የመጠጥና የንጽህና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት፣ የጤና አገልግሎት ሽፋን እና የመዝናኛ ክበባት ማሟላት 100% ለማሳካት ይሰራል፤ በዕቅድ ዘመኑ 1 የሥነ-አእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል የማቋቋም እና 7 አዳዲስ የታራሚዎች መጠለያ የመገንባት ስራ ይሰራል።
- የታራሚዎች ደህንነት ለማረጋገጥ የማረሚያ ተቋማት የጥበቃና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት 100% የማጠናከር፣ ለታራሚዎች የተቋሙ ዓላማ፣ ደንብና መመሪያ 100% እንዲያውቁ የማስተማር፣ ወደ ማረሚያ እንዳይገቡ የተከለከሉ ቁሳቁሶች ላይ የቁጥጥር ስርዓቱ 100% የማጠናከር ስራ ይሰራል። በዕቅድ ዘመኑ 1,000 የማረሚያ ፖሊስ አባሎች የተሃድሶ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን 2,540 አዲስ የማረሚያ ምልምል ፖሊሶች የማሰልጠን ስራም ይሰራል።
- የፍትህ አካላት የህግ ባለሙያዎች አቅም ለማሳደግ የህግ ባለሙያዎች በቅድመ ሥራ ስልጠና 1,094፣ በሥራ ላይ ስልጠና 1,294 እና በአጫጭር ስልጠና 9,858 የህግ ባለሙያዎች እንዲሰለጠኑ ይደረጋል። በየበጀት ዓመቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች የፍትህ ተቋማቱና ባለሙያዎች ክፍተት ለመለየት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚደረግ ሲሆን የተሰጡ ስልጠናዎች ያስገኙት ፋይዳ 2 ዙር በጥናት የማረጋገጥ ስራ ይሰራል።
- በህጎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤታማነታቸው ለማረጋገጥ በተመረጡ 70 ህጎች ላይ ጥናትና ምርምር ለማድረግ በየበጀት ዓመቱ የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚደረግ ሲሆን በጥናትና ምርምር

ውጤቶች ያስገኙት ፋይዳ 2 ዙር የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል። በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች መካከል በሕግ ጥናትና ምርምር ዙሪያ በየበጀት ዓመቱ አንዱን በማሳተፍ በቅንጅት ይሰራል።

- የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ዙሪያ ለፍትህ አካላት 100% የማማከር ስራ የሚሰራ ሲሆን በፍትህ ዘርፉ የሚከናወኑ የማሻሻያ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ በሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። በየበጀት ዓመቱ ክልል አቀፍ የፍትህ ሳምንት እንዲከበር እና የፍትህ ተቋማት ጥምረት መድረክ በማዘጋጀት የፍትህ ተቋማት አፈጻጸም እንዲሻሻል በትኩረት ይሰራል። እንዲሁም የፍትህ መረጃዎችን ለጥናትና ምርምር እንዲረዳ የማሰባሰብ፣ የመተንተንና የማደራጀትም ስራ ይሰራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት ፍትህ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የማስፈፀም አቅምን በመግንባት ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የለውጥ መሳሪያዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን መተግበር፣ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር መርሆችን በመከተል በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ሲቪል ማህበራት፣ ባለድርሻ አካላት እና የህዝብ ክንፍ በማሳተፍ የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ይደረጋል።
- በሙስና፣ በታክስ እና በከባድ ወንጀሎች ምርመራ ከፖሊስ ጋር አብሮ በመስራት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከሴክተር መ/ቤቶች በቅንጅትና በትኩረት ይሰራል።
- የህብረተሰቡን የንቃተ ሕግ ደረጃ በማሻሻል ሕግና ሥርዓት የሚያከብርና የህግ ማስከበር ስራውን በንቃት የሚደግፍ አደረጃጀት በመፍጠር ሕጎች ለህብረተሰቡ በልዩ ልዩ መንገድ እንዲታወቁና እንዲሠራጩ ይደረጋል።
- ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ የሚሆኑበትን ስርዓት በመዘርጋት፤ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅሞች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣ እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን እንዲሻሻል የማድረግና ምርጥ ተሞክሮዎችንና የላቁ ውጤቶችን ቀምሮ ማስፋት አንደ ማስፈጸሚያ ስልት ተወስደዋል።

6.2.2 ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የቀጣይ አስር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የፍርድ ቤቶችና ዳኞች ነጻነትና ተጠያቂነትን ማጎልበት፣ የዳኝነት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ አላስፈላጊ የሆኑ የቅብብሎሽና የምልልስ አሠራሮችን መቀነስ፣ እሴት የማይጨምሩ ሥራዎችን ማስወገድ፣ ጥራት ባለው በአነስተኛ ወጪና በቅርበት እንዲሰጥ ማድረግ በተጨማሪም የስትራቴጂክ አመራርና ማስፈፀም አቅም ማሳደግ፣ ተቋሙን በሰው ኃይል በማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት፣ ውስጣዊ አሠራርና

አደረጃጀቶችን ማሻሻል፣ የመልካም አስተዳደርን ማስፈንና የሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን ችግሮች መቅረፍ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዓላማ እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ሕገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በማክበርና በማስከበር፣ ሕጋዊና ፍትሀዊ ውሳኔ በመስጠት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽነትን በማረጋገጥ የተገልጋዮች እርካታ ማሳደግ፤ እንዲሁም የሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከልና በመዋጋት መልካም አስተዳደር ሰፍኖ ማየት ነዉ።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የፍርድ ቤቶችን የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን በማሳደግ በተመለከተ በ2012 በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱት የክርክር ፋይሎች/መዛግብት ብዛት 231,701 ከነበረበት በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ በ2022 ወደ 449,276 ለማድረስ፣ ለቀረቡ ጉዳዮች የመወሰን አቅም በ2012 በጀት ዓመት 88% ከነበረበት በ0.5 በመቶ በአማካይ በየዓመቱ በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ወደ 93.1 በመቶ ለማድረስ፣ የማጣራት ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 100.4 በመቶ በ0.1 በመቶ በመቀነስ ወደ 100% ለማድረስ ፣ የፋይሎች የመጨናነቅ ሁኔታ 1.06 ከነበረበት በአማካይ በየአመቱ በ0.1% በመቀነስ ወደ ከ1.01 በታች ለማድረስ፣ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት ፍትህ በሁለት ወር የመስጠት አቅም በ2012 ከነበረበት 84.8 በመቶ በ2022 ወደ 94.8 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።
- በክልሉ ፍርድ ቤቶች የሴቶችና ህፃናት ጥቃትን በተመለከተ ከቀረቡ ጉዳዮች በ2012 ዓ.ም ዉሳኔ ያገኙ 92.3% ሲሆን በየአመቱ በአማካይ በ0.5% በማሳደግ በዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 96.3% ለማድረስ፣ ህገ-ወጥ የሰዎች ንግድ/ዝዉዉር ጉዳዮች በ2012 ዓ.ም ከቀረቡ መዘግብቶች ዉስጥ 87 በመቶ ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 100% ለማድረስ ግብ ተጥሏል።
- የህዝብና የመንግስት ጉዳዮች በ2012 ዓ.ም ከቀረቡት መዛግብት ዉስጥ 73% ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በ2022 ወደ 87% ለማድረስ፣ የገቢ ግብር ወይም ታክስ ማጭበርበር ጉዳዮች በ2012 ዓ.ም ከቀረቡ መዘግብቶች ዉስጥ 66% ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በ2022 መጨረሻ ወደ 97.8% ለማድረስ፣ የኮንትሮባንድ ጉዳዮች በተመለከተ በ2012 ዓ.ም ከቀረቡ መዛብብቶች 75% ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በ2022 መጨረሻ ወደ 97% ለማድረስ፣ በ2012 ዓ.ም የግብዓት ዕዳ አመላለስ ከቀረቡ መዘግብቶች 84 በመቶ ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 92.8% ለማድረስ፣ በ2012 ዓ.ም የብድር አመላለስ ከቀረቡ ጉዳዮች 67.4% ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 94.5% ለማድረስ፣ የሸማቾች መብት ጥበቃ ጉዳዮች በ2012 ዓ.ም ከቀረቡ ጉዳዮች 90% ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በ2022 መጨረሻ ወደ 97.4% ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

- የክልሉን ፍርድ ቤቶች ውጤታማነት ማረጋገጥ በተመለከተ በይግባኝ የሚሻሩ መዝገቦችን በመቀነስ የውሳኔ መፅናት አቅም በ2012 ከነበረበት 73.3 በመቶ በ2022 ወደ 87.46 በመቶ ለማድረስ፣ የተገልጋይ እርካታ በ2012 ከነበረበት 76.4 በመቶ በ2022 ወደ 86.4 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።
- የፍርድ ቤቶች ተደራሽነትን ከማጐልበት ረገድ በተዘዋዋሪ/ምድብ ችሎት ውሳኔ የሚያገኙ ጉዳዮች አፈፃፀም 36,852 ከነበረበት በየዓመቱ በ5 በመቶ በማሳደግ ወደ 47,203 ለማሳደግ፣ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ በተቀመጠው መሰረት በአዋጅ ተቋቁመው ለማህበረሰቡ በሸሪዓ ህግ መሰረት የቤተሰብ ጉዳዮችን በተለይም የጋብቻ፣ ፍቺና የንብረት ክፍፍል ጉዳዮችን ከቀረቡ መዛግብት ውስጥ 3,568 (97.8 በመቶ) ዉሳኔ ያገኙ ሲሆን በአማካይ በ0.1 በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 5,806 መዛግብት ዉሳኔ ለመስጠት ታቅዷል። አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት እርቅና ድርድር ጉዳዮች 19,166 ከነበረበት በ2022 መጨረሻ ወደ 22,832 ለማሳደግ፣ ወደ ተቋሙ ለሚመጡ ተገልጋዮች ነፃ የህግ ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት ከ63,333 ወደ 73,187 ተገልጋዮች ከፍ ለማድረግ፣ ለተገልጋዮች ንቃተ-ህግ ትምህርት መስጠት በተመለከተ ከ352,538 ወደ 494,270 እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአገልግሎት አሰጣጥን 100% ለማሳደግ ታቅዷል።
- የዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የዳኝነት ነጻነት 100% ለማረጋገጥ ፣ ከዳኝነት ተጠያቂነት ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በ2012 ከነበረበት 61.08 በመቶ በ2022 ወደ 91.08 በመቶ ምላሽ ለመስጠት እና ስለ ፍርድ ቤቶች ገለልተኝነትና ነጻነት የባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማጎልበት፣ የፍርድ ቤቶችን የበጀት ነጻነት የማረጋገጥ ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በመገኘት የፍርድ መዛግብትን አዲት ማድረግ ስራ በዕቅድ ዘመኑ ለመስራት እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህፃናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞችን ጉዳዮችን ዉሳኔ መስጠት በ2012 ከነበረበት 90 በመቶ ወደ 100% ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የለውጥ መሳሪያዎችን አጠናክሮ በመተግበር ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት፣ እየተሸሻሉ ያሉ የፍርድ ቤቶች የማቋቋሚያ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦችን በመጠቀም የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፣ ሙያዊ ክህሎት ያለዉን የሰዉ ሀይል ማሟላት፣ የፍርድቤቱን ስራ ሊያሳልጡ የሚችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ ውጤታማና ቀልጣፋ፣ እንዲሁም ተደራሽነት ያለውና ተገማች የዳኝነት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአደረጃጀት ስርዓት መዘርጋት፣ በፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች በተፋጠነና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የተለያዩ ስልቶችን መቀየስ፣ በሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ የህብረተሰቡን እውቀትና ግንዛቤ በማዳበር የህግ የበላይነትን በማጠናከር ለመልካም አስተዳደርና ለልማት እገዛ ማድረግ፣ የባለብዙ ዘርፍ

ጉዳዮችን አካቶ መተግበር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ማስፋፋት፣ ቅንጅታዊ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የተለያዩ የኮሙኒኬሽን ስራዎችን በመጠቀም የህዝብ ተሳትፎን ማጠናከር ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸዉ።

6.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ

6.3.1 የክልል ምክር ቤት

የቀጣይ አሥር ዓመታት ክልል ምክር ቤት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በክልሉ ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ሂደት ጥራትና ብቃት ማሳደግ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት እና የህዝብ ግንኝነትና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ማጠናከር እንደ ትኩረት አቅጣጫ ተወስደዋል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት ክልል ምክር ቤት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የምክር ቤቱ የቀጣይ አስር ዓመታት ዕቅድ ዋና ዓላማ ባለፉት አስር ዓመታት እንደ ምክር ቤት ታቅደው የተፈፀሙ የህግ ማውጣት፣ የክትትልና ቁጥጥር ስዎች እና የውክልና ተግባራት በማጠናከር፣ የአባላቱን በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሊኖራቸው የሚገባውን ዋነኛ ተልኮ ሊያሳኩ እንዲችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቱን በማጎልበት እንደ ክልልም ሆነ እንደ ሀገር የተያዙ የልማት ዕቅድ በማሳካት የህዝቡን የዴሞክራሲ፣ የልማትና መልካም አስተዳደር ተጠቃሚነት እና የስልጣን ባለቤትነት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት ክልል ምክር ቤት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን ማሳደግ፣ በህገ መንግስቱ መሠረት የም/ቤቱ መደበኛና እንደ የአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ጉባኤዎች ወቅቱን ጠብቀው ማካሄድ፣ የመንግሰት አስፈጻሚ አካላት በግልጸኝነትና በተጠያቂነት መርህ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣ ሕግ አውጪው እና ሕግ አስፈጻሚው በክልሉ በሕገ መንግስትና ሕጎች መሠረት በግልጽ የስልጣን ክፍፍል መሥራት የሚያስችላቸው ቁመና ለመፍጠር ይሰራል።
- የህዝብ ተሳትፎን በማጠናከር፣ የስልጣን ባለቤትነት የማረጋገጥ እና የአሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሠፈነበት የመንግስት አሠራርና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፣ የተደነገጉ የሰብዓዊ መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍና እና ግልጽነት ያለው የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ ይሰራል። እንድሁም ለዜጎች ሁሉን አቀፍ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል።
- ለሙስና ወንጀል የሚያጋልጡ አሠራሮችንና የሕግ ክፍተቶችን በመለየት የመንግስትም ይሁን የግል ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ታቅዷል።

- የምክር ቤቶች የጋራ ምክክር መድረኮችን አጠናክሮ በማስቀጠል በክልልና በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ምክክር ለማካሄድ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡
- በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች የሚያከናወኗቸው ተግባራት በሚዲያ እንዲታጀቡና የምክር ቤት መረጃዎች በአግባቡ ለማደራጀት፣ የሴት ተመራጮች ኮከስ አደረጃጀትን በማጠናከርና የአባላቱን አቅም በማሳደግ በፖለቲካ፣ በልማትና በመልካም አስተዳደር ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡

የቀጣይ አስር ዓመታት ክልል ምክር ቤት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የምክር ቤቶችን አሰራር ሥርዓቶችን የማሻሻል፣ በየአስተዳደር እርከኑ የየምክር ቤት አደረጃጀቶችን የማጠናከር፣ የምክር ቤት አባላትን ብቃት ለማሳደግ ሰፊና ተከታታነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፤
- ምክር ቤቱ የሚያስተላለፋቸው ውሳኔዎችና የመንግሥት የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች እንዲለዩ በማድረግና በማዘጋጀት ለምክር ቤት አባላት፣ ለአስፈፃሚና ለህግ ተርጎሚ አካላት እና በየደረጃው ለሚገኙ ምክር ቤቶች በወቅቱ እንዲደርሱ ማድረግ እንዲሁም የወጡ ህጎችና የማስፈፀሚያ ደንቦች በወቅቱ ተዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲውሉ ጠንካራ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው።

6.3.2. ብሔረሰቦች ምክር ቤት

የቀጣይ አሥር ዓመታት ብሔረሰቦች ምክር ቤት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የህገ-መንግሥትና በፌዴራላዊ ሥርዓት ላይ ግንዛቤን ማሳደግና ህገ-መንግሥታዊ የመብት ጥያቄዎችን በመመለስ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት፣ የብሔረሰቦች የጋራ እሴቶችን በጥናት መለየትና ማጎልበት፣ የአለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት በመዘርጋት የሕዝቦችን አንድነትና ተስስር ማጠናከር ናቸው፡፡

የቀጣይ አሥር ዓመታት ብሔረሰቦች ምክር ቤት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በክልሉ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጎለብት በማድረግ በብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል በእኩልነት፣ በመተሳሰብና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነትና ትስስር በማጠናከር አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት ነዉ፡፡

የቀጣይ አስር ዓመታት ብሔረሰቦች ምክር ቤት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የክልሉን ብ/ብ/ሕ/ ፍትሀዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥናቶችን በማካሄድ የጥናት ውጤቶችን መነሻ በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። የህገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ ወደ ምክር ቤቱ የቀረቡና ምላሽ ያልተሰጠባቸውን ጥያቄዎች እና የህገ-መንግሥት ትርጉም ጥያቄዎች ታይተው ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- በህገ መንግስት እና ፌደራሊዝም ላይ ግንዛቤ የማሳደግ ስራዎች አጠናክሮ ለመስራት እና የክልሉን ህዝብ ወንድማማችነትና አንድነት የማጠናክሩ ስራዎችን በትኩረት ለመስራት የታቀደ ሲሆን በተጨማሪ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውንና ታሪካቸውን በማጥናት ባህላቸዉንና ቋንቋቸዉን ለመንከባከብ፣ ለማሳደግና ለመጠቀም እንዲችሉ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት ብሔረሰቦች ምክር ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- ምክር ቤቱ በህገ-መንግሥቱ የተሰጠውን ሀላፊነትንና ተግባሩን የሚወጣው የህገ-መንግሥቱን መርሆዎች መሰረት ባደረገ መልኩ ሲሆን ማንኛውም የቡድንና የግል ህገ-መንግሥታዊ የመብት ጥያቄዎችን በህገ-መንግሥቱ መሰረት በቅልጥፍና ምላሽ የሚሰጥ ሲሆን የም/ቤቱን እሴቶች በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል።
- በምክር ቤቱ የአመራር ግልፅነት በማስፈን ሠራተኛው የሥነ-ምግባርና የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣና የጋራ ኃላፊነት እንዲሰማው በማስተማርና በማበረታታት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብቃት ያለው የአመራር ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል።
- ለውስጥና ለውጭ ግንኙነት የሚረዳ ስትራቴጂና ሥርዓት በመቅረፅ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች እና በአካል ከሠራተኞችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት በጋራ በመስራት የተሻለ የመረጃ ልውውጥና ልምድ መፍጠር ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው።

6.3.3. ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ሥራዎች

የቀጣይ አሥር ዓመታት የስነምግባርና ጸረ-ሙስና የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የስነ-ምግበር ትምህርት፣ ስልጠና እና ስርፀት፣ የሥነ-ምግባር አውታሮች ማስተባበር፣ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን መከላከል፣ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ የሙስና መረጃ አስተዳደር አገልግሎት እንደ ትኩረት አቅጣጫ ተወስዷል።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የኮሚሽኑን ስትራቴጂያዊ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችንና ስትራቴጅያዊ ጉዳዮችን አንጥሮ በማውጣት ኮሚሽኑ በቀጣይ አስር ዓመታት የሚመራበትን መሪ ዕቅድ በማዘጋጀትና ከፈፃሚዎች ጋር በማስተሳሰር ኮሚሽኑ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በላቀ ደረጃ እንዲወጣ ማስቻል ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የስነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከከል ትምህርትና ስልጠና ከመስጠት አንፃር በአስር አመቱ የአገሪቱን ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት ያደረጉ 39 የስልጠና ሞጁሎችን የማዘጋጀት፣ ለ5,104 ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት፣ ለ29,709 ከክልሉ መምህራን ኮሌጆች ለሚመረቁ እጩ መምህራን ስልጠና ለመስጠት

ታቅዷል። ሁሉንም የክልሉን ኤፍ.ኤም ሬዲዬ ጣቢያዎችን በመጠቀም የሥነ ምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለማሰራጨት 100% ታቅዷል። 696 ፕሮግራም በቴሌቪዥን እንዲተላለፍ ይደረጋል። የሥነ-ምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ በጋዜጣ በየሳምንቱ ሁለት አምድ አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዷል። የስልጠና እና ሚዲያ ትምህርት ተደረሽነት በየዓመቱ ሁለት ዙር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ይሰጣል። 5 የሥልጠና እና ትምህርት ስኬታማነት ጥናት ለማድረግ ታቅዷል።

- የስነ-ምግባር አውታሮች አደረጃጀት በተመለከተ በሁሉም ተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የማጠናከር፣ ጠንካራ እና ታላፊነቱን በብቃት ሊወጣ የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር፣ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል የሥነ ምግባር አስተምህሮዎችን በማስተማር፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ የቅድመ ሙስና መከላከል ሥራዎችን በመሥራት፣ በህጉ መሠረት የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ሥራዎችን በብቃት በመፈፀም እና ከሌሎች የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ይሰራል።
- የስነ-ምግባር ክበባትን በሁሉም 1^{ኛ} እና በ2^{ተኛ} ደረጃ ት/ቤቶችና ኮሌጆች የማጠናከር ሥራ ይሰራል። ለሁሉም የሥነ-ምግባር አውታሮች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ የሚሰራ ሲሆን የስነ-ምግባር አውታሮች የጋራ መድረኮች የመፍጠር እና በስነ-ምግባር አውታሮች አማካኝነት በአስቸኳይ ቅድመ-መከላከል ሥራ በሙሰኞች ሊመዘበር የነበረና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት እንዲመለስ ይደረጋል።
- በክልሉ ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ የሆኑ የአሰራር ስርዓቶችን በመለየት ክልል አቀፍ የሆኑ 60 ጥናቶችን ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በተጠናቀቁ የአሰራር ስርዓት ጥናቶች ዙሪያ የትግበራ ድጋፍና ክትትል ማከናወን፣ በተግባር ላይ የዋሉ ጥናቶች ያስገኙትን ፋይዳ መገምገም፤ ለስነምግባር ኦፊሰሮች የአሰራር ስርአት ጥናቶችን ሲያካሂዱ ሙያዊ ድጋፍና እገዛ ማድረግ፤ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጉዳዮች እና የህግ የምክር አገልግሎት ጉዳዮች ዙሪያ 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዷል። በተጨማሪም ከተቋማት የቀረቡ የህግ ማእቀፎች ላይ አስተያየት መስጠት እና የፀረ-ሙስና ህጎች አፈፃፀም ላይ 100% ክትትል የሚደረግ ይሆናል።
- የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ በተመለከተ በቁጥር 101,000 አዲስ የተለዩ ታላፊዎችና ሠራተኞች ሀብት ምዝገባ፤ የ236,598 አስመዝጋቢዎች የምዝገባ እድሳት ስራዎችን ማከናወን፤ የ2,760 የሀብት አስመዝጋቢዎችንና የቤተሰቦቻቸዉን ሀብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና ባጠቃላይ የ337,598 የሀብት አስመዝጋቢዎችን መረጃ በሀርድና ሶፍት ኮፒ ለማደራጀት ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የስነምግባርና ጸረ ሙስና ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የኮሚሽኑን የማስፈፀም አቅም መገንባት /የተደራጀ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር/ የመንግስት፣ የሕዝቡን፣ የሲቪል ማህበረሰብ እና የግሉን ዘርፎች ተቋማት የመፈፀም አቅም መገንባት፤ የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ሊያደርጉ የሚያስችሉ መንገዶችን በመለየትና አደራጅቶ በማሰማራት ሕዝቡን

ተሳታፊና ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፣ የተቋማትንና የሕዝቡን ስለ መልካምሥነ-ምግባር ጠቀሜታና ስለሙስና ጎጂነት ግንዛቤና ዕውቀት መጨመር፣ በመልካምሥነ-ምግባር መታነፅና ሙስናን መፀየፍና መከላከል የተቋማትና የሕብረተሰቡ እምነት/ባህል/ እንዲሆን በማድረግ ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን የሚያወግዝና የሚያጋልጥ ሕብረተሰብ መገንባት።

- የሥነ-ምግባር መርሆዎች እንዲተገበሩ ማድረግ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አገልግሎት መስጠት፣ የመንግሥትን ሥራ ሰዓትና ንብረት በጥንቃቄ መጠቀም፣ በቡድን መንፈስ መሥራት፣
- የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች መረጃ እና ማስረጃ በማደራጀት የህዝብና የመንግስት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መሥራት እንደ ማስፈፀሚያ ስልት ተወስዷል።

6.3.4 የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን

የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የመንግስት ኮሚዩኒኬሽንና ሚዲያ ግንኙነት ማጠናከርና መዘርጋት፣ የሚዲያ ሞኒተሪንግና ጥናት ምርምር ማድረግ እና የዘመነ የመረጃ አስተዳደር የማልማትና በመረጃ የረካ ተገልጋይ መፍጠር የትኩረት አቅጣጫ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዓላማ እንደሚከተለው ተለይቷል፥

- በክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰቡን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያነሳሳ፣ የሚያጎለብትና ተጠቃሚ የሚያደርግ የኮሚዩኒኬሽን ስርአት በማጎልበት ተአማኒና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ በማድረስ የሚዲያ ሞኒተሪንግና የህዝብ አመለካከት ጥናት ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም የመንግስት መረጃ ማዕከልና ዲጂታል ሚዲያዎችን በማልማት በመረጃ የበለጸገ ህብረተሰብ መፍጠር እና የክልሉን ገጽታ መገንባት ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የልዩ ልዩ ህትመቶችን ማዘጋጀትና ማሰራጨትን በተመለከተ፡- ዓመታዊ መጽሀፍ ህትመት አሁን ካለበት 1,500 ኮፒ ወደ 10,000 ኮፒ፣ የመጽሄት ህትመትና ስርጭት አሁን ካለበት 76 ዕትም ወደ 815 ዕትም፣ ዜና መጽሄት በዕትም 530 ካለበት ወደ 6,129፣ ብሮሸርና በራሪ ወረቀት በዕትም 1,600 ወደ 18,109 እና ስቲከር፣ፖስተርና ፖስት ካርድ ህትመትና ስርጭት በዕትም ከ 300 ወደ 1,540 ለማሳደግ ታቅዷል።
- መረጃዎችን በብሮድካስት አዘጋጅቶ የማሰራጨትና ተደራሽ የማድረግ አገልግሎት፡- የሬዲዮና የቴሌቪዥን ዜና ከ6,400 ወደ 98,761፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ከ4,015 ወደ 28,578፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ዶክመንታሪ ከ289 ወደ 889 እና የቪዲዮ ቀረጻና ፎቶ ማንሳት በዙር ከ1,260 ወደ 2,607 ለማሳደግ ታቅዷል።

- የመንግስት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን ዕቅዶችንና አፈጻጸሞችን የማስተዋወቅ አገልግሎት የፎቶ ኤግዚቢሽ በዙር ከ869 ወደ 14,989፤ የመስክ ልማት ጉብኝቶች በዙር ከ 1,010 ወደ 10,867፤ ዲዛይንና ሌይ አውት በዕትም ከ 1453 ወደ 17,000 ለማሳደግ ታቅዷል።
- መንግስትና ህዝብን ከማገናኘት አንጻር፡- የሚዲያ ግንኙነትን በዙር ከ 2,838 ወደ 19,698፣ መድረክ ማመቻቸት በቁጥር ከ2,766 ወደ 8,942 እንዲሁም ወቅታዊ መልዕክት፣ መሪ ቃልና የአቋም መግለጫ በዙር ከ703 ወደ 6,135 ለማሳደግ ታቅዷል።
- የሚዲያ ሞኒቶሪንግና ጥናት ምርምር አገልግሎቶች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በሀገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች የሚተላለፉ ዘገባዎችንና ሪፖርቶችን ሞኒተር ማድረግ ከ3,600 ወደ 7,945 ለማድረስ ታቅዷል።
- የህዝብ አስተያት መሰብሰብ ማደራጀትና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ፤ የህዝብ አስተያየት አዝማሚያ ጥናት ማካሄድና ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ታቅዷል።
- የመንግስት የመረጃ ማዕከልና ዲጂታል ሚዲያ አስተዳደር ስራዎችን ተደራሽ ለማድረግ በተቀመጠ ግብ መሰረት በመንግስት መረጃ ማእከልና ዲጂታል ሚዲያ አስተዳደር ስር የዌብሳይትና ማህበራዊ ሚዲያ አስተዳደር አሰጣጥ ተደራሽነትን ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ስትራቴካዊ አጋርነትናትና ግንኙነት አሰራር መመሪያ፤ የሴክተር መስሪያ ቤት ከሚዩኒክሽን ግንኙነት መመሪያ፤ የመረጃ ነጻነት አዋጅ፤ የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ፤ የህዝብ አስተያየት ጥናት አሰራር መመሪያ፤ የኢዲቶሪል ፖሊሲ፤ የሚዲያ ሞኒቶሪንግ አሰራር ማንዋል፤ የመንግስት መረጃ እና ዲጅታል ሚዲያ ልማት አስተዳደር መመሪያ፤ የቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻህፍት አሰራር መመሪያ፣ የዳታ ቤዝ አሰራር መመሪያ መጠቀም የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው።

ምዕራፍ ሰባት

የሰላምና ፀጥታ ግንባታ ዕቅድ

7.1. የሰላምና ፀጥታ

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሰላምና ጸጥታ የትኩረት አቅጣጫ እንደሞከተለው ተለይተዋል፥

- የሰላም፣ የብዝሀነት፣ የአብሮነትና የመከባበር እሴትን መገንባት፣ የመረጃ ስርዓትን በማጠናከር የፀጥታ ስጋትንና ግጭትን መከላከል፣ በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን በዘላቂነት መፍታትና የህግ የበላይነትን ማስከበር፣ የሚሊሻ ሀይል ምልመላና አቅም ግንባታ፣ በአካባቢ ፀጥታ ጥበቃ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የወንጀልና ትራፊክ አደጋ መከላከል፣ የወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ፣ የወሳኝ ኩነት መረጃ ማደራጀትና ማስተዳደር፣ ስልጠናና ስርጸት እንዲሁም በዘላቂነት የዘርፉን የማስፈጸም አቅም መገንባት በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት የሚሰጣቸው ዋና ዋና ናቸው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሰላምና ፀጥታ ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ የአሰራር፣ የአደረጃጀትና የግብዓት ችግሮችን በማሟላት፣ የፈፃሚ አካላትን የሥራ ተነሳሽነት እንዲጎለብት በማድረግና በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መልካም አስተዳደር በማስፈን የተጀመረዉን ሀገራዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በማስቀጠል እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ በማድረግ የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ ነው።

የቀጣይ አሥር ዓመታት የሰላምና ፀጥታ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ መረጃ በየቀኑ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ በማድረግ ሊከሰቱ የሚችሉ የሃይል ግጭቶችን የተለያዩ የፈጣን ምላሽ መስጫ ስልቶችንና ዘዴዎችን በመጠቀም 95 በመቶ የፀጥታ ችግሮችን አስቀድሞ መከላከል በተጨማሪም ለክልሉ ፀጥታ ስጋት በሆኑ ጉዳዮች መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ጥቅም ለይ በማዋል የፀጥታ ስጋትን ለመቀነስ ይሰራል። በዕቅድ ዘመኑ በሰላም እሴት ግንባታ፣ ሀይማኖት ነክ የፀጥታ ችግሮች እንዲቀንሱና የብዝሀነት የአብሮነት እሴት እንዲገነባ በማድረግ ዙሪያ ለ32,145,660 የህብረተሰብ ክፍሎችና ለ2,024,253 ባለድርሻ አካላትና ተባባሪ ወገኞች በመቀናጀት የማህበረሰብ ተኮር ዉይይት በማካሄድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይሰራል። በዚህም በየዓመቱ ለ2,200 የሰላም ኮሚቴ፣ ለ1,500 የሰላም ክበባትና ለ23 የሰላም ፎረም አደረጃጀቶችን ማቋቋምና ዉጤታማ የሚሆኑበት ስልት ተቀይሶ በስልጠና በግብዓት በማጠናከር ወደ ተግባር እንዲገቡ በማድረግ ህብረተሰቡ በሰላም ባህል ግንባታው ተሳትፎው እንዲያድግና የህዝብ ለህዝብ ትስስሩና አንድነቱ የተጠናከረ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል። በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሰላም አቅሞች ላይ 10 መሰረታዊ ጥናት በማካሄድ እንዲጎለብቱ ለማስቻል ክልላዊ የሰላም አቅምን ለማጠናከር ይሰራል።

- ሀይማኖት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ያለመግባባቶችንና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ የማድረግ፣ ህግንና ደንብን ያልተከተሉ የአምልኮ ስርዓት አካሄዶች በህግ አግባብ እንዲመሩ አቅጣጫ የማስያዝ እና በቤተ-እምነቶች መካከል የሚከሰት አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዲቀንሱና ለሠላም ግንባታ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ይሠራል።
- በክልሉ በተለያዩ አካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶችንና ያለመግባባቶችን መንስኤዎችን በጥናት በመለየትና ዘላቂ በመፍታት መፍትሄ የመስጠት ስራዎች ይሰራል።
- በአካባቢ ጥበቃ ስራን በማጠናከር የህበረተሰቡን ስጋት ለመቀነስ የሚሊሻ አባላት በአማካይ በየዓመቱ አዲስ 10,857 በህብረተሰብ ተሳትፎ በመመልመል የማሰልጠንና የማሰማራት ስራ ይሰራል። እንዲሁም ነባር የሚሊሻ አባላት አቅም ከማሳደግ አንጻር ለ81,432 አባላት የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና በመስጠት የአከባቢ ጸጥታ ጥበቃ ውጤታማነት እንዲሻሻል ይደረጋል።
- የብሄራዊ ተጠባባቂ ሀይል አሁን ካለበት 50 በመቶ ወደ 100 ፐርሰንት ለማሳደግ ፣ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በሚሰጠን ኮታ መሰረት 100 ፐርሰንት ተተኪ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከክልሉ በመመልመል ወደ ሀገር መከላከያ እንዲቀላቀሉ ይደረጋል።
- በማህበረሰብ አቀፍ ወንጀል መከላከልና በትራፊክ ደህንነት ዙሪያ ለ58 ሚሊየን የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት ህ/ሰቡን በወንጀልና ትራፊክ አደጋ መከላከል ተሳታፊ ለማድረግ እና የፖሊስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በሰው ኃይልና በማቴሪያል በማደራጀት በ2012 ዓ.ም 2,416 ከነበረበት በ2022 ዓ.ም ወደ 1,527 በማሳደግ የፖሊስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ይሰራል።
- በ2012 በጀት ዓመት 26,693 የነበረውን የወንጀል መጠን በየዓመቱ በ10 በመቶ ለመቀነስ፣ የተለያዩ ወንጀል አይነቶችን ምርመራ አቤቱታዎች፣ ክሶችና ጥቆማዎችን በስታንደርዱ መሠረት ምርመራ በማጣራት 90 በመቶ የምርመራ መዝገብ ለዐ/ህግ ለመላክ ይሰራል። ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የቀረቡ ክሶች፣ አቤቱታዎችና ጥቆማዎችን 100% በፍጥነትና በተደራሽነት ምርመራ የሚጣራ ሲሆን የተገልጋዮችን ሰብዓዊ መብቶችን 100% ለማክበርና ለየክልሉን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ እና የፀጥታ ችግሮች ሲከሰቱ መከላከልና ማስቆም እንዲቻል ተጨማሪ ለ68,500 ልዩ የፖሊስ ኃይልና ለ23,650 ተጨማሪ መደበኛ ፖሊስ ለማፍራት፣ የተለያዩ ፀጥታ አካላትን ለማሰልጠን አንድ ማሰልጠኛ ኮሌጅና አንድ ማሰልጠኛ ተቋም ለመገንባት ታቅዷል።
- የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስራዎች ሽፋንና ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አንጻር ወደ ምዝገባ የገቡ ቀበሌያ ከ94% ወደ 100% ለማሳደግ እና የተመዘገቡ የወሳኝኩነቶች ምዝገባ መረጃ ከ46 በመቶ ወደ 95 በመቶ ከፍ እንዲል ለማድረግ፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ደህንነቱ የተረጋገጠና የዳበረ የመረጃቋ ት ከ75 በመቶ ወደ 100 ፐርሰንት ለማድረስ ፣ የተጨኑና ለምዝገባ ዝግጁ የሆኑ ሰፍትዌሮች ከ27% ወደ 100% እና ወደ መረጃ ቋት የገቡ የወሳንኩነት መረጃዎች ከ4 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ይሰራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሰላምና ፀጥታ ግንባታ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- ብዝሀነትንና ክልላዊ እንድነትን የሚያጎለብቱ የሰላም ግንባታ ፕሮጀክት፣ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች በዘላቂነት ማቋቋም፣ የአርብቶ አደር አካባቢ የግጭት አፈታትና የእርቅ ስራ መስራት፣ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ፈጣን ምላሽ ስርዓት መረጃ ስርዓት የማዘመንና ግብዓት የማሟላት፣ በክልሉ የግጭት መንስኤ ጥናት እና ዘላቂ መፍትሄ ቀረጻ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የተቋማት ማዘመን፣ የህግ ማስከበር፣ የአጎራባች አካባቢዎች እና የአካባቢ አስተዳደር አካላት ትብብርና ማዕቀፍ፣ አካባቢያዊ የሰላም አቅሞችን የመለየትና የማበልጸግ እና የሰላም ትምህርቶችን ተደራሽነት ማስፋት እንደ ማስፈፀሚያ ስልት ተወስዷል።

ምዕራፍ ስምንት

የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ዕቅድ

8.1. የደንና አካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የክልላችንን የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳትና ሌሎች የብዝሃ ሕይወት ሀብትን በማልማት፣ በማንበር፣ በመጠበቅና ዘላቂ አጠቃቀምን በማስፈን እንዲሁም ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብርን በማሳደግ ዘላቂ ክልላዊና ሀገራዊ ልማትና ዕድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመጤ ወራሪ ዝርያዎችን የመለየትና እያደረሱ ያሉትን ጉዳት በጥናትና ምርምር በመታገዝ በቅደም ተከተል መቅረፍ፣ የተለያዩ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን በመሰብሰብ የጀኔቲክ ሀብትን ማንበር፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት በክልሉ የልማት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተትና እንዲተገበር በማድረግ ከዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መጠን መቀነስና የደን፣ የብዝሀ ህይወትና የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃን ማጠናከር የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- በዕቅድ ዘመኑ የተለያዩ የዛፍ ዘሮች በህብረተሰቡ ተሳትፎ በማዘጋጀት 6.1 ቢሊዮን ችግኝ ለማፍላትና 5.2 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል 1,183,000 ሄ/ር መሬት ለመሸፈን የታቀደ ሲሆን ክልላዊ የደን ሽፋን አሁን ካለበት 15 በመቶ በየዓመቱ 0.7 በመቶ በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ላይ ወደ 22 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። የችግኞች የፅድቀት አቅም በ2012 ዓ.ም 81 በመቶ ከነበረበት በየዓመቱ አንድ በመቶ በማሳደግ በአሥር ዓመቱ መጨረሻ ላይ 91 በመቶ ለማድረስና በዓመት 2 ጊዜ የፅድቀት ቆጠራ ለማካሄድ ዕቅድ ተይዟል።
- የአካባቢ ሃብቶች ብክለት በተገቢዉ ሁኔታ ለመከላከል በየአመቱ 96 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁና እንዲተገብሩ ይደረጋል። በተለያየ ደረጃ የሚገኙ 1500 ኢንዱስትሪዎች፣ 2500 የኬሚካል መጋዘኖች ላይ የብክለት ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዷል። እንዲሁም የድምጽ ብክለት በሚያስከትሉ 1500 ተቋማት ላይ ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ መውሰድና እንዲወሰድ ለማድረግ ይሰራል። በተጨማሪም በተለያዩ የማምረቻ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አካባቢ በዓመት ሁለት ጊዜ የአፈር፣ የአየርና የውኃ ናሙና በመውሰድ የብክለት ምርመራ ለማከናወንና የውሳኔ ሀሳብ ለመስጠት ታቅዷል።

- በደን ልማትና ጥበቃ ዘርፍ በሚከናወኑ ተግባራት አማካይነት ለ70,000 ወጣቶች፣ ሴቶችና ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረትሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ድጋፍ ለማድረግ ታቅዷል።
- የደን ልማት ለክልላዊ ኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ በክልሉ ያሉ የእንጨት ኢንዱስትሪዎች በአሥር ዓመት የማምረት አቅማቸው 100,000 ቶን እንዲ ያድግ፣ ዘላቂ በሆነና አከባቢያዊ ተፅዕኖ በሌለው መንገድ ለማገዶ ሊውል የሚችል እንጨት 1.2 ሚሊዮን ሜ/ኩ እንዲመረት፣ ለግንባታ ሊውል የሚችል 4.4 ሚሊዮን ሜ/ኩ ምርት እንዲመረት ድጋፍ የመስጠት ዕቅድ ተይዟል።
- የተለያዩ የዘር ባንኮችን ግንባታ ማካሄድ በ2012 ካለበት 11 ይዞታ በ2022 ወደ 29 ማሳደግ፤ በክልሉ በተመረጡ ቦታዎች ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር ከተቋቋመው አንድ አፀደ እጽዋት ወደ 3 ማሳደግ፣ አንድ ወካይ አፀደ እፅዋት እና የመስክ ጂን ባንክ ለማቋቋም ይሰራል።
- በክልሉ በመጥፋትና በመመናመን ላይ ያሉ የብዝሀ-ሕይወት ዝርያዎችን አሁን ካለበት 125 ዝርያዎች/ንዑስ ዝርዎች ከኢንስቲቲዩቱና ከሌሎች አካላት ዝርያዎችን በማምጣት ወደ 200 የብዝሀ-ህይወት ዝርያዎችን የማበልፀግ (Restoration) ስራ በመስራት ከሀብቱ የሚገኘውን ጥቅም የሚጎለብት ሲሆን በተጨማሪም ሁለት የለማዳ እንስሳት የዘር ፈሰሽ /semen/ ከጂን ባንክ በማምጣት መልሶ የማራባት ስራ የሚሰራ ሲሆን በተጨማረም 2 ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለቸው የዱር እና ውሃ ውስጥ እንስሳት ዝርያ/ንዑስ ዝርያ በኢ-ዘቦታ በማራባት ጥቅም እንዲሰጡ እና በተጓዳኝ ወደ ተፈጥሯዊ ቦታቸው እንዲመለሱ ይደረጋል።
- ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ነባር የተለያዩ የሰብል፣ የደን እፅዋት፣የአትክልትና ፍራፍሬዎች ዝርያዎችን ተለያይነትን ማጥናት መጠበቅ /ማንበር/ አሁን ከለበት 107 ዝርያ ወደ 191 ዝርያ ለማድረስ ይሰራል። ከፍተኛ የብዝሀ-ሕይወት ክምችት የሚገኙባቸው ስርዓተ-ምህዳር ቦታዎችን መለየትና መከለል ከነበረበት 12 ቦታዎች ወደ 27 በማሳደግ 27 ካርታ ማዘጋጀት፣ በክልሉ ከፍተኛ የብዝሀ-ህይወት ሀብት ክምችት የሚገኝበት ተከልሎ ካርታ የተዘጋጀለት ስርዓተ ምህዳር ከነበረበት ወደ 1500ሄ/ር ወደ 9500 ሄ/ር ማድረስ፣ የተመረጡ አገር በቀል የዕጽዋት ዝርያዎች በተራቆቱ የውሃ ዳርቻዎችና በተከለሉ የእጽዋት ፓርኮች መትከል፣ እንክብካቤ ማድረግ አሁን ካለበት 18,153 ሄ/ር ወደ 40,340 ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል።
- ለዘ-ቦታ የለማዳ እንስሳት ዝርያዎች (ን/ዝርያዎች) ለመጠበቅ ተቋቁሞ የነበረውን 24 ጠባቂ ማህበራትና 1,207 አባላት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 61 ማህበራትን በማቋቋም የማህበሩ አባላትን 3,914 እንዲደርስ ይሠራል። በዘ-ቦታ ጥበቃ የተወለዱ/ የተባዙ በመመናመን ላይ ያሉ የለማዳ እንስሳት ብዛት አሁን ካለበት 900 ጥጆች ወደ 5,400 ጥጆች/ግልገሎች ለማድረስ ይሰራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የአከባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ፤ የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ማጠናከር እና የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው።

ክፍል አራት

የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ምዕራፍ አንድ

የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች

ዘላቂ ልማትና ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚቻለው ውስን ሀብቶችና አቅሞችን በአግባቡ አስተባብሮና አሰናስኖ በመጠቀም አዳጊ፣ ተለዋዋጭና እየሰፉ የሚሄዱ በርካታ ፍላጎቶችን በቅድመ ተከተል በማሟላት ብቻ ነው። ስለዚህ የልማት ዕቅዱ ሲካሄድ በአጠቃላይ ያሉትን የሀብት አይነቶችና አቅሞች አሟጥጦ መጠቀምና በሂደት የአቅሞቹን አድማስ እያሰፉ መሄድ ጠቃሚ ይሆናል። እነዚህም እንደሚከተለው ተዳሰዋል።

የተፈጥሮ ሀብት፡- በገጸ ምድርና በከርሰ ምድር የሚገኙ እንደ መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድን፣ መልካም የአየር ንብረት፣ የብዝሃ ሕይወት እንዲሁም የንፋስና የፀሃይ ኃይል የመሳሰሉ መሠረታዊ የተፈጥሮ ጸጋዎችን ያካትታል። ክልላችን ባለዉ የሥነ ምድር አወቃቀር፣ የተለያየ ሥነ ምህዳርና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምክንያት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ያለዉ ሲሆን እነዚህም እንደሚከተለው ተዳስሰዋል።

መሬት፡- ክልላችን ሰፊ የመሬት ሀብት ያለዉ ሲሆን ካላዉ አቅም ውስጥ እስካሁን ጥቅም ላይ የዋለው ትንሽ ነው። በተለይም መታረስ ከሚችለው መሬት ውስጥ የተጠቀምነው ዝቅተኛ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። በዚህም በሚቀጥሉት ዓመታት ለግብርና ምርት እንዲሁም ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ የልማት ፍላጎቶች መዋል የሚችል ሰፊ የመሬት ሀብት ታሳቢ ተደርጓል።

ማዕድን፡- የተለያዩ የከበሩ፣ ብረትና ብረት ነክ፣ የኢንዱስትሪ፣ የግብርናና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ የጌጣጌጥና የኢነርጂ ማዕድናት እንዳሉ ባለፉት ዓመታት በዘርፉ የተካሄዱ የሥነ ምድር ጥናቶች ያሳያሉ። በቀጣዮቹ አስር ዓመታትም የከሰል ድንጋይ፣ የብረት፣ የፖታሽ፣ የእምነ በረድ እና ሌሎች ማዕድናት የማውጣትና የማልማት ሥራዎች ይከናወናሉ።

ውኃ፡- በውኃ ረገድ ያሉን ከሀይቆች፣ ከኩሬዎችና ክረምት ከበጋ ከሚፈሱ ወንዞች የምናገኘው የውኃ ሀብት ያለውን አቅም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመት ይህንን አቅም ጥቅም ላይ ለመዋል ታሳቢ ተደርጓል።

የተፈጥሮ መስህብ፡- የተፈጥሮ መስህብ ሀብቶች ማለትም ማራኪ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣ ፏፏቴዎች፣ የተፈጥሮ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት፣ ደኖችና በውስጣቸው የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አእዋፋት ለቱሪዝም፣ ለትምህርትና ለምርምር ሥራዎች አቅሞች ናቸው።

ቁሳዊ ሀብት፡- ቁሳዊ ሀብቶች በሰው ልጆች የተገነቡና ለተለያየ ጠቀሜታ ሊውሉ የሚችሉ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረቶችን ያጠቃልላል። የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የሚመጣው ከተሜነት ከፍተኛ የቁሳዊ ሀብት ልማት ዝግጅትን የሚጠይቅ ሲሆን እስካሁን በኃይል፣ በመጠጥ ውኃ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በመስኖ፣ በማምረቻ ፋብሪካዎች (የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ) የተፈጠሩት አቅሞች ለቀጣይ ልማት መነሻ ይሆናሉ። ቀጣይ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሰው ሠራሽ የቁሳዊ ሃብቶች አቅምን አሟጥጦ ከመጠቀም በተጨማሪ በተለይም የኃይል

አቅርቦት፣ የአይሲቲ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመስኖ፣ የመጠጥ ውኃ፣ የመንገድ፣የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶችን በማጎልበት ረገድ ተጨማሪ አቅሞች የሚፈጠሩ ይሆናል።

የኢነርጂ ሀብት፡- ክልላችን ከተለያዩ ምንጮች ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ እምቅ ሀብት ያለዉ ሲሆን፣ እስካሁን በሥራ ላይ የዋለው ግን አነስተኛው ክፍል ነው። የውኃና ታዳሽ ኢነርጂ ሃብትን በፍትሐዊነትና በዘላቂነት በማልማትና በማስተዳደር የዜጎችን የኃይል ፍላጎትና ሁለንተናዊ ሕይወት ማሻሻል፣ የኢነርጂ አቅርቦትና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ለፈጣን ልማትና ዕድገት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

መስኖ፡- በአሁኑ ወቅት በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬት 700,000 ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ የለማው መሬት 40,548.83 ሄክታር (5.8 በመቶ) ብቻ ነው። ከዚህ አንጻር በቀጣዩ አስር ዓመታት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። በዚህም መሠረት በአነስተኛ፣ በመካከለኛ እና በሰፋፊ መስኖ 135,198 ሄክታር ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለይቶ መገንባትና ከዚህ በፊት የተጠኑና ወደ ሥራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ገምግሞ ወደ ግንባታ ማስገባትና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ።

ትራንስፖርትና መገናኛ፡- በሀገር ደረጃ የተዘረጉ መንገዶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አውታሮች በዕቅዱ ዘመን ለሚጠበቀው አጠቃላይ ዕድገት ብሎም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። የእነዚህ መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ሎጂስቲክስን በማቀላጠፍ የሌሎች ዘርፎችን አፈጻጸም ያቀላጥፋል። ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ልማቶች ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪና ለሰርቪስ ሴክተር ልማት ለተያዙ ግቦች መሳካት እንደ ትልቅ መሠረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል።

ሰብዓዊ ሀብት፡- በክልል ደረጃ አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት፣ በተለይም ከፍተኛ የወጣቶች ድርሻ፣ የትምህርት፣ የዕውቀትና የክህሎት ዝግጅት ደረጃ እንዲሁም ጤንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ለዘላቂ ልማትና ብልጽግና መሳካት ቁልፍ ምንጮች ናቸው። በዚህ ረገድ የክልሉ ሕዝብ ብዛት በ2012 ከተገመተው 14 ሚሊዮን በ2022 ወደ 16.8 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በክልሉ እየተስተዋለ ያለው የሥነ ሕዝብ ሽግግር (demographic transition) በቀጣዮቹ የልማት ዓመታት እንደሚቀጥል ይገመታል። ይህ ወጣት የሠራተኛ ኃይል የዕድገት ምንጭነት አቅሙ ከፍተኛ ነው።

በአጠቃላይ የሰብዓዊ ሀብት መሻሻል በራሱ ለምርት ግብዓትነት ከመዋሉም በላይ የቴክኖሎጂ አቅሞችን አሟጥጦ ለመጠቀም ይረዳል። ሆኖም ይህ እንዲሳካ የሕዝብ ብዛት የዕድገት ምንጭ እንዲሁም ምርታማ እንዲሆን በትምህርት፣ በሥልጠናና በምርምር ዙርያ ከፍተኛ ሥራዎች መሥራትን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ እስካሁን በትምህርት ዘርፍ የተገነቡ አቅሞች ሀገሪቷ ብሎም ክልላችን የተሻለ የሰብዓዊ ሀብቶች አቅም እየገነባች ስለመሆኑ አመላካች ነው። በአሁኑ ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በትምህርት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በሺዎች

የሚቆጠሩት ከግልና ከመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ጨርሰው ለሥራ ዝግጁ ይሆናሉ። የተያዘውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እየተመረቁ ለሥራ ዝግጁ ከሚሆኑ ዜጎች ቁጥር አንጻር ክልሉ ከፍተኛ የሰብዓዊ ሀብት አቅም ያለው መሆኑ የማያከራክር ሲሆን ይህም ለታቀዱት የልማት ግቦች ከፍተኛ አቅም ይፈጥራል።

የፋይናንስ ሀብት፡- አንድ ክልል በጥሪት መልክ ያፈራውን በቀጣይም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨውም ሆነ ከሌሎች ምንጮች ሊያሰባስብ የሚችለውን ክልላዊ የፋይናንስ ሀብት መጠን ለልማት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ወሰኝ ናቸው። በዚህ ረገድ ክልላችን ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከዚህም የሚሰበሰበው ገቢ እንዲሁም ቁጠባ ለተለያዩ የልማት ፋይናንስ ፍላጎቶች ማሟያነት ሲውል ቆይቷል። በሚቀጥሉትም ዘመናት የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማስቀጠልና ከዚህም ሊሰበሰብ የሚችለውን የገቢ መሠረትንና መጠንን እንዲሁም ቁጠባን በማሳደግና እነዚህንም ሀብቶች በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ዘላቂ ልማትንና ብልጽግናን ማሳካት ይቻላል።

ማህበራዊ ሀብት፡- ህዝቦች ለዘመናት አብሮ በመኖር ሂደት የገነቧቸው ባህሎች፣ ልማዶችና ሌሎች የጋራ እሴቶች የሀገሪቷን ብሎም የክልሉን የልማትና የብልጽግና ጉዞ ለማሳካትና የዜጎቿን መሻቶች ለማሟላት ከሚያስፈልጉ ውድ ፀጋዎች ውስጥ ይካተታሉ። ከላይ የተገለጹ ሀብቶች አቅም አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ እነዚያን ሀብቶች በሚፈለገው መልኩ አቀናጅቶ ሥራ ላይ ለማዋል መልካም ማህበራዊ መስተጋብርና ዘላቂ ሰላም የሚያመጡ እሴቶች ያስፈልጋሉ። በዚህ ረገድ ለዘመናት የኖረው የመከባበር፣ የመደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመሥራት ባህሎችና እሴቶች እንዲሁም በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ የተሰናሰሉ አዎንታዊ ሥርዓታት በቀጣይ የታቀዱ የልማት ግቦችን በማሳካት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

ምዕራፍ ሁለት

የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ሊደረስባቸው የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚሆኑ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ስልቶች በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ተመላክተዋል። በዚህ መሠረት የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች በጥቅሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ጥራት ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥና ወደ አስተማማኝ የዕድገትና ብልጽግና ጎዳና ለመሸጋገር ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በአንድ ሀገር ወይም በአንድ ክልል ውስጥ የሚመዘገብ አነስተኛ የካፒታል ክምችት ከአነስተኛ ቁጠባና ኢንቨስትመንት የሚመነጭ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ትርጉም ያለው የልማት ፋይናንስ በማመንጨት ከብክነት በፀዳ መልኩና በቅልጥፍና ለታለመለት ዓላማ ላይ በማዋል ጥራት ያለው ዕድገትን ማስመዝገብና የካፒታል ክምችትን ማሳደግ ይቻላል።

በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችንና ዋና ዋና ግቦችን ዕውን ለማድረግ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍን (financial resource envelope) ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የልማት ፋይናንስ ምንጭን ከሀገር ውስጥ ገቢ፣ ቁጠባ እና ከሌሎች ምንጮች በአግባቡ በመለየት፣ የኢኮኖሚውን ገቢ የማመንጨት አቅም ከግምት በማስገባት፣ የልማት ዕቅዱ ባስቀመጣቸው የትኩረት መስኮችና አቅጣጫዎች ቅደም ተከተል መሠረት ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ባገናዘበ መልኩ አቅርቦትንና ፍላጎትን በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠንና ዝርዝር የልማት ፋይናንስ ምንጭ የሚያሳይ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

በዕቅዱ የትግበራ ዘመን የመንግሥት የኢንቨስትመንት ወጪ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ዋና ዋናዎቹን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዘርፎች ላይ በማተኮር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም ጥራት ያለውን የመንግሥት ኢንቨስትመንት በማከናወን በዕቅዱ የተመለከቱትን ግቦች ከማሳካት አንጻር ያላቸው ፋይዳ በተለይም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገብ፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከማስፈን፤ ድህንትን ከመቀነስ፤ የግል ዘርፉን ድርሻ ከማሳደግ፤ የክልሉን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ከማዋል፣ ዘርፎች መካከል ትስስርና ተመጋጋቢነት በማጎልበት የሥራ ዕድል ከመፍጠርና ከማሳደግ አንጻር የኢንቨስትመንቱን ቅደም ተከተል የሚመሩ መሠረታዊ መነሻዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

በዚህም በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ በመንግሥት የሚከናወኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርተው በጥልቀት እንዲዘጋጁ ይደረጋል። ፕሮጀክቶቹም በገለልተኛ ወገን ተገምግመው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ። በተጨማሪም በዕቅድ ዘመን የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነትና ቅልጥፍናን ለማሳደግ ከላይ በተጠቀሱ መስፈርቶች መሠረት በየዘርፉ የተለዩትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል። ጥራት ያለው የሰው ኃይል የኢኮኖሚን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ በዕቅዱ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል። የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነትና በጥራት ማቅረብ ካልተቻለ የዕቅዱን ትላልቅ ግቦች ለማሳካት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም ከኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አቅርቦትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን ከኢኮኖሚው ባህሪ ጋር ተለዋዋጭ በመሆኑ ይህንን ቀድሞ በማቀድ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም የትምህርት ዘርፉ የሚያቀርበው የሰው ኃይል ከኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከሰተውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን (skill mismatch) ከማስወገድ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ዘላቂ ምርታማነትን በማሳደግ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ያለው አዎንታዊ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፍላጎት በክህሎት አይነት፣ መጠንና የጥራት ደረጃ በየዘርፉ በዝርዝር የሚለይ የልማት ዕቅዱ የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

ዘላቂ የሆነ የስርዓታት ግንባታ ማዕቀፍ፡- ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎችን ወጥና ተናባቢ ማድረግ፣ ዘላቂ የሆነ የተቋማት አደረጃጀት መፍጠር እና አቅም በመገንባት አዳዲስ ሥልቶች አማካኝነት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል።

ምዕራፍ ሶስት

የልማት ዕቅዱ ስጋቶችና ስጋቶቹን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች

3.1. የልማት ዕቅዱ ስጋቶች፦

ስጋቶች፡- የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ ውጤታማነት ሊያደናቅፉ የሚችሉና በልማት ዕቅዱ የታቀዱ ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ክስተቶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ስጋቶች ከመከሰታቸው በፊት የመከላከያ ስትራቴጂ ለመንደፍና የሚያስከትሉትን አደጋ ለመቀነስ ከወዲሁ መለየት ይገባል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱን ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ስጋቶች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

1) የአስር ዓመቱን ዕቅድ ለማስፈፀም የሚጠይቀው ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ ፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በሚፈለገው መጠንና ጥራት ካልተገኘ በልማት ፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ ድልድል፣ በግብዓት አቅርቦትና በመሳሪያዎች ግዥ ላይ ሊፈጥር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆን፤
2) በሰው ሠራሽ እንዲሁም በተፈጥሮ ለሚከሰቱ አደጋዎች ማለትም ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጤና ወረርሽኞች ተጋላጭ መሆንና አደጋዎችን ለመቀልበስ የሚወሰዱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ለልማት ሊውል የሚችለውን ሀብት የሚሸሙ መሆናቸው፤
3) የኮቪድ-19 አሉታዊ ተጽዕኖ ለሚቀጥሉት ሦስትና አራት ዓመታት ሊቀጥል እንደሚችል ጥናቶች የሚያመለክቱ ሲሆን ይህም ኢንዱስትሪዎቻችን በዋናነት ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ወረርሽኙ በዘርፉ ምርትና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መመላከቱና የዓለም ሀገራት በተናጠልና በቡድን ኢኮኖሚያቸውን ለማነቃቃት በሚወስዱት አስተዳደራዊና የፖሊሲ እርምጃዎች የሀገራችንንና የክልላችንን ምርት ተወዳዳሪነት ሊቀንስ እንደሚችል ይህም በአስር ዓመቱ ልማት ዕቅድ የተጣሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ግቦች ስኬት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆን እና
4) ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን እየተስተዋለ የመጣው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ይህን ተከትሎ በክልላችን በተለያዩ አካባቢዎች የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ክልላዊ አደረጃጀት ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ አለመረጋጋቶች መከሰታቸው፣ ይህንንም በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት ረዘም ያለ ጊዜ የሚፈልግ ሲሆን በልማት ዕቅዱ ስኬት ዙሪያ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ስጋቶች ናቸው።

3.2. የልማት ዕቅዱ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች

ስጋቶች ከመከሰታቸውና ወደ አደጋ ከመሸጋገራቸው በፊት ለመከላከል የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል። በተለይም ደግሞ የአደጋ ስጋትን በመለየት፣ በመተንበይ፣ በመተንተንና የቅድመ ጥንቃቄ ዕርምጃዎችን በመውሰድ ጉዳት እንዳያደርሱ ወይም የሚስያከትሉትን ጉዳት መቀነስ የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል።

የፋይናንስ እጥረትን በተመለከተ የተጀመረውን የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ዘመናዊ የማድረግ ሥራ አጠናክሮ

በማስቀጠል እንዲሁም የታክስ መሠረቱን በማስፋት፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባን በማሳደግ፤ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚኖረውን የትብብር ማዕቀፍ ወደ መሬት ማውረድ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

የአደጋ ተጋላጭነትን በተለይም የድርቅና የጎርፍ ተጋላጭነትን ከመከላከል አንጻር የህዝቡን ግንዛቤ ይበልጥ በማስፋትና በማዳበር በተለይም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ የሚተገበሩ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራምን በማስቀጠል የክልሉን የደን ሽፋን ለማሳደግ በትኩረት ይሠራል። በተመሳሳይ በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የውኃ ሀብቶችን በማነጽ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በአጠቃላይ ለተፈጥሮ አደጋዎች የማይበገር ማህበረሰብ ለመገንባት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የኮቪድ-19 ተጽዕኖን ለመቀልበስና ኢኮኖሚውን ወደ ነበረበት ፈጣን የዕድገት መስመር ለመመለስ ለምርታማና ሰፊ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ ለሚችሉ ዘርፎች ትኩረት መስጠት፣ የመንግሥት ኢንቨስትመንት የግሉን ዘርፍ በሚያበረታቱ የተመረጡ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣ ውጤትን መሠረት ያደረገ የማበረታቻና የድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣ ዘመናዊ የአመራረት ስልትን መከተልና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በአንድ ሀገር በተለያዩ ጊዜያት የፖለቲካ ችግሮች፣ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮች ቢሆንም ችግሮቹ ለልማት፣ ለሰላምና ለመሰረታዊ የዜጎች ደህንነት አስጊ ሆነው እንዳይቀጥሉ ዘላቂ መፍትሄ ሊቀመጥላቸው ይገባል። በልማት ዕቅዱ የተያዙትን ውጥኖች ከግብ ለማድረስ የፖለቲካ ችግሮችን እንዲሁም በክልሉ ለሚከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶች፣ በቡድኖች መካከል ለግጭት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ያደሩና ሌሎች አዳዲስ አስጊ የግጭት ምክንያቶች እልባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

ለዚህም ይረዳ ዘንድ የቤተሰብ፣ የማሕበረሰብና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር፣ የዕምነት ተቋሞቻችን ለልማት አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ለውይይትና መግባባት የሚረዱ መድረኮችንና ጉባኤዎችን በማጠናከርና በአግባቡ በመጠቀም ችግሮች እንዳይስፋፉ የማድረግ ሥራ ይሠራል። በተለይም በዞኖችና በወረዳዎች መካከል የሚነሱ የድንበር ይገባኛል ጉዳዮችና የማንነት ይከበርልኝ ጥያቄዎች ሀገራዊና ክልላዊ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጣቸው ይሆናል።

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚከሰቱ አለመስማማቶችና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ሕጋዊነት ባለው መልኩ እንዲፈቱ በማድረግ ዜጎች የፈለጉትን የፖለቲካ አመለካከት የማራመድ መብታቸው እንዲጠበቅና ለሀገራቸው ብሎም ለክልሉ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ይከናወናል። ይህንንም በአግባቡ ለመምራት የሕግ ማስከበር፣ የሰላም፣ የደህንነት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማት በተሻለ ደረጃ ከፖለቲካ ገለልተኛና ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል።

ምዕራፍ አራት

የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ክልላዊ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዋና ዓላማ በየጊዜው የሚታቀዱ የልማት ዕቅዶችን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በመከታተልና በመገምገም ውጤታማ ሆነው እንዲፈፀሙ ማድረግ ነው። የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መከታተልና መገምገም በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት ለመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል።

በዚህ ረገድ በክልል ደረጃ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደታየው ባለፉት የዕቅድ ዘመናት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የክትትልና ግምገማ አሠራር በክልሉ ለተመዘገበው ልማት የራሱ አስተዋጽዖ ቢኖረውም በርካታ ድክመቶችም ነበሩበት። ከድክመቶች መካከል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የክትትልና ግምገማ አቅም ውስን መሆን፣ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተዛባ አመለካከት መኖር፣ የክትትልና ግምገማ አሠራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ ከስኬት ይልቅ ሂደትና ውጤት ላይ ማተኮር እንዲሁም በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከላይ የተገለፁትን ተግዳሮቶች ለመፍታትና በክልል ደረጃ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለመገንባት የሚረዳ ክልላዊ የክትትልና ግምገማ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል። መመሪያው በሚዘጋጅበት ወቅትም መካተት የሚገባቸው የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ማለትም ባለቤትነት፣ አሳታፊነት፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የመረጃ ጥራትና ተዓማኒነት፣ ቅንጅት፣ ወጥነት፣ ተመጋጋቢነት፣ የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ይዘቶችና የማቅረቢያ ጊዜ፣ የዕቅድ አፈጻጸም ስታንዳርዶችን እና የምዘና አሠራር ዋና ዋና የተለዩ የክትትልና ግምገማ መመሪያ ስትራቴጂዎች ይሆናል።

4.1. የክትትል ሥርዓት

ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩበት ግልጽና መለካት የሚችሉ ቁልፍ አመልካቾች (key performance indicators) ያስፈልጉታል። ይሄንንም ለማሳካት የክልሉ ፕላን ኮሚሽን ከሁሉም አስፈፃሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የራሱን ዘርፍ ቁልፍ አመልካቾች እንዲለይ በማድረግ ክልላዊ ቁልፍ የውጤት አመልካቾች ይዘጋጃል። በመሆኑም የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩት በእነዚህ አመልካቾች መሠረት ይሆናል።

የልማት ዕቅዱ የክትትል ሥርዓት በዋናነት ሁለት የመረጃ ምንጮችን ይጠቀማል። እነዚህም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚመነጩ የናሙና ጥናትና የቆጠራ መረጃዎች እንዲሁም በዘርፍ አስፈፃሚ ተቋማት የሚመነጩ የአስተዳደር መረጃዎች ናቸው። በተጨማሪም በክልሉ የመረጃዎችን ወጥነትና ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ቼክ ሊስት በፕላንና ልማት ቢሮ የሚዘጋጅ ሲሆን በቀጣይ ይህንን መሠረት በማድረግ መደበኛ የአፈጻጸም ሪፖርቶች የሚዘጋጁ ይሆናል።

በዓመታዊ ዕቅድና በጀት የተደገፈ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፡- የልማት ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ በሁሉም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በባለቤትነት ተይዞ መፈጸም ያለበት ትልቅ ኃላፊነት ነው። በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱን የክትትልና ግምገማ ማትሪክስ መሠረት ያደረገ፣ ቁልፍ የውጤት መስከችን፣ ኢላማዎችንና ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን በግልጽ ለይቶ ያስቀመጠና በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀት ይህንንም ተፈፃሚ ማድረግ ከእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካል የሚጠበቅ ይሆናል። የክትትልና ግምገማው ሥራ በተለያዩ አካላት በተለያየ ደረጃ የሚከናወን ቢሆንም የማክሮ ኢኮኖሚና የዘርፍ መረጃዎችን በመጠቀም አጠቃላይ ዓመታዊ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም በፕላን ኮሚሽን እየተዘጋጀ ለመንግሥት የሚቀርብ ይሆናል።

በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፡- የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃን ለማረጋገጥ በተመረጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ የሚዘጋጅ ጉብኝት ሆኖ ዓላማው በየጊዜው ከሚዘጋጁ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የአፈጻጸም ልዩነቶችን በማረጋገጥና የአፈጻጸም ክፍተቶች ካሉም የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ እንዲወሰዱ ማስቻል ነው። ይህም በዓመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሐ ግብር በሚገባ በመካተት በሃላፊዎችና በከፍተኛ አመራሮች ደረጃም በተመረጡና ፋይዳቸው ከፍተኛ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ የሚከናወን ይሆናል። የመስክ ጉብኝቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከማመንጨት በተጨማሪ በአንድ የመረጃ ምንጭ ወይም በሪፖርት ላይ ከመወሰን ይልቅ የመረጃ ምንጮችን ማስፋትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመስክ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳካር (triangulation) ጠቃሚ በመሆኑ ነው።

ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን በባለድርሻ አካላት ማስገምገም፡- የምክክር መድረኮችን በክልል፣ በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃዎች በማዘጋጀት በዓመታዊ የልማት ዕቅዱ ረቂቅ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ይካሄዳል። ይህም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈንና ለማጠናከር እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ከምክክር መድረኮች የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት የአፈጻጸም ሪፖርቱ ታትሞ ለባለድርሻ አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ ይደረጋል።

4.2. የግምገማ ሥርዓት

የዕቅድ ትግበራ ዘመን አጋማሽ ግምገማ (mid-term review)፡- ሌላው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በዕቅድ ዘመኑ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው። ዓላማውም በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ግቦችና የማስፈጸም ኢላማዎች ምን ያህል እየተሳኩ እንደሆነ በዝርዝር ለመፈተሽና ለማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች ካሉም በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድና በቀሪው የዕቅድ ዘመን የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንዲረዳ ነው። በመሆኑም የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ የሚከናወን ይሆናል።

የዕቅድ ትግበራ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ (final evaluation) ፡- የዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ የሚከናወን ግምገማ ሲሆን፣ ዓላማውም የልማት ዕቅዱ ግቦችና ኢላማዎች በዕቅዱ በተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች መሠረት መፈፀማቸውንና የዕቅዱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ መልካም ተሞክሮዎችንና የአፈጻጸም ጉድለቶች ካሉ ከነምክንያቶቻቸው በመለየት በቂ ትንተናና ግምገማ ማካሄድና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው።

የግምገማ ጥናት (evaluative research) ማካሄድ፡- ሌላው የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ዘዴ በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የግምገማ ጥናት ማካሄድ ሲሆን በተመረጡ የማክሮ ኢኮኖሚ ወይም በዘርፎች የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ስኬቶች እንዲሁም ተግዳሮቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የግምገማ ጥናቶች ዓላማም በየጊዜው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን በማካሄድ እየተመዘገበ ያለውን ለውጥ፣ ውጤትና ስኬት እንዲሁም እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥልቀት በመዳሰስ ለፖሊሲ ውሳኔዎችና ለዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ማመንጨት ነው።

4.3. የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች

የክትትልና ግምገማ አሠራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም ማጠናከር፡- የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ አሠራርና አደረጃጀቶችን አስመልክቶ በተለያዩ የመንግሥት አስተዳደር ዕርከኖችና የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሰፊ ክፍተቶች ይታይባቸዋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን እነዚህን ክፍተቶች በማስወገድ የልማት ዕቅዱን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በጠንካራ አሠራርና አደረጃጀት እንዲሁም በአስፈላጊ የሰው ኃይል በመደገፍ የሚጠበቀውን ዓላማ ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

በልማት ሂደት ውስጥ አሠራርና አደረጃጀት ብቻቸውን የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ አይችሉም። አሠራርና አደረጃጀት ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ የሚችሉት በተሟላ የሰው ኃይል ሲደገፉ ብቻ ነው። በልማት ሂደት ውስጥ ወሳኙ አቅም የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል ነው። በመሆኑም ይህን የልማት ዕቅድ ውጤታማ ለማድረግና በሀገራችን ብሎም በክልላችን የተጀመረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማህበራዊና የአካባቢ ልማት ለማስቀጠል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የዜጎችን የልማት እኩል ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ ለማረጋገጥ የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በተለያዩ የመንግሥት የአስተዳደር እርከኖች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተመድበው የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቀጣይነት ባላቸው የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲታነፁ በማድረግ የሰው ኃይል አቅም በየደረጃው እንዲጎለብት ይደረጋል።

ለክትትልና ግምገማ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት መገንባት፡- የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በሕግ ከተሰጧቸው ኃላፊነቶች ጋር በተገናኘ ለልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የሚያግዙ መረጃዎችን ያመነጫሉ። የእነዚህ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና ሥርጭት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓትን የተከተለና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ከተወሰኑ የመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት በስተቀር የአብዛኛዎቹ አሠራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ አይደሉም። በመሆኑም የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ አቅም በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና የተቀናጀ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል።

በተጨማሪም መረጃዎቹን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት በመዘርጋትና ሶፍትዌሮችን በማልማት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። የዘርፍ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የመረጃ ቋቶች ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመረጃ ቋት ጋር የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት በመፍጠር የመረጃ ፍሰትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ሪፖርት አቀራረብ በቴክኖሎጂና ሶፍትዌር እንዲደገፍ ይደረጋል።

የዕቅድ አፈጻጸም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማጎልበት፡- የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዓላማ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላትን የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ማሻሻልና በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው። ይህም በዕቅድ አፈጻጸም የሚታዩ ድክመቶች መንስዔያቸው ምን እንደሆነ ከመለየት ጀምሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማመላከትንና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተልን ይጠይቃል።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ደካማነት ከተቋሞቹ የበላይ ኃላፊዎች የሥነ ምግባር ችግር፣ የባለቤትነትና የቁርጠኝነት ጉድለት፣ የሕዝብ ጥቅምን ያለማስቀደምና የአቅም ማነስ ችግር ጋር የተያያዘ ከሆነ በየደረጃው የተቀመጡ የልማት ግቦችና ኢላማዎችን ለማሳካት የሚደረገውን የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ድጋፍ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ተገልጋዩ ሕዝብም በመንግሥት ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ እንዲሄድ ያደርጋል። ይህም በሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማህበራዊ ቀውሶች ሁሉ በዋናነት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚመነጩ ናቸው። በመሆኑም የአስፈፃሚ ተቋማትንና ተቋማቱን የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎችን የሥራ አፈጻጸም በተሟላ ሁኔታ በየጊዜው በመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃ በመስጠት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን፣ ይህንንም ለዜጎች ለማሳወቅና ይፋ ለማድረግ ከሚዲያዎች ጋር የሚሰራ ይሆናል።